# ከአሲምባ ድረ-ገጽ አዘጋጅ
# አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ሕዝባዊ ንቅናቄንና ሚኒፌስቶውን አስመልክቶ

የአሲምባ ድረ-ገጽ ይህ ማኒፌስቶ እንደተላከልን እንዳለ ከዚህ በታች አቅርበናል። ይህ ማኒፌስቶ ለውይይት እንዲቀርብላቸው ከማድረግ ያለፈ የአሲምባ ድረ-ገጽ ከዚህ ንቅናቄ ጋር ምንም ግንኙነት ስለሌው አንባቢያን በሰነዱ ውስጥ የተቀመጡትን የኢ-ሜል አድራሻዎች በመጠቀም ጥያቄአችሁንና አስተያየቶቻችሁን በቀጥታ ለንቅናቄው እንድትልኩ እያሳሰብን፣ ንቅናቄውን በሚመለከት ወይም ተጨማሪ አስተያየት እንደማናስተናግድ እናስታውቃለን።

የአሲምባ ድረ-ገጽ የዚህ ሕዝባዊ ንቅናቄ መሥራቾችና የማኒፌስቶው ባለቤቶች በቅርቡ በኢትዮጵያውያን መድረኮች ወጥተው ራሳቸውን በማስተዋወቅ ስለ ማኒፌስቶውና ስለ ንቅናቄው ሰፋ ያለ ውይይት ያደርጋሉ የሚል ከፍተኛ ዕምነት አለን። እንጠብቃለንም።

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያቸንፋል!

የአሲምባ ድረ-ገጽ አዘጋጅ

# አንድ ሀገር ! አንድ ሕዝብ ! ማንፌስቶ

ሀገር አድን ሕዝባዊ ንቅናቄ

**እኛም ለኢትዮጵያችን**

**ነሐሴ 24 ቀን 2008 ዓ.ም.**

ክፍል 1

ኢሜል ፡ ethiopiachen@gmail.com
info@ethiopiachen.org

**© የባለቤትነት መብቱ በሕግ የተጠበቀ**

## Contents


ማሳሰቢያ ..... 4

1.0 መቅድም ..... 5

3.0 መግቢያ ..... 7

3.0 ሀገር ፍቅርና ኢትዮጵያዊነት ..... 8

4.0 ጎሰኝነት፣ ዘረኝነትና ኢትዮጵያዊነት ..... 10

5.0 ሃይማኖትና ኢትዮጵያዊነት ..... 13

6.0 በረሃብ መግዛትና ትውልድ ማቀጨጭ ..... 15

7.0 በባህል አኳያ ..... 15

8.0 ኢትዮጵያና ኤርትራ ..... 16

9.0 ምን ዓይነት መንግሥት ..... 17

10.0 የኢትዮጵያ ክፍለሀገራት አከፋፈል ..... 20

11.0 የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ..... 21

12.0 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ ..... 22

13.0 የያ ትውልድ እንቅስቃሴ ለምን ተኮላሸ? ..... 23

13.1 የካቲት 66 ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አቅጣጫን መሳት ..... 26

13.2 የኢሕአፓ እንቅስቃሴ በአጭር መቀጨት ..... 28

14.0 የኅብረት ግምባርና ትግል ..... 31

14.1 አምባገነን ገዥዎች ሥልጣናቸውን ለማጠናከር የሚፈጥሩት ኅብረት ..... 32

14.1.1 የደርግ አገዛዝ ..... 32

14.1.2 ህወሀት ..... 32

14.2. አምባገነን ገዥዎችን ለመጣል የተደረጉ ኅብረቶች ..... 32

14.2.1 ኢዴኃቅ (የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት) ..... 33

14.2.2 ፓሪስ አንድ ጉባዔ ..... 33

14.2.3 የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ..... 33

14.2.4 ፓሪስ ሁለት ኢተፖድኅ ..... 33

14.2.5 የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ..... 34

14.2.6 ቅንጅት ..... 34

14.2.7 ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ (AFD) ..... 34

14.2.8 የህዝቦች ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ (PAFD) ..... 34

15.0. ኅብረት፣ ቅንጅት እና 1997 እንቅስቃሴ መኮላሸት ..... 35

15.0.1. የምርጫ ፖለቲካና የኅብረት ትግል ..... 35


አንድ ሀገር ! አንድ ሕዝብ !

16.0. የኀብረት ትግል....39
17.0. ብሔራዊ ዕርቅ....40
18.0. የቅራኔ አያያዝ መርሆዎች....43
19.0. የባዕዳን ኃይሎች ሤራ....43
20.0. ምን መደረግ አለበት....44
21.0. ዋናው ትኩረታችን....45
22.0. አዲሱን ትውልድና ወጣቶችን ያቀፈ....46
23.0. ለትውልድ ዘላቂነት ያለው ሕገ መንግሥት....48
24.0. ዴሞክራሲያዊ መብት....50
25.0. ምን ዓይነት ሥርዓትና ምጣኔ ሀብት....51
26.0. የምሁሩ ሚና....54
26.1. ምሁር ስንል....54
26.2. የእኛዎቹ ወዴት ናቸው?....54
26.3. ምሁር ማነው....54
27.0. የትግል ስልት....56
27.1. ሰላማዊ የትግል ስልት....56
27.2. ሰላማዊ ትግልና የምርጫ ፖለቲካ....58
27.3. የትጥቅ ትግል....59
27.4. ሁለገብ የትግል ስልት....60
27.5. የትኛው ይሻለናል?....60
28.0. ለምን አስፈለገ?....61
29.0. ቀጣይ ሂደት....63

ለአስተያየት የቀረበ

## ማሳሰቢያ

የኢትዮጵያ ሀገራችንን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ፣ በሕዝቧ መካከል ያለውን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የባህልና የሃይማኖት ትሥሥር በማጠናከር ዴሞክራሲያዊ አንድነትን ለመገንባት፣ የዘር ፖለቲካ አክትሞ ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ያብብ ዘንድ የሁሉም ዜጐቿ የሆነች ሀገር በልማትና ዕድገት ጎዳና ከኋላ ቀርነት ለመላቀቅ ጥረት ለማድረግ፣ በአሁኑ ወቅት በሀገሪቷ በተለይ በኦሮሞውና አማራው አካባቢ የተንቀሳቀሰውን ሕዝባዊ ትግል ለማገዝ፣ የህወሀት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ለአንዴም ለመጨረሻ የሚያበቃበትን ጊዜ ለማፋጠን በ "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!" ሕዝባዊ ንቅናቄ ስም ብቅ ብለናል።

የ "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!" ሕዝባዊ ንቅናቄን ድህረ የፖለቲካ ፕሮግራምና የድርጅቱን ህልውና ማሳወቂያ የሆነውን "ኢትዮጵያችን" ሠነድ ለውይይትና ለተጨማሪ ሀሳብ ማሰባሰቢያ ይረዳን ዘንድ ረቂቅ ሠነዱን ማሰራጨት አስፈላጊ መሆኑን አምነንበታል። በመሆኑም ይህ ሠነድ አግድሞሽ **ለአስተያየት የቀረበ** የሚል በቢጫ ያለበት ባለ 64 ገጽ መሆኑን በትህትና እናሳውቃለን።

ይህ ሠነድ ለሕዝብ አስተያየት የቀረበና በርካታ ነጥቦች መዳበር እንዳለባቸው ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። ሠነዱን የተለያየ አመለካከት፣ ችሎታ ያላቸውን ወገኖች ዕይታና ሀሳብ አግኝቶ መስተካከል እናደርግበት ዘንድ ለሕዝብ አስተያየት የተበተነ ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ ያለችበትንና የደረሰችበትን አስከፊ ችግር በመመልከት ምን ማድረግ እንደሚገባን ለቅድመ ዝግጅታችን አስተያየት ለማሰባሰብ የተዘጋጀ ሠነድ ነው። ሠነዱ በዋና ዋና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መሆን ያለበትን እንደ አማራጭ አስቀምጧል። ሠነዱ በሀገር ቤትና በውጭው ዓለም ላሉ ኢትዮጵያዊ ወገኖች ተለቋል። በውጭው ዓለም ከሀገራችን ከራቅን በርካታ ዓመታት ያስቆጠርን ብንኖርም፣ በተለያየ ምክንያት ዜግነታችንንም የቀየርን ትውልደ ኢትዮጵያ ብንኖርም፣ ሀገራችን ሀገራችን ናት። ወደድንም ጠላን ሁል ጊዜ እናነሳታለን፣ እንከራከርላታለን። የእናት የአባቶቻችን የቀደምት ኢትዮጵያውያን አደራ አለብንና ክፉዋን አንወድም፣ አደጋዋን አንፈልግም። ከዚህ አንፃር ዛሬ የተደቀነባትን የዘር፣ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ ስንመለከት ኢትዮጵያ ሀገራችን እንደ ኢትዮጵያ መቀጠሏ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል። ሀገራችን ተበታትና የተደገሰላትን የዘር፣ የሃይማኖትና የእርስ በርስ ግጭት አስተናጋጅ ከሆነች በኋላ ብንጮህ ብዙ ነገር ይበላሻልና አስፈሪ ነው። ቀድመን መድረስ ይኖርብናል። አሁን ምን አገባኝ? ብለን ቁጭ ብለን የምንመለከትበት ወቅት አይደለምና ነው፤ ሀገራችንን ለማዳንና ከወያኔ/ህወሀት ውድቀት በኋላ መደረግ ስለሚገባው ያለንን አማራጭ ለማቅረብና ከአሁኑ ተዘጋጅቶ መገኘት አስፈላጊ በመሆኑ ይህ መንደርደሪያ ሠነድ ተዘጋጅቷል።

መልካም ንባብ

ኢትዮጵያችን

አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ሕዝባዊ ንቅናቄ

ኢሜል ፡ ethiopiachen@gmail.com
info@ethiopiachen.org

ስልክ፡

ለአስተያየት የቀረበ

## 1.0 መቅድም

በሀገራችን ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪክ ውስጥ ብዙ ያልተፈቱ የታሪክ እንቆቅልሾች አሉ። እነኝህንም የታሪክ እንቆቅልሾች ለመፍታት የሞከረ ሀገር በቀል የታሪክ ሊቃውንት ለግዜው ደምቆ ባይታይም በውጭው ዓለም ሰዎች በራሳቸው ልምድና ተመክሮ የሠሩት ደፍራሳ የታሪክ ትርጉም እንቆቅልሹን እንኳን ባይፈታ ለእኛ የታሪክ ሙግት ጠቅሟል።

መቸም እንደ ኢትዮጵያ ባለ ታሪከ ብዙ ሀገር ሁሉም የሚስማማበት ወጥ የታሪክ ትርጉም ባለመኖሩ ሀሳባችን በዛ። ቁም ነገርም አጣን። ግና የሚበጀው ለዚህ እንቆቅልሽ መፍቻውን እስክናገኝ ሁላችንም ጥረታችንን ማሳየት በተገባን ነበር።

“አንድ ሀገር! አንድ ህዝብ!” ከሰው ሀገር በፊት ደምቆ፣ በልጦ፣ በግዜው ታላላቅ ከሚባሉት ሀገሮች አንዱ እንዳልነበረ፡ አሁን ድህ ከሚባሉት እንኳዋ የማይደርስ የድህ ድህ ሲሆን “ምን ነካን? ምን ሆንን?” ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው።

የአክሱምን ሀውልት ያቆመ፣ የፋሲልን ሕንጻ ያነጸ፣ ላሊበላን ከአንድ ወጥ ድንጋይ የቀረጸ፣ የሐረርን ግምብ የገነባ ህዝብ፡ ምነው! ከርሞ ከርሞ ከደሳሳ ጎጆ ውስጥ ሳይወጣ እዛው ቆሞ ቀረ።

በኢትዮጵያ ከ1000 ዓመት በፊት ሥረገላ፣ የመስኖ እርሻ፣ የመገበያያ ገንዘብ ነበር። ከ400 ዓመት በፊት የኢትዮጵያ ህዝብ ድልድይ ይሰራ ነበር። ታዲያ ይህ ሁሉ ጥበብ ስለምን ቆመ። ባለፉት 100 ዓመት ውስጥ ኢትዮጵያ የተለያዩ ታላላቅ ጦርነቶች ገጥማለች። ከነዚህም ውስጥ አጼ ቴዎድሮስ ከእንግሊዝ ጋር መቅደላ፣ አጼ ዮሐንስ ከድርቡሾች ጋር መተማና አጼ ምኒልክ ከጣሊያን ጋር ዐድዋ ላይ የተደረጉት ሚጠቀሱ ናቸው። በዐድዋ ጦርነት አፄ ምኒልክ በለስ ቀናቸውና በድል አድራጊነት ተወጡት። ውጊያው ሲታይ ግን የጣሊያን ጦር ዘመናዊ የነበረ፣ በታንክ፣ በመድፍ፣ በመትረየስ፣ በቦምብ እና በዘመናዊ ሥንቅና ትጥቅ፣ የመጓጓዣ ከባድ መኪና ይዞ ነበር ጦርነቱን ድል የተመታው። የኢትዮጵያ ጦር ግን በራሱ ስንቅና ትጥቅ፡ ትጥቁም ጎራዴ፣ ጦር እና ጋሻ፣ ከጠመንጃ በጣም ኋላ ቀር ከተባሉት ሆኖ፡ ጠመንጃ የታጠቀው ብዛቱ ከጎራዴ ጦርና ጋሻ ከያዘው ሠራዊት ትንሽ ነበር። ግን ጦርነትን የሚዋጋው መሳሪያ ሳይሆን ቁርጠኛነት ያለው ሠራዊት ነው፡ የሚባለው ዕውነት ሆኖ ድሉ የኢትዮጵያ ሆነ።

እንደገና ከ40 ዓመት በኋላ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን የኢትዮጵያ ጦር ማይጨው ላይ ከጣሊያን ጋር ሲገጥም፡ የጣሊያን ጦር ከበፊቱ በጣም ተሻሽሎ፣ ቦምብ ጣይ እና መትረየስ ተኳሽ አውሮፕላን፣ የመርዝ ጭስ ይዞ፣ ታንኩንም፣ መትረየሱንም፣ ቦምቡንም፣ ሁሉንም አሻሽሎ በመምጣቱ ጦርነቱ ለኢትዮጵያ ከዐድዋው ግዜ ትጥቅ አንድም ነገር ሳይጨምር እዛው እነበረበት ንቅንቅ ሳይል ለጠበቀው የኢትዮጵያ  ሠራዊት የቁም ቅዠት ነበር የሆነበት። ጦርነቱንም እንደ ዐድዋው ግዜ ሳይሆንልን ቀርቶ የሀገራችን ህዝብ ከዚህ በፊት አይቶት የማያውቀው የመከራና የስቃይ ግዜ የዘመን ግፍ እና መከራ ውስጥ ገባ። ታላቅም መስዋዕት ከፈለ። ስለዚህም ይህ ሆነ? ግን የእኛ ሕዝብ 40 ዓመት ሙሉ ምን ያደርግ ነበር? የሚገርም ነው። የረሳንን ዓለም እረስተን ለብዙ ዘመን አንቀላፋን።

የዓለም ህዝብ ዕቃውን በታላላቅ የዕቃ መጫኛ መርከብ፣ በትልልቅ የጭነት መኪና፣ በጭነት አውሮፕላን፣ ሲያጓጉዝ በአብዛኛው የሀገራችን ሰው ጓዙን በአህያና በቅሎ ነው የሚያጓጉዘው። የዓለም ህዝብ በድምጽ ፍጥነት ሲጓዝ፡ እኛ በበቅሎና ፈረስ  ፍጥነት ነው የምንጓዘው። የዓለም ህዝብ ምድርን አካሎ ጠፈርን ሲያሥስ፤ አብዛኛው የገራችን ህዝብ ከራሱ መንደር ውጪ ሌላ ዓለም ስለ መኖሩ በእርግጠኛነት አይናገርም። ይህ ሁሉ እውነት እንደሆነ አውቆ ለራስ አሁን እንደሚታየው “እሩቅ አሳቢ ቅርብ አዳሪ” እየሆን የዕንቧይ ካብ ለመገንባት ከምንታገል ለሁላችን መኩሪያ፣ ለልጆቻችን የምትተላለፍ ጠንካራ ኢትዮጵያን እንድናንጽ የዚህን ሰነድ ጥሪ በአንክሮት እንድናየው ይህ አጋጣሚ ይጋብዛል።

ሀገርና መንግስት ሲመሰረት፣ ሲገነባ በዚህች ዓለም የሰዎች ታሪክ በአብዛኛው የወራሪና የተወራሪ ታሪክ ነው። ይህም ጦርነት፣ ይህም ወረራ ነው አሁን የምናየውን ሀገርና መንግስት መልክ የሰጠው እንጂ፤ እንዲህ ዛሬ እንዳለው የተፈጠረ አይደለም። ኢትዮጵያ ሀገራችንም የዚህ ዓለም ሰዎች ባለፉበት ታሪክ ጎዳና ውስጥ እሷም አልፋለች። እዚህ ዓለም ውስጥ

ስላለች። በታሪክ ሌላው ዓለም ያለፈበትን ውጣ ውረድ ተምረን፡ ይህ ውጣ ውረድ በእኛ ሲደርስ ሌላ ትርጉም መስጠቱ፡ የተማርነው ትምርት ዘልቆን ነበር አያስብልም።

እንግዲህ ሰው ባለው እንጂ በሚመኘው አይኖርም። ስለሆነም የሀገራችን የታሪክ ምሁራን ሙሉ በሙሉ እንኳ ባይሆን ጥቂቶቹ የኢትዮጵያን እንቆቅልሻዊ ታሪክ አፈታቱን ባይስማሙበትም ለመከራከሪያ የሚሆን ቁም ነገር ጠቆም አርገዋል።

ከነዚህም ቁም ነገሮች፡

1. ኢትዮጵያ የሚለው ስም ጥንታዊ እንደሆነ፣
2. ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ በካርታ መልካዓምድሯ ምን እንደሚመስል እና
3. የኢትዮጵያ ግዛቶች የሚባሉትን በግልጽ አስቀምጠዋል

ከዚህም በመቀጠል **ኢትዮጵያዊው ማን ነው?  የኢትዮጵያ ታሪክስ የማን ታሪክ ነው?** ብለው ጥያቄ በማንሳት ታላላቅ ክርክሮችን ተከራክረዋል።

በክርክሮቻቸው የኢትዮጵያን ኤምፓየር፡ በኋላም የኢትዮጵያን ሀገርና መንግስት፡ በዚህም መንግስት ስር የነበሩ ግዛቶችን፡ የሀገሪቷ ነገስታቶች በግዛታቸው ላይ የነበራቸውን እምነት እና በዚህ መንግስት ሥር የነበረውም ህዝብ በግዜው የተነሱበትን የውጭ ወራሪዎች እንዴት በአንድነት እንደመታ እና ሀገሩን ከውጭ መጤ ጠላቶች እንደጠበቀ ይገልጻሉ።

በተለይ ከ1270 እስከ 1624 ዓ.ም. የ354 ዓመት የፊጂ ታሪካችን በእኛው ሰዎች በደንብ ተጽፈዋል። ቀጥሎም ከ1769 እስከ 1853 ዓ.ም. የመሳፍንት ዘመን የሚባለውን ታሪክ ሁኔታ እና የኢትዮጵያ ሀገርና መንግስት፡ እንዴት እንደተዳከመና የመንግስቱ ግዛቶች ከነገስታቱ ቁጥጥር ስር ውጭ እንደሆኑ እስከ 1855 የአፄ ቴዎድሮስ መነሻ ድረስ ጽፈዋል።

ከዚህ በኋላ ከዘመነ መሳፍንት መጨረሻ እና ከአፄ ቴዎድሮስ መነሻ እንደገና የኢትዮጵያን ማዕከላዊ መንግስት እንደ ጥንቱ ለመመስረት ያደረጉትን ተጋድሎ በመከተል አፄ ዮሐንስ፣ አፄ ምኒልክ፣ ከዛ አፄ ኃይለሥለሴ እስከ ሺህ 1966 ዓ.ም. የደርግ ዘመን መጀመሪያ ድረስ የኢትዮጵያን ማዕከላዊ መንግስት በመገንባት ዓላማውን አጠናክረዋል። ይህም ሀገር ግንባታ የታላላቅ ወገኖቻችን የአባቶቻችን፣ የእናቶቻችን ሕይወት፣ ንብረትና ጉልበታቸውን ወስዷል። በቀላሉ እዚህ አልተደረሰም። ይህን በማስተዋል የጥንቱን ታሪክ በአሁን ዘመን መመዘኛ መዳኘቱ አዋቂነት አይደለም ።

ወትሮም አበው "ትልቅ ሰው፡ ትልቅ አይወልድም" እንዲሉ ቀጣዩ ትውልድ የደረሰበት የኢትዮጵያ ሀገርና መንግስት ታሪክ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በኩል እየተናጠ፡ ኢትዮጵያዊውን የ1966 አብዮት ቢወልድም፡ ዋና ምልክቱ እንደ ግራዚያኒ ጨፍጫፊ የሆነው ወታደራዊው ደርግ የህዝቡን እንቅስቃሴ አኮላሸቶ፣ በሀገሪቱ የተነሳውን ቅራኔ ሁሉ በጦር ኃይል እና በጭፍጨፋ እመልሳለሁ ብሎ ሀገሪቱን ለዘረኛው ህወሀት/ኢሕአዴግ ጥሎ ሄደ፡፡ የኢትዮጵያም ሀገርና መንግስትነት ነቀዝ እየበላው መጣ። አንዳንዶቻችንም ዘመነ መሳፍንትን እየሻን ነው። ስለሆነም በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ሀገርና መንግስትነት ጥያቄ ላይ ብቻ ሳይሆን አደጋ ላይ ወድቋል። ይህም አደጋ እንደሚደርስ ኤርትራን ልብ ይሏል። እንግዲህ አጣዳፊነቱ ኃላፊነቱ ለተስማን ሁሉ ግዜው አሁን ነው።

ለኢትዮጵያ ህዝብ፡ ታላቅነትም ይሁን ሥልጣኔ አዲስ አይደለም። አክሱምን ያቆመ፣ ላሊበላን የቀረፀ፣ የፋሲልን ግምብ ያነጸ፣ የሐረርን ግምብ ያቆመ ህዝብ፣ ሌላም ሌላ በአሁኑ ባለንበት በ21ኛው ክፍለ ዘመን ዘላቂ የሆነ ስነ መንግስት፣ በሕገ መንግስት የሁሉን የግለሰብ/ዜጋ መብት እንዳይነካ የሚደነግግ፣ በዴሞክራሲው ትልቁ ትንሹን እንዳያጠቃው ህግ የሚያረግ፣ የሰውነትን ሰብአዊ መብት የተቀበለ፣ የህግ የበላይነትን ያፀደቀ ሀገርና መንግስት ማቋቋም አያቅተውም።

ስለዚህም በልባችን ቂምና በቀል ሳንይዝ፣ በየአንዳንዳችን ሙሉ ፍቃድ፡ ሀገራችንን ለታላቅ ሰላም፣ ለሰልጣኔ፣ ሰው የደረሰበት እንድትደርስ፣ በህብረት እንድንሰራ፣ ይህ ሠነድ ማንንም ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይጋብዛል።

## 3.0 መግቢያ

ኢትዮጵያ ሀገራችን በትንሹ ለአለፉት አራት አሥርተ ዓመታት እጅግ ውስብስብና ዘርፈ ብዙ ችግር ውስጥ ተዘፍቃለች። በደርግ 17 ዓመት አገዛዝና በህወሀት/ኢሕአዴግ 25 ዓመት አገዛዝ ከቀን ወደ ቀን የሀገራችንና የሕዝባችን ሁኔታ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል።

ዘመነ መሳፍንትና የዓፄዎቹ አገዛዝ የራሳቸው ደካማና ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩትም ኢትዮጵያን በዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ እንደ ሀገር ዳር ድንበሯ ታውቆ፣ ታፍራና ተከብራ ትኖር ዘንድ ያበረከቱት አስተዋጽዎ ቀላል አይደለም። የተለያየ እምነት በአንድነት አቅፋ እንድትጓዝ፣ የተለያዩ ጐሳዎች፣ ብሔር/ብሔረሰቦችን በአንድ ሀገር ጥላ ሥር ተከባብሮ እንዲኖር የተደረገው በኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ነበር። በአንድ ሰንደቅ ዓላማና በአንድ ሀገር ኢትዮጵያዊነትን ስሜት ያንፀባረቀ ትውልድ፣ ብሔራዊ ስሜትና ጀግንነት መለያው የሆነ ዜጋ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው በዓፄዎቹ አገዛዝ እንደነበር የበርካታ ጀግኖች ተግባር ምስክር ነው። ይህም ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜትና የማንነት መግለጫ አኩሪ ታሪካችን ነው፤ ኢትዮጵያ ነፃነቷንና ሉዓላዊነቷን ጠብቃ እንድትኖር ያደረጋት። በተለያየ ወቅት የተነሱ የውስጥ ቅራኔዎችንና የባዕድ ወረራዎችን ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ለማስቀጠል በተደረጉ ተጋድሎዎች ድል አድራጊነት ኢትዮጵያ ሀገራዊ መለያዋን ይዛ ቆይታለች።

ይህ ኢትዮጵያዊነት ስሜት ግና ለአለፉት አርባ ዓመታት እየተቀጠቀጠ ዛሬ "ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ትቀጥላለችን?" የሚለው ጥያቄ ጐላ ብሎ ወጥቷል። በሀገር ውስጥ በበቀሉ አምባገነን ገዥዎችና የውጭ ኃይሎች ያላቋረጠ ሤራ ሀገራችን በጐጥ ተከፋፍሎ፣ ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ተዳክሞ፣ በአፍሪካ አኩሪ ታሪክ የነበራት ሀገራችን ወደ መበታተንና ወደ እርስበርስ ግጭት እንድታመራ ጥርጊያው መንገድ እየተዘጋጀ ያለበት ሁኔታ ላይ ደርሰናል።

በሀገር አንድነትና በኢትዮጵያዊነት ስሜት ጥሩ ዝናን የተላበሱት ነገሥታት ደካማ ጐን ሀገሪቷን ወደ ልማት ጐዳና ለመውሰድና ድህውን ሕዝባቸውን አለመመልከት ችግራቸው ነበር። ይህ ኋላ ቀርነትን ተገን ያደረገ አገዛዝ ደግሞ የራሱ ችግር ነበረውና የተማረው ክፍልና ከጀግኖች አባትና እናቶቹ የወረሰውን ኢትዮጵያዊነትን አራማጁ ክፍል በአንድነት የሀገር አንድነቱና ብሔራዊ ስሜቱ እንደተጠበቀ ሕዝብ ከአስከፊው የድህነትና ኋላ ቀር አገዛዝ በመላቀቅ በሀገሩ መብትና ነፃነቱን ያገኝ ዘንድ በየጊዜው በተለያየ የሀገሪቷ ክልል የተነሱ አካባቢያዊና ሕዝባዊ ጥያቄዎች ጥርቅም ውጤት ሕዝባዊ ቁጣንና ማዕበልን በማስነሳት የካቲት 1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ተቀጣጥሎ ለአንዴም ለመጨረሻ ጊዜ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ንጉሣዊ የዘውድ አገዛዝ ገረሰሰው።

መጠነ ሰፊና ውስብስብ ችግሮችን አርግዞ የፈነዳው የየካቲት 66 አብዮት የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን አካቶና አማክሮ ዘላቂ መፍትሄ ለማግኘት መሸጋገሪያ ድልድይ ሊዘረጋ ባለመቻሉ የታጠቀው ወታደራዊ ክፍል እራሱን አሰባስቦና አደራጅቶ የሥልጣን ኮርቻ ላይ ወጣ። ተነስተው የነበሩ ሕዝባዊ አጀንዳዎችንና ጥያቄዎችን በማፈን ወይም ለራስ መጠቀሚያ በማድረግ "እኔ አውቅልሃለሁ" ባይ አምባገነን ወታደራዊ አገዛዝ በሀገሪቷ ላይ ነገሰ።

ደርግ በኢትዮጵያዊነት ስም እየማለና ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለበ የተነሳውን ሕዝባዊ ጥያቄ በጠመንጃው አንበረከከ። ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜትን የተላበሰ ትውልድ በመቅበር ኢትዮጵያ ሀገራችን ላይ ያነጣጠረው ዘመቻ የመጀመሪያው ምዕራፍ ተከፈተ። ደርግ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው የጮሁ ህፃናትን፣ ወጣቶችን፣ አዛውንትን ፆታ፣ ሃይማኖት፣ ዕድሜና ዘር ሳይለይ ጨፈጨፈ። የዚህ የ17 ዓመት የፋሺስት ደርግ ጭፍጨፋ ውጤት ከሀገሩ ኢትዮጵያ የሚሸሽ ዜጋ አበራከተ። ስለ ኢትዮጵያ በሚሞግት ትውልድ ምትክ ስለ እራስ የሚያስብ በቦታው ተተካ። የዚህ አስከፊ የጦርነትና የጭፍጨፋ ዘመን ውጤት ከኢትዮጵያዊነት ስሜት ይልቅ ጐሰኝነትን፣ ጠባብ ብሔረተኝነትን ወለደ። ሀገራችን የነበራትን አኩሪ ታሪክ ለመቅበርና ለማጥፋት መከፋፈል አንዱ ዘዴ ነውና ከኢትዮጵያዊነት አጀንዳ ይልቅ ቋንቋንና ዘረኝነትን ተገን ያደረገ አገዛዝ ደርግ በጭፍጨፋ ያመቻቸውንና የቀበረውን ኢትዮጵያዊነት ስሜት ድልድይ አድርገው በቀጣይነት በሀገርና በሕዝብ ላይ ተንጠለጠሉ።

በዘር ለተደራጁት ወያኔ/ህወሀት እና ሻቢያ ጊዜ ተመቻቸላቸው። መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በደርግ ላይ የቋጠረውን ጥላቻ መሰላል አድርገው ለሥልጣን በቁ። በህወሀት ስም መላ ኢትዮጵያን ማስተዳደር እንደማይችል የተረዳው የመለስ ዜናዊ ወያኔ

ለሥልጣን ኮርቻ እየተቃረበ በመጣበት ወቅት በአማራ፣ በኦሮሞ፣ በደቡብ ሕዝብ፣ ወዘተ ስም የቀፈቀፋቸውን የብሔር ድርጅቶች አሰባስቦ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) በማለት ህወሀት/ወያኔን ማዕከል ያደረገ አስተዳደሩን ኢትዮጵያዊነት ጭምብል አልብሶ ቀጠለ። ሻቢያ ኤርትራ ምድር ላይ ሰንደቁን ተከለ።

የወያኔ የጅምር አገዛዝ በቀጥታ ኢትዮጵያዊነት ላይ ያነጣጠረና የዘረፋ አገዛዝ ነው። የዘር ፖለቲካን ማዕከሉ ያደረገው አገዛዝ ሀገሪቷን በዘር በማካለል ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ዘረኝነት እንዲጠናከር በሩን ከፈተ። በረዥም ዕቅዱም ታዳጊ ሕፃናትና ወጣቶች ላይ ያነጣጠረ የዘረኝነት መርዙ ተረጨ። ዛሬ በሰላሳዎቹ/አርባዎቹ ዕድሜ ያሉ ወጣቶች በየቀዬው፣ በየትምህርት ቤቱ፣ በየመንደራቸው ኢትዮጵያዊ ስሜትን በማዳከም ዘረኝነት ሲሰበኩ ያደጉ ናቸው። ለሀገርና ሰንደቅ ዓላማ ተቆርቋሪ ዜጋ እንዳይበቅልባት የተደረገው የወያኔና የባዕዳን እኩይ ተግባር ዛሬ ላይ ሆነን ስናየው "እውን ሀገራችን እንደ ሀገር ትቀጥላለችን?" የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል።

ሀገራችን ዛሬ በህወሀት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ከገጠማት ፖለቲካዊ፣ ኤኮኖሚያዊና ማኅበረሰባዊ ቀውስ በተጨማሪ ዘረኝነት እጅጉን አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል። የወያኔ የመጨረሻው ደረጃ ኢትዮጵያን መበታተን ነውና ሲዘርፋትና ሲቸበችባት የኖረችውን ኢትዮጵያና ሕዝቧን እርስ በርስ በማናከስ ሀገሪቷ ትበታተን ዘንድ የቀበረው መርዝ ዛሬ ሊፈነዳ ዕይታው አለ። ይህንን አሳስቢ የሀገራችንን ሁኔታ ከግምት በማስገባት በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ትንተና በመስጠት "ምን መደረግ አለበት?" የሚለውንም በስተመጨረሻ በመመለስ ይህ ሠነድ ለአስተያየት ተዘጋጅቷል።

ሠነዱ ከተለያዩ ወገኖች በሚሰጡ አስተያየቶች ዳብሮ ለወደፊት የሀገራችን ሂደት አቅጣጫ ሰጪና አታጋይ ሠነድ ይሆናል የሚል ተስፋ አለን። "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!" ብሎ የተዘጋጀው ይህ ሠነድ ኢትዮጵያችን እንደ ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷና የግዛት አንድነቷ ተጠብቆ የሁሉም ዜጎቿ ያልተገደበ ዴሞክራሲያዊ መብት ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ማታገያና አቅጣጫ ሰጪ ይሆናል በሚል ነው። ሁሉም ዜጋ ሀገሬ ብሎ ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ይገነባ ዘንድ ሠነዱ ትኩረት ሰጥቶታል። ወደ ዕድገትና ልማት ጎዳና ሀገራችን ተጉዛ በልጆቿ ለልጆቿ ትሆን ዘንድ ይህ ሠነድ ለአስተያየት ቀርቧል።

## 3.0 ሀገር ፍቅርና ኢትዮጵያዊነት

ይህ ሰነድ የተዘጋጀው፡ ገንቢ ሙግት እንዲደረግበት ነው። ስለሆነም የሙግታችን ቀጠና፡ ግልጽ እንዲሆን እና ሙግታችንም በንድፈ ነገር እና በመነሻ ሰበብ እንዲደገፍ በማለት፡ ሀገር ፍቅር  እና ኢትዮጵያዊነት ምን ማለት እንደሆነ፡ ለዚህ ውይይት ለዛ፡ መተርጎሙ ግድ ይላል።

የሀገር ፍቅር የምንለው በግልም ይሁን በወል ያለንን ጠንካራ ስሜታዊ ፍቅር ሀገሬ ለምንለው ልዩ ቦታ ወይም ሀገርና መንግስት ያለንን ጥልቅ ትስሥር (ግንኙነት) የሚገልጥ ስሜት ነው። ሀገሬ ስለምንለው ልዩ ቦታ ክፉም ይሁን ደግ ነገር ስንሰማ በሆድ ብሶት የምንገልጸው ስሜት ማለት ነው። ይህ ስሜት የሚሰማው ሰው ያንን ሀገር ሀገሬ ይለዋል። በዛ ሀገር ላይ የሚታየው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚም ሆነ የማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ስሜትን ስለሚኮረኩሩ የዛ ሀገር የዜጋ ባለቤት የመሆንን ስሜት ያጠናክሩበታል። ይህ ስሜት የሀገር ፍቀር ሊባል ይችላል።

**ኢትዮጵያዊነትስ? ምን ማለት ነው?**

ኢትዮጵያዊነት ዜግነት ነው። የኢትዮጵያ ዜጋ መሆንን ነው የሚያመለክተው። ዜግነትስ ምንድን ነው? ዜግነት ተለዋጭ ነው። ዜግነት አንድም በመወለድ ወይም በህግ የሚገኝ ነው። የአንድ ሀገር መንግስት የዛ ሀገር መንግስት ዜጋ ለመሆን የሚያበቃ ህግ ነው ብሎ ያወጣውን ህግ በመቀበል፡ በራስ ሙሉ ፍቃድ የዛ ሀገር መንግስት ዜጋ መሆን ይቻላል። የአንድ ሀገር መንግስት ዜጋም መሆን የዜግነት መብትና ግዴታን መቀበል ግድ ነው። ታክስ መክፈል፣ የሀገሪቱን የፖለቲካል ምርጫ መካፈል፣ የሀገሪቱን ህገ መንግስት መቀበል፣ ሀገሪቱ ላይ የውጭ ወራሪ ጠላት በተነሳ ግዜ መከላከል ግዴታ ነው። ግን! ይህን በህግ የሚገኘውን የዜግነት መብት ሁሉም የዓለም መንግስታት ዕድሉን አይሰጡም። በአገራችን ኢትዮጵያም ህግ፡ ዜግነት

በመወለድ እንጂ በህግ አይገኝም። በመሆኑም እኛ የተወለድንባት እና እራሳችንን የኢትዮጵያ ዜጋ፡ ለምንል ሁሉ ስለ ኢትዮጵያ ያለን ፍቅር የሀገር ፍቅር ከሚለው ትርጉም ጋር አንድ ነው።

ይህ የዜግነት ፍቅር በኢትዮጵያ አዲስ መጤ ነገር አይደለም። ባለፉት 150 ዓመታት ውስጥ ይህችን አሁን የምናገዋልላትን ኢትዮጵያ ዳር ድንበሯን ለመጠበቅ የኢትዮጵያ ህዝብ በወል ሥንቁን ሰንቆ፣ ኢጋሰሱን ጭኖ፣ ጦሩን ሰብቆ፣ ጋሻውን ወድሮ፣ የመጡበትን የውጭ ወራሪዎች የራሱን፣ የልጁን፣ የወዳጁን፣ ሕይወት ሰጥቷል፣ ንብረቱን አፍሶበታል። አገራችን የምንላት ኢትዮጵያንም እዚህ አድርሰው ነበር። እኛ የልጅ ልጆቻቸው እስክንደርስ።

የሀገር ፍቅር ብዙ ጊዜ የሀገር አንድነትን በማስከበሩ ላይ ጐልቶ ቢታይም በሁሉም አቅጣጫ ማለትም በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውና በማኅበራዊ ህይወት በኩል የሚደረጉት ሀገራዊና ሕዝባዊ ጥረቶችም መዘንጋት የለባቸውም። በኪነ ጥበብ፣ በሥዕሉ፣ በስነ ሥሁፍ፣ በዝማሬና እንጉርጉሮ የሀገር ፍቅር ስሜቶች ይስተጋባሉ፣ ለትውልድ ይተላለፋሉ። በስፖርት መስክ ሀገራችንን ኢትዮጵያ በማስጠራት በተለይ በሩጫው በርካታዎች ይታወሳሉ። በሃይማኖቱም አባቶች ስለ ሀገር አንድነትና ስለ ሕዝባባቸው ይፀልያሉ።

የኢትዮጵያ ነገሥታት የሀገር ፍቅር ስሜትና የሰንደቅ ዓላማ ክብር በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ቦታ ይይዝ ዘንድ ጥረዋል። የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ክብር ለማስጠበቅ መሪዎቹ እራሳቸው መስዋዕትነት በመክፈል ለሀገሩ አጥንቱን የሚከሰክስ ደሙን የሚያፈስ ጀግና ትውልድ ተክተውልናል። የአባት እናቶቻችን ጀግንነት እያልን የምንጠቅስላቸው ለሕይወታቸው ክብር ስላለን ነው። ኢትዮጵያዊ ባህል እንዲዳብር፣ የራሳችን ቋንቋ ሳይበረዝ እንዲቀጥል፣ ኢትዮጵያዊነት ክብርና ኩራታችን መቼም እንዳይናድ በተግባር አስተምረውናል። ያልተፃፈላቸው በርካታ ጀግኖችን ለሀገር አበርክተዋል። ከምስኪኑ ድሀ አርሶ አደር፣ ላብ አደር ጨምሮ ሁሉም ዜጋ እምዬ ኢትዮጵያን እንዲወዳት፣ እንዲጠብቃት፣ እንዳይከዳት፣ ጡት ነካሽ ዜጋ እንዳይወለድ በባህል፣ በሃይማኖት፣ በግብረገብም አስተምረው አልፈዋል። በተለይ ከዘመነ መሳፍንት በኋላ የዓፄ ቴዎድሮስ አንድ መንግሥት ሥር የምትተዳደር ኢትዮጵያ ዕልምና ጥረት በዓፄ ዮሐንስና በዳግማዊ ዓፄ ምኒሊክ ተጠናክሮና ተግባር ላይ ውሎ ዛሬ ኢትዮጵያ የምንላትን ጥንታዊት ሀገር ተወለደች።

ወደ ዓፄ ኃ/ሥላሴ የተሸጋገረው ዘውዳዊ አገዛዝ እንደ ዓለም ተጨባጭ ሁኔታ ሀገሪቷን ወደ ልማትና እድገት ጎዳና ለመውሰድ ጥረቱ ቢኖርም የኋላ ቀሩ ፊውዳላዊ ሥርዓት እንቅፋት ሆኖበታል። ኢትዮጵያን በዓለም መንግሥታት ኅብረት መሥራች ያደረገ፣ በአፍሪካ ኅብረት ጀማሪና ከፍተኛውን ሚና እንድትጫወት ያደረገው፣ በዓለም የሰብአዊ መብት ሠነድ የመጀመሪያዋ ፈራሚ ሀገር በመሆን ሀገራችን ያላትን ዓለም አቀፋዊ ሚና አጉልተው ያሳዩት ዓፄ ኃይለሥላሴ ጥሩ ጎናቸው ሁሌም ሊጠቀስ ይገባዋል። ሀገሪቷ ወደ ዕድገትና ልማት አቅጣጫ ትጓዝ ዘንድ የተማረ የሰው ኃይል አስፈላጊነቱን በመረዳት የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ትምህርት ዕድል እንዲስፋፋ ጥረቱ ቢኖርም የሥርዓቱ ኋላ ቀርነትን አለመስተካከል ሀገሪቷን ሊለውጣት አልቻለም። እንደውም የሕዝቡ ግፍና መከራ እየባሰ መጣ። ሀገርና ሰንደቅ ዓላማውን አፍቃሪው ትውልድ በሕዝቡ ላይ የተከሰተው መረን የለቀቀ ግፍና ብዝበዛ አገዛዙንና የባላባታዊ ሥርዓቱን እንዲጠላ አደረገው። ለድህው የህብረተሰብ ክፍልና ለሀገሩ ዕድገት ቆርጦ የተነሳው ትውልድ እኩልነት መፈክሩ አድርጎ ሲያያዝ የመጣው ዘውዳዊ አገዛዝ ላይ ዐመጸ። ያ ትውልድ የሀገሪቷን ባህልና ሃይማኖት እንዴት ተመለከተው የሚለው የራሱ ትንታኔ ቢኖረውም ሀገሩን አፍቃሪ፣ ሰንደቅ ዓላማውን አክባሪ፣ ሕዝቡን ወዳድ ለመሆኑ የከፈለው መስዋዕትነት በታሪክ ማህደር ያለ ሀቅ ነው።

የሀገር ፍቅር ስሜት ሲያያዝ የመጣውን ኢትዮጵያ ባህላችንን፣ ሃይማኖታችንን፣ አኗኗራችንን፣ ሁሉንም ሕይወታችንን ያካተተ ነው። በእንግዳ ተቀባይነቷ ባዕድ ሳይቀር የፃፈላት ሀገራችን የዜግነት ኩራታችን ኢትዮጵያዊ ማንነታችን አሁንም ክብራችንና ኩራታችን መሆኑን ለትውልድ ማውረስ ይኖርብናል። ባዕዳን ወራሪ ኃይሎች ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛትነት ሊቀራመቱ አለመቻል አይደለም ለጥቁር ሕዝብ አርኣያ የሆነው የዐድዋ ድል ቂም በቀል ያኔ አይደለም ዛሬም አልወጣላቸውም። አፍሪካ ብቻ ሳትሆን ሌሎች በቅኝ የተያዙ ሀገራት በመሳሪያውና በጡንቻው ተማምኖ ሀገር በመውረር ያልዘራውን አንጡራ ሀብት ለመዝረፍ የመጣውን ወራሪ ኃይል መከላከል ሳይሆን፣ አላስነካ ማለት ብቻ ሳይሆን፣ ዳግም ዝር ሊል እንደማይችል ትምህርት የሆነበት ጦርነት ቢኖር ዐድዋ ነው። ዐድዋ የኢትዮጵያ ሳይሆን የዓለም ጥቁር ሕዝቦች ድል ነው። ነጮችን ያሸማቀቀ፣ ያሳፈረ ድል። ዐድዋ ኢትዮጵያዊነት ነው። ለዐድዋ የፈሰሰው ደም ለኢትዮጵያ ልምላሜ ነው። የኢትዮጵያ የግዛት ድንበር የተከለለው በጀግኖቿ አጥንት ነው። አሉላ ዶጋሌ፣ ዮሐንስ መተማ፣ ቴዎድሮስ መቅደላ. . . በርካታዎች በመላ

ኢትዮጵያ አጥር ሆነው ኢትዮጵያን በደማቸው ጠብቀዋል። የኢትዮጵያ ታሪክ በአብዛኛው ነገሥታቱ ላይ ቢያተኩርም በርካታ የኦሮሞ፣ የወላይታ፣ የሲዳማ፣ የአኝዋክ፣ የሀዲያ፣ የአፋር ወዘተ ልጆች ዛሬ ሀገራችን የምንላትን ኢትዮጵያ በደምና አጥንታቸው አስረክበውናል።

ይህች ናት ሀገራችን ኢትዮጵያ። በድህነታችን የምንወዳት፣ ተርበን ምንመግባት፣ ተራቁተን የምናለብሳት። ዘፍነን የማይወጣልን፣ ጨፍረንላት የማይደከመን፣ አንጎራጉረንላት ያደግን፣ በፀሎታችን ያለየናት፣ ይህች ናት ኢትዮጵያ የምንላት። ቆሎዋ ሚናፍቀን፣ ዳቦዋ ሚጣፍጠን፣ የከብቶቹ ጩኸት አብሮን ያለው፣ ወንዞች ተራሮቿ የአዋፍ ዝማሬ ሁሌም ሚመጣብን፣ የ13 ወር ፀጋ አደይ አበባዋ ልባስ ሆኖ ያደመቃት፣ የዓመት ባህል ጭፉ የሚያደምቃት ይች ናት ኢትዮጵያ መመለስ ያለባት። ማበብ የሚገባት። ዐልፋ ኦሜጋ ለዘላለም ትኑር ብለን የምንላት።

ዛሬ ይህችን ሀገር እንዴት እንጠብቃት? ምላሽ የሚሻው ጥያቄ ነው። "ተረት ተረት" ሲሉን "የጀግና በረት" ብለን ሕይወትን እንስጣት። ኢትዮጵያዊነትን ብሔራዊ ስሜት ለመሸርሸር በዘርና በጐጥ በመከፋፈል አንዱን ዘር በሌላው ለማነሳሳት፣ አንዱ ዘር ለሌላው እንደጠላት እንዲታይ በዘርና በሃይማኖት በመከፋፈል ሀገራችንን ለማዳከም የተወጠነው የባዕዳን ወራሪዎችና ጎረቤት ሀገሮች ውጥን ዛሬ በራሳችን ዜጎች እየተተገበረ ይገኛል። መንግስት ዘረኛ ሆኖ በሀገር ላይ ተነስቷል። ዛሬ "ኢትዮጵያ የእኛ አይደለችም" ባይ መንግስት ሆኗታል። ባዕዳን ዘራፊዎች በወረራ ያቃታቸውን ሀገራችንን ዛሬ መንግስት እየሰጣቸው ነው። ባዕዳን መበረዝ ያቃታቸውን ባህላችንን እና ሃይማኖታችንን ዛሬ መንግስት እያዳቀለላቸው ነው። ኢትዮጵያዊነት ኩራት ዛሬ በነጭ አምላኪነት ይተካ ዘንድ በመንግስት ደረጃ ተዘምቶባታል። ሀገር ተኪ ብቁ ዜጋ በቀጣዩም ትውልድ እንዳይኖር ሕፃናት በረሃብ እየተቀጡ ነው፣ በማደጎ እየተሸጡ ነው፣ ያለ ዕድሜአቸው ወደ ሴሰኝነት እየተነዱ ነው። ይህ በወያኔ/ህወሀት መርዘኛ አገዛዝ ሀገራችን ላይ ያንዣበበውን አደጋ "ወያኔ አብቅቶለታል" በማለት የምንንቀው አይደለም። ወያኔ ቢያበቃለት ችግሩ አላበቃም። የተቀበረው ፈንጂ መምከን አለበት። የዘረኝነት ፈንጂ ለማምከን ቁልፉ ኢትዮጵያዊነት ነው። ኢትዮጵያ ያለ ኢትዮጵያዊነት የትም አትደርስም። የሀገር መውደድን ስሜት ገንብተን ካልተነሳን "እንደ ተመኘኋት አገኘኋት" ላሉት "እንደ አቀድንላት በታተናት" የሚሉበት ግዜ እሩቅ አይሆንም። ከወያኔ መንግስት ባሻገር የተፈጠረላቸውን የዘረኝነት አጀንዳ ሕዝብና ሀገርን ለማጥፋት ሊጠቀሙበት ያሰፈሰፉትን ፍላጎታቸው ቅዠት ይሆን ዘንድ ኢትዮጵያዊነት አሸናፊ ነውና አጥብቀን መስበክ ይኖርብናል።

አዎ የንግሥት ማክዳ ኢትዮጵያ፣ የዓፄ ዮሐንስ፣ የዓፄ ቴዎድሮስ፣ የእምዬ ምኒልክ፣ የጎበና ዳጬ ኢትዮጵያ፣ የደረሰ ዱኪ ኢትዮጵያ፣ የያ ትውልድ ኢትዮጵያ ለማለት ከደፈርን ሀገርና ሕዝብ ከጎናችን ናቸው። ኢትዮጵያ ሀገራችን ብለን ሰንደቅ ዓላማዋን ለማውለብለብ የወደቁላትን ሰማዕታት ከፍ ማድረግ ይኖርብናል። ጊዜው የዘረኝነት ነው ብሎ ታሪክን ሳያገናዝቡ መቦራጨቅ በሀገራችንና ሕዝባችን ላይ ሊያደርስ የሚችለው ከፍተኛ አደጋ ቢታይም የመጨረሻው አሸናፊ ግና ኢትዮጵያዊነት እንደሚሆን ጥርጣሬ አይግባን።

በአሁኑ በዘመነ ህወሀት/ኢሕአዴግ ብል እየበላው የመጣው ኢትዮጵያዊነት በጎሰኝነት መተካቱ የእነኛ ሳይኖራቸው፣ ሳይመቻቸው ሀገሬ ኢትዮጵያ ብለው የሞቱላትን ጀግኖች እርም እንደመብላት ይቆጠራል። ስለሆነም! ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሳንቸኩል እረጋ ብለን "ችግራችን ምንድን ነው?" ብለን የምንጠይቅበት ሰዓት አሁን ነው። በሰለጠነው ዓለም አንድ ጉዳይ ሲከሽፍ ግንባታ የሚጀመረው ከስህተታቸው በመነሳት ነው። እኛም እንዲሁ እናደርግ ዘንድ የኢትዮጵያ ቀጣይ ዕድል ላይ ውይይት በማድረግ እንፈታው ዘንድ ሁላችን እንድንተጋ ይህ ሠነድ ይጋብዛል።

## 4.0 ጎሰኝነት፣ ዘረኝነትና ኢትዮጵያዊነት

ጎሰኛነትእና ኢትዮጵያዊነት፡ ምንድን ነው?። ጎሳ የምንለው ተመሳሳይነት ወይም ከሌላው ጎሳ የተለየ ጉልህ የመልክና ቁመና እና ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸውን የሰዎች ስብስብ የሚገልጽ ነው፡፡ ሳይንሳዊም ባይሆን።

ዘረኝነት ግን አንዱ ጎሳ(ዘር) ሌላውን ጎሳ (ዘር) ከራሱ ዝቅ አድርጎ የሚያይበት ሰው ሰራሽ ዘይቤ ነው።

ኢትዮጵያዊነት ግን ዜግነትን የአንድ ሀገርና መንግስት አባልነትን ያመለክታል።

ሀገር የምንለው የብዙ ጎሳዎች ጥርቅም በግዜ እና በኢኮኖሚ እድገት ምክንያት ተደበላልቀው በአንድ በተወሰነ የጂኦግራፊ ቦታ እና ክልል ለኗሪው የየግል ጥቅም በማለት ለራሳቸው የጋራ ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋ እና በሙሉ ፈቃደኝነት ሥርዓት አበጅተው የሚኖር ሕብረተሰብ ማለት ይሆናል።

እንዲህም ይባል እንጂ ይህ ዓለም የተመሰረተው አንዱ ጎሳ አንዱን ወርሮ በጦርነት ተሸጋሽጎ ነው። በመሆኑም ተቻችሎ የማይኖር ሀገር በዚህ በምንኖርበት ምድር የለም።

ወደ እኛ ሀገር ስንመጣ፡ የእኛ ሀገር ኢትዮጵያ ከሌላው ዓለም የተለየች የሚያደርጋት ነገር አለ? ያለ አይመስለንም። ታዲያ ስለምን! አሁን በሀገራችን በጎሳ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ይታይባታል? ይህ የጎሳ ፖለቲካ ምንጩ ምንድን ነው? ተቻችሎ ለሁላችን የሚሆን የጋራ አካፋይ መፍጠሩ ለምን ከምር አልታየንም? አስከፊ ባህሪ ነው። ለሀገራችን ጥሩ ነገር ከእኛ ከህዝቦቿ ሌላ፡ ሌላ ህዝብ ያስብልናል፣ ይሰጠናል ብለን እንጠብቃለን? መጠበቁ የዋህነት አይሆንም ወይ? ሆኖም! ይህ ጎሳን ማዕከሉ ያደረገ ጥያቄ በዓለም ላይ ብቅ ያለው ዓለም ከፊውዳሊዝም ሥርዓት ወደ ካፒታሊዝም በተሸጋገርበት ወቅት አዲሱ የካፒታሊዝም ሥርዓት የፊውዳሊዝምን የጎሳና የመሳፍንት ግዛት ክልሎች አጥፍቶ የተደበላለቀ የጎሳ ክምችት ሀገር እና ከተማ በመፍጠሩ፡ በተፈጠረው ድብልቅልቅ ሁኔታ ጥቅሜ ተነክቷል፣ ባህሌ ተረግጧል፣ አዲሱም ሥርዓት አድሎአዊ ነው፣ በማለት የሚነሳ ጥያቄ እንደሆነ፡ የሶሻሊስት ርዕዮት ተከታይ ተራማጆች "የብሔር ጥያቄ" ብለው ይተነትኑታል። ለዚህም በዋነኛነት የራሺያው እስታሊን በአገራችን በተለይ በያ ትውልድ ሲጠቀስ ኖሯል። ለነገሩ ይህ "የብሔር ጥያቄ" የሶሻሊስት ርዕዮት አራማጆች አካባቢ ነው ጎልቶ የሚታየው። በካፒታሊስቱ ዓለም፡ ይህ ጥያቄ የለም ማለት ሳይሆን ጥያቄው እንደ ዴሞክራሲ መበት ጥያቄ ነው የሚቀርበው። የሶሻሊስትም ምሁራን ቢሆኑ ይህ ጥያቄ የዴሞክራሲ ሙብት ጥያቄ አይደለም አይሉም፡፡ በዚህ ሁለቱም ካምፖች ጥያቄው የዴሞክራሲ ሙብት ጥያቄ ለመሆኑ ይስማማሉ። በመሆኑም ይህ ጥያቄ በካፒታሊስቱ ሀገር ተጠይቆ በህጋቸው መሰረት ለጥያቄው በህዝቡ ፍቃድ ላይ በመመርኮዝ መልስ ሲሰጥ ቆይቷል። ኩቤክዋንና ካናዳን በቅርቡ ብሪታንያንና እስኮትላንድን ልብ ይሏል። ይህ እነሱ ያደረጉት እኛን ለምን ያቅተናል? ለመማር ካሻን።

እንግዲህ ይህን የሌሎች ሀገር ሁኔታ በሀገራችን ላይ ለመፈተሽ ከሀገራችን ሁኔታ ጋር ለማዋደድ፣ ለመጥመድ መሞከር የተገባ ብልህነት ነው የሚመስለን። ልብ እንበል! የየካቲቱ ታላቅ አብዮት ያላሰበበት፣ ያላደረው፡ ሁኔታዎችን ከሀገሪቱ ታሪክ፣ ባህልና የዕድገት ደረጃ ጋር ማዋደድ እና ማዛመድ ስላቃተው ነው። ህብረተሰብ አዝጋሚ ነው። ፈጣን ተራማጅ አይደለም። ስለሆነም አሁን ሀገራችንን የወረረው የጎሳ ጥያቄ ዴሞክራሲያዊቷን ኢትዮጵያ ሳንገነባ እንዲህ በቀላሉ የምንመልሰው መልስ እንደማይሆን ግልጽ ነው። ምክንያቱም የተነሱት ጥያቄዎች የዲሞክራሲ ሙብት ጥያቄ በመሆናቸው የዴሞክራሲ ሙብት በሌለበት ሀገር የዴሞክራሲን ሙብት ጥያቄ እንዴት መመለስ ይቻላል? አይቻልም። በተለይ አሁን የሀገራችን ፖለቲካ ውሉ በጠፋበት ሰዓት፡ በሀገሪቱ የጎሳ ፖለቲካ የግዜው ፋሽን በሆነበት ግዜ፣ የዚህ ወረርሽኝ ሕመም አስተላላፊ የሆነው ህወሀት/ኢሕአዴግ ፍጹም ዘረኛ፣ እራሳቸውን በጎሳ እንጂ በኢትዮጵያዊነት የማያውቁ፣ በባዕድ ቋንቋ እንጂ በሀገራቸው ቋንቋ የማይናገሩ፣ ልባቸው ወደ ውጭው ዓለም ሄዶ የውጪ ሰው መጤ መሆንን የሚናፍቁ አዲስ ትውልድ ፈጥሯል። በሀገሪቱም "አሻሮ ይዞህ... ተጠጋ" እንዲሉ የአሁኑ ኢትዮጵያ ባለንብረቶች ህንድ፣ ዓረብ፣ ጃፓኖችና ቻይናዎች ሆነዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ የለበትም። ይህ እንደሆነ አውቀን እስከ ዛሬ ችግሮቻችንን ለመፍታት የተጠቀምንበትን የጸብ መንገድ ትተን በንድፈ ነገር እና መነሻ ሰበብ ባለው ሙግት እንተካው። አዲስ ፖለቲካዊ ባህል እንድንማር እንድናዳብር ይህ ሰነድ አንባቢውን በአክብሮት ይጋብዛል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ጐሳዎችና ብሔር/ብሔረሰቦች ሀገር ናት። አንዱ ብሔር ከሌላው ተዋልዶና ተከባብሮ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር የኖረባት ሀገራችን ዛሬ በ25 ዓመቱ የዘረኝነት አገዛዝ ሲሸረሸርና ሲቦረቦር አሁን አለንበት ደረጃ ደርሰናል። በዘውዳዊው አገዛዝ በየጊዜው የነበሩት ገዥዎች ከነበረው የስልጣኔ ኋላ ቀርነትና በኢትዮጵያ ላይ ካነጣጠሩት ወራሪዎች አንፃር የዘመናቸው ትኩረት የሀገሪቷን አንድነትና ሉዓላዊነት ማስከበር ላይ ያተኮረ ነበር ቢባል ያስኬዳል። የመንግሥታቸውንም ስልጣን ለማስጠበቅ በአመራራቸው ውስጥ የዘር ልዩነት ሳያደርጉ ሊገዙ እንደሞከሩ ሁሉ የነበረውም ጭቆና ዘርን ሳያማክል ሁሉንም ነበር። በዓፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ከኢትዮጵያዊነት ስሜት፣ ከሀገር ፍቅር ጋር እያቆጠቆጠ

የመጣው የመብት ጥያቄ ዘርና ሃይማኖት ሳይለይ ሁሉንም ያሳተፈ ቢሆንም የብሔረትኝነትም ጥያቄ ያቆጠቆጠበት ዘመን ነበር። አንዱ ብሔር ሌላውን ጨቋኝ ተደርጎ ለአደባባይ የቀረበው በዚሁ ትግል ውስጥ ነው። የነበሩት የገዥ ክፍሎችም የአማራውን ብሔር የበላይነት የያዙ የአማራ የገዥ መደብ ተደርገው የተፈረጁበት ይህ ወቅት ነበር "የብሔር/ብሔረሰቦችን ጥያቄ" ይዞ ብቅ ያለው። ኢትዮጵያ ሀገራችን ያቀፈችውን በርካታ ጎሳዎችና የቋንቋ ሀብትነት ሊገኝ የማይችል ብርቅዬ ስጦታ መሆኑን ተገንዝቦ ለሁሉም የሆነች ሀገር ለማበልጸግ ትግሉ አቅጣጫውን ቢተልምም አንዱ ብሔር በሌላው ያነጣጥር ዘንድ የዘር ጥያቄም በተጠናከረ መልኩ የተነሳው በዚሁ ወቅት ነው።

የኤርትራን እንቅስቃሴ አጣምሮ የኦሮሞ፣ "የሱማሌ አቦ"፣ የትግራይ ማንነትና የዘር ጥያቄ ብቅ ያለው በዚሁ ወቅት ነበር። ይህ የዘር ፖለቲካ በጊዜው የነበረው የመደብ ትግል ላይ የጣለው ጥቁር ነጥብ ቀላል አልነበረም። "የብሔር/ብሔረሰቦች መብት እስከመገንጠል" የሚለው መፈክር ከፍ ብሎ ማታገያ የሆነው በዚሁ ዘመን ነበር። ዛሬ የዚህ የዘር ፖለቲካ ጥያቄ አቅጣጫውን ስቶና የበላይነቱን ይዞ ኢትዮጵያችንን ለመበታተን ባዕዳን ኃይሎች የጠነሰሱልንን ጥንስስ ህወሀት ሲያፈላው ሌሎች ሊተገብሩት ጫፍ ላይ ደርሰው እናያለን።

ጦረኛው የደርግ አገዛዝ የየካቲት 66ን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አኮላሽቶ ማንነቱን በደም ካጨማለቀ በኋላ ምንም የማይሰማ ጭፍን "ሀገር ወዳድነቱን" በመሳሪያው ሊተገብር ያቀደው ዕቅድ አድማሱን አስፍቶ ሀገሪቷን በላ። የኤርትራንም ጥያቄ ሆነ በጊዜው ያቆጠቆጡትን የብሔር ድርጅቶች ማለትም በኦሮሞ፣ በትግራይና በሱማሌ ብሔር/ብሔረሰቦች ስም በመንቀሳቀስ ላይ የነበሩትን ድርጅቶች እንቅስቃሴ በጦር አጠፋለሁ በማለት ሕጻናትን፣ እናቶችንና አባቶችን ጨምሮ በቦምብ ከማጋየት በጊዜው የነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶችና ሕዝባዊ ወገኖች ቢመክሩበት ዛሬ እተደረሰበት አስከፊ ሁኔታ ላይ ባልተገኘን ነበር።

የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ደርግ የቀበረለትንና ያዳከመለትን የአንድነት ኃይል ተገን በማድረግ ይዞት የተነሳው የዘረኝነት ፖሊሲ ዛሬ የመጨረሻው መጀመሪያ ላይ ደርሷል። ለአለፉት 25 ዓመታት በቋንቋ፣ በባህል፣ በማንነት ጥያቄ ኢትዮጵያችን ተሸርሽራለች። ሰንደቅ ዓላማዋ ተዋርዷል፣ ጥንታዊ ቅርሶችዋ ተጥለዋል፣ የጀግንነት ታሪኳ ተበርዟል፣ ምድሯ ለባዕዳን ተቸብችቧል። ሀገር ማጥፋት ነውና የተያዘው ተኪ ትውልድ እንዳይኖር ሕፃናት ገና በጨቅላነታቸው በዘረኝነት እንዲዋጡ ተጥሯል፣ በርካታ ዜጐቿ የስደት ሕይወት ይገፉ ዘንድ በመላው ዓለም ተበትነዋል።

ደርግ በጦረኝነቱ፣ ወያኔ በዘረኝነቱ ያቦኩትና ያወሳሰቡት የብሔር/ብሔረሰቦች ችግር ተፈትቶ የሁሉም ዜጎቿ የሆነች ሀገር፤ ኢትዮጵያዊነት ስሜት ዳግም እንዲያብብና ትልቁን ድርሻውን ይይዝ ዘንድ "ሀገሬ ኢትዮጵያ" ብለን ከተነሳን ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ለማስቀጠላችን ጥርጣሬ አይግባን። ለዚህ ደግሞ ትልቁ ኃይል ልጆቿ ናቸውና ኢትዮጵያ ከማንም በላይ የኦሮሞው ሀገር መሆኗን ኦሮሞው፣ የትግራይ መሆኗን ትግሬው፣ የጉራጌው መሆኗን ጉራጌው፣ የጋምቤላው መሆኗን ጋምቤላው፣ የአማራው መሆኗን አማራው ወዘተ በጋራ ተያይዞ ከተነሳ በስማቸው ሊነግዱ ያሰፈሰፉ የብሔር/ብሔረሰብ ድርጅቶችና ዘረኛው ወያኔና ውድቀቷን የሚቋምጡ ሻቢያን ጨምሮ ባዕዳን ኃይሎችን የምናሳፍርበት ቀኑ ሩቅ አይሆንም።

የሁሉም ብሔር/ብሔረሰብ ባህል፣ ቋንቋ፣ መብት የተከበረባት ኢትዮጵያን እንደገና ለማንሳት ሁሉም ሀገሬ ብሎ ሊዘምርላት ይገባል። የአንዱ ጎሳ/ዘር/ብሔር ጥያቄ ከሌላው የተያያዘ መሆኑን ግንዛቤ በመውሰድ ትግሉ ያለው አምባገነንና ዘረኛ አገዛዝ ላይ ያነጣጠረ መሆን ይገባዋል። ድህነትን፣ ድንቁርናን፣ ረሃብን፣ በሽታን፣ ስደትን፣ እንግልትን፣ ግርፊያን፣ መታሰርን፣ መገደልን ወዘተ የሰቆቃ ዓይነቶችን እንድንሸከም ያደረገችን ሀገራችን ኢትዮጵያ ሳትሆን በየጊዜው የሰፈሩት አምባገነን አገዛዞች ችግር ነው። አሁን ደግሞ ዘረኛውና ሀገር በታኙ ወያኔ ያጋጋለው መሆኑን በመረዳት ሀገራችንን ከጥፋት መጠበቅና ማዳን የሁሉንም ዘር/ዜጋ የጋራ ጥረትን ይጠይቃል።

የኦሮሞ፣ የአማራው፣ የትግሬው፣ የጉራጌው፣ የሱማሌው፣ የሀድያው፣ የጋምቤላው፣ የደቡቡ፣ ያኣኘዋኩ፣ ወዘተ ጥያቄ አምባገነን አገዛዞች ላይ ያነጣጠረ የሁሉም ቤት የሆነችዋን ኢትዮጵያ እንደገና የማንሳትና የማደስ መሆን ይገባዋል። በዘር፣ በብሔር/ብሔረሰብ ላይ ያነጣጠረ ጥያቄ ሀገር ለመበተን አጀንዳ ከያዙ ኃይሎች፣ ወያኔን ጨምሮ መሰሪ ተንኮልና ሤራ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባዋል። ከእንግዲህ "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!" ብለን በጋራ መሰለፍ ይኖርብናል።

የወደፊቷ ኢትዮጵያ ኦሮሞው ከትግሬው ከአማራው ከጉራጌው ወዘተ ዘር ሳይመርጥ የሚኖርበት፣ የሚጋቡበት፣ ክልሉ ኢትዮጵያ የሆነችበት አንዱ በሌላው ባህልና ቋንቋ የሚኮራበት፣ ሁሉም ኢትዮጵያዬ ብሎ ሀገሩንና ሰንደቅ ዓላማውን ከፍ የሚያደርግበት ሀገር መመስረት የሁሉም ዜጋ ግዴታና ሀላፊነት ሊሆን ይገባዋል። የዘር ልዩነታችን ፀጋችን፣ የክርስትናና የእስልምና እምነት ቤታችን ኢትዮጵያ መሆኑን ማስተማር ይኖርብናል። የበርካታ ቋንቋና ዘር ባለሀብት መሆናችን ያኮራናልና ልዩነታችን ክብራችን ነው። ጥላ ከለላችን ኢትዮጵያ ናት። ኢትዮጵያ ኦሮሞ ልጆች፣ ትግሬ ልጆች፣ አማራ ልጆች፣ ጉራጌ ልጆች፣ ወላይታ ልጆች፣ ሱማሌ ተናጋሪ ልጆች፣ ከምባታ ልጆች ተዘርዝረው የማያልቁ ወዘተ ወዘተ አሏት። እናታቸው አንድ የሆነች ዘሮች። ቋንቋቸው ኢትዮጵያ የሆነች ዘሮች። ክልላቸው ኢትዮጵያ የሆነች ዘሮች። ልናጠናክረው የሚገባን አንድነታችን። ልዩነታችን አንድነታችን። "አንድ ሀገር! አንድ ህዝብ!" ብለን በጠላቶቻችን መቃብር ላይ ለምናለመልማት ኢትዮጵያችን በጋራ እንነሳ እንላለን።

## 5.0 ሃይማኖትና ኢትዮጵያዊነት

በአፈ ታሪክም ቢሆን የኢትዮጵያ ታሪክ ሦስት ሺህ ዘመናት ያስቆጠረና የክርስትናን እምነት ከማንም በቀደምትነት የተቀበለች እንደሆነች ታሪክ የዘገበው ነው። ሰሎሞናዊው ሥርወ መንግስት በንግስት ሳባ ልጅ በቀዳማዊ ምኒልክ መሠረቱን እንደጣለ ይነገራል። ኢትዮጵያ ከሰሎሞናዊ ንጉሳዊ አገዛዝ ወደ ዛጉዌ ሥርወ መንግስት ከዚያም በለይኩኖ አምላክ ንግስና እንደገና ወደ ሰሎሞናዊ የዘር ሐረግ ሲዛወር ቆይቶ በመካከሉ የጎንደር የየጁ ኦሮሞ ነገሥታት ሲያስተዳድሩ ቆይተው ኢትዮጵያ በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ትተዳደር ዘንድ ያላቸውን ራዕይ ይዘው በቀጣይነት ዓፄ ቴዎድሮስ፣ ዓፄ ዮሐንስና ዓፄ ምኒልክ እንደቅደም ተከተላቸው እስከ ዓፄ ኃይለሥላሴ ድረስ ኢትዮጵያን መርተዋል። በዚህ የአገዛዝ ሂደት ኢትዮጵያ ግዛቷን አስፍታ የያዘች ገናና ሀገር ብትሆንም በየጊዜው የሚፈታተኗት ባዕዳን ኃይሎችና የውስጥ ጠላቶች አላጣችም።

የኦርቶዶክስ ተዋህዶን መሠረት ያደረገች ኢትዮጵያ ከከባቢዎቿ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ሀገሮች ሳይቀር ፈተናዎች ገጥመዋታል። የቱርክ ኢምፓየርን መስፋፋት፣ የድርቡሾችን ጦርነት በተለያየ ጊዜ ልትጋፈጥ ተገዳለች። የሀገሪቷን ቅርሶች በተለይ ቤተ ክርስቲያንን እያወደመች በትንሹ ለአርባ ዓመታት ያወከችው አይሁዳይዋ ዮዲት ጉዲት ዘመን ለኢትዮጵያ ትልቁ የጥፋት ዘመን ነበር። በቀጣይነትም የግራኝ አህመድ የሥልጣን ዘመን እንዲሁ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ቅርሶችንና ተከታዮችን አውድሟል። በእነኚህ ሁለት ዘመኖች (ዮዲትና ግራኝ) ከፍተኛ ጉዳቶች በሀገራችን ቅርሶች ላይ ደርሷል። በተለይ የክርስትና ሃይማኖት አባቶች የቤተክህነትን ቅርሶችና ንብረቶች በተቻላቸው አቅም እየደበቁና እየተከላከሉ ለትውልድ ለማስተላለፍ ቢጥሩም ፈተናውና ችግሩ ዛሬም አላባራም።

የዓለም "ኃያላኖች" አፍሪካንና ደሀ አህጉራትን ለመቀራመትና በቅኝ ለመግዛት በነበራቸው ህልም ሀገራችን ኢትዮጵያ በጠንካራ ጀግኖቿ እና በሕዝቧ ጥንካሬና ብርታት ተከላክላና ሉዓላዊነቷን አስጠብቃ ብትኖርም የተከፈለው መስዋዕትነት ቀላል አይደለም። በዓፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት እንግሊዞች በርካታ የኢትዮጵያን ንብረቶች ዘርፈው ወደ ሀገራቸው አግዘዋል። በየቤተክርስቲያኑና አድባራቱ የነበሩ መጽሐፍትና ቅርሶች ተዘርፈው ሄደዋል። ከዚያም በዓፄ ቴዎድሮስ፣ በዓፄ ዮሐንስም ሆነ በዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ከውጭ አገራት ጋር መልካም ግንኙነት ለመመስረት በሚደረገው ዲፕሎማሳዊ ጉዞ ላይ በርካታ ንብረቶች እየተዘረፉ ሄደዋል። በመጨረሻም በአምስቱ ዘመን የኢጣሊያን ወረራ ዘመን እንዲሁ በርካታ ቅርሶቿንና ንብረቶቿን ኢትዮጵያ አጥታለች።

ኢትዮጵያ ከዛሬ አርባ ዓመታት በፊት መንግስትና የክርስትና ሃይማኖትን ባጣመረ ንጉሳዊ አገዛዝ ስትተዳደር ኖራለች። በዚህ ሂደት የእስልምና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ዘመን አንስቶ ኢትዮጵያ በአንድ ጥላ ስር እስላሙንና ክርስቲያኑን ይዛ ኖራለች። በእርግጥ በዓፄዎቹ አገዛዝ ዘመን የእስልምና ሃይማኖት በሀገራችን ጐልቶ የታየ አልነበረምና ነው ኢትዮጵያን የክርስቲያን ደሴት ያሰኛት። በተጨማሪም ነገስታቱ እያንዳንዱ እንቅስቃሴአቸው ከእምነት ጋር የተያያዘ ብቻ ሳይሆን ቤተ ክህነት ራሷ የመንግስቱ ተቋዳሽ ነበረች። በሌላም መልኩ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ቅርሶች የአክሱም ሐውልቶችን ጨምሮ በአካባቢው ያሉት አድባራት፣ የላሊበላ አድባራት፣ የዓፄ ፋሲል ግምብ፣ ከክርስትና እምነት ጋር ተያይዘው የተገነቡት አብያተ ክርስቲያን ቅርሶች በአጠቃላይ ኢትዮጵያ የክርስትና ሃይማኖት ቀደምት ተቀባይነቷን አጉልተው ያሳያሉ።

በነገስታቱ ዘመን ኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት የበላይነቱን የያዘበትና ጎልቶ የታየ ቢሆንም ለእስልምና ሃይማኖት ከበሬታን የሰጠችና እስላምና ክርስቲያኑ በጋራ የኖረባት ሀገር ነች። በተለይ የሃይማኖት ልዩነትን አስመልክቶ የየካቲት 1966 አብዮት ይዞት ብቅ ያለው ጥያቄ በሀገራችን ኢትዮጵያ የእስልምና ሃይማኖት በዓላት በብሔራዊ ደረጃ እንዲከበሩ ከማድረጉም በላይ ለእስልምና ሃይማኖት ተገቢውን ሥፍራ ተሰጥቶትና ሃይማኖትን ከመንግስት በመነጠል ሁሉም እንደ እምነቱ ተፈቃቅሮና ተከባብሮ የሚኖርባት የጋራ ሀገር ይዞ ተጉዟል።

በዘመነ ዓፄዎቹም ሆነ በቀጣይነት በትረ ሥልጣኑን ከያዙት ደርግም ሆነ ወያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመብት አኳያ የሁለቱም ሃይማኖት ተከታዮች ሆኑ ሃይማኖት የለሹ እኩል ነው የተበደለው። ረሃቡ፣ ችግሩ፣ መሃይምነቱ፣ ሰቆቃው፣ እስሩ፣ ግድያው፣ ስደቱ፣ ወዘተ ሃይማኖትንና ዘርን ተገን ሳያደርግ በአጠቃላይ ሁሉንም የሀገሪቷ ልጆች ያዳረሰ ነበር፤ ነውም። ከሕዝብ መንግስት ምስረታ፣ ከዴሞክራሲያ መብት አኳያ፣ ከእምነት ነፃነት አኳያ ጥያቄው የእስላሙም የክርስቲያኑም ነው። ዛሬ በወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የደረሰባትንና እየደረሰባት ያለውን ጥቃትና ጥፋት ማንም ሊታዘበው የሚችል ነው። በመላው ዓለማት ታቦት ይዘው የተሰደዱት ምህመናን ሀገራቸውን ጠልተው አይደለም። የችግሩና የመሰደዱ ደረጃ አድማሱን አስፍቶ የኢትዮጵያን ማንነት ገላጭ የሆኑት ቅርሶቿና እምነቶቿ ሁሉ ይጠፉ ዘንድ ባዕዳንና ሀገር በቀል ከሀዲዎች ውጥን ውጤት እንደሆነ መገመት አይከብድም።

ኢትዮጵያ እስልምናንና ክርስትና ሃይማኖትን ያካተተችና እስላምና ክርስቲያኑ ተከባብሮ፣ ተፈቃቅሮ፣ ተጋብቶ የኖረባት የሃይማኖት ሀገር ነች። ዛሬ ላይ ሆነን ስናየው ወይም ነበረች። ወያኔ ሀገሪቷን ከተቆጣጠረ ጊዜ አንስቶ ክርስቲያኑንና እስላሙን ለመከፋፈል ዋናውን መርዙን እየረጨ እስከዛሬ አለ። በሀገራችን የሃይማኖት ብጥብጥ ይነሳ ዘንድ በአንዳንድ አካባቢዎች ጥረት አድርጓል። ወያኔ በዓለማችን እየታየ ካለው እስልምና ተከታይ ነን ባዮች አክራሪዎች ጋር በማያያዝ በሀገራችን በሃይማኖት ስም አሸባሪነት ያቆጠቁጥ ዘንድ ጥረት ያደርጋል። ዛሬ በእስላሙ ሕብረተሰብ ዘንድ እየተነሱ ያሉትን የመብት ጥያቄዎች በአሸባሪነት ስም ለመፈረጅ ይጥራል።

አሁን ያለው የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ኢትዮጵያን ለማጥፋትና ለማዳከም ተልሞ የመጣ በኢትዮጵያ መንግስታት ታሪክ አንፃር "መንግስተ ጥፋት" ቢባል አያንሰውም። ተከባብሮ የኖረውን የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት መካከል ቅራኔ ለመፍጠርና የሃይማኖት ግጭቶች ይነሱ ዘንድ ይጥራል፣ ጥሯል። ኢትዮጵያ ውስጥ የሃይማኖት ጦርነት በማስነሳት የዕልቂት ዘመቻ ይከሰት ዘንድ ኢትዮጵያን ከማጥፋት ትልሙ አንዱ ነውና በሁለቱም በኩል ያሉት የሃይማኖቱ መሪዎችና ተከታዮች ነቅተው መጥበቅ ይኖርባቸዋል። የኢትዮጵያችን ችግር የመልካም አገዛዝ ችግር እንጂ በክርስቲያኑና በእስላሙ ወገኖች መካከል ምንም ዓይነት ቅራኔ አለመኖሩን መረዳት አስፈላጊ ነው። የወያኔና ባዕዳን መሰሪ ተልዕኮ ወጥመዳቸው ውስጥ ከገባንላቸው ሀገራችን እንደሀገር እንዳትቀጥል የጠነሰሱት እኩይ ዕቅዳቸው ተግባራዊ ይሆንላቸዋልና ሁላችንም ሀገራችንን መመልከት ይኖርብናል። ሁለቱንም ሃይማኖቶች አቅፋና አስተቃቅፋ የኖረች ሀገራችን አንድነቷ የሚጠበቀው አሁንም በሁለቱ እምነቶች ጠንካራ ፀሎት፣ ድጋፍና ትብብር መሆኑን የሃይማኖት አባቶች መስበክ፣ ምህመናኑና አማኙ የእምነቱ ችግር ፈጣሪ በየጊዜው ያጋጠሙ አገዛዞች እንጂ ኢትዮጵያ ሀገራቸው እንዳልሆነች ሊያሰምሩበት ይገባል። እስላሙ ለሚጠይቀው የመብት ጥያቄ ክርስቲያኑም ይጠይቃልና። የክርስቲያኑ በደል እስላሙም ውስጥ አለ። እስላሙ ሲደበደብ ክርስቲያኑም ይደማል። ለሀገራችን መኖርና ለአንድነቷ እስላሙም ክርስቲያኑም አንድ ነን። ከዚህ አንፃር ሀገራችን የገጠማትን አደጋ በመመልከት ለሀገራችን መኖር ሃይማኖታችን፣ ለሃይማኖታችን መኖር ሀገራችን ሚና አላቸውና ለአጥፊዎች ሳንጋለጥ ምንጊዜም እጅ ለእጅ ተያይዞ መታገሉ፣ መጓዙ ከሕዝብ ድል በኋላም ሀገርን በጋራ ማገዙ የሁለቱም ሃይማኖቶች ህግጋትና ስብከት መሆን ይገባዋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ የሃይማኖት ሀገር ናት። የክርስቲያን፣ የእስላም እንዲሁም በተፈጥሮ በጣኦት፣ አሊያም በምንም የማያምኑ ህዝቦች የሚኖሩባት ሀገር ብትሆንም ሁሉም ህዝቦቿ ለአገራቸው አንድነት፣ ደህንነት፣ እራሳቸውን ሰውተዋል። በመሆኑም የወደፊቷ ኢትዮጵያ ለሁሉም ዜጋዎቿ ዕምነት እኩል እንድትሆን "መንግስትና ሃይማኖት የተለዩ ተቋዋም ናቸው" የሚለውን አቻቻይ መመሪያ ኢትዮጵያ ትቀበላለች። በአገሪቱ ውስጥ የሚንቀሳቀስ ማንኛውም የሃይማኖት ተቋም ከሀገሪቱ ህገ መንግስት ስር ነው። ከሀገሪቱ ህገ መንግስት ውጪ የበላይ ዳኛ በአገሪቱ ላይ የለም። ስለሆነም ሃይማኖት እና መንግስት እርስበርሳቸው ጣልቃ ሳይገባቡ በራሳቸው ነፃነት በእኩልነት የየራሳቸውን ሀላፊነት የሚሰሩበት ስነ ስርዓት እንዲፈጠር ይህ ሰነድ ሀሳብ ያቀርባል።

## 6.0 በረሃብ መግዛትና ትውልድ ማቀጨጭ

በወያኔ 25 ዓመታት አገዛዝ አብዛኛው የሀገራች ሕዝብ እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ ኑሮውን ይገፋል። ኢትዮጵያ ዛሬ ቁርስ፣ ምሳና እራት በአግባቡ የማይበላባት ሀገር ሆናለች። ቁርስ ሳይበሉ ወደ ትምህርት ቤት የሚላኩ ሕፃናት ከትምህርቱ ይልቅ ሲመለሱ ስለሚበሉት ሲያሰላስሉ እንዲያድጉ በማድረግ ሆን ተብሎ በምግብ ትውልድ ማቀጨጭ የወያኔ አንዱ ፖሊሲ ሆኗል። ሕዝቡ ከሆዱ ሌላ እንዳያስብ ረሀብ ተችሮታል። ሕዝብን አሜንና ጾጥ ለጥ ብሎ ይገዛ ዘንድ በችጋር መጥበስ የዘረኛው ወያኔ ተግባር ሆኗል። ወጣቶች እጅግ በሚያሳዝንና በሚያሳፍር ሁኔታ የሆቴል ቤቶችን ትርፍራፊ ምግብ እየተቸበቸበ ተመጋቢ ሆነዋል። ሌሎችም ከቆሻሻ ገንዳ የተጣለ ምግብ ለመመገብ የተገደዱበት ሁኔታ በሀገራችን የተለመደ ከመሆኑ የተነሳ አያስደነግጥም። እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ለመመገብ ገላቸውንና ስብህናቸውን በየመንገዱና ቡና ቤቱ የሚቸረችሩት እህቶቻችን ቁጥር ሕፃናትን ጨምሮ በሚዘገንን ሁኔታ ተበራክቷል። የወያኔ ሕዝብን አዳክሞና አስርቦ የመግዛት ፖሊሲ በተጨማሪ ኢትዮጵያዊነት ስሜት እንዲጠፋና ስደተኛውና ሀገሩን እየጣለ የሚሄደው ይበራከት ዘንድ አስተዋጽዎ ማድረጉ ዓመታት ያስቆጠረ ተግባር ነው። የስቃዩን መከራና አደገኝነት እየተረዱት ከሞት አይሻል ሕይወት እያሉ ወደ አረቡ ሀገር የሚጓዙት እህቶቻችን ቁጥር ቀላል አይደለም። በየመንገዱ የሚረግፉት፣ በውቅያኖስ የሚሰምጡትን ቤቱ ይቁጠራቸው።

ወያኔ ልማትንና ዕድገትን ተገን ያደረገ የኢኮኖሚ ዕቅድ ከማራመድ ይልቅ የዝርፊያ ሽሚያ ላይ በማተኮሩ ሀገራችን ዛሬ እደረሰችበት በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝቧ ለረሃብ ሊዳረግ የቻሉበትን ሁኔታ እናያለን። ለውጭ ባዕዳን በሊዝና በሌላ እየተቸበቸበ ያለው የሀገሪቷ ለም መሬት ኢትዮጵያን ለዕዳና ለውስብስብ ችግር እየዳረጋት ነው። የውጭ ባለሀብቶች በሀገራችን የሚያመርቱትን የእኛ ሕዝብ እየተራበ ለሀገራቸውና ለውጭ ገበያ ያወጣሉ። ሀገራችን የውጭ ሽቀጦች በተለይ የቻይና መርካቶ ሆናለች። የወያኔ ቱጃሮች ኪሳቸውን በዶላር ለማዳበር ምርቶቻችንን ከሕጻናትና ከሕዝባችን አፍ እየነጠቁ ወደ ውጭው ዓለም እየላኩ ይገኛሉ። ሕዝባችን የዕለት ኑሮውን ሲያስብ የቀን ጉርሻውን ሲያሰላ ብቻ ይኖር ዘንድ በረሃብ አለንጋ እየገረፉት ይገኛሉ። የገንዘባችን መግዛት አቅም መዳከም ለወያኔ ዕድገት ሆኗል። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዕድገት የአሥር ሚሊዮን ሕዝብ ለረሀብና አደጋ መጋለጥ ሆኗል። ሙስናና ዝርፊያ ያጠገባቸው ወያኔና ቱጃሮቹ ቀን ተሌት ሕዝባችን ላይ ይጨፍራሉ፣ በስካርና ዝሙት ሀገር ላይ ይስቃሉ። የዘረፉት የሀገርና ሕዝብ ሀብት ማንነታቸውን አስቷቸዋል። በሀገርና ሕዝብ ሕመም ይዝናናሉ። ሀገርና ህዝብ ላይ እያላገጡ ናቸውና፣ የረሃባችን መንስዔ ናቸውና፣ በሽታና ድህነት አሽክመውናልና እጅ ለእጅ ተያይዘን በአንድነት ልንታገላቸው መሰባሰቢያ አጀንዳችንን ኢትዮጵያ እናድርግ።

ለወያኔ ሀገር ገንዘቡ ነውና ይህንን በሀገርና ሕዝብ ላይ የመጣ መቅሰፍት በኢትዮጵያዊነት መንፈስና በጀግንነት ካልመከትነው እነሱ እፍረት የላቸውም። ለወራሪ ያልተበገረ ክንዳችን ለሀገር በቀል ዘራፊዎችና፣ አጥፊዎች መበገር የለበትምና "አንድ ሕዝብ! አንድ ሀገር!" ብለን እንነሳ። በሕዝባችን ላይ የደረሰው ኤኮኖሚያዊ ችግር እጅግ ብዙ ሊፃፍበት ይችላል፤ የችግሩ ገፈት ቀማሽ ያለበትን ችግር በየቤቱ ያውቀዋል። የወያኔ አገዛዝ በ25 ዓመት ዕድሜው የሕዝቡን ስቃይ ማየት፣ የሕፃናት መነሳቀል፣ የወጣቶች ረሀብ፣ የአዛውንቶች መቆራመት የዕቅዳቸው አንዱ ክፍል ነውና ይህን በሀገር ላይ የመጣ ዘመነ ጥፋት ድል ለማድረግ "አንድ ሕዝብ! አንድ ሀገር!" ሕዝባዊ ንቅናቄን በማጠናከር መሰባሰብ ይኖርብናል እንላለን።

## 7.0 በባህል አኳያ

ባህል የአንድነት መሠረት ነው። ለምሳሌ የተለያዩ ምግቦቻችን፣ መጠጦቻችን፣ አለባበሶቻችን፣ አጨፋፈራችን፣ በሀዘን ለቅሶአችን፣ በደስታ ሠርጋችን፣ የእርሻ መሣሪያዎቻችን፣ የሙዚቃ መሣሪያዎቻችን፣ ስለ ልጅ አስተዳደግና ቤተሰባዊ አኗኗራችን የአብዛኛው ጎሳ ተወራራሽና ተዛማጅነት ያለው ነው። እነዚህም የተለያዩ እሴቶች ለአንደነታችን ማጠናከሪያ ማገርና ግድግዳ ናቸው።

ኢትዮጵያ ሀገራችን የአኩሪ ባህሎችና ቋንቋዎች ሀገር ናት። ኢትዮጵያዊነት ሰው አክባሪነት፣ እንግዳ ተቀባይነት፣ ኩሩነትና ጀግነት መሆኑ ተረት ተረት ሆኖ ይቀር ዘንድ የወያኔ 25 ዓመታት አገዛዝ ውጤት እያስመዘገበ መምጣቱ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ዛሬ ባዕዳንን አፍቃሪ፣ ለባዕዳን ሽቀጥ ተሸካሚ፣ ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ውጫዊነት የሚመኝ ትውልድ


አንድ ሀገር አንድ ሕዝብ

እየተፈለፈለ አለበት ዘመን ላይ ደርሰናል። ከራሳችን ባህል ይልቅ የባዕዳንን ማክበርና ማስገባት ስልጣኔ አድርገነዋል። ከራሳችን ቋንቋ ይልቅ በባዕዳኑ መፃፍና መናገር ከሀገር በላይ ያደረገን መስሎናል። ሆቴሎች፣ የንግድ መደብሮች ወዘተ ከኢትዮጵያዊነት ስያሜ ይልቅ የባዕዳን ቋንቋ ሲይዙ ታዋቂ ጀግኖቻችን ተቀብረው ይቀሩ ዘንዳ በባዕዳን ተወላጆች ስም ተሰይመው ማየቱ ተበራክቷል። ኢትዮጵያዊነትን ባህል በማዳከምና በሂደት በባዕዳን ባህል ይዋጥ ዘንድ የሚደረገው ጉዞ ኢትዮጵያን ከማጥፋት ትልሞች አንዱ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል።

የኢትዮጵያ ያካተተችው በርካታ ባህሎች፣ ቋንቋዎች የጋራ ሀብታችን መሆናቸውን ተረድተን በጋራ ልንጠብቃቸውና ልናዳብራቸው ይገባል። የአንዱ ባህል የሌላው እዲሆን የሁላችንም ሃላፊነትና ጥረት ያስፈልጋል። የኦሮሞው ባህል የትግሬው፣ የትግሬው ባህል የኦሮሞው የሌላውም እንዲሁ ሲሆን ሁሉም ባህላችን የሀገርና ህዝብ ሀብት ይሆናሉ። ይህንን ደግሞ ከግብ የምናደርሰው የዚያኛውም፣ የዚህኛውም ሁሉም የእኛ ባህል ነው ብለን ስንቀበል ነው። እጅግ ኮርተንበት ዓለም ሊደነቅበት የሚችል የተቀበሩ ባህሎቻችን ብቅ የሚሉት በመከፋፈል ሳይሆን በጋራ ስንይዛቸው ነው። እንደ ብርቅዬ የተፈጥሮ ሀብታችን፣ የዱር አራዊትና አህዋፎቻችን የባህል ቅርሳችንንም ልንጠብቅና ልናሳምር የምንችለው ኢትዮጵያን ብለን ስንጮህ ነው። ዛሬ መጥኔ ለወያኔ መጤና የባዕዳን ባህል ሀገራችንንና ሕዝባችንን ሲወር ከመከራችን አንዱ መሆኑን ተገንዝበን ሀገራችንን እናድን ስንል ባህላችንን አናስወርር ማለታችን እንደሆነ ግልጽ መሆን አለበት።

የተለያዩ ባህላዊ ሙዚቃዎቻችንን፣ አለባበሳችንን፣ አመጋገባችንን፣ አኗኗራችንን በሀገራችን ኢትዮጵያ፣ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ውስጥ ሊዳብርና ሊያድግ ይገባዋል። የእኔ ብቻ ነው የምንለው አይደለም። የሀገራችን ሀብት የሕዝባችን ሀብት የሁሉም ኢትዮጵያውያን ናቸው። የተበታተነችና የተከፋፈለች ኢትዮጵያ ለባዕዳን ዘራፊዎችና ሀገር በቀል አጥፊዎች የተመቻቸች ናትና፣ ዘርን ተገን አድርገው ለመከፋፈል በባህላችን ላይ መዝመቱ አንዱ አካሄዳቸው ነውና፣ አኩሪ ባህላችንን ልንጠብቅና ልናሳድግ የምንችለው "አንድ ሕዝብ! አንድ ሀገር!" ብለን ስንነሳ ነው።

ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ለመሸርሸር ዘመቻው እየተካሄደ ያለው ባህልን፣ ቋንቋን፣ ዘርን፣ ሃይማኖትን፣ ክልልን፣ ተገን አድርጎ መሆኑን ተገንዝበን ያሉትን መለስተኛ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ቅራኔዎች ወደ ጎን አድርገን የጋራ ሀገራችንን ዳግም ልናድሳት መዘጋጀት ይኖርብናል።

## 8.0 ኢትዮጵያና ኤርትራ

በዓፄ ኃይለሥላሴ ዘመን መነሻው ያደረገው የኤርትራ ጥያቄ በደርግ አገዛዝ ሽንፈትና በወያኔ ተባባሪነት ኤርትራ ከኢትዮጵያ በመገንጠል በ1983 ዓ.ም. ተደምድሟል። የኤርትራን የመገንጠል ጥያቄ ተግባራዊ ለማድረግ "ኢትዮጵያ ኤርትራን በቅኝ ይዛለች" የሚለው የፈጠራ ታሪክም ይሁን "የብሔር/ብሔረሰቦች መብት እስከመገንጠል" መፈክር ሻቢያ በመሳሪያው ኤርትራን እንደ ሀገር ካስቆጠረ 25 ዓመት ሞልቶታል። የኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠል ጉዳይ የጉልበትና የይስሙላ ምርጫ መሆኑ ነበር ዋናው ተቃውሞ። በኤርትራም ሆነ በቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃ ውይይት ከታሪክ አንፃር፣ ከሁለቱ ሕዝቦች የተሳሰረ የባህል፣ ቋንቋ እና ሌሎች ጉዳዮች አኳያ በአግባቡ ጥናት ተደርጎ ባለመካሄዱ በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዘንድ ተቃውሞ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ለዚህም የህወሀት/ኢሕአዴግ አገዛዝ በታሪክ ተጠያቂ ያደርገዋል። ወያኔ እንደ መንግስትነት የራሱ አካል የሆነች ኤርትራን መገንጠል በተባበሩት መንግስታት እውቅና ከመስጠት አልፎ አሰብ ወደብ ለኤርትራ እንዲሆን ያደረገ ኢትዮጵያ ላይ ከጅምሩ የዶለተ የዘመነ ጥፋት ቡድን ነው።

በደርግ ዘመን የኤርትራ ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ ይፈታ ዘንድ ከተለያዩ ድርጅቶችና አካላት ጥያቄ ቢቀርብም ደርግ ከጦርነት ሌላ አማራጭ ሊታየው አልቻለም። ይህም ሁኔታ በኤርትራ የሚንቀሳቀሰውን ኃይል ይበልጥ ትግሉን እንዲያጠነክር ረድቶታል። በተጨማሪም ደርግ በሌሎቹ የሀገሪቷ ግዛቶች የሚያደርገው ኢ-ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርና ጭፍጨፋ የሕዝብ ድጋፍን ሲያሳጣው በተቃራኒው ለሻቢያና ወያኔ መጠናከር አመቺ ሁኔታ ፈጠረላቸው።

በሌላም በኩል በያ ትውልድ እንቅስቃሴ ይቀነቀን የነበረው "የብሔር/ብሔረሰቦች መብት እስከ መገንጠል" በሚል ከውጭ የተቀዳው ንድፈ ሃሳብ ማታገያ መፈክር መሆን ዛሬ ሀገር ላስገነጠሉት ሻቢያና ወያኔ የሞራል ድጋፍ እንደነበር መሠመር

ይኖርበታል። ይህ መፈክር ኤርትራን ከማስገንጠል አልፎ ዛሬም ለህወሀት/ወያኔ የዘር ፖለቲካ ተግባራዊ መሆንና ለሌሎች በዘር የተደራጁ ድርጅቶች አሁንም ሲያቀነቅኑት ይስተዋላል። የዚህ መፈክር አተረጓገምና አስተዋጽዎ ኢትዮጵያን ለማዳከምና ለመከፋፈል አመቺነ በመሆኑ በሙብት ስም ያመጣውን ጉዳትና የተደቀነብንን አደጋ በሚገባ በመመርመር የዜጎች ዴሞክራሲያዊ አንድነት ይዳብር ዘንድ የሁሉንም የጋራ ጥረት እንደሚጠይቅ ግልጽ ነው።

በ1983 ዓ.ም. ሥልጣን ላይ የተቆናጠጡት ሻቢያና ወያኔ ገና ከጅምሩ ኢትዮጵያዊነት ላይ አነጣጥረው ሀገሪቷን በመከፋፈል ለማዳከም ተልዕኳቸውን ይዘው አደባባይ ብቅ አሉ። ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የኤርትራ ነፃነት ታወጀ። ይባስ ተብሎም አግባብነት የሌለው አሰብ ሙሉ በሙሉ ለኤርትራ ተቸረ። ሻቢያና ወያኔ በጋራ ሀገርን መዝረፍና ሕዝብን ማሰቃየት ተያያዙት። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ውጭ እንደ ሀገር ለመኖር የተፈጥሮ ሀብቷም ሆነ ተፈጥሮአዊ ፀጋ የላትምና ከወያኔ በስተጀርባ ኢትዮጵያን ተቆጣጥራ ልትመዘብርና ልትገዛ ቋመጠች። ሌላውን የኢትዮጵያ ግዛት በማተራመስና በማዳከም ሻቢያ በዘራፊነት ኤርትራን ለማበልፀግ፣ ወያኔ/ህወሀት ትግራይን ባስቀደመ ብልጽግና የዘረጉት የጋራ አጀንዳቸው አሥር ዓመት ከተጓዘ በኋላ የእርስ በርስ መባላትን ወለደ። የባድመን ጦርነት አስነሳ።

የኢሳያስ ሻቢያ ወያኔን በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ኢትዮጵያን እንደፈለገው ሊዘርፍ፣ ኤርትራውያን ቅኝ ያዘችን ባሏት ሀገር ላይ የፈለጉትን ሊነግዱ፣ የኢትዮጵያን ምርትና ሸቀጥ አስመጭና ላኪ በመሆን በኢኮኖሚውም ቁልፍ ስፍራ ለመያዝ የተንደረደሩበት ዕቅድ ሳያስቡት ተዳፍኖ እየተለቀሙ "ነፃ" ወደወጡባት ኤርትራ ይላኩ ጀመር። ነፃነት በዝርፊያ አይደምቅምና እስከዛሬ ያለው የኤርትራ መመሰቃቀልና የ25 ዓመት የድህነትና የአፈና ጉዞ ብቻቸውን የትም እንደማይደርሱ አመላካች ነው ቢባል ሚዛናዊ ነው።

ኤርትራ ዛሬ ሀገር ተብላለች። በ25 ዓመት ውስጥ አዲስ ትውልድ ተተክቷል። የኤርትራም ሆነ የኢትዮጵያ አዲስ ትውልድ የሁለቱን ሕዝቦች አንድነት በታሪክ ነው የሚያውቁት። ያውም ታሪኩ ሳይዛባ ከተዘገበ። ኤርትራን ለማስገንጠል የተደረገው የይስሙላ "ሕዝበ ውሳኔ" አግባብነት የሌለው ነው። ኤርትራን እንደ ሀገር የመቀበል ጉዳይ ወደፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ ውሳኔ ነው። ዛሬ ባሉት ሁኔታዎች አስገዳጅነት ወደፊት ኢትዮጵያ ለኤርትራ እንደ ሀገር እውቅና ከሰጠች የሁለቱ ሀገሮች ቀጣይ ግንኙነት በሚገባ መጤን ይኖርበታል። ቀጣይ የሀገሪቷ መንግስት በኢትዮጵያ ሕዝብ ውሳኔ መሠረት ኤርትራን እንደ ሀገር ከተቀበለ ግንኙነቱ ግና በሚገባ መመርመርና አቅጣጫውን ማሳመር ይኖርበታል። ኤርትራ ያለ ኢትዮጵያ ብቻዋን የመኖር አቅሟ ውሱን ሲሆን በተቃራኒው ኢትዮጵያ ያለ ኤርትራ መኖር ሚከብዳት አይደለችም። የኤርትራን ታሪካዊና ጥንታዊ የኢትዮጵያ ግዛት አንፃር ኤርትራ አካላችን ብትሆንም ጊዜ የፈጠረውን የመለያየት እውነታ ከተቀበልን ቀጣዩ መንግስት ከኤርትራ የሚፈልገውና የሚጠይቀው ቢኖር ያለአግባብ በወያኔና ሻቢያ ጥምር ሤራ የተቸራትን አሰብ ወደብን ለኢትዮጵያ ማስመለስ ነው። በፖለቲካው ረገድ ዳር ድንበሩን በሚገባ አካሎና ተከባብሮ ከመኖር የዘለለ ከኤርትራ ጋር በተለይ ሻቢያ ከሚመራት ኤርትራ ጋር "ጉሮ ወሸባዬ" ማለት ሌላ ጥፋት በኢትዮጵያ ላይ ማምጣት ነውና ከጅምሩ ጥንቃቄ የተሞላበት ግንኙነት አስፈላጊ ነው። በኢኮኖሚው መስክም ኤርትራ ኢትዮጵያ ውስጥ ዜጎቿን አስገብታ እንደፈለጉ በተለያየ የንግድ ዘርፍ ሊሰማሩ ያላቸው ፍላጎት ለኢትዮጵያ ጎጂ እንጂ ጠቀሜታ አይኖረውምና "ቅኝ ከያዘቻት" ኢትዮጵያ "በደስታ" እንደተገነጥሉ ችግራቸውንም በሀገራቸው ኤርትራ ምድር መወጣት ይኖርባቸዋል።

በአጠቃላይ ከኤርትራ ጋር ወደፊት መኖር የሚኖርበት ግንኙነት ተከባብሮ በጉርብትና ከመኖር ባሻገር በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውም ሆነ በባህልና በሌላ ሌላ ያለን ግንኙነት ለኢትዮጵያ ጎጂ መሆኑ መታየት ይኖርበታል። እነሱ በእኛ ምድር ሀገራቸውን ሲያበለጽጉ ያላቸውን ቅዠት ማጤን አስፈላጊ ነው።

## 9.0 ምን ዓይነት መንግሥት

እንደ ሀገራችን ኢትዮጵያ ያለ ሀገር ብዙ ችግር ካለው ማገር እንደተሰራ ቤት አውሎ ነፋስ ሲነካው አለበት መቆም እንደሚያቅተው ሁሉ፡ ሀገራችን ኢትዮጵያም አሁን አውሎ ነፋሱ እየመታት አለችበት ላይ እየተወዛወዘች ነው። አውሎ ነፋሱ ብቻ ሳይሆን ሌላም ኃይል በመመሳጠር ገፍቶ ለመጣል ትግሉ ቀጥሎአል።

እንግዲህ ይህንን ግፊት አቁመን ከሰመጥንበት የጎሳ፣ የብሔር/ብሔረሰብ እንቆቅልሽ እኩይ ትርጉም ወጥተን ለሁላችን የሚሆን የእንቆቅልሹን መልስ ከየት ነው የምናገኘው። ከምን ዓይነት ፍልስፍና፣ ከምን ዓይነት ርዕዮተ ዓልም ስር ነው መልሱ የተደበቀው።

ከዚህ በፊት ካልሞከርነው የተለየ እንደምንመኘው እንኳ ባይሆን የገነትን ልዑል ተስፋ የሚሰጥ በልዩነታችን ሳይሆን በተመስሎአችን ላይ የቆመ የጋራ አካፋይ መድረክ የሚሰጠን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ ርዕዮተ ዓለም የቱ ነው? ብሎ መጠየቅ ግድ ይላል።

ለዚህ ግድ ለሆነብን ጥያቄ መልስ ለማግኘት ሀገራችን ኢትዮጵያ ማን ነች?

ሀገራችን ኢትዮጵያ የተለያየ ቀለም ካለው ቤተሰብ፣ ነገድ፣ ጎሳ፣ እና ህብረተሰብ የተሰራች፡ በታሪኳም አንዴ በፍቅር ሌላ ግዜ በፀብ እየተጎናተለች ለዘመናት የኖረች ጥንታዊ ሀገር ነች። "የኢትዮጵያ ታሪክ የጦርነት ታሪክ ነው" ይላሉ የሀገራችን ሰዎች። እርግጥ ነው፡፡ "የሀገራችን ታሪክ የጦርነት ታሪክ ነው" ይባል እንጂ ግማሹ ጦርነት ከውጭ ከመጡ ጠላቶች ጋር ሲሆን፡ የቀረው የራሳችን ጦርነት ነው እንደ አደፍራሽ ታሪክ ተቆጥሮ ለአሁኑ ችግር ጥንሥስ እየሆነ የመጣው። ይባል እንጂ በዚህ ተረቶ ወደፊት መራመድን የሚያቆም ተፈጥሮ ባለመኖሩ፡ እንደ ሎጥ ሚስት ወደ ኋላ ማየታችን ባለንበት ደርቀን እንድንቆም ሳይሆን ካለፈው ስህተት ትምህርት ቀስመን፣ ከጥንትና ከአለፈው ታሪካችን ትምህርት ቀስመን፣ ኢትዮጵያዊ ባህላችንን፣ ሃይማኖታችንን በሚገባ አውቀን ወደፊት በመጓዝ አዲስ ምዕራፍ እንድንከፍት ይህ ሠነድ አንባቢውን ይጋብዛል።

ኢትዮጵያ ከወያኔ ውድቀት በኋላ የዛሬ 40 ዓመት የተነሱትን ሕዝባዊ ጥያቄዎች አካቶ የሀገሪቷን አንድነት በመግባባትና በመተማመን ሊገነባ የተዘጋጀ አስተዳደር እንዲገጥማት መዘጋጀት ይጠይቃል። የልጆቿ የሆነች ኢትዮጵያን ለመመሥረት፣ መብትና ነፃነት የተከበረባትና የግዛትና የህዝብ አንድነቷን የጠበቀች ኢትዮጵያን ለማየት፣ የሁሉንም ብሔር/ብሔረሰብ መብት፣ ባህልና፣ ቋንቋ የሀገርና የሕዝብ ሀብት አርጋ ያቀፈች ሀገር ለመመስረት፣ የሀገሪቷ ተፈጥሮአዊ ሀብት ከጥቂቶች ዘራፊዎች ይልቅ የሕዝብ ሀብት መሆኑን ለማየት፣ ሀገሪቷ በልማትና ዕድገት ጎዳና ከፍ ብላ ለማየት፣ ጥቃቷን ለሚፈልጉ ባዕዳን ኃይሎች ያልተበገረች የጀግና ሀገር ለመገንባት፣ ሕፃናት ቦርቀው፣ አዛውንቶች ተመስገን ብለው፣ ወጣቶች ሀገሬ ብለው፣ ስደተኞች ወደ ሀገራችን ተመልከተን፣ ላብ አደሩ፣ አርሶ አደሩ የልፋቱ ተጠቃሚ የሚሆንባት ኢትዮጵያን ለማየት የጋራ ምክክርና አመራር በቀጣይነት አስፈላጊ መሆኑ ሊጤን ይገባዋል።

በሀገራችን የምርጫ ፖለቲካ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት በጋራ መሠራት ያለባቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ። ዛሬ ወያኔ ሊያዳክም የሞከረውን ኢትዮጵያዊነት ስሜትና፣ የተከለብንን ዘረኝነት፣ የፈጠረብንን የሃይማኖት ልዩነት ጉዳይ ለማስተካከል በጋራ መሠራት መመከር ያለበት ጉዳይ በርካታ ነው። 25 ዓመቱን የወያኔን አገዛዝ ብንወስድ በ30/40ዎቹ ዕድሜ ክልል ያሉ ጎልማሳዎች ስለ ኢትዮጵያ ያላቸው ስሜት ይዳከም ዘንድ በወያኔ አስተዳደር ተጥሯል። በክልል ከፋፍሎ ወጣቶች ስለ ሀገራቸው ኢትዮጵያ ስሜት እንዳይኖራቸው ከሕፃንነታቸው ጀምረው ተቀጥቅጠዋል። ይህን ልናስተካክል የምንችለው ሁሉም የፖለቲካ ድርጅትና የኅብረተሰብ ክፍሎች በጋራ ስንመክርበትና አቅጣጫ ስንሰጥ ነው።

በኢኮኖሚውም በኩል ዛሬ ሀገራችን በሊዝ ስም ለውጭ ባዕዳን ተቸብችባለች። ወያኔ የማይታወቁና ግልጽ ያልሆኑ በሀገርና በህዝብ ስም ከውጭ ኃይሎች ጋር ውል ተፈራርሟል። እነኚህ ውሎች ደግሞ ሀገራችንን በማጥፋት ላይ የተደረጉ በመሆናቸው ውሉን የወሰዱት ባዕዳን ኃይሎች ዝም ብለው ይቀመጣሉ ማለት ሞኝነት ነው። ሀገራችን ውስጥ የተለያየ ፕሮጀክቶች የያዙ የውጭ ኃይሎች በሙሉ ለሀገራችን ሳይሆን ለራሳቸው ሀገር ጥቅም የቆሙ እንደሆነ ጥርጣሬ አይግባን። የእኛ እርስ በርስ በመከፋፈል መዳከም የሚፈልጉትን ዝርፊያ ይቀጥሉ ዘንድ ይጠቅማቸዋልና ኦሮሚያን፣ ኦጋዴንን፣ ትግራይን ገነጣጥለው ሌላውንም ክፍል አዳክመው ጥንት ያጡትን በወረራ ዝርፊያ በአሁኑ ዘመን ሊቀጥሉበት ይፈልጋሉና ይህንን ልንቋቋም የምንችለው መለስተኛ ቅራኔዎችና ልዩነት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ የጋራ አመራር ለተወሰነ ጊዜ ተግባራዊ ሲሆን ነው።

በፖለቲካውም አንፃር ዛሬ በሀገራችን በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ። በጥቅሉ ተመሳሳይ ፕሮግራም ያላቸውና አንድ ዓይነት መፈክር በሀገራችን ጉዳይ የያዙ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ። በሀገራችን ፖለቲካ ተመሳሳይ አመለካከት

ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች የአባላት ቁጥራቸው ስለበዛና ስላነሰ ሳይሆን በጥልቅ ውይይት እየተዋሃዱና ቁጥራቸው እያነሰ ይሄድ ዘንድ የጋራ ውይይትንና አመራርን በቅድሚያ ይጠይቃል። በትንሽ በትልቁ እየተነታረኩ፣ መግባባትና የቅራኔ አያያዝ እየራቃቸው የሄዱትን የፖለቲካ ድርጅቶች ለሀገርና ሕዝብ ሲባል የመወያየት ባህልን፣ ልዩነትን በጸጋ የመቀበል አካሄድን፣ ቅራኔን በአግባቡ የመያዝ ባህልን ማዳበር ይለምዱ ዘንድ በጋራ መድረክ ተቀምጠው ሀገርን በጋራ ምክክር ለመምራት ይዘጋጁ ዘንድ እራሳቸውን መመርመር ይኖርባቸዋል። ከወያኔ ውድቀት በኋላ "እኔ ብቻ" ባይ ካለ አሁንም ወደ ሌላ አምባገነንነት መሄድን ያመጣልና ማንም ማንን አግላይ ሳይሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የብዙሃን ድርጅቶችን አካቶ ሌሎችንም የኅብረተሰብ ክፍል ያቀፈ የጋራ አመራር ኃይል ረዘም ላለ ጊዜ ሀገሪቷን መገንባት ይኖርበታል።

ከወያኔ በኋላ ቀጣዩ የሀገሪቷ መንግሥት ቢያንስ ለ10 ዓመት የሚጓዝ የጋራ አመራር ቢሆን ይመረጣል። ይህ የጋራ አመራር በሀገሪቷ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችን፣ የብዙሃን ድርጅቶችን፣ የሃይማኖት አባቶችን፣ ታዋቂ ግለሰቦችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን፣ ምሁሮችን፣ ሴቶችን፣ ወጣቶችን፣ ተማሪዎችን፣ መምህራንን፣ ሠራተኞችን፣ አርሶ አደሮችን፣ ነጋዴዎችን፣ ወዘተ አካቶ የሚመሠረት የጋራ አመራር ይሆናል።

ይህን የጋራ አመራር ተግባራዊ ለማድረግ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በመሀከላቸው ያለውን ልዩነቶች አጥብበው ለጋራ ሀገርና ለአንድ ሕዝብ ሲሉ በቅድሚያ የኅብረት ስምምነት ማድረግ። በተጨማሪም በተለያየ አጋጣሚ የተናቆሩና የተከፋፈሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ልዩነቶቻቸው እንደተጠበቁ ለኅብረት ስምምነቱ ቀናነትን እንዲያሳዩ መጣር።

በአሁኑ ጊዜ ሀገራችን ከገጠማት ዓይነተኛ ችግሮች አንዱ የብሔር/ብሔረሰቦች የማንነት ጥያቄዎች ናቸው። በሀገራችን ብዙ ብሔር/ብሔረሰቦች እንደመኖራቸው መጠን ወቅቱና በተለይ የህወሀት አገዛዝ ያጋጋለው እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ የማንነት ጥያቄ አንሺዎችን በሰከነና በእርጋታ የውይይት መድረክ ለመፍታት ጥረት መደረግ ይኖርበታል። እነኚህን በዘር የተደራጁ የህብረተሰብ ክፍሎች ለማቀራረብና አንድነት ይፈጥሩ ዘንድ ጥርጊያ መንገዱን ለማዘጋጀት ገለልተኛ የሆነ ስብስብ ኑሮ በትጋት መሥራት ይኖርበታል። የዘር ፖለቲካ አክተሞ በኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት የተገነባ፣ ስለ ሀገር ዕድገትና ልማት ትኩረት የሠጠ ትውልድ ለማፍራት አንድነታችንን የተፈታተኑት ችግሮች መፍቻ ቁልፉ ግልጽነትን በተላበሰ መልኩ ዴሞክራሲያዊ ውይይት መሆን ይኖርበታል። በመሆኑም የዚህ የጋራ አመራር ቀዳሚ ተልዕኮ የዘር፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ ልዩነቶቻችን የሀገራችን ፀጋዎች መሆናቸውን ትኩረት ሠጥቶ በአገዛዝ ዘመኑ የሁሉም ዜጎቿ የሆነች ኢትዮጵያን በተግባር መፍጠር ይሆናል።

ይህ የጋራ አመራር

1. ለትውልድ የሚተላለፍ ሕዝብን በአግባቡ ያሳተፈ ሕገ መንግስት በማርቀቅ በሕዝበ ውሳኔ ያፀድቃል
2. ሀገሪቷ ልትከተል የሚገባውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት (ለምሳሌ ሊበራል፣ ሶሻል፣ ወይስ ሌላ) በ10 ዓመት ቆይታው ተግባርና ተመክሮ በመነሳት ተገቢውን የሀገሪቷን የፖለቲካ ሥርዓት ይቀይሳል
3. ኢትዮጵያዊነት ስሜትና ሀገራዊ ፍቅር እንደገና ያብብ ዘንድ ፖለቲካ ድርጅቶች ቅድሚያ አጀንዳቸው ኢትዮጵያዊነት ይሆን ዘንድ ይጥራል
4. የብሔር/ብሔረሰቦች ባህል፣ ቋንቋ፣ ሌላም ይዳብር ዘንድ የብሔር/ብሔረሰቦችና የቋንቋ ኢንስትቲዩትን ማቋቋም
5. ሃይማኖትን ከፖለቲካ በመነጠል የሃይማኖት እኩልነትንና ነፃነትን ያመቻቻል
6. የተለያዩ ሕብረብሔር የፖለቲካ ድርጅቶች በስምምነትና በነፃ መግባባት እየተዋሃዱ ውስን የፖለቲካ ድርጅቶች በሂደት ጎልተው ይወጡ ዘንድ ያመቻቻል
7. ተጠሪነቱ ለጋራ አመራር አካል የሆነ ዘርን ያላማከለ ጠንካራ ሕዝባዊ የመከላከያ ሠራዊት ይገነባል
8. ከጋራ አመራሩ የሥልጣን ገደብ በኋላ ለሚኖሩ የምርጫ ፖለቲካ ሂደቶች አስፈላጊ ተቋሞችን ይመሠርታል፣ ይገነባል
9. የሀገሪቷን የልማት አውታሮች በሁሉም ክፍለ ሀገራት በተመሳሳይና አግባብነት በአለው አቅጣጫ ይስፋፉ ዘንድ ይጥራል
10. የሕዝቡ ዴሞክራሲያዊ ባህል ይዳብር ዘንድ የሚቻለውን ያደርጋል

11. የኢትዮጵያ ቀጣይ አመራር የወቅቱ ትውልድ መሆኑን በመቀበል አመራር ሰጪ ወጣቶችን በሚገባ በሀገርና ሕዝብ ፍቅር መገንባት
12. ሌሎች ተጨማሪ ይኖራሉ

## 10.0 የኢትዮጵያ ክፍለሀገራት አከፋፈል

በተለያየ ጊዜ ነገስታቱ የኢትዮጵያን የግዛት ክልል አስፍተው ቢይዙም በስተመጨረሻው እንደማንኛውም ዓለም የተፈጠረችው ኢትዮጵያ ዓለምና ታሪክ የዘገባት ናት። ዓፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መሳፍንትን ወደ አንድ የኢትዮጵያ አስተዳደር ለማምጣት የነበራቸውን ትልም ዓፄ ዮሐንስና ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ በቀጣይነት ያቀኗትና ያስከበሯት ኢትዮጵያ ዛሬም አለች። ያች ኢትዮጵያ ዳግም ታብባለች። ወራሪው ኢጣሊያና እንግሊዞች የረጩት የመከፋፈልና የማዳከም ተልዕኮ ዛሬ በመንግስት ደረጃ በወያኔ ቡድኖች ተግባር ላይ ሊውል ጥረቱ ቢኖርም የኢትዮጵያ ልጆች በጋራ ዘላለማዊ ሕይወቷን ያድሱታል።

ከዐድዋ ጦርነትና ከቅኝ ግዛት ማክተም ጋር ተያይዞ ሀገራት የያዙት ግዛታቸው እንደተጠበቀ ሁሉ ኢትዮጵያም ከዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ጀምሮ እንደ ሀገርነት የግዛቷ መለያ ካርታ አላት። የዚህ ግዛት ባለቤት ኢትዮጵያ ነች።

ወራሪ ጠላት ያልደፈረውን ግዛት ዛሬ ወያኔ እየቆረሰ ለባዕዳን ሊሰጥና ሊቸረችር ቢራወጥም ሀገራችንንና ግዛታችንን የማስከበር ሃላፊነት የያንዳንዳችን ኢትዮጵያዊ ዜጋ ግዴታ ነው። በትውልድ ላለመወቀስና በታሪካችን ጥቁር ነጥብ ጥለን ላለማለፍ ከፈለግን ኢትዮጵያን የልጆቿ ለማድረግና የግዛት ሉዓላዊነቷን ለማስጠበቅ አስፈላጊውን መስዋዕትነት ለመክፈል ጊዜው አሁን ነው።

የኤርትራ ጉዳይ ከላይ እንደተገለፀው ቢቀመጥም አሰብና ባድሜ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የኢትዮጵያ አካሎች መሆን ይገባቸዋል። ዛሬ ወያኔ ለሱዳን እየሰጠ ያለው የምዕራብ ኢትዮጵያ ግዛት ያለምንም ጥያቄ የኢትዮጵያ አካል ነው። ወንበዴ መንግስት ሀገር ሊያጠፋ ተነስቷልና ጥፋቷን ቁጭ ብለን መመልከት አይኖርብንም። ዛሬ በመንግስትነት ያለው ወያኔ/ህወሀት ሀገር አስገነጠለ፣ ግዛታችንን ለባዕዳን ኃይሎች እየሰጠና ቀሪው ግዛታችንም በለኮሰው የዘር ፖለቲካ ሊበታትነን መጨረሻው ምዕራፍ ላይ ሲደርስ ቁጭ ብለን የምናይበት ጊዜ ላይ አይደለንም። የአባቶቻችን፣ የእናቶቻችን ተጋድሎና ጀግንነት የተገነባችውን ኢትዮጵያ ዛሬ በእኛ ዘመን ስትፈርስ ማየት የቁም ሞት ነው። ሕይወታችን ለሀገራችን ካልሆነ እኮ ለማን? ሀገር ልትኖር ሊከፈል የሚገባው መስዋዕትነት ከሁሉም ዜጎቿ አሁን ይጠበቃል።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ክልሏ እንደተጠበቀ የውስጥ አከላለሏ ከቅርቡ ብንነሳ በዓፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት ኢትዮጵያ በ14 ጠቅላይ ግዛት ተከፋፍላ ትተዳደር ነበር። ይህ አከላለል በአብዛኛው በዘር ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት ስሜት እና በተፈጥሮአዊ ወንዞቿ ላይ ያተኮረ ነበር። የዓፄ ኃይለሥላሴ አገዛዝ ችግር ሁሉም ጠቅላይ ግዛቶች ላይ ይንፀባረቅ ነበር። የትኛውንም ጠቅላይ ግዛት በዘር ተገን አድርገው አልገዙም። ሁሉንም ዘርና ጠቅላይ ግዛት "በስዩመ እግዚሐብሔር" ስም ገዝተዋል አስተዳድረዋል።

በቀጣይነትም ደርግ ከዓፄ ኃይለሥላሴ የተረከበውን ጠቅላይ ግዛት የስም ለውጥ በማድረግ 14 ክፍለ ሀገሮችን እስከ ስያሜአቸው አስተዳድሯል። ደርግ በአገዛዙ ዘመን ወደ መጨረሻ የራስ ገዝ አስተዳደሮችን በመጨመር ለአንዳንድ ክልሎች የራስ ገዝ አውቶኖሚ በመስጠት አስተዳድሯል። የደርግ ዘመን አከላለልም ዘርን ተገን ሳያደርግ እስከ ግዛት መጨረሻው ቀጥሏል። በደርግ ዘመን የትኛውም ክፍለ ሀገርና ዘር የደርግ ጅራፍና ጥይት ሰለባ ሆኗል። የደርግ ግድያ መለያው ዘር ሳይሆን ተቀናቃኝ፣ ተቃዋሚ ነበርና ዘርና አካባቢ ሳይለይ ትውልድ ቀብሮ አሸልቧል።

መርዘኛው ወያኔ አንድ ዘርን ተገን አድርጎ እንደመምጣቱ ሀገሪቷን በዘር ከፋፍሏል። ለአገዛዙ በተመቻቹለት የዘር ድርጅቶች አማካይነት ዘረኝነትን ገና ከጅምሩ በማራመድ ዛሬ ከኢትዮጵያዊነት ስሜት ይልቅ ዘረኝነት እንዲበራከት የረጨው መርዝ ቀላል ባይሆንም የዕቅዱን ያህል አልሰመረለትም፤ አይሰምርለትምም። ወያኔ በዘርና በሃይማኖት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሊያጋጭ

ሥልጣን ከመቆናጠጡ በተለያዩ አካባቢዎች በተለያየ ጊዜ ሞክሯል። አሁንም እያደረገ ይገኛል። በዚህ ሂደት የበርካታዎች ንፁሐን ደም ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ አዛውንት እናት አባቶች ቢፈስም የከፋ የዘር መጨፋጨፍ ውስጥ ላለመግባት ሁሉም ዘር በራሱ እየተቆጣጠረው ይገኛል። በቀጣይነትም ይህ አኩሪ ኢትዮጵያዊ ባህል መቀጠል ይኖርበታል። በአንድ ቀዬ የኖረ፣ ከአንድ ወንዝ የጠጣ፣ በአንድ ግጦሽ ከብቱን ያሰማራ፣ በደቦ አርሶ የኖረ ህብረተሰብ አሁንም በአንድ ኢትዮጵያ መሬት ላይ በጋራ የመኖር ባህሉን መጠበቅ ይኖርበታል። ዛሬ የዘር ፖለቲካ ለሀገር እድገት የሚያበረክተውን እንቅፋት በወያኔ አይተናልና ኢትዮጵያዊነት ያብብ ዘንድ በጋራ ስለ ለሀገራችን መጮህ ይኖርብናል። የዘር ክልል ማብቃት ይኖርበታል። የሁሉም ዘር ክልል ኢትዮጵያ ብቻ መሆን ይኖርበታል።

በሀገራችን ዘርን ያማከለ አከላለልና አስተዳደር ማብቃት ይኖርበታል ሲባል፡-

- የብሔር/ብሔረሰቦችን መብት መጋፋት ሳይሆን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በፈለገው አካባቢ የመኖርና የመሥራት የዜግነት መብቱን ማወቅ ነው።
- ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዘር በሀገሩ ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ ግባችን ከሆነ ሀገራችን ኢትዮጵያ መሆኗን መቀበል ተገቢነት ይኖረዋልና ነው።
- የዘር ፖለቲካና አከላለል በአንድ ጀምበርና በጉልበት ይናዳል ሳይሆን ለሀገርና ሕዝብ አንድነት ሲባል ከሁሉም የብሔር/ብሔረሰብ ወገኖችና ድርጅቶች ጋር የሽግግር መንግስቱ በሚያደርገው ቀና ውይይትና መግባባት ላይ የተመሠረተ መሆን ይገባዋል።

ዘርን ያላማከለ የኢትዮጵያ ክልል እንደገና ማዋቀር አስፈላጊ ነው። ይህ ሠነድ የኢትዮጵያን ጂዎግራፊያዊ አቀማመጥ (ወንዞቿን፣ ተራሮቿን...) ያማከለ ወይም በዓፄ ኃይለሥላሴ ጊዜ የነበረው 14 ክፍላተ ሀገራት አከላለል ከነስያሜአቸው መቀጠል አስፈላጊነቱን እንደ አማራጭ ያቀርባል። ወያኔ በአገዛዙ ዘመን ከአንዱ ክልል ወደሌላው እየወሰደ የቀላቀለው ወደ ድሮው መመለስ ይኖርበታል። ያለ አግባብ ወደ ትግራይ ክልል የተወሰዱ አካባቢዎች ወደ ጥንት መሠረታቸው መካተትን ይጨምራል።

በመሆኑም በዚህ ሠነድ አቀራረብ መሠረት መጪዋ ኢትዮጵያ ሁሉንም ልጆቿን በዘር፣ በብሔርና/ብሔረሰብ፣ በጎሳ፣ በሃይማኖት ሳትለይ ማንም በፈለገው የሀገሪቷ ግዛት ሊኖርባት የምትችለዋን ኢትዮጵያ መገንባት ነው። ለዚህም የተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦችን ባህል፣ ቋንቋ፣ ማንነት ከማዳበር በዘለለ መልኩ ሀገሪቷን በዘር ማካለል ጠቀሜታ ሳይሆን ጉዳቱ ስለሚያመዝንና ሀገራችን ለጠላት እንድትመቻች በር ስለሚከፍት ማክተም ይኖርበታል። ዘረኝነት ኢትዮጵያዊነትን ብሔራዊ ስሜት ሸርሻሪ ነው፣ ኢትዮጵያን ሀገሬ ያለ የእናት ሆድ ዥጉርጉርነቱን መቀበል ይኖርበታል። እንደጥንቱ ከየት ነህ/ነሽ ሲባል ከወለጋ፣ ከጅማ፣ ከሐረር፣ ከጎጃም፣ ከዴሴ ወዘተ. የሚል/የምትል ኢትዮጵያዊ ዜጋ ትኩረታቸው መሠረቱ የሀገር ዕድገትና ልማት የሆነ መፍጠር ይጠበቅብናል። ኢትዮጵያን እንደ ሀገር እናስቀጥል ካልን ዘንዳ ሁሉም በግዛቷ ያለ ዜጋ ኢትዮጵያዊነቱን መቀበል ይኖርበታል። ሀገራችን አንድነቷንና የግዛት ሉዓላዊነቷን ጠብቃ እንድትኖር ከፈለግን፣ ዘላለማዊ ሕይወቷን የምንጠብቀው ከዘር ፖለቲካ በራቀ መልኩ መሆኑ ይሰመርበት ዘንድ "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!" ሠነድ ጥሪ ያደርጋል።

## 11.0 የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ

የ"አንድ ሕዝብ! አንድ ሀገር!" መነሻ ሠነድ ኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ባስጠበቀ መልኩ ሁሉንም ዜጎቿን በዴሞክራሲያዊ አንድነት ይዛ ማስቀጠል በመሆኑ ሁሉም ዜጐቿ ከፍ የሚያደርጉት የሀገሪቷ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ አንድና አንድ መሆን ይኖርበታል።

የሀገራችን መለያዋ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ኢትዮጵያዊነት ኩራታችን ክብራችን ነው። ወራሪ ኃይል ዝቅ ያላደረገው ሁሌም ከሀገር ጫፍ የሚውለበለበው የጀግኖች መኩሪያ የነፃነት አርማ ነው ሰንደቅ

አላማችን። ቅኝ አገዛዝን በደሙ የመለሰው ሕዝባችን፣ ነፃነታችንን በሕይወቱ ያስከበረው ሕዝባችን፣ ዳር ድንበራችንን በአጥንቱ የከለለው ሕዝባችን መኩሪያ ነው ሰንደቅ ዓላማችን። ነፃነትን ለዓለም ያስተማረች ሀገራችን አርኣያነቷ፣ ተምሳሌትነቷ ነው የተለያዩ አፍሪካ ሀገራት በተለያየ አቀማመጥ የእኛን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ መደብ የተጠቀሙት። ከኢትዮጵያ በወሰዱት የነፃነት ተጋድሎ ትምህርት ነፃ በመውጣታቸው ምስክርነታቸውን ነው የገለጹት።

የሀገራችንና የሰንደቅ ዓላማችን ፍቅር ነው ሦስቱን መደባዊ ቀለማት በአልባሳት በነጠላው፣ በኩታ፣ በጃኖው መልክ የምንለብሰው። በመለዮው፣ በባርኔጣው፣ በካኒቴራው፣ በማህተቡ፣ በገበታ ትሪው፣ በቡና ስኒው፣ በጠረጴዛ ልባሱ፣ በሁሉም በሁሉም ዓርማችንን ተሸክመን ምንደምቀው ማንነታችንን ስናስተዋውቅ፣ ኩራትና ክብር ለሀገራችን ስንሰጥ ነው።

ከላይ እንደተገለፀው የብሔር/ብሔረሰቦችን መብት ማክበርና በዘር የተካለለች ሀገር መመስረቱ ለሀገር እድገትም ሆነ ልማት እንቅፋት ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ የምንላትን ሀገር እንደሀገር ማስቀጠሉም አጠያያቂ እንደሚሆን በመጠኑም ቢሆን ተገልጿል። በመሆኑም ኢትዮጵያዊነትን ቀዳሚ ያደረገ ሀገር ለመገንባት ሀገርን በዘር መሸንሸኑ ቦታ ሊኖረው እንደማይገባ ሁሉ የኢትዮጵያችን ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ በላዩ ላይ ምንም ምልክት የሌለው አረንጓዴ ቢጫ ቀይ መሆኑን ይህ ሠነድ በአንክሮት ትኩረት ያደርግበታል።

የቀስተደመና ተምሳሌት ጥንታዊ ሰንደቅ ዓላማችን ጥንታዊ ቀለሙንና አቀማመጡን እንደያዘ በላዩ ምንም ዓይነት ተደራቢ ዓርማም ሆነ ምስል ሳይኖረው ከኢትዮጵያዊነት ጋር መቀጠል ይኖርበታል።

የ"አንድ ሕዝብ! አንድ ሀገር!" ኢትዮጵያ አከላለል የሀገራችንን ተፈጥሮአዊ አከላለል ወይም የጥንቱን የ14 ጠቅላይ ግዛቶች መሠረት በማድረግ ይሆን ዘንድ አስቀምጠናል። በዚሁ መሠረት የሚዋቀሩት አስተዳደራዊ ጠቅላይ ግዛቶች ከባህላቸው፣ ከተፈጥሮ ምርቶቻቸው፣ ከባህላዊ ቅርሶቻቸው፣ ከታዋቂ ጀግኖቻቸው በመነሳት አካባቢያዊ መለያ ሊኖራቸው ይችላል። ለምሳሌ ከፋ ጠቅላይ ግዛት በቡና፣ ትግራይ በአክሱም፣ ወለጋ በጆቲ ወርቅ፣ ወሎ በቁንጅና፣ ባሌ በሶፎመር፣ ሐረር በሐረር ግምብ፣ ጎንደር በፋሲል ግምብ፣ ወዘተ. መለያ ሊኖራቸው ይችላል።

## 12.0 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ

ኢትዮጵያ ሀገራችን የብዙ ብሔር/ብሔረሰቦች ሀገርና የበርካታ ቋንቋዎች ባለሀብት ነች። የራሷ ቋንቋና ሆዬሃት ያላት ቀዳሚ አፍሪካዊት ሀገር ኢትዮጵያ አኩሪ ቋንዎቿንና ባህሏን መጠበቅ፣ ማዳበር ያስፈልጋታል። ቋንቋ እንደ መግባቢያነቱ ከአካባቢ አልፎ በብሔራዊ ደረጃ ከዛም በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊያድግ ይችላል።

ኢትዮጵያ የተለያዩ ቋንቋዎቿን በሚገባ መጠበቅና ማሳደግ ይገባታል። ከዚህ ባሻገር እንደ ሀገር ብሔራዊ ቋንቋ አስፈላጊ ነው። አማርኛ፣ ትግሪኛ፣ ኦሮምኛ፣ ጉራግኛ ወዘተ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ባይናገራቸውም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ናቸው። የቋንቋው ባለቤት ኢትዮጵያ ብቻ ናት። ከነዚህ ሁሉ ቋንቋዎች አንድ የጋራ ቋንቋ የሀገሪቱ ብሔራዊ ቋንቋ መሆኑን መቀበል ኢትዮጵያዊነትን ከመቀበል ጋር ይያያዛል። ለዚህም ነው "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!" አንድ ሰንደቅ ዓላማ፣ አንድ ብሔራዊ ቋንቋ የሚዳብረው።

አሁን አሁን እየታየ ያለው የባዕድ ቋንቋ ተፅእኖ የሀገራችንን እያዳከመው ይቀጥል ዘንድ የሚሸረቡ ተንኮሎች ኢትዮጵያዊነት ላይ ከሚደረገው ዘመቻ አኳያ መታየት ይኖርበታል። የእንግሊዘኛ ቋንቋ በሀገራችን የመሥሪያ ቋንቋ እየሆነ ከመጣ ጥቂት ዓመታት ቢያስቆጥርም በምንም መልኩ ውብ ቋንቋዎቻችንን ሊውጥ አይገባውም። የምንኮራበት የራሳችን አለንና።

በሀገሩ ላይ እንግሊዘኛ ቋንቋን ያላስገባ ወደ ሥልጣኔና ዕድገት ጎዳና አይጓዝም ካልን ተሳስተናል። ለአብነት ያህል ፈረንሳይን፣ ጃፓንን፣ ቻይናን፣ ጣልያንን፣ ጀርመንን ብዙ መጥቀስ ይቻላላል። የሀገራቸውን ቋንቋ ጠብቀውና አክብረው ነው ወደ ሥልጣኔና ዕድገት የገቡት።

ለአስተያየት የቀረበ

ከእነ ዕምቅ አቅሙ የሀገራችን ቋንቋዎች የውበታችን መግለጫዎች ናቸው። መድመቅ ያለበት የራስ ወርቅ ነው። አማርኛ እንበለው፣ ኦሮምኛ...ትግርኛ...ጉራግኛ...ሌላም ሌላም የየራሳቸው ኃይልና ምስጢር አላቸው። ከቋንቋ አንጻር ብዙ ጥናት ተደርጎባቸው ልንኮራባቸው ሲገባን በባዕድ ቋንቋ እንዲተኩ መተባበር አሳፋሪ ተግባር ይሆናል።

ኢትዮጵያ ከአላት በርካታ ቋንቋዎች አንፃር በአንድ በኩል፣ በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛው ሕዝብ የሚናገረውንም ከግምት በማስገባትና ለዘመናት ሲሰራበት የነበረውንም በማካተት ይህ ሠነድ አሁንም አማርኛ ቋንቋ የሀገሪቷ ብሔራዊ ቋንቋ ሆኖ ማገልገል ይኖርበታል ሲል ያቀርባል። አሁንም ግልጽ ለማድረግ የሚፈለገው ሀገራችንን ኢትዮጵያ በጋራ የሕዝቧ ለማድረግ እስከሆነ ድረስ ማንም ዜጋ በፈለገው አካባቢዋ ሠርቶ የሚኖርባት፣ በጋራ የሚያውለበልበው ሰንደቅ ዓላማና የጋራ ቋንቋ አስፈላጊነቱ አጠራጣሪ ሊሆን አይገባውም። የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ቋንቋ መሆን ሌሎች ቋንቋዎች ያቀጭጫል ወይም ተጽዕኖ ይኖረዋል የሚል ትንታኔን ወደ ጎን አድርገን የሁሉም ብሔር/ብሔረሰቦች መብት እስከተከበረ ድረስ ባህላቸውም ሆነ ቋንቋቸው የማይዳብርበት ምክንያት የለም።

አማርኛን፣ ኦሮምኛን፣ ትግሪኛን፣ ጉራግኛን እና ሌሎች ቋንቋዎችን በተጨማሪ ከተናጋሪው ጐሣ ቁጥር ማነስ እየጠፉ የሄዱትንና ሊጠፉም የተቃረቡትን አካቶ በሥነ ጽሁፍ፣ በኪነ ጥበብ፣ በመግባቢያነት፣ በምርምር ወዘተ ለማሳደግ የኢትዮጵያን ቋንቋዎች አካዳሚን እንደገና ማዋቀር ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል የሀገራችን የተለያዩ ቋንቋዎች ለጽፈትና ለሥራ ቋንቋ ከሀገራችን ፊደላት ይልቅ ላቲንን መጠቀሙ የተወሳሰበ ሊያደርገው ስለሚችል ወደፊት በቋንቋ ምሁራን በሚገባ ጥናት ተደርጎበት ኦሮምኛና አንዳንድ የሀገራችን ቋንቋዎች በሀገራችን ሆሄሃት ይጠቀሙ ዘንድ አቅጣጫ መስጠቱ ተገቢ ይሆናል። ይህ የተለያዩ ብሔረሰብ ቋንቋዎችን ለማቀራረብና ለማዛመድ አንድ ወጥ ፊደል/ሆሄሃት መጠቀሙ አስፈላጊ ይሆናል።

## 13.0 የያ ትውልድ እንቅስቃሴ ለምን ተኮላሸ?

ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ስማቸው በታሪክ መዝገብ የሠፈሩ የቁርጥ ቀን አርበኞቿን አርኣያ ተከትሎ ለሀገሩና ለሕዝቡ ተቆርቋሪ ዜጋ በመሆን ብቅ ያለው 1960ዎቹ ያ ትውልድ እንቅስቃሴ ለምን ሊኮላሽ ቻለ? በወቅቱና ከዚያም ወዲህ ለአለፉት 40 ዓመታት የተፈጠሩና ዳዴ እያሉ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችን ጨምረው ትንሽ ሳይራመዱ የከሰሙት ሁሉ ችግራቸው ምንድነው?

ኢትዮጵያዊነትን አጀንዳው አድርጎ፣ ብሔራዊ ስሜትን አንግቦና ሕዝባዊ ጥያቄን አንግቦ የተነሳው ያ ትውልድ ከነጠንካራ ጉልበቱ ሲኮላሽ የትም አይደርስም የተባለው የዘረኝነትንና የአንድን ክልል ዓላማ ይዞ የተነሳው ቡድን ለመንግሥት ሥልጣን ከመብቃት አልፎ ዛሬም ሀገርና ሕዝብ ለማተራመስ ዕድሉ "ሲሰምርለት" የኢትዮጵያ ልጆች ያቃታቸው ምንድን ነው? ለ25 ዓመታት በዘር ከፋፍሎ እየገዛ ያለው ወያኔ አልበቃ ብሎ ዛሬም ከሀገር ይልቅ ዘርንና ሃይማኖትን ተገን ያደረገ ስብስብ አየሩን ሲሞላው፣ ለቀጣይ የመንግሥት ሥልጣን ሲንደረደር ምን እያደረግን ነው? የትላንት በሕዝብና ሀገር ላይ ያደረሱት ግፍና መከራ ሳያንሳቸው ዛሬ በሀገር አንድነት ካባ "ሀገር ወዳድ ነበርን" ባዮች ለዳግም ሥልጣን ሲሰባሰቡ በዝምታ ተመልካች ያደረገን ምስጢሩ ምን ይሆን? የአላቸው ዕምቅ ችሎታና ዕውቀት ለሀገርና ለሕዝብ ከማድረግ ይልቅ በፍራቻና በዝምታ ዳር ሆኖ ተመልካች የሆነው የያ ትውልድ አካል የተሰበረ ስሜቱን፣ የተኮላሸ ማንነቱን፣ የተዘጋ አንደበቱን፣ የተራበ ዓይኑን፣ የዝሆን ጆሮውን፣ አምስት ጣቱን በአጠቃላይ የትግል ሕዋሳቱን የሚያነቃቃበት ወቅት መቼ ይሆን?

ይህንንና መሰል ጥያቄዎችን በመዳሰስ ከአለፉት የትግል ታሪካችን አሉታዊና አዎንታዊ ጎን ትምህርት መቅሰሙ አስፈላጊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለቀጣይ ትልማችንም የመሠረት ድንጋይ ነውና መዳሰስ ይገባናል። ያለፈ የትግል ታሪክን በሚገባ በመቃኘት ለእኛም ሆነ ለቀጣይ ትውልድ ትምህርት ይሆን ዘንድ ኢትዮጵያ ዛሬ ለደረሰችበት አሳሳቢ ሁኔታ ቀደምት የትግል እንቅስቃሴዎች ምን አስተዋጽዎ አድርገዋል? ስህተታቸው ምን ላይ ነበር? ከአለፈው ስህተት ትምህርት ተቀስሞ በቀጣይነትስ ምን ማድረግ ይኖርብናል? ሌላ የፖለቲካ ድርጅት፤ ፓርቲ፣ እንቅስቃሴ መፍጠሩ ለምን አስፈለገ? የአሁኑ ትውልድ ለሀገሩና ለህዝቡ ሞጋች ይሆን ዘንድ ከያ ትውልድ ትግል ታሪክ ምን ይቀስማል? ሀገሩንና ህዝቡን በአንድነት መነጽር ይመለከት ዘንድ

ምን ማድረግ ይኖርብናል? የሚሉትን ለመቃኘት ወደ ኋላ መለስ ብሎ የኢትዮጵያ ተማሪዎችን እንቅስቃሴ መቃኘት አስፈላጊ ይሆናል።

ባለፉት 50 ዓመታት የነበሩት የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ከ1930ዎቹ በፈረንጅ ወይም በእኛ በ1920ቹ ጀምሮ እስከ አብዮት ፍንዳታ ድረስ ያለውን የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ በአጭሩ ለመመልከት እንሞክር፡፡

ከ30ዎቹ እስከ 70ዎቹ ያሉትን የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ በአሉበት ዘመን ብንመለከት ቀለል ያደርገዋል ብለን እንገምታለን። ሁሉም የተማሪዎች እንቅስቃሴ በተለይ በውጭው ዓለም የነበረው ሁሉም በሚመስለውና በአመኑበት መንገድ ሀገራቸውን ወደ ጥሩ አቅጣጫ ለመውሰድ የተደረጉ ነበሩ። ከቀደምት የተማሪዎች እንቅስቃሴ በመነሳት ወደ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ የነበረው የተማሪዎች እንቅስቃሴ የኋለኞቹ ከቀደምት እንቅስቃሴ ትምህርት እየወሰዱ የመጡበት ነበር ለማለት ይቻላል። በ60ዎቹ ወቅት የነበሩት የተማሪዎች እንቅስቃሴ መሪዎች ከበፊቶቹ አብራክ የወጡና ቀጣይነትና ተያያዥነት የነበራቸው እንደነበር መረዳት ያስፈልጋል።

የተማሪውን እንቅስቃሴ ቀለል ለማድረግ በሦስት ክፍል ከፍሎ ማየት ይቻላል፦

እነዚህም የተማሪ እንቅስቃሴዎች የመጀመሪያው ከጣሊያን ወረራ በፊት በ1920ዎቹ  አካባቢ ወደ ውጭ ሀገር የሄዱት ተማሪዎች ናቸው። እንደ መላኩ በያን የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ዶክተር፣ በሻወረድ ሀብተወልድ፣ ሀብተ ሚካኤል፣ ወርቁ ጎበና መኮንን ደስታ የተባሉ ሲሆኑ እነዚህ አመጣጣቸው በዚያን ጊዜ ራስ ተፈሪ የሚባሉት ከዛ በኋላ ዓፄ ኃይለሥላሴ ድጋፍ ነበር ወደ ውጭ የሄዱት። አብዛኞቹ የእሳቸው ሎሌ ወይም አገልጋይ በቤተመንግሥት ዙሪያ የነበሩ ናቸው። በወቅቱ ዘመናዊ ትምህርት በኢትዮጵያ ገና በዳዴ እየሄደ ነበር፤ በወቅቱ ምኒልክና ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤቶች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ወደ አሜሪካ ሲመጡ ምንም የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያልነበራቸው ሲሆኑ በግብጽ አሌክሳንድርያ አድርገው ቋንቋ ተምረው የመጡ ነበሩ። በወቅቱ በአሜሪካን የነበረው የኢትዮጵያ ተማሪ በአጠቃላይ ቁጥር ከአምስት እስከ አሥር አይበልጥም ነበር። በ1920ዎቹና 30ዎቹ ዘመን ራስ ተፈሪ ሥልጣናቸውን የሚያጠናክሩበት ዘመን ነበር። እንዲሁም የተወሰነ መፈንቅለ መንግሥት ተሞክሮ ነበር፦ የልጅ እያሱ። በኋላም ከራስ ጉግሳ ጋር ጦርነት ነበረ፣ አሜሪካንም በዚያ ጊዜ የአሜሪካን ውድቀት የሚባለው ድፕሬሽን ነበር። እነዚህ በቁጥር ከአሥር የማይበልጡ ተማሪዎች ወደ አሜሪካ እንደመጡ ለመደራጀት ችግር ነበረባቸው። ሀገሩንና ቋንቋውን እስኪለምዱ። በወቅቱ ጎልቶ የሚታየው መላኩ በያን ሲሆን ከ1920ዎቹ ጀምሮ ከተለያዩ ጥቁር አሜሪካ  ሐርለም ኒዎርክ ከነበሩ ከማርከስ ጋርቪ የሚመሩ እንቅስቃሴዎች ጋር አብሮ በመጠጋት የኢትዮጵያን ሁኔታ እያስረዳቸው እነሱም ስለ ኢትዮጵያ ግንዛቤአቸውን እያሰፉ በተለይ ጣልያን ኢትዮጵያን ከወረረች በኋላ ወደ አሜሪካ በመመለስና በዚያ ጊዜ «ቮይስ ኦፍ ኢትዮጵያ» የሚል ጋዜጣ በማዘጋጀት ጀምሮ ነበር። በፈረንጅ ከ1937 ጀምሮ እስከ 1941 እስኪሞት ድረስ ያዘጋጅ ነበር። እንዲሁም ለአርበኞችና በሱዳን ላሉ የኢትዮጵያ ስደተኞች ገንዘብ በመሰብሰብ፣ ቴምብር በማሳተም በየመደብሮች በመሄድና በር እያንኳኳ ገንዘብ ይሰበስብ የነበረ ብርቱ ተማሪ ነበር መላኩ በያን። በዚህ ሥራው ብዙ ገፍቶ ኢትዮጵያም ነፃ መውጣቷን ሳያይ በኒሞንያ በሽታ ሕይወቱ ሊያልፍ ችሏል። በወቅቱ በኢትዮጵያ ይታተም በነበረው ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ መጣጥፎች እየላከ ያወጣ ነበር። መላኩ በያን እስከዛሬ የሚታወቅበት በ19 የመሠረተው  «ኢትዮጵያን ወልፍ ፈደሬሽን» የሚባል በ1937 ድርጅት ነበር እስከዛሬም አለ። በጃይማካዎች ራስታ በሚባሉት በኩል የሚተዳደር ሲሆን አርባ ቅርንጫፎች በዓለም ደረጃ መሥርቶ የተለየ ወገን ነው። የመላኩ በያን ዘመን ተማሪዎች ከቁጥር አሥር የማይበልጡት በአብዛኛው በኢጣሊያን ወረራ ጊዜ ሲገደሉ የተረፉት ሁለት ወይም ሦስት ናቸው።

ከዚያ በኋላ ከ1950ዎቹ እስከ 1960ዎቹ ድረስ ደግሞ ሌላ ተማሪዎች ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ መምጣት ይጀምራሉ። እነዚህ እንደነ ገርማሜ ነዋይ ያሉ፣ በኋላም እነ አክሎግ ቢራራ፣ እነ ኤፍሬም ይስሃቅ የመሳሰሉ ቡድኖች ይመጣሉ። እነኚህን በአንድ ቡድን ከተን ልናያቸው እንችላለን። የነኚህ አመጣጥ ደግሞ እንደ ቀደምቶቹ የንጉሡ ሎሌ በመሆን ሳይሆን በስኮላር ሽፕ ነበር የሚመጡት። የትምህርት ድጎማ እያገኙ ሲሆን ብዛታቸውም ከ200 እስከ 500 ደርሶ ነበር። የዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ በዚያ ጊዜ አስተዳደራዊ መዋቅሯ እየተገነባ የተማረ የሰው ኃይል ያስፈልጋት ነበርና ነው። በወቅቱም የተለያዩ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም ተከፈቱ፣ በመሆኑም በርከት ያሉ ተማሪዎች ማፍራት ተጀመረ። ይህን የእነ ኤፍሬም ይስሃቅ ቡድን ልንለው እንችላለን፤ ዘመናቸውም በዚያ ጊዜ በአሜሪካ ውስጥ የመብት፣ የሰብአዊ መብት እንቅስቃሴ (ሲቭል ራይት ሙቭመንት) ይደረግበት የነበረበት ወቅት ነበር። ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ ከጦርነት መልስ የተለያዩ ልማታዊ ሥራዎች

የታቀዱበትና የሚሠሩበት ወቅት ነበር። እነኒህ ሁለተኛው ክፍሎች በዚያ ጊዜ ቁጥራቸውም ስለበዛ ስብሰባዎችን ማዘጋጀት ጀመሩ። ኮንፍረንሶች ማለት ነው። እነኒህም ስብሰባዎች በኋላ ለኢዙና ኮንፍረንስ መካሄድ መሠረት የሆኑ ነበሩ። የመጀመሪያ ስብሰባቸውም በፈረንጆቹ አቆጣተር 1959 በእኛ በ1951 ዓ.ም. ከታህሳሱ መፈንቅለ መንግስት በፊት ማለት ነው። በወቅቱም ሀሳባቸውን ለማሰራጨት የተለያዩ መጽሔቶች መውጣት ይጀምራሉ። በአጠቃላይ ስለ ኢትዮጵያ በጎ አስተሳሰብ ያላቸውን እያሰባሰቡ አብረው መሥራት ይጀምራሉ። በዚህም ሁኔታ ኢትዮጵያም በዓለም ደረጃ መታወቅ ትጀምራለች። ተማሪዎቹም ቁጥራቸው የተበራከተ በመሆኑ መደራጀት ይጀምራሉ። በወቅቱ ይህንም ያህል ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ አልነበራቸውም ይበልጡን የሚሠሩት በልማት እንቅስቃሴ ላይ በማተኮር ነበር። የልማት መልኩም በተለይ "ፊደል ሠራዊት" የሚባል እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ነበር። ይህ የፊደል ሠራዊት እንቅስቃሴ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ያሉትን በዕድሜ ገፋ ያሉትን ፊደል እንዲቆጥሩ ለማስቻል የተቋቋመ ነበር። በተጨማሪም ተማሪዎቹ የሀገራችንን ወጥ እየሠሩና እያበሉ፣ የኢትዮጵያን ጥለት እየሠሩ፣ ከሀገራችንም ባህላዊ ዕቃዎች እንደ መሶብ የመሳሰሉትን በማስመጣትና ትላልቅ እግዚቢሽኖች እያዘጋጁ በአንድ በኩል ኢትዮጵያን በማስተዋወቅ በሌላ በኩል የሚገኘውን ገቢ ገንዘብ ኢትዮጵያ በመላክ እዚያ ካሉ ተማሪ ቡድኖች ጋርና ከመንግሥት ጋር በመተባበር የተለያዩ ልማታዊ ሥራዎች ይሠሩ ነበር።

በመቀጠል በፈረንጆቹ 1960ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ የእነ ESUNA (የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በሰሜን አሜሪካ) ቡድኖች መፈጠር ይጀምራሉ ማለት ነው። ይህ ሦስተኛው ቡድን እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ ይጓዛል። በዚህ ወቅት የተማሪዎቹ ቁጥር በሺዎች የሚቆጠር ነበር። በወቅቱ ለትምህርት ከሚመጡት ሌላም ኢትዮጵያ ስደተኞችም መምጣት የጀመሩበት ወቅት ነበር። ተማሪዎቹም እየሠሩ የሚማሩም ነበሩባቸው። አንዳንዶቹም ከ1953 መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ጋር በተያያዘ የመጡ፣ በኢትዮጵያም የተማሪዎች እንቅስቃሴ እንደነ መስፍን ሀብቱ የመጡበትና እውጭ የነበረውን እንቅስቃሴ የሚያጠናክሩበት ወቅት ነበር።

በ1970ዎቹ የተለያዩ የግራ እንቅስቃሴዎች ነበሩ። የተለያዩ ሀገራት ነፃነታቸውን የሚያውጁበት ነበር። በተለይ የአፍሪካ ሀገራት ከቅኝ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት የሚታገሉበት ወቅት ነበር። የዓፄ ኃይለ ሥላሴም መንግስት እንደሚፈራው ሳይሆን ሊወድቅ እንደሚችል በ1953 ሙከራ የታየበት ነበር። በመሆኑም ይህኛው አካል በፖለቲካውም ያላቸውን አመለካከት ማስፋት የጀመሩበት፣ የግራ ንቅናቄ ወቅትም ስለነበርና የጊዜው ትውልዶች ነበሩ። አሠራራቸውም በሁለተኛው ቡድን እንደተጀመረው ዓመታዊ ስብሰባዎች ያካሂዱ ነበር። የተለያዩ መጣጥፎች በህትመት መልክ ይወጡ ነበር። በመንግሥት ላይም ተቃውሞ ያሰሙበትና በ1960ዎቹ የኢትዮጵያን ኤምባሲ እስከመያዝ የደረሱበት ደረጃ ነበር። ከተለያዩ ግራ ክንፍ ቡድኖች ጋር በመገናኘትና አብሮ በመሥራት የተጠናከሩበትና አባሎቻቸውም ትምህርታቸውን በማቋረጥ ሙሉ በሙሉ ለእንቅስቃሴው ጊዜያቸውን የሰጡበት ወቅት ነበር። የፖለቲካል ውይይት ቡድን ነበራቸው፣ መጽሐፍ በማንበብና በመወያየት፣ ሠራተኞች የነበሩትም ከሚያገኙት የተወሰነ ገንዘብ እየሰጡ ይንቀሳቀሱ ነበር። ከኢትዮጵያ ጋርም የነበራቸው ግንኙነት እንደነ መስፍን ሀብቱ፣ ሀጎስ ገብረየሱስ ሌሎችም በኢትዮጵያ እንቅስቃሴ ውስጥ ሚና የነበራቸው በየጊዜው እየመጡ የሚያበረታቱበት ወቅት ነበር።

እነኒህ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ናቸው እንግዲህ ከ1970ዎቹ ወዲህ ወደ ፖለቲካ ድርጅትነት የተቀየሩት በአውሮፓ መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)፣ በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ብቅ ያሉት። ይህ ደግሞ ከአብዮቱ ፍንዳታ ቀጥሎ ያለውን እንቅስቃሴ እንድንቃኝ ያደርገናል።

በጥቅሉ ሦስቱንም እንቅስቃሴዎች ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ብንመለከታቸው አግባብነት አለው። የነመላኩ በያን ዘመን ኢትዮጵያ ገና ወደ ዓለም ጉባኤ የገባችበት ወቅት፣ በኢጣልያን የተወረረችበት ወቅት ስለ ነበር ያኔ በራስ ተፈሪ ዕቅድ ሥር ሁነው ነበር ተማሪዎቹ የሚንቀሳቀሱት። በ1950-60ዎቹ የነበሩት ወቅት ኢትዮጵያ ዕውቅና ያገኘችበትና እንዲሁም አፍሪካን በማቀናጀት ትልቅ ሚና የምትጫወትበት ጊዜ በመሆኑ በዚያ ድባብ የተፈጠሩ ናቸው፣ በንጉሡ ነገሥቱም የተለያዩ የልማት ሥራዎች የሚካሄዱበት ወቅት ስለነበር ተማሪዎቹ በመሰላቸው መንገድ ለማገዝ ይሠሩ ነበር። ሦስተኛው ክፍል ኢዙናና በኋላ ፖለቲካ ፓርቲ የተመሠረተበት የተነሱበት ድባቡ የግራ ክንፍ ንቅናቄ የፖለቲካ ንቅናቄ የነበረበት፣ ሁሉም ሕዝብ ወደ መደብ ትግል ላይ ያተኮረበት፣ አፍሪካ ሀገሮች ደግሞ ከቅኝ አገዛዝ ነፃ የሚወጡበት ያልወጡትም የሚታገሉበት ወቅት ነበርና ሰውንም የሚቀርጸው አካባቢው ነውና በአካባቢያቸው ከነበሩና ከሚነሱ ጥያቄዎች ስለ መደብ ትግል፣ ስለ ነፃነት፣ ስለመሬት ጥያቄዎች በመመርኮዝ ሕዝባቸውን ለማገልገል ተነሱ።

ከነዚህ ሦስት አመጣጦችና አካሄዶች እንደምንረዳው ሁሉም በሚያምንበት መንገድ ሀገሩን ለማሳደግ እንደጣረና እንዳሰበ እንመለከታለን። የመጀመሪያው በንጉሡ ጥላ ሥር ሆኖ፣ ሁለተኛው ደግሞ በልማት ጎዳና ሲጥር ሦስተኛው ደግሞ በሀገሪቷ ሥርነቀል ለውጥ ለማምጣት ጥረዋል። ሦስቱም ክፍሎች በሚያምኑበት መልኩ መስዋዕትነት ከፍለዋል የተቻላቸውን ጥረት አድርገዋል።

ሌላው ጉዳይ እነኚህ ሦስት ክፍሎች የተያያዙና አንዱ የሌላኛው ተወላጅ እንደነበር መገንዘብ ያስፈልጋል። የመጀመሪያው ቡድን በአብዛኛው በኢጣልያን ጊዜ ተረሽነዋል፣ ተገድለዋል። ከነዚህ መሃል መኮንን ደስታ የተባለ በ1950ዎቹ 60ዎቹ ወደ አሜሪካ መጥቶ ከእነ ፕሮፌሰር ይስሀቅ ቡድን ጋር ልምዱን አካፍሎ ነበር። እንዴት አድርገው ከአሜሪካኖች ጋር እንደሚነጋገሩ። ይበልጥ ግንኙነት የሚታየው ግን በሁለተኛውና በሦስተኛው ቡድን መካከል ነው። ኢትዮጵያን በልማት እያገዘ የመጣውና ሦስተኛው ክፍል ለኢትዮጵያ ሥርነቀል ለውጥ ያስፈልጋታል በሚለው። ለምሳሌ ሀጎስ ገብረየሱስ፣ መለሰ አያሌው፣ እንድርያስ እሸቴ እንቅስቃሴውን ይመሩ የነበሩ ናቸው። ሦስቱ የጀመሩት በልማት መልክ ለምሳሌ ለ"ፊደል ሠራዊት" ገንዘብ ያዥ በመሆን፣ አብሮ በመሥራት ቀስ ብሎም በሂደት "ቻሌንጅ" የሚለውን መጽሔት በማዘጋጀትና በዚህ ተወልደው ለሦስተኛው ክፍል ሌላ መልክ ሰጡት ማለት ነው። በመሆኑም በአሠራራቸው ባይመሳሰሉም እንኳ አንዱ ከሌላው ተያያዥነት እንደነበረውና ከወቅቱ ጋር እንዴት እንደተጓዙ መገንዘብ ይቻላል።

# 13.1 የካቲት 66 ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አቅጣጫን መሳት

ከ1966 ሕዝባዊ አብዮት መቀልበስና ወታደራዊ አምባገነን መንግሥት ሥልጣነ ዘመን፡- ዘመነ ሽብር

በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ሚና ከፍተኛ ነበር። በዓፄ ኃይለሥላሴ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው እንቅስቃሴ የዘውድ አገዛዝ ሥርዓቱን ገርስሶ ለመጣል መሪው መፈክር "መሬት ለአራሹ" በማድረግ በግምባር ቀደምትነት ተሰልፏል። የዚህ መፈክር አንቀሳቃሾችና ተሸካሚ መሪዎች በአብዛኛው ከመሬት ባላባትና በወቅቱ ከደህና ቤተሰብ የወጡ ተማሪዎች ለመሆናቸው እነ ጥላሁን ግዛው ምስክር ናቸው። የሥርዓቱን አስከፊነት ተመልክተው ለድሀው ሕዝብና ለሀገራቸው የጮሁና ግምባር ቀደም በመሆን የታገሉና ያታገሉ ብለውም እንቅስቃሴው የተቀናጀ መልክ ይኖረው ዘንድ የመደራጀትን እርሾ የዘረጉ ናቸው።

ከ1953 ዓ.ም. የገርማሜና መንግስቱ ነዋይ በንጉሡ ላይ የተደረገ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ በኋላ የተማረው ክፍል የነበረው ባላባታዊ ሥርዓት ላይ የሚያካሂደው እንቅስቃሴ እየተጠናከረ መምጣትና ጥያቄዎቹም ከአካባቢያዊነት አልፈው ፖለቲካዊ ይዘት እየያዙ መምጣት ጀመሩ። ቁጥሩ ቢያንስም በወቅቱ አንድ ጥላሁን በሺህ ታጋይ ይታሰብ ነበርና ጥላሁን ግዛው ላይ በንጉሡ ወታደሮች የተወሰደው እርምጃ ይበልጥ ተማሪውን አነሳሳ። ከሕዝብ በሚሰበሰብ ቀረጥ የሚማረው ተማሪ ወገንተኛነቱን ለተበዳዩ ሕዝብ ሰጠ። ትልቁን የባላባታዊ ሥርዓት ማናጊያ መፈክሩን ይዞ ግምባር ቀደም ፋና ወጊ ሆነ "መሬት ለአራሹ!"።

ቅድመ የካቲት 66 በውጭ ሀገር የነበሩት የተማሪዎች እንቅስቃሴ ወደ ፖለቲካ ድርጅትነት ያደጉበት ነበር። በአውሮፓ በኃይሌ ፊዳና ዶር ነገደ ጉበዜ የሚመራው መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)፣ በሀገር ቤት በእነ ብርሃነመስቀል ረዳና ተስፋዬ ደበሳይ የሚመራው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ግምባር (ኢሕዴግ) የተመሠረቱበት ወቅት ነበር። እኚህ ሁለት የፖለቲካ ድርጅቶች በሕዝቡ ውስጥ ገና መሠረታቸውን ሳይዙ ነበር የካቲት 1966 አብዮት የተከሰተው። በወቅቱ ኢሕዴግ በኢትዮጵያ የዘውድ አገዛዝ ሊወድቅ የሚችለው በመሣሪያ ትግል መሆኑን በማስረገጥ የትጥቅ ትግል መሠረቱን ለመጣል ወደ ትግራይ በረሃ በ1964 ዓ.ም. በመግባት የመጀመሪያው አስኳል የሠራዊቱ አካል ወደ ፊልስጤም ለወታደራዊ ሥልጠና ተጉዟል። በሌላ በኩል መኢሶን በወቅቱ  የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ ወቅት የፖለቲካ ንቃቱ ዝቅተኛ በመሆኑ ከመሳሪያው ትግል በፊት ሕዝቡን ማንቃትና የፖለቲካ ሥራ መስራት አስፈላጊነቱን በማስረገጥ በኢሕዴግ የተጀመረውን የትጥቅ ትግል ጉዞ ባለመቀበል ልዩነቱን አስመዝግቧል።

በተጨማሪም በወቅቱ ከነበረው “የመሬት ለአራሹ” ጥያቄ በተጨማሪ ከፍተኛውን ሥፍራ የያዘው የብሔር ጥያቄ ነበር። በዚህ የብሔር ጥያቄ ለመጀመሪያ ጊዜ በዋለልኝ መኮንን በኢትዮጵያ የብሔር ጥያቄ ጽሁፍ ሲቀርብ በተራማጁ ክፍል ከፍተኛ ጭቅጭቅን ያስነሳ ነበር። በወቅቱ የኤርትራም ሽምቅ ተዋጊዎች እንቅስቃሴአቸውን ያጠናከሩበት ወቅት ነበርና የብሔር ጥያቄ ዋና ትኩረትን ስቦ ነበር። በዚህም ጥያቄ በኢሕዴግ በኩል በኋላ ኢሕአፓ “የብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከመገንጠል” ሲደግፍ በመኢሶን በኩል “የብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ በዴሞክራሲያዊ መንገድ” ይገፋ ነበር። በሁለቱ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል እነዚህ ልዩነቶች እንዳሉ ነው የየካቲት 1966 ዓ.ም. አብዮት የተቀጣጠለው።

የየካቲት 1966 አብዮት የሀገርና የህዝብ ስለሆነ ነው ሕዝባዊ አብዮት የሚባለው። የሕዝብ ብሶት በየአቅጣጫው ስለተቀጣጠለ ነው ግብታዊ አብዮት የሚባለው። የጋራ ጭቆና፣ አድልዎ፣ ብዝበዛ ያንገበገበው ሕዝብ የጋራ ጥያቄው የአለው ሥርዓት ላይ እንዲያምጽ አድርጎት የእንቅስቃሴው መሪ ኃይል ይዞት የተነሳው የጋራ ጥያቄ በመሆኑ ነው መሪ አልባ እንቅስቃሴ የሚባለው። እንቅስቃሴውን ሁለቱም የፖለቲካ ድርጅቶች (መኢሶን፣ ኢሕአፓ) ለመምራትም ሆነ አቅጣጫ ለማስያዝ በማይችሉበት ደረጃ ድንገት የተከሰተ ማዕበል ነበር። ይህን ከነበረው የዘውድ አገዛዝ ቁጥጥር ውጭ የተንቀሳቀሰውን የህዝብ ቁጣ ሊያስቆመው የሚችል ኃይል ባለመኖሩ የዓፄው ሠራዊት ሳይቀር የእንቅስቃሴው አካል ሆኑ። በወቅቱ በመሳሪያ ኃይል ታጥቆ ያለው ክፍል ወታደሩ በመሆኑ ወታደሩ ቀስ በቀስ የእንቅስቃሴው አካል ከመሆን አልፎ መሰባሰብ ጀመረ። በዚህም ሂደት ከተለያዩ የጦሩ ክፍሎች የተውጣጣ ኃይል እራሱን እያጠናከረ ሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም. የጦር ኃይሎች የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ደርግ ተቋቋመ። ደርግ ከመቋቋሙ ቀደም ብሎ የንጉሡን ከፍተኛ የሲቭልና ወታደራዊ ባለሥልጣናትን ጨንሮ በወቅቱ የነበሩ ባላባትና መኳንንትን በየጊዜው ማሠር ጀምሯል። ደርግ ከተቋቋመ በኋላ የራሱን አስተዳደራዊ ኮሚቴዎች በማቋቋም ቀስ በቀስ የንጉሡን መዋቅሮች መቆጣጠር ያዘ። በዚህ ሁሉ ሂደት ሲጓዝ ደርግ የሕዝቡን ጥያቄዎች እያስተጋባ ነበር። የዚህ ወታደራዊ ኃይል ስብስብ ደርግ እራሱን እያጠናከረ በቀጣይነት መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም. ንጉሱን ከሥልጣን አውርዶ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ስም የመንግሥት ሥልጣንን ያዘ። የንጉሱን ምክር ቤት ዘጋ፣ የደህንነት አካሉን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠረ።

ደርግ ሥልጣን እርከኑን እንደያዘ ወዲያውኑ ማንኛውንም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፣ የሥራማቆም አድማ፣ ወዘተ መብት የሚያግድ አዋጅ አወጣ። የዚህ አዋጅ መውጣት የተራማጁን ክፍል አስቆጣው። የተነሳው ሕዝባዊ እንቅስቃሴም አደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሆነ ፍንጭ ሰጠ። ደርግ የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ተራማጅ ኃይሎች በተለይ ከ1953 ዓ.ም. የታህሳሱ ንቅናቄ ጀምሮ የታገሉለትንና የተሰዉለትን የዴሞክራሲያ መብት ጥያቄ ማገዱ ብዙዎችን ያለው አማራጭ ትግሉን መቀጠል እንደሆነ ግንዛቤ አመላከተ። በየጊዜውም የሚወሰዱ ወታደራዊ እርምጃዎች የደርግን አገዛዝ ጥያቄ ውስጥ እያስገባ ከመምጣቱም በተጨማሪ ቀደም ሲል የተደራጀው ክፍል ወዴት ማምራት እንዳለበት መስቀለኛ መንገድ ላይ አስቆመው።

ደርግ በቀጣይነት በጥቅምት ወር 1967 ዓ.ም. ያወጀው የኅድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ በበርካታዎች ዘንድ ተቃውሞ ገጠመው። የመሬት ባለቤትነትን አዋጅ ተግባራዊ ሳይሆን ወጣቱንና የተማረውን ክፍል ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ መላክ በታጠቁ ባላባቶች ማስፈጀት ይሆናል ከሚል አዋጁን “ከፈረሱ በፊት ጋሪው” በሚል ተቃውሞ ቢገጥመውም የደርግ በራሱ አካሄድ መጓዝ መፈለግ አሁንም የወታደራዊው አገዛዝን አካሄድ ጠቋሚ እየሆነ መጣ። ዘመቻውም ለልማትና ለዕድገት ሳይሆን ወጣቱንና ተማሪው በከተማ በተለይ በአዲስ አበባ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ለመበታተንና ደርግ እፎይታ ለማግኘት ያቀደው ተግባር መሆኑ ተፃፈ፣ ተሰበከ። በቀጣይነት ደርግ ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም የደርጉን ሊቀመንበር ብርጋዴል ጄነራል አማን አንዶምን ጨምሮ በድንገት የረሸናቸው 60 የዓፄ ኃይለሥላሴ ባለስልጣናት ድርጊት ብዙዎችን አስደነገጠ። የደርግን ማንነት ይበልጥ ገላጭ ሆነ። ሕዝባዊ አብዮት እዚህ ምዕራፍ ላይ አከተመ። በዚህ ሁኔታ አሁን ቅድመ አብዮት ጥንስሳቸውን ያደረጉት ኢሕዴግ እና መኢሶን የየራሳቸውን ግልጽ ያለ አቋም በመውሰድ በደርግ የተጠለፈውን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ፣ ምላሽ ያጣውን ሕዝባዊ ጥያቄ ለማስመለስ የሚወስዱት አቋም ወሳኝ ነበር።

ኢሕአፓ ሕዳር 15 ቀን 1967 ዓ.ም ባወጣው ዴሞክራሲያ ዕትሙ ቅጽ 1 ቁጥር 17 “ጭፍን ፋሺዝም በኢትዮጵያ ነገሠ” ሲል ግልጽ አቋሙን ሲያስቀምጥ መኢሶን በበኩሉ “ለነቃ፣ ለተደራጀና፣ ለታጠቀ” ሕዝባዊ ትግል ለደርግ መንግሥት ሂሳዊ ድጋፍ መቀጠል አለብን በማለት ወደ ደርግ ተጠጋ።

በነዚህ ሁለት ድርጅቶች እርስ በርስ በሚገባ ተወያይተውና ተመካክረው አንድ የጋራ ስምምነት ላይ ከመድረስ ይልቅ ከውጭ ይዘውት የመጡትን ልዩነት በማጠናከርና በእልህና ካለመደማመጥ በወሰዱት አቋም መኢሶን ጠቅልሎ ደርግ ጉያ መግባት ብቻ ሳይሆን የደርግ ፖሊሲ አውጭና ዋና ተዋናይ ለመሆን በቃ።

በቀጣይነት ደርግ የካቲት 11 ቀን 1967 ዓ.ም. የወሰደው ሥርነቀል አዋጅ ለዘመናት የነበረውን የባላባትና የጭሰኛ ግንኙነት "በመሬት ለአራሹ አዋጅ" በጣጥሶታል። ይህ አዋጅ በኢሕአፓ በኩል ተቀባይነት ቢያገኝም ለተግባራዊነቱ የ"ዴሞክራሲ መብታ ያለገደብ" ተግባራዊ መሆና ከሁሉም ኅብረተሰብ ክፍል የተውጣጣ "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" አስፈላጊነትን አጠንክሮ አስቀመጠ።

የደርግ አንዱ መለያው ብሔረተኝነት ነው። ይህ ደግሞ ከፋሽስቶች ሒትለር "ጀርመን ከሁሉም በላይ" እያለ ነው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች የፈጀው። ደርግም "በኢትዮጵያ ትቅደም" ስም በሀገርና ሕዝብ እየማለ አጋጣሚ በፈጠረለት የያዘውን ሥልጣን በሀገሪቱ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችን አካቶ፣ ከተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች የተውጣጡ አካላትን አካቶ ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት ለመመሥረት ቀናነቱ ሊኖረው በተገባ ነበር። ሀገርን፣ ገንዘብን፣ ተቋማትን፣ መሳሪያን የያዘው መንግሥት ደርግ ነውና ለሀገርና ለሕዝብ እስከሆነ ድረስ የተጠየቀውን ጥያቄ ያለምንም ማቅማማት በቀና መንፈስ ተግባራዊ ለማድረግ የሚቀለው ቤተመንግሥት ላለው ኃይል ነበር። ሆኖም በተቃራኒው የደርግና የመኢሶን ጣምራ መንግሥት ያለውን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በማፈን ለመቀጠል ሲሉ በሕዝቡ ላይ የሚጥሉት የመብት አፈናና ግፍ ይበልጥ ትግሉን እያቀጣጠለ፣ ለኢሕአፓ ሕዝባዊ መሠረት በሁሉም የሀገሪቷ ክፍል እየሰጠው ሄደ። የሕዝብ ጥያቄ አልተመለሰምና ሕዝብ ለመብቱ ከሚሞግትለት ድርጅት ጎን ተሰለፈ። ኢሕአፓ በአጭር ጊዜ ከፍተኛ ሕዝባዊ መሠረት በሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ዘንድ አገኘ። በሌላ በኩል ደርግን የከበቡ ሌሎች ምሁራን እራሳቸውን ወደ ፖለቲካ ድርጅትነት እየቀየሩና በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም የሚመራውንም ደርግ የራሱን ፖለቲካ ድርጅት ይመሠርት ዘንድ እያበረታቱና እያስተማሩ ወታደራዊ ባህሪውን ለመጠቀም አቅጣጫ ቀያሽ ሆኑ።

ደርግ ሥልጣን ከያዘ ለሁለት ዓመት የተጓዘው ትግል የደርግን ፋሽስታዊና ጦረኛነት ግልጽ ያደረገ ነበር። በየጊዜው ግድያ፣ የፍየል ወጠጤ፣ አዋጅ፣ ወዘተ የደርግ መለያው ሆነ። የኤርትራን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚቀርብለትን አሳብ አሻፈረኝ አለ። በትግራይ ያቆተቆጡ የዘር ድርጅቶችን፣ በኦነግ በኩል የሚቀርቡ የኦሮሞን ጥያቄ፣ በምስራቅ ኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎችን ሁሉ ምላሽ በጦር ለመስጠት ወሰነ። በዚህም ሂደቱ በውስጡ የሚገጥሙትን ተቃውሞዎችና የሀሳብ ልዩነቶች ማስተናገጃው ግድያ ሆነ። አብረው የመሠረቱትን የደርግ አባላት በሦስት ወር ዕድሜው በጄነራል አማን አንዶም የጀመረው፣ እነ ሻለቃ ኪሮስ ዓለማየሁ፣ ሻምበል ሲሳይ ሀብቴንና ሌሎች የደርግ አባላትን እየበላና ሌሎችንም በፍርሃት እያሸማቀቀ ወደ አንድ ፈላጭ ቆራጭ አምባገነን ፋሽስታዊ ገዥ መንግሥቱ ኃይለማርያም እጅ ሀገሪቷ የወደቀችው ገና ከጅምሩ ነበር።

ደርግ ሥልጣን ከጨበጠበት ወቅት አንስቶ ዕለት ተዕለት እየወሰዳቸው ከአለው የመብት ረገጣ ጀምሮ ሕግን ተገን ያላደረገ በፖለቲካ ውሳኔ ብቻ የሚደረጉ ግድያዎች የየካቲት ሕዝባዊ አብዮት እንዳከተመ ፍንጭ ሰጡ። ሕዝባዊ አብዮቱን ተገን አድርጎ የሥልጣን ኮርቻ ላይ የወጣው አምባገነናዊ ወታደራዊ አገዛዝ በአንድ በኩል ተነስተው የነበሩ ሕዝባዊ ጥያቄዎችና መፈክሮች በሌላ በኩል ቀጣይ ትግል ገጠሙ። የካቲት 66 ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የዘውድ አገዛዝን ገርስሦ ፋሺዝምን አነገሰ። የተደራጀ ሕዝባዊ ኃይል ባለመኖሩ መሳሪያ የታጠቀው የወታደር ክፍል ሕዝባዊ መነቃነቅ የቀደደለትን በር አስታኮ ቤተ መንግሥት ገባ። በሌላ በኩል ሕዝባዊ ትግሉ ቀጠለ።

## 13.2 የኢሕአፓ እንቅስቃሴ በአጭር መቀጨት

ኢሕአፓ ገና ራሱን እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ይፋ ሳያወጣ በጊዜው የነበሩት ተራማጅ ኃይሎች የዓፄውን ፊውዳላዊ የግፍ አገዛዝ በሥር ነቀል ለውጥ መወገድ ያለበት ሥርዓት መሆኑን ተገንዝበው በአብዛኛው ወደ ትጥቅ ትግሉ አድልተው ለትጥቅ ትግል የሚያመቹ አካባቢዎችንና ሁኔታዎችን በማጥናት፡ የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶችን ለማድረግ ወደ ሜዳው ገብተዋል። በዚህ ሂደት ላይ የካቲት 66 ዓ.ም. አብዮት በግብታዊነት ፈነዳ። በወቅቱ እነኚህ ኃይሎች በቅጡ የተጠናከሩና የተደራጁም

አልነበሩምና የሕዝቡን አብዮት ሊመሩ አልቻሉም። መሣሪያ ያለው ኃይል፡ ደርግ ስልጣኑን ተረከበ። ደርግ መስከረም ሁለት ቀን 1967 ዓ.ም. ንጉሡን አውርዶ ስልጣኑን የሕዝብ መንግስት እስኪቋቋም በሞግዚትነት ለማስተዳደር አዋጅ አወጣ። ይህን አዋጅ ከማወጁ ቀደም ብሎ በነሐሴ 66 መጨረሻ ላይ ደርግ ማንኛውንም ዓይነት ተቃውሞ ሰልፍ፡ ሕዝባዊ ስብሰባ ማድረግን፡ በአዋጅ ከለከለ። በማግሥቱ ንጉሡን አውርዶ ሥልጣኑን ያዘ። ደርግ ሶሻሊዝምንና ኢትዮጵያ ትቅደምን መመሪያው አድርጐ አወጀ። አያይዞም የኢትዮጵያ ትቅደምን መርህ መቃወም የአድሃሪው ርዝራዥ ኃይሎች እንደሆኑ ፈረጀ። ማንኛውንም ዓይነት ሰላማዊ ተቃውሞ አገደ። በጊዜው የነበሩ የሲቪክ ማኅበራትን ማዋከብ ጀመረ።

ደርግ በየካቲት 1967 ዓ.ም. የመሬት አዋጅን አወጀ፡፡ ይህ አዋጅ የነበረውን ፊውዳላዊ ሥርዓት ከሥሩ ነቅሎ ጣለው። ኢሕአፓም በወቅቱ በዴሞክራሲያ እትሙ የአዋጁን አስፈላጊነትና ቀና መንፈስ አወድሶ ሆኖም ግን ስለተግባራዊነቱ ያሉትን ጥያቄዎች አስቀምጧል። በተለይ አብሮ የተካተተውን የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት መቋቋም ላይ ያለውን ቅሬታ ዴሞክራሲያ አስተጋባች።

የየካቲት 67ቱ የመሬት አዋጅ በጊዜው በነበሩ ተራማጅ ኃይሎች ላይ የነበረውን አለመግባባትና ክፍፍል ይበልጥ አጠናከረው። በኢሕአፓ እራሱ ለትጥቅ ትግሉ አስፈላጊውን ዝግጅት ለማድረግ በሜዳ ከነበሩ ውስጥ "ከእንግዲህ የምንታገልለት ዓላማ "መሬት ለአራሹ" ጥያቄ መልስ ከአገኘ "የምን ትጥቅ ትግል ነው"" ብለው ወደ ደርግ የገቡ እንደነበሩ ታሪክ ዘግቦታል። በተጨማሪ ከመኢሶን ጋር የነበረው አለመግባባት እየጨመረ፡ ቅራኔው እየከረረ መምጣትን አስከትሏል። ኢሕአፓ በወቅቱ "ለጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ምሥረታና ለዴሞክራሲያ መብት ያለገደብ" መፈክሩን ከፍ ሲያደርግ፡ መኢሶን "ደርግን ሂሳዊ ድጋፍ (critical support) እየሰጠን መጓዝና የዴሞክራሲ መብትም በገደብ" ብሎ ልዩነቱን ይፋ አደረገ። ሙሉ በሙሉም ድጋፉን ለደርግ ሰጠ። ኢሕአፓ በበኩሉ ዘር፡ ሃይማኖት፡ ፆታ፡ ክልል ሳይለይ ሕዝቡን ማደራጀት ያዘ።

ነሐሴ 1967 ዓ.ም. ኢሕአፓ እራሱን ይፋ አድርጐ ፕሮግራሙን ለሕዝብ አሰራጨ። በዚህ ፕሮግራሙ ላይ የሚከተለው የትግል ስልት የትጥቅ ትግል መሆኑን ይደንግግ እንጂ በተግባር ሰላማዊ የትግል ጐዳናውንም ተጠቅሟል።

በ1967/68 ዓ.ም. የሰላማዊ ትግል ጐዳና ኢሕአፓ ከመንግሥት ሚዲያ ጀምሮ ያገኘውን ዘዴ ሁሉ ተጠቅሟል። በየቀበሌው ወጣት ማህበራት፡ በሴቶች ማህበራት፡ በቀበሌ ማህበራት ከሰላማዊ ትግል አኳያ መድረኩን በሰላም ተጠቅሞበታል። በሠራተኛ ማህበራት፡ በመምህራን ማህበራት የተጫወተው የቅስቀሳና የትግል ዘዴ ሁሉ ሰላማዊ ነበር። ተቃውሞዎች ይደረጉ የነበረው ትምህርት በማቆም፡ ሥራ በማቆም ነበር። በቀበሌ ማኅበራት የመሠረተ ትምህርትን ፕሮግራም በመጠቀም ከፍተኛውን የማደራጀት ሚና ኢሕአፓ ተጫውቷል። በአስፈላጊው ወቅት የኢሕአፓን አቋም የሚያስተጋቡ መፈክሮች፡ በራሪ ወረቀቶች ይበተናሉ፤ የኢሕአፓን አርማ የያዙ ሰንደቆች በየኤሌክትሪክ ሽቦው ላይ ይሰቀላሉ። በአጥሮች፡ በቴሌፎን ሳጥኖች ላይ ወቅታዊ መፈክሮች ይፃፋሉ። ይህ ሁሉ ከኢሕአፓ በኩል በሰላም የሚደረግ ትግል ነበር። የትግሉ ዘዴም በ14ቱም ክፍላተ ሀገራት እየተካሄደ ነበር። የደርግን የእድገት በኅብረት ዘመቻ ኢሕአፓ ገበሬውን በማንቃት፡ በማደራጀት ተጠቅሞበታል።

ወቅቱ እጅግ በጣም የለውጥ ፍላጎት የተፈለገበት ነበርና እያንዳንዷ ደቂቃ በርካታ ለውጦችን እያስመዘገበ በፈጣን ሁኔታ ነበር የሚጓዘው። ኢሕአፓም በአጭር ጊዜ በሁሉም አቅጣጫ ሕዝባዊ መሠረቱን ለመዘርጋት የተደረገው ተጋድሎ የዚያን ትውልድ ጥንካሬ ያንጸባርቃል። በዚህ ሁሉ ሰላማዊ ትግል ጐዳና ታዲያ ሰልፍ የሚወጣው ላይ ደርግ ይተኩሳል፡ ይገድላል፡ ያስራል። የሠራተኛና የመምህራን ማኅበርን ያዋክባል፡ አባላቱንና መሪዎቹን ያስራል ይሰውራል። ተጠርጣሪ የተባሉ የኢሕአፓ አባላትን በተለይ መኢሶን፡ ወዝ ሊግ እና ሌሎች አሳልፈው ስማቸውን ለደርግ የሰጡዋቸውን ደርግ በየአካባቢው ያሳድድ ነበር። ያገኛቸውን አስሯል፡ ገድሏል። ኢሕአፓ እጅግ በጣሙን በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ጥሩ ተደማጭነት እያገኘ መምጣት ደርግ በየአቅጣጫው የሰላማዊ መንገዱ ተቃውሞ ጫና እየበዘበትና ሊቋቋመው እያቃተው ሲመጣ የሚወስዳቸው አጸፋዊ እርምጃዎች እጅጉን እየከበዱ መጡ። ደርግ በኢሕአፓ መሪነት የሚካሄደውን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለማዳከምና ለመምታት ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ ቁጥራቸው በመጠን ይነስ እንጂ ያስራል፣ ይገርፋል፣ ይሰውራል። ትግሉ እየቀጠለና በኢሕአፓ የበላይነት እየያዘ ሲመጣ በተለይ ከ1968 ዓ.ም. የሜይ ዴይ በዓል ዝግጅት በኢሕአፓ የበላይነት በመከበሩ ደርግ፣ መኢሶንና ወዝ ሊግ እንዲሁም ሌሎች ካድሬዎች ኢሕአፓ ካልጠፋ ዘመናቸው እንዳበቃላቸው የተረዱበት ወቅት ነበር። ማንኛውንም ተቃዋሚ በተለይ ኢሕአፓን "በአብዮቱ ላይ የመጣ ጠላት" በማለት ደርግ የማጥቃት እርምጃውን

በሠፊው ለማካሄድና ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት መስከረም 1969 ዓ.ም. በኢሕአፓ ላይ ጦርነት አወጀ። የደርግ የማጥቃት እርምጃ ሰላማዊ መድረኮችን በመጠቀም ይካሄድ የነበረውን እንቅስቃሴ ማገድ፡ ማፈን የኢሕአፓን እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ በህቡዕ እንዲሆን አስገደደው። የብዙሃን ድርጅቶች ሳይቀሩ በህቡዕ መንቀሳቀስ ግድ ሆነባቸው። የነበሩ ሕዝባዊ መድረኮች ሁሉ እየጠበቡ መጡ። በተጨማሪ የኢሕአፓ አባላት ናቸው በመባል የሚጠረጠሩትን ማሳደድና ማሰር፡ መግደል የደርግ የዕለት ተለት ተግባር ሆነ። ደርግ በኢሕአፓም ላይ በይፋ መስከረም ወር 1969 ዓ.ም. ጦርነት አወጀ።

ኢሕአፓም በሰላም ትግሉ ሂደት የኢትዮጵያን ላብ አደር፡ ወጣት፡ ተማሪ፡ ሴቶችን፡ መምህራንን፡ ወታደሩን፡ አርሶ አደሩን ወዘተ. ለማደራጀት የተጠናከረ ትግል ለማድረግ ቢጠቀምበትም የደርግን ሥርዓት ግን በሰላማዊ መንገድ መቀየር እንደማይቻል ከጅምሩ የታወቀ ነበርና ኢሕአፓ እራሱን ለመከላከል የከተማውን ትጥቅ ትግል ጀመረ። ደርግ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤትን ሲያቋቁም አብሮ የንብረት ግምባር ጥሪ አሰምቶ ኢሕአፓ ለጥሪው አዎንታዊ ምላሽ ነበር የሰጠው። ጥሪውን በበጎ ጐኑ ተመልክቶ መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ግን አስቀምጧል። ደርግም ባህሪውን ሊለውጥ ሳይሆን ለይስሙላ የጠራው ጥሪ ስለነበር ፋሽስታዊ አገዛዙና ዱላው ላይ ጠነከረ። ኢሕአፓም በትጥቅ ትግሉ ደርግን ተናነቀው። የከተማው የመሣሪያ ትግል እየተካሄደ ጎን ለጎን ሰላማዊ ትግሉ አላቋረጠም። ሰላማዊ ሰልፎች ይካሄዳሉ፡ ሰላማዊ የሥራ ማቆም አድማ ይጠራል፡፡ በትጥቅ ትግል ስልት መሣሪያ ቢያዝም በተግባር የሰላማዊ ትግሉ አስተዋጽዖ ከሁሉም በላይ መሆኑን በመረዳት በሰላም ብዙ ክንዋኔዎች ተካሂደዋል።

ከ1969 ዓ.ም. መስከርም ወር በኋላ ኢሕአፓም መከላከል አለበትና የከተማ ጥቃት መሰንዘር ጀመረ። የደርግም የጅምላ እሥርና ግድያ በቤት ለቤት አሠሳ በተለያየ ቦታና ጊዜ እየተጠናከረ መሄድ ጀመረ። ይህም አሠሳ በርካታ አባላቱንና ብርቅዬ አመራሩን አሳጣው። በተጨማሪ በደርጉ ውስጥ የነበሩ ቅን ዴሞክራት አባላትን መንግሥቱ ኃይለማርያም ጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም. በአካሄደው ሴራ ከገደላቸው በኋላ የዚህ ፋሽስት አምባገነን መሪ የበላይነትና ፈላጭ ቆራጭነት ግልጽ እየሆነ መጣ። አሁን መንግሥቱ ኃይለማርያም ያለምንም ተቀናቃኝ እራሱም ገዳይ በመሆንና በሥሩ ያሉትን የደርግ አባላትና ካድሬዎች በሞላ ከነመኢሶንና ወዝ ሊግ ዓይነት ድርጅቶች ጋር ያላቋረጠ አሰሳና የግድያ ዘመቻ በሰፊው ቀጠሉበት።

ማንንም ተጠርጣሪ ግለሰብና ወጣት የሆኑትን በመንገድ ገድሎና ሬሳ ጥሎ በመሄድ የማሸበር ቅድመ ቀይ ሽብር "ነፃ እርምጃ" በሚል ስያሜ በመላ ሀገሪቷ በደርግ ገዳዮችና ወኪሎች አማካኝነት ተካሄደ። በዚህም በርካታ የፓርቲው አባላት በየጊዜው ይገደሉ ጀመር። የደም ጥማቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው ፋሽስቱ መንግሥቱ ኃይለማርያምና ተባባሪዎቹ በከተማ ከቀበሌ እስከ ክፍለሀገር በገጠር ከትናንሽ መንደር አውራጃዎች እስከ ክፍለሀገር በተዋቀረ የግድያ መምሪያና ሁሉም የደርግ አባላትና የከበቡት ካድሬዎች በተሰማሩበትና በተሳተፉበት የእሥር፣ ማሰቃያና መግደያ እሥር ቤቶች በየሠፈሩ ተከፍተው ለመታሰር፣ ለመገረፍና ለመገደል መለያው ወጣትነት ብቻ ሆኖ በርካታ ሕጻናትንና አዛውንትን ጨምሮ ያልተቋረጠ የቀን ተቀን ግድያ በመላዋ ኢትዮጵያ "ቀይ ሽብር" የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ተካሄደ። በዚህ ዘመቻ ኢሕአፓ ብቻ አይደለም ሀገር ተመታች፣ ተገደለች። እስከ ዛሬ እንዳንታንሰራራ ሆና ተሽመደመደች። በዚህ ሂደት የነበረው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በሙቶ ሺህ በሚቆጠሩ ዜጐች መስዋዕትነት ድልን ሳይሆን ፀፀትን አበሰረ። ሕዝብን ሳይሆን ፋሺዝምን አነገሠ። ሙብትን ሳይሆን ግድያን አስከበረ። የኢሕአፓም ታሪክና ትግል ታሪክ ሁኖ ተቀመጠ።

ደርግ በኢሕአፓ ላይ የበላይነቱን አጠናክሮ በቀይ ሽብር እርምጃው በተለይ የከተማውን እንቅስቃሴ "ፀጥ" ከአደረገው በኋላ ኢሕአፓ በአብዛኛው ወደ ገጠሩ ትጥቅ ትግሉ አደላ። በከተማ ውስጥም ሆነ በየትኛውም የሀገሪቷ ክልል የኢሕአፓ እንቅስቃሴ መዳከም ሳይሆን ተመታ። በሰሜኑ የሀገራችን አካባቢ፡ በትጥቅ ክፍሉ አካባቢ ብቻ እንቅስቃሴው ተወሰነ።

የአውሬ ለማዳ የለውምና መኢሶንና ወዝ ሊግ አለማምደው አሰልጥነው እንዲያጣጥም ያደረጉትን ኢሕአፓን ሳይጨርስ እነሱም ላይ ዘፍ አለባቸው። ፋሽስት መንግስቱ ኃይለማርያም ይመኝ የነበረውን ያለምንም ተቀናቃኝ ፈላጭ ቆራጭነቱን በማረጋገጥ ከደርግነት ወደ ፕሬዘዳንትነት፣ ከወታደር ወደ ሲቪል ተሸጋገረ። ብቸኛነቱንና ወሳኝነቱን ለማረጋገጥ "ከጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም ቆራጥ አመራር ጋር ወደፊት" አስጨፈረ። ከገዳይነት ወደ ፈርጣጭነት የተሸጋገረው መንግሥቱ ኃይለማርያም ለራሱ ጓደኞች ያልሳሳ ምርጫ የሌለው የሰው አውሬ ነበር። ነውም።

ኢሕአፓ በተለይ በደርጉ ውስጥ ዋንውን መረጃ የሚሰጡትንና ቅን ዴሞክራት የደርግ አባላት የነበሩትን ፋሽስት መንግሥቱ ኃይለማርያም ጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም. በረቀቀ ዘዴ ከገደለ በኋላ ሁኔታዎችን ቆም ብሎ መመልከት ነበረበት። ኢሕአፓ ከዚህ ወሳኝ ወቅት ጀምሮ በቀጣይነይ መንግሥቱ ኃይለማርያም ወደ ሰው አውሬነት መቀየሩን በአደባባይ በአደረገው ደም የተሞላ ጠርሙስ ሰበራ ሚያዝያ 6 ቀን 1969 ዓ.ም. ሲያጓራ ወዴት እየተጓዘ እንደሆነ መቃኘትና የትግሉን አካሄድ

መገምገም አስፈላጊ ነበር። ደርግ አብቅቶለት በአንድ ፈላጭ ቆራጭ ገዳይነት የሚመራ ደርግ ግድያን በዘመቻ ሊያካሂድ ሲነሳ የጠላትን ኃይል አውሬነት ተረድቶ እልህ ከመጋባት ይልቅ ቢያንስ ሊከሰት የሚችለውን ጭፍጨፋና ሊከተል የሚችለውን ውጤት ገምግሞ አፋጣኝ እርምጃ በመውሰድ ትግሉ ወደ አሲምባና ሌሎች የገጠር አካባቢዎች ላይ እንዲያመዝንና ቀሪ አባላቱንም በማትረፍ፣ ትግሉም ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ የደርግን "ቀይ ሽብር" በመጠኑም ቢሆን ማሳለፍ በተቻለ።

በደርግ የቤት ለቤት አሰሳ ብርቅዬ አመራር አባላቱንና ከፍተኛ እርከን ላይ የነበሩትን አባላቱን ቀን ተቀን እያጣ ፓርቲው የተገዳይ ተመልካች መሆን ለመጥፊያው አስተዋጽዎ አድርጓል ቢባል ሚዛን ይደፋል። ፓርቲው ከደርግ አውሬአዊ ባህሪ ጋር ተዳምሮ በውስጡ የተፈጠረው የአንጃ ሁኔታ ምን ያህል የድርጅቱ ምስጢር ለጠላት እየሾለከ መሆኑን በመረዳትና በመገንዘብ የአሠራር ለውጥ ለማድረግ አለመቻሉ ከኢሕአፓ በኩል በተለይ ከአመራር አካሉ ዘንድ የሚጠቀስ ደካማ ጎን ትግሉ ለድል እንዳይበቃ አስተዋጽዎ ማድረጉን መቀበል ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ የያ ትውልድ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያን ታሪክ በሚገባ አለማወቅ ወይም ትኩረት አለመስጠት ለስህተት ዳርጎታል። የኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ሲነገር፣ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ ሰሎሞናዊ አገዛዝ ሦስት ሺህ ዘመን እንዳስቆጠረ ሲተረክ፣ ከዛም የዛጉዌ አገዛዝ እንደገና በለይኩኖ አምላክ አማካይነት ወደ ሰሎሞናዊ አገዛዝ፣ እንደገና ወደ ዘመነ መሳፍንት፣ ኢትዮጵያ በአንድ አስተዳደር እንድትገዛ በዓጼ ቴዎድሮስ የታቀደውን ዓፄ ዮሐንስ በቀጣይነትም በዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ በአንድ አስተዳደር ግዛቷንና ሉዓላዊነቷን ጠብቃ የኖረች ሀገራችን እስከ ዓፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ድረስ የሕዝቧን ባህል ሃይማኖት አጥንተነዋልን? ከእምነቱ የተነሳ ከወሩ አብዛኛው ልደታ፣ ሥላሴ፣ ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ማርያም፣ ወዘተ እያለ ከየአድባራቱ እራሱን አቆራኝቶ የኖረውን ህዝብ አጥንተነው ነበርን? የእስላሙ ወገናችን እምነትና ባህል፣ እምነት የሌላቸውንስ ዜጎች ባህል ታሪክ ዳስሰን ለሀገራችን ኢትዮጵያ የሚስማማውን ሥርዓት፣ አስተዳደር ለማየት ተሞክሯልን? የኢትዮጵያ ጥንታዊ ቅርሶች ሦስት ሺህ ዘመን ያስቆጠረው አክሱም ሐውልት፣ የላሊበላ አድባራት፣ የፋሲለደስ ቤተመንግሥት፣ አሥርቱ ትዕዛዛትን የያዘው የቃል ኪዳን ታቦት አለበት የሚባለው ጽዮን ማርያም፣ በባሌ ስለሚገኘው ሶፎመር ዋሻ፣ ስለ ሐረር ግምብና መስኪዶች ታሪካዊነትና ምስጢራዊነት ግንዛቤ ቀስመናልን? እነኚህ በቀደምት ነገሥታትና ምህመናን ተጠብቀው ለትውልድ የተላለፉ በርካታ ቅርሶች ስለ ሀገራችን ምን ያመለክታሉ? እውን ኢትዮጵያን አውቀናታልን? ያለፈ ታሪክን በሚገባ አለመመርመርና የታሪክ ክፍተት ለስህተት በር ከፋቾች መሆናቸውን ማጤን አስፈላጊ ነው። የካቲት 66ን ስንዳሥስ የትግሉን አነሳስና አወዳደቅ ለቀጣይ ትውልድና ተመራማሪዎች ሳይጋነንና ሳይዛባ ማስቀመጥ እኛ የሰራነውን ስህተት ሌላው እንዳይደግመው ጠቃሚነቱ የጐላ ነውና ነው።

## 14.0 የኅብረት ግምባርና ትግል

ኅብረት የሚለው ቃል ማበርንና ማስተባበርን የሚገልጽ ነው። የኅብረት ተቋም በመንግስታት መካከል (United Nations, North Atlantic Treaty Organization (NATO), WARSAW) ወይም በሀገር ደረጃ በተደራጁ ወታደራዊ ክፍሎች፣ የሽምቅ ውጊያን በሚያካሂዱ የታጠቁ ኃይሎች፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ብዙሃን ድርጅቶች መካከል ወይም በይዘትም ሆነ በዓይነት እንዲሁም በመጠን ከእነዚህ ዝቅና ለየት ባሉ ክፍሎች መካከል ሊመሠረት ይችላል።

ዓለምን በቁጥጥር ሥር ለማድረግ ተነስተው የነበሩ ትዕቢተኞችን (የጀርመን ናዚና ፋሽስት ኢጣልያን) ለመደምሰስ መንግሥታት ያደረጉት ኅብረት፣ ወራሪ ኃይልን ከሀገር ለማሶጣት የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚያደርጉት መተባበር፣ በአንድ ሀገር ውስጥ አምባገነን አገዛዝን ለማስወገድ በተለያዩ ድርጅቶችና የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል የሚደረግ ትብብር፣ የፓርላማ መቀመጫን አስተባብሮ የኅብረት መንግሥት ለመመሥረት የሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉ የኅብረት ትግል፣ የኅብረት እንቅስቃሴ፣ የኅብረት ተቋም የተለያዩ መልኮች ናቸው።

በፖለቲካው እንቅስቃሴ በተለያዩ መጠሪያዎች የሚቋቋም የኅብረት ተቋም ለተወሰነ ዓላማ የተለያዩ ክፍሎች የተወሰነ ኃይልን ወይም ተግባራዊ እንቅስቃሴን ለማስተባበር የሚመሠርቱት ተቋም ነው። የኅብረት ተቋሙን የሚመሠርቱት ኃይሎችም ሆኑ የሚያስተባብራቸው ተግባራት እንዲሁም ግብ አድርገው የተነሱባቸው ዓላማዎች የተለያዩ ሊሆን ይችላሉ።

በሀገራችን ኢትዮጵያ ከፖለቲካው አኳያ ስንመለከት በአንድ በኩል አምባገነን ገዥዎችን ለመጣል በሌላ በኩል አገዛዞች እራሳቸውን ለማጠናከር ኅብረት ይፈጥራሉ።

# 14.1 አምባገነን ገዥዎች ሥልጣናቸውን ለማጠናከር የሚፈጥሩት ኅብረት

### 14.1.1 የደርግ አገዛዝ

የየካቲት 1966 ሕዝባዊ አብዮት አቅጣጫ ሰጪ ድርጅት ባለመኖሩና የመለዮ ለባሹን ሕዝባዊ ወገንተኛነት ተገን በማድረግ ባለ መለስተኛ መኮንን ወታደሮች ከየጦሩ ክፍል በመሰባሰብ የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስ ሰራዊትና አስተባባሪ ደርግን ሰኔ 21 ቀን 1967 ዓ.ም. መሠረቱ። ደርግ በቀጣይነት የንጉሡን መንግሥታዊ መዋቅሮች እየዋጠ ተጉዞ መስከረም ሁለት ቀን 1967 ዓ.ም. በትረ ሥልጣኑን ሊጨብጥ በቅቷል።

ደርግ እራሱን ቀያይሮ እስከመጨረሻው ለመግዛት በነበረው ፍላጎት እራሱን ከወታደራዊ አገዛዝ ወደ "ሲቪል" አገዛዝ ሲቀይር የተጠቀመበት ዘዴ ኅብረት ነበር። ደርግ ሕዝባዊ መፈክሮችን በማስተጋባትና የሶሻሊስት ሥርዓትን ጭምብል በማጥለቅ ሚስተካከለው አልነበረምና የኢትዮጵያን ሪፓብሊክ ለመመስረት በሚል የተጠቀመበት ዘዴ መለዮውን አውልቆ ሲቭል ነኝ በማለት የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲን (ኢሠፓ) መመስረት ነበር። ለዚህም ምሥረታ ቅድመ ዝግጅት ይረዳ ዘንድ አምስት የፖለቲካ ድርጅቶችን አካቶ ማለትም የመንግሥቱ ኃይለ ማርያም አብዮታዊ ሰደድ፣ በሰናይ ልኬ የሚመራው ወዛደር ሊግ፣ በኃይሌ ፊዳ የሚመራው መኢሶን፣ በተስፋዬ ቸርንት የሚመራው ኢማሌድህና በአሰፋ ጫቦ የሚመራው ኢጭአት በጋራ ሁነው ኢትዮጵያ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሪቮሉሽነሪ ድርጅቶች ኅብረት (ኢማሌሪድኅ)ን መሠረቱ።

ከኢማሌሪድኅ ምሥረታ በሂደት የመንግሥቱ ኃይለማርያም አብዮታዊ ሰደደ አራቱንም ድርጅቶች በማጣጣም የሠራተኞቹ ፓርቲ በኅብረት ሳይሆን በውህደት እንደሚመሠርት በማጨናበር የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን (ኢሠፓአኮ) በመመሥረት ከወታደር አገዛዝ ወደ ሲቪል አገዛዝ ጎዘው ተጀመረ። ኢሠፓን የደርግ አባላቱ መለዮአቸውን ጥለው በኮትና ሱሪ ተቀበሉት። ይህ ሂደት የሚያሳየን አምባገነን አገዛዞች እራሳቸው የሥልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም ኅብረትን እንዴት እንደሚጠቀሙበት ነው።

### 14.1.2 ህወሀት

ህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ ዓላማውና ምሥረታው የብሔር ትግልን መሠረት አድርጐ የትግራይን ሕዝብ ከደርግ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት ነበር። ስሙም እንደሚጠቁመው ለትግራይ ሕዝብ የቆመ ድርጅት ነው። ሻቢያ ኤርትራን ቅኝ ከያዘቻት ኢትዮጵያ ነፃ ለማውጣት ህወሀት ትግራይ ሪፓብሊክን ለመመሥረት ተጠንስሰው የጋራ ጠላት ባሉት ደርግና ሌሎች ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ላይ በጋራ ዘምተዋል።

ህወሀት ትግራይን ከደርግ አገዛዝ በጦርነት ካስለቀቀ በኋላ የደርግን በኢትዮጵያ ሕዝብ መጠላትና የሌሎች ሕዝባዊ ድርጅቶችን መዳከም ምክንያት በማድረግ እንቅስቃሴውን ወደ ሌሎች የሀገሪቷ ክፍለሀገራት አዛመተ። ህወሀት ይህንን እርምጃ ከመውሰዱ በፊት እንቅስቃሴውን በትግራይ ነፃ አውጪ ስም ሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶች ውስጥ ለመንቀሳቀስ የሚከናነበው ጭምብል ያስፈልገዋልና ጠፍጥፎ ከሠራቸው አምስት የተለያዩ ብሔረሰብ ድርጅቶች ኢሕአዴግን መሠረተ። አሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚል ስያሜ ይዟልና በዚህ መልኩ ሀገሪቷን እስከዛሬ ተቆጣጥሮ ይገኛል። ይህም ደርግ ከወታደርነት የሲቪል ጭምብል እንዳጠለቀ ሁሉ ወያኔም ህወሀት የኢትዮጵያን ጭምብል አጥልቆ ሀገር እያመሰ ይገኛል። ለሁለቱም አምባገነን ገዥዎች በኅብረት ስም የሚደረግ "ሕዝባዊነት" ተጠቅመውበታል።

# 14.2. አምባገነን ገዥዎችን ለመጣል የተደረጉ ኅብረቶች

በዘመነ ደርግ ሻቢያና ህወሀት በኅብረት ግምባር ሳይፈጥሩ በሽምቅ ውጊያ በመተጋገዝ የደርግን አገዛዝ ለመጣል ተባብረዋል፣ ተጋግዘዋል። እነኚህ ሁለት ሽምቅ ተዋጊ ኃይሎች የደርግን አገዛዝ በመጣል ላይ በጋራ ተስማምተው ተዋግተዋል።

በዘመነ ህወሀት/ኢሕአዴግ የተለያዩ ፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ ኅብረት በመፍጠር ያለውን የወያኔ አገዛዝ ታግለዋል እየታገሉም ይገኛሉ። ከነዚህም ተፈጥረው/ተመስርተው ከከሰሙትና አሁንም በኅብረት የሚንቀሳቀሱትን ለመጥቀስ ያህል፦

### 14.2.1 ኢዴኃቅ (የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት)

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ) ፦ የተመሠረተው ሚያዝያ 1983 ዓ.ም. የሕወሀት/ኢሕአዴግ ቡድን በአዲስ አበባ ሥልጣን ሊይዝ አንድ ወር ሲቀረው ነበር። የኢትዮጵያን ህልውና ለመጠበቅና ዘረኛ የሆነ አምባገነን አገዛዝን ለመከላከል የተወሰኑ አምስት ድርጅቶች፤ ልዩነታቸውንና የየግላቸውን አቋምና ጥቅም ወደ ጎን አድርገው፤ የሀገር አድን መርሆ በማንገብ ኢዴኃቅን ለመመስረት ችለዋል። ኢዴኃቅ በርከት ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችን፤ ስብስቦችን (ፎረሞችን) ግለሰቦችን፤ አሰባስቦ ለማታገል ያደረገው ጥረት፤ የኅብረቱን መሠረት ለማስፋትና እንቅስቃሴውን ለማጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽዎ ነበረው። ኢዴኃቅ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለማስገንጠል ለተሰበሰበው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ በብዙ ገጾች በተጠናከረ ታሪካዊ ማስረጃ የተደገፈ ሰነድ በመስጠት ተቃውሞውን አሰመዝግቧል። የፓሪስን ስብሰባና የአዲስ አበባውን የግዮን የእርቅና የሰላም ስብሰባ በማዘጋጀት ላይ በሀገራችን ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመሥረት፤ ለሰላምና ለእርቅ የሚገባውን ሚና ተጫውቷል። ኢዴኃቅ በተቋቋመ ማግስት ሁለት መስራች ድርጅቶች አፈንግጠው በመውጣት ወደ ወያኔ ጎራ መሄዳቸው ኢዴኃቅን በመጠኑም ቢሆን የጎዳ ክስተት ነበር። ከመስራች የኢዴኃቅ አባል ድርጅቶች ውስጥ ዋናዎቹ መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) እና የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) እንደነበሩ ይታወቃል።

### 14.2.2 ፓሪስ አንድ ጉባዔ

የፓሪስ አንድ ጉባዔ፦ በመጋቢት 1985 ዓ.ም. እ.አ.አ. ከማርች 11 – 13 1993 ዓ.ም. ባሉት ቀናት ሰባት ሕብረ ብሔራዊ የፖለቲካ ድርጅቶችና የብሔር እንቅስቃሴዎች በፓሪስ ከተማ ተሰብስበው አንድ ጉባዔ አድርገዋል። ይህ ጉባዔ በሀገር ውስጥ በገዥው ፓርቲ ሕጋዊነት ተሰጥቷቸው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችና በገዥው ፓርቲ ሕጋዊነት የተነፈጋቸው ድርጅቶች በአንድ ላይ የመከሩበት ጉባዔ ነበር። የዚህ ገባዔ ዐብይ ዓላማ የሀገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታ ገምግሞ ለዋና ዋና ችግሮች መፍትሄ የሚገኝበትን ዘዴ ለመሻትና አንድ ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶችና የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚያካትት ሁሉን አቀፍ ጉባዔ የሚጠራበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነበር። ስብሰባውን የተካፈሉት ድርጅቶች ሰፊና ጥልቅ ውይይት ካካሄዱ በኋላ ሁሉንም የሚያካትትና ሀገር አቀፍ የኢትዮጵያ የሰላምና የዕርቅ ጉባዔ ተብሎ የሚጠራ አዲስ አበባ ላይ እንዲጠራ ተስማሙ። ስምምነቱ ወደ ተግባር ሊለውጥ የሚችል አንድ የሰላምና የዕርቅ ኮንፈረንስ አስተባባሪ ኮሚቴ አቋቁመው ተለያዩ። ኮሚቴው በተቋቋመ በስምንት ወራት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ የተካሄደውን የሰላምና የዕርቅ ጉባዔ አዘጋጅቷል።

### 14.2.3 የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት

በታህሳሥ 1986 ዓ.ም. አዲስ አበባ ላይ የታቀደው የሰላምና የዕርቅ ጉባዔ ተካሂዷል። በጉባዔው ላይ በሀገር ቤትና ከሀገር ውጭ ያሉ፤ የታገዱና ያልታገዱ፤ ሁለ-ገብ ትግል የሚያካሂዱና በሰላም ብቻ የሚታገሉ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ የሙያ ማህበራት፤ የሲቪክ ማኅበረሰብ ተወካዮችና ታዋቂ ግለሰቦችም እንዲሁም የገዥው ፓርቲ ተወካዮች እንዲሳተፉ ጥሪ ተላልፏል። ምንም እንኳን ሕወሀት/ኢሕአዴግ በዚህ ጉባዔ ላለመገኘት ቢወስንምና ለዚሁ ስብሰባ ከውጭ የመጡትን የድርጅቶች ተወካዮችን አስሮ (አቶ አበራ የማነ አብ ከመኢሶን፣ ወ/ሮ ገነት ግርማና አቶ መስፍን ተፈራ ከኢሕአፓ) ወዲያውኑ ወደ ወህኒ በመወርወርና የተለያዩ ተጽእኖዎች በማድረግ ስብሰባውንም ለማጨናገፍ ቢሞክርም፤ ጉባዔው እንደታቀደው ሊካሄድ ችሏል። ጉባዔው ሰፋ ያለ ቁጥር ያላቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች ያቀፈ የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤትን መስርቷል።

### 14.2.4 ፓሪስ ሁለት ኢተፖድኅ

በኤፕሪል 2000 እ.አ.አ. ላይ የተገናኘው የስምንት የፖለቲካ ድርጅቶች ስብስብ ኢተፖድኅ የተሰኘውን አካል ለመፍጠር ችሏል። ይህ ስብሰባ የተጠራው ወያኔና ሻቢያ ሲያካሂዱት የነበረው ጦርነት በተጋጋለበት አካባቢና በሀገሪቱ ውስጥ የፖለቲካ

መረጋጋት፤ በሕዝቡም ውስጥም የዓላማና የትብብር አንድነት እንዲኖር በተጠየቀበት ወቅት ነበር። ተሰብሳቢዎቹ ለሀገሪቷ ችግር የፖለቲካ መፍትሄ ይረዳ ዘንድ የብሔራዊ ዕርቅ ጥሪ አቅርበዋል

### 14.2.5 የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የተመሠረተው በጁላይ 26 እስከ ኦገስት 1, 2003 እ.አ.አ. አሜሪካ ውስጥ በተካሄደ የፖለቲካ ድርጅቶች ጉባዔ ነው። ይህን ጉባዔ ለማዘጋጀት ሀሳቡ የመነጨው በኤፕሪል 2000 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሀገራዊ ጉባዔ የሚባለው የሲቪክ ድርጅት በተጠራና ሰባት የፖለቲካ ድርጅቶች በተገኙበት ሀሳብ የመለዋወጫ መድረክ ላይ ነበር። በተገኙት የፖለቲካ ድርጅቶች ስምምነት ተደርጎ አዘጋጅ ኮሚቴ ከተመሠረተ በኋላ የጉባዔው ዝግጅት ከሁለት ዓመት በላይ ወስዷል። በመጀመሪያ ስድስት አባላት የነበሩት በኋላም ወደ ዘጠኝ ከፍ ያለውና ከነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶች የተውጣጣ አዘጋጅ ኮሚቴ ተመስርቶ ለሁለት ዓመታት ያህል ድርጅቶችን በማነጋገር ሲያግባባና እንዲሁም ለጉባዔው ዝግጅት የቴክኒክና የፋይናንስ ዝግጅት ሲያደርግ ከቆየ በኋላ የፖለቲካ ድርጅቶች ጉባዔ ለመጥራት ተችሏል። በዚህ ጉባዔ ላይ የተሳተፉት የ15 የፖለቲካ ድርጅቶች ተወካዮች ለአንድ ሳምንት ያህል በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይተው ስምምነት ላይ ደርሰዋል። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) እየተባለ የሚጠራውን የኅብረት አካል መስርተዋል

### 14.2.6 ቅንጅት

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) እንደተመሠረተ ሁለት ድርጅቶች ማለትም በአቶ ልደቱ አያሌው የሚመራው ኢዴፓና በኢንጅነር ኃይሉ ሻውል የሚመራው መኢሕድ ኅብረቱን ጥለው በመውጣትና ከዶር ብርሃኑ ነጋ ቀስተ ደመና እና ከፐሮፌሰር መስፍን ወልደየስ ሊግ ጋር በመጣመር ቅንጅትን በሀገር ቤት ለሚደረገው የምርጫ እንቅስቃሴ ሊመሠርቱ ችለዋል። ቅንጅት በ1997 የምርጫ ሂደት ላይ ከፍተኛ ሚና የተጫወተና ምርጫውንም በአዲስ አበባ ሙሉ በሙሉ እንዲሁም በሌሎች ክልሎች በአብዛኛው በማሸነፍ የመንግሥት ወንበር ለመያዝ የነበረው ዕድል በራሱ ውስጣዊ ችግርና በወያኔ ጭፍጨፋ ታሪክ ሊሆን በቅቷል።

### 14.2.7 ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ (AFD)

AFD ከምርጫ 1997 ውድቀት በኋላ (The **Alliance for Freedom and Democracy** (**AFD**) ) ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ በሚል 22 ሜይ 2006 በኔዘርላንድ ዴንሀግ ላይ የተመሠረተ ትብብር ነው። መሥራች ድርጅቶቹም Oromo Liberation Front (OLF), የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) the Ogaden National Liberation Front (ONLF), የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር (ኦብነግ) the Sidama National Liberation Front (SNLF), የሲዳማ ብሔራዊ ነፃነት ግንባር (ሲብነግ) the Coalition for Unity and Democracy (CUD), ትብብር ለአንድነትና ለዴሞክራቴ (ትአዴ) and the Ethiopian Peoples' Patriotic Front (EPPF, also known as *Arbegnoch Gimbar* or Patriot's Front) የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግምባር (ኢሕአግ) ናቸው።

በወቅቱ ትብብሩን ከበስተጀርባ ያቀነባበረውና ያዘጋጀው የ ኤርትራው ሻቢያ በመሆኑ ተቃውሞ በማሰማት የትብብር ሠነዱን ሳይፈርምና ስብሰባውን ሳይጨርስ አቋርጦ የወጣው በወቅቱ የነበረው ኅብረት (UEDF) እንደነበር ይታወቃል።

AFD እንደተቋቋመ በተለይ በውጭው ሀገር በሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች መሃል ከፍተኛ አለመግባብትንና ብዥታን ለጥቂት ዓመታት አስከትሎ ነበር። የውዝግቡም መነሻ በአብዛኛው የተሰባሰቡት ከኢትዮጵያ የመገንጠል ዓላማ የሚያራምዱ ነፃ አውጭ ድርጅቶች ከመሆናቸው በተጨማሪ በሻቢያ አስተባባሪነት የተደረገ በመሆኑ የኅብረቱ ስብስብም ሆነ የሌሎች ፖለቲካ ድርጅቶች ተቃውሞ ዳግም የኢትዮጵያ አንድነት ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ ነበር።

#### 14.2.8 የህዝቦች ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ (PAFD)

PAFD ፦ በቅርቡ በዚሁ መልክ የተሰባሰቡ ነፃ አውጭ ድርጅቶች የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ (PAFD) በሚል ስያሜ ከመጋቢት 21 እስከ 25 ቀን 2016 ዓ.ም. በኤርትራ (አሥመራ) ጉባኤ ማካሄዳቸውን March 25, 2016 በአወጡት

ጋዜጣዊ መግለጫ አሳውቀዋል። ይህ ስብስብ የኢትዮጵያ ህዝቦችን ነጻ ለማውጣት እየተካሄደ ያለውን የነጻነትና የዴሞክራሲ ትግል በጋራ ለማፋፋም ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም. በኦስሎ ከተማ ከአምስት የፖለቲካ ድርጅቶች የተቋቋመ ሲሆን እነሱም፡-

የቤኒሻንጉል ህዝቦች ነፃነት ንቅናቄ (ቤህነን)፣ የጋምቤላ ህዝቦች ነፃነት ንቅናቄ (ጋህነን)፣ የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባር (ኦብነግ)፣ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) እና የሲዳማ ብሔራዊ ነጻነት ግንባር (ሲብነግ) ተወካዮች፣ በድርጅቶቹ የሴቶችና ወጣቶች ተወካዮች የተመሠረተ ነው።መቋቋማቸውን አስታውቀዋል።

ወደ ዝርዝሩ ይበልጥ ባይገባም ከላይ ከተጠቀሱት የኅብረት ትግሎች መክሸፍ በኋላ ኅልተው ባይታዩም በአሁኑ ወቅት ሸንጎ በመባል የሚጠራ የተለያዩ ፖለቲካ ድርጅቶች ስብስብ ሲኖር በሌላ በኩል ደግሞ የግንቦት ሰባትና በአርበኞች ግንባር ጣምራ ኅብረት ይገኛል።

### 15.0. ኅብረት፣ ቅንጅት እና 1997 እንቅስቃሴ መኮላሸት

## 15.0.1. የምርጫ ፖለቲካና የኅብረት ትግል

ሀገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ያለችበትን የፖለቲካ፡ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ቀውሶች መመልከት ለአንድ የፖለቲካ ድርጅት ቀጣይ ዕቅዱ አስፈላጊና ወሳኝ ነው።

ዛሬ ኢትዮጵያ በአንድ ፈላጭ ቆራጭ አምባገነን አገዛዝ መዳፍ ሥር ትገኛለች። የ17 ዓመቱ ፋሽስታዊ ዕመቃ በሌላ አምባገነን ተተክቶ ይኸው በትንሹ ለ42 ዓመታት ሕዝባችን በፈላጭ ቆራጭ፡ ጐጠኛ ቡድን መዳፍ ሥር እየማቀቁ ይገኛሉ። ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዕይታ አኳያ፤ እየተራበ፣ እየተጠማ፣ እየተሰደደ ከአለው ዜጋ አኳያ፣ ሰብዓዊ መብቱንና ኢትዮጵያዊ ነፃነቱን ከተነፈገው ሕዝብ አንፃር፣ በሀገሩ እንደ ባይተዋር፣ እንደ ሁለተኛ ዜጋ እየተገፋ ከአለው ኅብረተሰብ አንፃር፣ የደርግም ሆነ የወያኔ አገዛዝ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸው። በሕዝቧ አንድነትና እኩልነት ላይ ለተመሠረተች ኢትዮጵያ ግንባታ፣ ለዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር፣ ለሕዝብ መንግሥት ምስረታ ከዛሬ 42 ዓመት በፊት የተነሳው ጥያቄ ዛሬም ምላሽ አላገኘምና የኢትዮጵያ ሕዝብ ለረዥም ዓመታት ከፈላጭ ቆራጭ አምባገነን አገዛዞች ጋር እየተፋለመ ይገኛል። እፎይ ብሎ ያረፈበትና ተመስገን ብሎ የኖረበት ጊዜ ተዘንግቶታል። ወያኔ በ25 ዓመት አገዛዙ አምባገነናዊ መዋቅሮቹን እያጠናከረ: የስለላ መረቦቹን፣ የአፈና አውታሮቹን በሰፊው እየዘረጋና እየገነባ በአንፃሩ ሕዝባችን ለከፍተኛ የኑሮ ውድነትና እረሃብ አደጋ የተጋለጠበት ሁኔታ ላይ ደርሰናል። ኢትዮጵያዊ ስሜት ከቶም የሌለው፣ የሕዝብ ብሶትና ሰቆቃ ለአፍታም ሽው የማይልበት ዘረኛ አገዛዝ ሀገራችንንና ሕዝባችንን ቀፍድዶ ይዟል።

ወያኔ በአገዛዝ ዘመኑ ጠንካራ ተቀናቃኝ እንዳይኖርበት ያመቸኛል ያለውን ዘዴ ሁሉ እየተጠቀመ ተጉዟል። ለውጭው ዓለም ዴሞክራሲያዊ ገጽታውን ለማሳየት፣ ለጋሽ ሀገሮች ፊታቸውን እንዳያዞሩበት፣ የውጭ ረድኤት ድርጅቶች የጀመሩት “የልማት” ሥራቸው እንዳይቋረጥበት፣ የዴሞክራሲ ጭምብሉ ተጋሪዎችን በይስሙላ ፓርላማው በማሰባሰብ ለአለፉት 25 ዓመታት የፖለቲካ ቲያትር ተጫውቷል። አሁንም እየተጫወተ ይገኛል። ጠንከር ብለው የታዩ ታማኝ ተቃዋሚዎችን በተካነው የመከፋፈልና የሰርጎ ገብነት ሤራው ያዳከማቸዋል። ለዚህ ደግሞ እራሳቸው የፖለቲካ ድርጅቶቹ ልምድና ተመክሮ አለመኖር፣ ድርጅታቸውንና ውስጣዊ አሠራራቸውን ማዝረክረክ ይበልጡን አመችቶታል። በግለሰብ ደረጃ በገንዘብ፣ በጥቅም ይደልላል፡፡ እምቢ ያለውን ያስራል፣ ያዋክባል፣ ከሀገር እንዲሰደዱ ያደርጋል፤ ሲያሻውም ይገድላል።

በፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ላይ ከማዋከብ እስከ ግድያ የደረሰው ትርዕይት፣ የመምህራን ማህበር መሪ የነበሩትን ዶር. ታዬ ወልደ ሰማያትን የማዋከብና በእስር የማንገላታት ጉዳይ ብሎም በስደቱ ዓለም ይካተቱለት ዘንድ የተወጠነው ውጥን፣ የአበራ የማነ አብ የሰላም ተልዕኮ በእስር እንዲረሳ ተደርጐ ለረዥም ዓመታት መከርቸም ሁኔታ፣ የአሰፋ ማሩና የሌሎች በረቀቀ ዘዴ የመገደልና የመሠወር ሂደት፣ ወይዘሪት ብርቱካን ሜዴቅሳ ላይ የደረሰው የግፍ እስርና ከዚያም ሀገር ለቃ እንድትወጣ የተወጠነው ትያትር፣ አሁንም ቢሆን አገዛዙ ይዞት ከተነሳው የአጥፊነት ባህሪው ፈቀቅ እንዳላለና እንደማይል የሚያሳዩ የራሱ የምስክርነት ተግባራት ናቸው። የርዕዮት ዓለሙ እስርና እንደሌሎቹ አሁን የስደት ሕይወት ውስጥ መግባት፣ የእስክንድር ነጋ፣ አንዱዓለም አራጌ፣ ተመስገን ደሳለኝ፣ የዞን ዘጠኝ አባላት እስር፣ እጅግ የረቀቀና ምስጢሩ ያልተገለጸው የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ወደ ሀገር ታፍኖ መወሰድ ወዘተ አገዛዙ ምንጊዜም የለየለት ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ባህሪ የተላበሰ መሆኑን ያሳያሉ።

ተቃዋሚና የምርጫ ፖለቲካ ወያኔ ለዴሞክራሲያዊ ጭምብሉ እስከጠቀመው እንጂ ገፍቶ ከመጣበት አውልቆ እንደሚጥለው በትንሹ የ196 ንፁሃንን ደም ጠጥቶ ያቆየው ሥልጣኑ ወደ ግንቦት 97 የባህሪው ምስክርነት ይወስደናል። በአገዛዝ ዘመኑ ተቀናቃኝ/ተቃዋሚ መኖሩን ወያኔ ለዴሞክራሲው ሲፈልገው ገደቡ ከሥልጣን ጥያቄ ባሻገር መሆኑ ግንቦት 97 መስክሮልናል። ወያኔ ከሰላማዊ የምርጫ ድራማ ባሻገር የፖለቲካ ስልጣን ጥያቄ ለሚያቀርብ ያለው ክፍት ቦታ ስደት፣ እስርና መቃብር መሆኑን ላላመንን ግንቦት 97ን ማስታወስ ከበቂ በላይ ነው።

- በግንቦት 97 ምርጫ፡ አብዛኛውን ተቋሞች ወያኔ በቁጥጥሩ ሥር አድርጓል። ሚዲያው (የሬዲዮና ቴሌቪዥን ስርጭቱ) በአብዛኛው ለአገዛዙ ሲውሉ፣ እጅግ በጣም መጠነኛ የአየር ሰዓት ነበር ተቃዋሚው የተጋራው።
- በጊዜው የነበሩ የነፃ ጋዜጦችና መጽሔቶች ሚና፣ አገዛዙን በማጋለጥና የየዕለት እንቅስቃሴዎችን በመዘገብ የተጫወቱት ሚና ቀላል አልነበረም። ወያኔ በወቅቱ ከቁጥጥሩ ውጭ የሆነበት የነፃ ጋዜጦችና መጽሔቶች ሥርጭት ነበር።
- ምርጫ ቦርዱ፣ አወቃቀሩ፣ አሰራሩ፣ ታዛዥነቱ፣ ሁለመናው በወያኔ ቁጥጥር ሥር ነበር።
- ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የተለያዩ ሲቪክ ማኅበራት ተወካዮች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ነፃ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የተካተቱበት፣ ነፃ የምርጫ ታዛቢ አካል አልነበረም። ቢጠየቅም ጥያቄውን ውድቅ አድርጐታል።
- በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚያመቸው መንገድ የሚገቡ ታዛቢዎችን ቢያመቻችም፡ ከአቅሙ በላይ ሆነው ያመለጡት፡ በተለይ የምርጫውን ኢ-ዴሞክራሲያዊነት ለውጭው ዓለም ያጋለጡት ሃና ጐሜዝ የሚዘነጉ አይደሉም።
- በየአካባቢው፣ በየክልሉ፣ በሁሉም የሀገሪቷ ክፍሎች ወያኔ ሙሉ በሙሉ መደበኛ ወታደሮቹን ከመጠቀም ጀምሮ፣ በስውር የተሰማሩት የፀጥታ ኃይሎቹ ጭምር፣ ከምርጫው ዋዜማ ጀምሮ የተቃዋሚ ኃይሎቹን ዕጩ ተመራጮችና አባላትን ማዋከቡን፣ ማሰሩን፣ መሰወሩን እያከናወኑ እንደነበር የሚዘነጋ ጉዳይ አይደለም።
- በገንዘብ ኃይሉ ከተቃዋሚው አንፃር እጅጉን የተጠናከረ አገዛዝ ነበርና በምርጫው ያለ የሌለ ኃይሉን አውሎ ምርጫው ወደ ወያኔ እንዲያደላ በገንዘብ መደለል ቅስቀሳውን በሰፊው ለማካሄድ ይደረግ የነበረው ዘመቻ ተቃዋሚ ኃይሎች ከነበራቸው የገንዘብ አቅም አኳያ ሲነፃጸር የትዬ ለኔ ነበር።

እነኚህንና በርካታ ሌሎች መሠረታዊ ጉዳዮች፡ ወደ ወያኔ ምርጫ ትርይት ከመገባቱ በፊት ምላሽ ማግኘት የሚገባቸው ጉዳዮች ሁሉ፡ በአገዛዙ እምቢተኝነትና ዕብሪት ለአገዛዙ አድልተው ነው ምርጫ 97 ተካሂዶ ወያኔ ለሽንፈት የበቃው። ወያኔ ሁሉንም ይዟል ግና የኢትዮጵያን ሕዝብ አልያዘምና:: ምን ቢታጠቁ፣ ምን ቢቆጣጠሩ የሕዝብ ኃይል አሸናፊነቱን ያስመሰከረበት ትዝታ ግንቦት 97።

ተቃዋሚው ኃይሎች በወያኔ የግንቦት 97ቱ የምርጫ ድራማ ሲሰማሩ የመጀመሪያው ሂደት ምርጫውን በተናጠል በመሳተፍ ተቃዋሚዎች የተበታተነ ድምጽ ከማግኘት ይልቅ በአንድ ጥላ ሥር፣ በጋራ ኅብረት ምርጫውን መሳተፍ በሚል የጋራ መድረክ መመስረት አብላጫው ትኩረት ተሰጥቶት ነበር። በመሆኑም በሀገር ቤት ያሉ፣ በሀገር ቤት የሌሉ፣ ሕጋዊ፣ ሕገወጥ፣ ሳይባል የትግል ስልት እንደ መመዘኛ ሳይወሰድ፤ ኅብረ-ብሔር የሆኑ ድርጅቶች፣ በብሔር/ብሔረሰብ የተደራጁ ሳይለይ፤ በፖለቲካ አቋማቸው በኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት የሚያምኑ ኃይሎች በሙሉ በጋራ በመምከር በ1995 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረትን (ኢዴኃኅ)ን መሠረቱ።

ኅብረቱ ዋናው ዓላማው አድርጎ የተነሳው ምርጫውን በአብላጫ ድምጽ በማሸነፍ ለመንግሥት ምሥረታ የሚያበቃውን ቁጥር ከአገኘ በስምምነቱ መሠረት ቀጣዩ የሀገሪቷ መንግሥት የጋራ የሽግግር መንግሥት እንዲሆንና፡ በእኩልነትና በአንድነት ላይ ለምትመሠረተዋ ኢትዮጵያ አስተማማኝ ዋስትና ለመጣል ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ነበር። በዚህ ዋና የኅብረቱ ዓላማ ላይ በመስማማት ኅብረቱ ተመሥርቶ የራሱን አመራር በመሰየም ነበር እንቅስቃሴውን የጀመረው። በሀገር ቤት የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፡ የሀገር ቤቱን እንቅስቃሴ ለማጠናከር ሥራቸውን ጀመሩ። በውጭ ያሉትም የኅብረቱ አካሎች፡ በተለይ ከአላቸው ተመክሮ አንፃር በምክር፡ በውጭ ያለውን ኅብረተሰብ በቁሳቁስ፣ በገንዘብና በሌላም ድጋፉን ይሰጥ ዘንድ ቅድመ ዝግጅት ማድረጉን ተያያዙት።

ሆኖም ግን ኅብረቱ ብዙም ሳይጓዝ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ)ው አቶ ልደቱና የመላ አማራ ሕዝብ አንድነት ድርጅት (መኢሕአድ) ኢንጂነር ኃይሉ ሻወል ከኅብረቱ እራሳቸውን አገለሉ። ይህ በተጀመረው የጋራ ትግል ሂደት ላይ ከባዱን አደጋ አስከተለ። ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በጋራ ተስማምተው የተዘጋጁበት የምርጫ እንቅስቃሴ ከጅምሩ በራሱ

በኅብረቱ አባላት እንከን ገጠመው። በብሔር/ብሔረሰብ የተደራጁ ድርጅቶችን የማይቀበል፣ ከሀገር ውጭ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ላይ አግላይ ሚና የተጫወተው በዋናነት ኢዴፓንና መኢሕአድን ይዞ የፕሮፌሰር መስፍንን ሊግና የዶር ብርሃኑ ቀስተ ደመናን አካቶ በአራት የፖለቲካ ድርጅቶች አማካኝነት ቅንጅት ተመሠረተ።

ቅንጅትን የመሠረቱት ኃይሎችና ግለሰቦች ቅንጅትን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ወደ ምርጫው መግባትን አበሰሩ። በኅብረቱ በኩል በግንቦት 97 ምርጫ ለመሳተፍ ከመወሰኑ በፊት አገዛዙ ማሟላት አለበት ያሉትን ነጥቦች በማስቀመጥ ከአገዛዙ ጋር ድርድር ተቀመጡ። ወያኔ የቀረበለትን ቅድመ ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን ለማሟላት በማቅማማት ላይ በነበረበት ወቅት የቅንጅት ቅድመ ሁኔታዎችን መሠረዝ እጅጉን የሚፈልገው ጉዳይ ነበርና ወዲያውኑ ከኅብረቱ ጋር ያደርግ የነበረውን ድርድር አቋረጠ።

ከዚህ ሁኔታ መገንዘብና መረዳት ያለብን ጉዳይ በሁሉም ድጋፍ እጅግ በጥሩ ጅምር፤ ያለ አንዳች አግላይነት ሁሉንም ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች አካቶ የተመሠረተው ኅብረት ለምን ከጅምሩ አፈንጋጮች ገጠሙት? የግንቦት 97 ምርጫ ኅብረቱ መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ላይ በድርድር ላይ እያለ ቅንጅት ለምን የቅድመ ሁኔታዎች መቀመጥን ሠረዘ?

ወያኔ ከምርጫ 97 በፊት በተካሄዱ ምርጫዎችም ሆነ በምርጫ 97 ወደፊትም በሚካሄደው ዋናው ፍላጐቱ በሀገሪቷ ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች እንዳሉ ለሚመለከቱት ባዕዳን ጌቶቹ ለማሳየት የሚያደርገው ጨዋታ እንዲሰምርለት ነው። የቅንጅት ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ በምርጫው ላይ መሳተፍ፣ የሌሎቹን በተለይ በኅብረቱ በኩል ተሰባስበው የነበሩት በውጭ ያሉ ድርጅቶች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ቀጣይ ጭንቀትና ስቃይ አበረደለት። የኅብረትን የምርጫ ቅድመ ሁኔታ ጉዞ እዚህ ላይ አጨናገፈው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በ14 ዓመት የወያኔ አገዛዝ በዕለት ተለት ችግሩ፣ በኤድስ፣ ወባና ሌሎች በሽታ ስቃይ፣ በድንቁርና፣ በስደት፣ በእስር፣ በግርፊያ እየተቀጣ ያለው ራሱ ባለቤቱ ነውና የታመቀ ስሜቱን የሚተነፍስበትን መድረክ ሁሌም ናፋቂ ነበርና ቅንጅት በማካሄድ ላይ የነበረው እንቅስቃሴ ትኩረቱን ስቦታል። "በምርጫ ይቻላል" ሲል የካርዱ ባለቤት ሕዝቡ ራሱ መሆኑን ተገንዝቦ እምነቱንም ሊመርጣቸው ላለው ድርጅቶች ሰጠ። የሁለት ጣት ምልክት (✌) የሁሉም ኢትዮጵያዊ መግባቢያ ቋንቋ ሆነ። በየአካባቢው ያሉትን ወያኔና አጫፋሪዎቹን ለማብሸቅ፣ ተቃውሞን ለማሰማት፣ ድምጽ ማውጣት አስፈላጊ አልሆነም። ሁለት ጣትን ብቻ ማሳየት ከመናገር የበለጠ አብጋኝ ሆነ። ቅንጅት ይበልጡን ተሰሚነትን እያገኘ መጣ።

ኅብረቱም ሲያቅማማ የኖረበትን ወደ ምርጫው የመሳተፍ ያለመሳተፍ ጉዳይ በመጨረሻው ሰዓት ወስኖ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ወደ ምርጫው በመግባት እንቅስቃሴውን ጀመረ። መንግሥት ያዋክባል፣ ያሥራል፣ ይገላል። በሰላማዊ መንገድ ስለ ምርጫው የሚሰብኩ፣ ቅንጅት/ኅብረትን ምረጡ የሚሉ፣ በየአካባቢው መዋከብ ደረሰባቸው። ውስጥ ውስጡን የሚታሰሩ፣ የሚሰወሩ በርካታ ነበሩ።

የምርጫው ቀን ደረሰ። የግንቦት 97 ዋዜማ የወያኔ ሰልፍ በሱናሜ ማዕበል ተሰየመ። "ትላንት ለብራችን፣ ዛሬ ለሀገራችን" ያሉ ወያኔ በገንዘብ ያሰለፋቸው ሁላ በቀጣዩ የቅንጅትና ኅብረት የድጋፍ ሰልፍ ላይ አዲስ አበባን አጨናነቋት። ይህ ሰልፍ ትልቅ የሰጠው ትምህርት ቢኖር ለ14 ዓመት ወያኔ በዘር፣ በክልልና በሃይማኖት የረጨው መርዝ የሠመረለት የመሰለው ወያኔ ኢትዮጵያዊነትን ማጥፋት አይደለም ማቀዝቀዝ ከንቱ መሆኑን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ክልል ሳይለይ ሁሉም እጅ ለእጅ ተያይዞ፣ ትከሻ ለትከሻ ተቃቅፎ በአንድነት ለሀገሩ፣ ለአንዲት ኢትዮጵያ መቆሙን ያሳየበትና ሀገሬን ብሎ የዘመረበት ታሪካዊ ሰልፍ ነበር። የወያኔን ሥርዓት መገርሰስ እንዳለበት የመሰከረበት ታሪካዊ ቀን።

ለ14 ዓመታት በወያኔ አገዛዝ መከራውን ያየው ሕዝብ ከወያኔ አገዛዝ የመላቀቅና ያለመላቀቅ ድምጽ የሰጠበት ቀን። ግንቦት 7, 1997 ዓ.ም.። የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ ድምጽ "ሀገሬን" አለ። "ነፃነቴን" አለ። "መብቴን" አለ። ወያኔ ከመላው የሀገሪቷ አካባቢ አፍኖ ከያዘው የትግራይ ሕዝብ በስተቀር በዝረራ ተሸነፈ። መንግሥት ለመመሥረት የሚያስችለውን አብላጫ ድምጽ ቅንጅትና ኅብረት በጋራ አስቆጠሩ።

“የድምጽ ካርድ አናዘርፍም፣ አንዋሽም፣ የሕዝብ ድምጽ ይከበር!” ያሉ ንፁሃን ቤታቸው ቃልቲ፣ ከርቸሌና ደዴሳ ሆነ። የአገዛዙ አፈና በየአካባቢው ተቀጣጠለ። ወያኔ መሸነፉን ቢያውቅም ሊቀበል ፍላጎት እንደሌለው አወጀ። መለስ ዜናዊ “ኢንተር ሃሞይ” ሲል ለፈፈ። “ሕገ መንግሥቱን ለመናድ የተነሱ” ሲል ደሰኮረ። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አወጀ። የፖሊስ ኃይሉ፣ የመከላከያ ሠራዊት በሙሉ፣ የፀጥታ ኃይሎች በሙሉ በአንድ ግለሰብ ዕዝ ሥር ዋሉ። በአረመኔው መለስ የዕዝ ሰንሰለት ሥር።

ሕዝባዊ አመጽ የመነሳሻው ነባራዊ ሁኔታ እጅጉን እየጐላ መጣ። በየትኛውም አካባቢ በአገዛዙ ላይ እምቢተኝነት ሰፈነ። በየአቅጣጫው የተቀሰቀሰው ተቃውሞ ከአገዛዙ ቁጥጥር ውጪ እየሆነ መጣ። የተገኘውን ድል የማስጠበቅ ሕዝባዊ መነሳሳት።

በአንድ በኩል ወያኔ የጥፋት ዕቅዱን በመቀጠል እንደ ሂደቱ ግስጋሴ የሚወስደውን አረመኔያዊ እርምጃ መግፋት፣ በሌላ በኩል ሕዝብ እምነቱን የጣለባቸውንና የመረጣቸውን መሪዎቹን ትዕዛዝ በመጠባበቅ በሰላማዊ መንገድ ትግሉን መግፋት ፊት ለፊት ተፋጠጡ። ወሳኝ አመራር የጠየቀበት ወቅት። ከተቃዋሚው በኩል በሳል አመራርን የሚጠይቅ ሂደት አስፈለገ። አገዛዙ ብቸኛ ኃይሉን፣ ጡንቻውን በመለስ ዕዝ ሥር የሆነው የፀጥታ ኃይል ማንኛውንም ዓይነት እርምጃ በመውሰድ በኅብረተሰቡ ዘንድ ሽብር ይከሰት ዘንድ ትዕዛዝ ተሰጠው። በመለስ ትዕዛዝ የትዕዛዙ አስፈፃሚዎች ሕፃናትን ደበደቡ፣ ገደሉ። በ50 ሺህ የሚቆጠሩ ተማሪዎችና ወጣቶች በየማጎሪያው ተጋዙ፡፡ እናቶችና አባቶች ሳይቀሩ ተገደሉ። የደርግ ቀይ ሽብር መጠኑን አሳንሶ ተደገመ። ወያኔን ዴሞክራት አስተዳደር ብለው ያወደሱት ባዕዳን ጌቶቹን ሳይቀር ያሳፈረ አስደንጋጭ ጭፍጨፋ በሀገራችን ላይ ተከሰተ። ሊጠራ የታቀደውና በተለይ የአዲስ አበባ ሕዝብ በጉጉት ሲጠብቀው የነበረው “የሙት ቀን አድማ” በዶር በየነ ጴጥሮስ ቀጭን ትዕዛዝ መሠረዙ በዕኩለ ለሊት ተደመጠ። ተስፋ አስቆራጩ ውሳኔ። የሕዝቡን የፍልሚያ ስሜት ያቀዘቀዘ ውሳኔ። ለሀገርና ሕዝብ ቃል በገቡ አመራሮች የተሰጠ አሳዛኝ ውሳኔ። ድምጹን ለማስከበር የመጨረሻ ፍልሚያውን ለማድረግ የተነሳሳውን ሕዝብ ላይ፣ በተጠንቀቅ ይጠባበቅ የነበረው ኅብረተሰብ ላይ የተወረወረ ዱላ። ይህ ነው እንግዲህ ግንቦት 97 ያስተማረን። የምርጫ ድራማ በወያኔ አገዛዝ እንዴት? ለምን? ብለን እንድንጠይቅ የሚያስገድደን።

ዶር መራራ ጉዲናንና ዶር በየነ ጴጥሮስን ማዕከሉ ያደረገው ኅብረትና ዶር ብርሃኑ ነጋን ማዕከል ያደረገው ቅንጅት እራሳቸው ግራ ገባቸው። የወያኔን አውሬያዊ ባህሪ ሊቋቋሙት ተሳናቸው። ትግል ብሎ መስዋዕትነት፣ ዓላማ ብሎ ጽናት የሞኝ ጨዋታ መሰላቸው። ያመናቸውን ሕዝብ ረሱት፣ ዘነጉት፣ ከዱት። “ወያኔ አውሬ ነው አይምራችሁም” እያሉ የሰበኩት መራራ እርምጃ ወሰዱ። የኅብረቱን አጠቃላይ ውሳኔ በመጣስ ለመለስና ለአገዛዙ ታማኝነታቸውን በመግለጽ ወደ ፓርላማ ዘው አሉ። በመራራ ጉዲናና በየነ ጴጥሮስ መሪነት የተገነባው ኅብረት በሕዝብ ዘንድ የፖለቲካ ክስረት ውስጥ ተወረወረ፡፡ ያ ሁሉ ልፋት፣ ያ ሁሉ ጊዜ፣ ያ ሁሉ ገንዘብ በሁለት ግለሰቦች ወደ ገደል ተወረወረ።

ከግንቦት 97 ምርጫ ዋዜማ ኅብረቱ የነበረበትን ድክመቶች ገምግሞ በተጠናከረ መንገድ ለመቀጠል ሳይቻል ለዓመታት ተጉዟል። ቅንጅትም አመራሩ እስር ቤት ከገባ በኋላ በድርጅቱ ውስጥ ይታይ የነበረው የፖለቲካ ውዥንብር የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። “ኢትዮጵያን እንደ አንድ ጐረቤት ሀገር ነው የምናያት”፡ “ለኢትዮጵያ እኛ ባዕዳን ነን”፡ “እኛ ጉዳያችን ኢትዮጵያ ሳትሆን ነፃነታችን ነው”፡ “ጥያቄያችን የኮሎኒ ጥያቄ ነው”፡ “ከኢትዮጵያ ተገንጥለን የራሳችንን መንግሥት መመሥረት” ከሚሉ ኃይሎች ጋር ይህን አቋማቸውን እንደያዙ በአንድነትና በዴሞክራሲ ስም የተመሠረተው AFD አይዘነጋም።

ከላይ የተነሱት ነጥቦች ቢያንስ ከግንቦት 97 ምርጫ ትረዕይት ምን እንማራለን? ለመጪውስ ምርጫ ምን ማድረግ አለብን? ብለን ከቃኘናቸው ጠቀሜታቸው የጐላ ነበር።

በወቅቱ በተቃዋሚው የፖለቲካ ድርጅት ዘንድ ከአንድነት ይልቅ መከፋፈሉ ጎልቶ ታየ። ቀስተደመና፣ ሊግ፣ መኢሕአድና ኢዴፓን አያይዞ የተመሠረተው ቅንጅት ከግንቦት 97 ማግስት የልደቱ ኢዴፓ የሀገርና የሕዝብ ትግል ከድቶ ወደ ወያኔ ፓርላማ ሲንደረደር አይተናል። ቅንጅት ኃይሉ ሻወል፣ ቅንጅት ብርሃኑ ነጋ ተሸጋግሮ በቀጣይነት ግንቦት 7 አንድነትና ፍትህ ፓርቲ እየተባለ ቅንጅት ሲሸነሸን፣ መኢሕአድም ወደ ድሮው ስሙ ተመልሷል። ይህ እየተከፋፈል ያለ ኃይል ያበረከተው አስተዋጽዎ ቢኖር የወያኔን ዕድሜ ማራዘም ነበር።

በዚህ ሂደት ነበር የግንቦት 1997 ምርጫ ሂደትና የኅብረትና ቅንጅት እንቅስቃሴ ዛሬ ታሪክ ሁኖ የተመዘገበው።

በቀጣይነት በተካሄዱ ምርጫዎች አምባገነኑና እፍረተቢሱ ህወሀት/ኢሕአዴግ 2002 ዓ.ም. 99.6% እና በ2007 ዓ.ም. 100% አሸነፍሁ እያለ በሀገርና ሕዝብ ላይ ያለውን ንቀትና ጥላቻ "ምን ታመጣላችሁ" ሲል አበሰረ። በህወሀት/ወያኔ ዘመን የምርጫ ፖለቲካ ማከተሙ ግልጽ ላልሆነላቸው ግልጽ ምላሽ ነበር። ወያኔን በምርጫ ማጀብ እንጂ የሥልጣን ጥያቄ ውስጥ ማስገባት አግባብነት እንደሌለው መቶ በመቶ ድፍረቱን አሳየ።

## 16.0. የኅብረት ትግል

ሕብረት ሲባል ለምን ያስፈልጋል? ምን ዓይነት ሕብረት? ዓላማውስ ምንድነው? ግቡስ? በሕብረቱ ውስጥ መካተት ያለባቸው እነማን ናቸው? ወዘተ. መልስ ሲያገኙና ሲብራሩ የሰመረ ሕብረት መገንባት ብቻ ሳይሆን የሚካሄደውም ትግል የፖለቲካ የበላይነትን በመያዝ ለአስተማማኝ ድል መሠረት ይሆናል።

ከዚህ በፊት ስለተፈጠሩና ስለከሰሙ ኅብረቶች ይህን ያህል ካልን በአሁኑ ወቅት ሀገራችን ከአለችበት አስከፊ ሁኔታ ለመላቀቅ የእያንዳንዱን ዜጋ ትብብርና ጥረት ይጠይቃል። በተለይ ደግሞ በማንኛውም መንገድ ከአለው የወያኔ አገዛዝ ጋር እየተፋለሙ ያሉ ድርጅቶች የጋራ መሰባሰብ አስፈላጊ ነው። የዚህ ኅብረት አስፈላጊነት ያሉት ጥቅሞች፡-

1. ምን ዓይነት መንግሥት በሚለው ክፍል እንዳስቀመጥነው ከወያኔ ውድቀት በኋላ በቀጣይነት ሀገሪቷን ለሚመራው የጋራ ሽግግር መንግስት መሠረት በመሆን በቀጣይነት ኢትዮጵያ ሀገራችን አንድነቷን ጠብቃ እንዴት ትጓዛለች የሚለውን አቅጣጫ ሰጭ ይሆናል፣
2. ማንኛውም ድርጅት የያዘውን ዓላማ፣ ተልዕኮና ራዕይ በግልጽ በመወያየት በድርጅቶች መካከል ያሉ ልዩነቶችን በማጥበብ ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸውን ወደ ድርጅታዊ ውህደት እንዲያመሩ በር ይከፍታል። ይህ በራሱ ያሉትን የድርጅቶች ብዛት እያሳነሰ ከመሄዱም ባሻገር ካለመወያየት በርቀት የተካረሩ ድርጅቶችን ወደ መስማማት ያመጣል፣
3. ለሀገር ህልውና እና ለሕዝብ ደህንነት ሲባል የዘረኛውን ወያኔ አገዛዝ ለማስወገድ በአንድ ወይም በሁለት ድርጅቶች የሚቻልበት ሁኔታ ቢኖርም በኅብረት መታገል የድሉን ጊዜ ያቀርበዋል፣
4. ኅብረቱ በጋራ መታገልን ባይችል እንኳ በድርጅቶች መካከል ያለውን አለመግባባት ለማስወገድ ኅብረቱ የመወያያ፣ የመከራከሪያና የመስማምያ መድረክ ሊሆን ይችላል፣
5. በወያኔ ዘመን በርካታ በብሔር/ብሔረሰብን ተሞርኩዞ የተደራጁ ድርጅቶችና ሀገራዊ አጀንዳ ይዘው ያሉ እንደመኖራቸው መጠን አንድ ድርጅት ብቻ ጎልቶ በመውጣት እኔ አውቅላችኋለሁ ባይ ሌላ አምባገነን አገዛዝ በቀጣይነት እንዳይተካ በጋራና በግልጽ ለመወያየትና ለመመካከር ኅብረቱ የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል
6. ኅብረቱ በሀገር አንድነት የሚያምኑና በብሔር/ብሔረሰብ የበላይነት የሚያምኑ፣ የተለያየ ዓላማ ያላቸው፣ የተለያየ የትግል ስልት የሚከተሉ፣ እኔ ትልቅ ነኝ ያ ትንሽ ነው የሚሉ፣ እኛ ሕጋዊ እነሱ ሕገወጥ የሚባሉ፣ ወዘተ ያካተተ ሆኖ ወያኔን በጋራ መታገል ባይቻል እንኳ እንደ ዜግነታችን እርስ በርስ ያለውን ሹክቻ ከማካረር ይልቅ በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ በማሰባሰብ ልዮነቶችን ለማጥበብ ይረዳል

የወያኔ አገዛዝ ለ25 ዓመታት የዘረጋው/የረጨው የዘረኝነት አባዜ በህዝባችንና በሀገራችን ላይ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ዛሬ በ35 ዓመት ዕድሜ ያሉ የሀገራችን ጎልማሶች ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜታቸው ቢዳከም፣ ኢትዮጵያዊነት መለያችንን ሰንደቅ ዓላማዋን የማያውቋት ቢኖሩ አይደንቀንም። ወያኔ በየመንደራቸው፣ በየቂያቸው፣ በየትምህርት ቤታቸው፣ ይህንን መርዙን ሲበትን ነውና ያሳደጋቸው። ወያኔ የዘራውን ዘረኝነት አጭዶ ኢትዮጵያዊነት ያብብ ዘንድ ችግሩ መኖሩን መቀበል አስፈላጊ ነው። በኃይልና በጉልበት ሳይሆን ለችግሩ እውቅና ሰጥቶ የሕዝቡን ዴሞክራሲያዊ መብት በተግባር በማሳየትና የሕዝብ የበላይነትን በመቀበል ችግሩ ተፈትቶ ሁሉም ኢትዮጵያ ሀገሬ ብሎ ይሰለፍ ዘንድ የጋራ ምክክርና መድረክ አስፈላጊ ነው። ከወያኔ ውድቀት በኋላ አምባገነን ገዥዎች ጥለውት ያለፉትን የቤት ሥራ በጉልበት ልንፈታው ከተነሳን እኛም እነሱን ተከተልን ማለት ነው። ከወያኔ ውድቀት በኋላ በለስ የቀናው እኔ አውቅላችኋለሁ ባይ አግላይ ፖለቲካ ከመጣ መታወቅ ያለበት ለህዝብ አይበጅምና ትግሉ ይቀጥላል።

በመሆኑም ለሀገርና ለሕዝብ እንጮሃለን፣ ኢትዮጵያ ከገጠማት አስከፊ አደጋ ለማዳን እንረባረብ ከተባለ በኅብረት መታገል ባይቻል እንኳ የኅብረት ስምምነት አስፈላጊ ነው። አለበለዚያ የሁሉም እሽቅድምድም ለሥልጣን ይሆንና ለሀገር መበታተን ወይም ለሌላ አምባገነን መተካት በር እንደምንከፍት ሊታየን ይገባል።

በጥቅሉ አሁንም ጊዜው አላነሰም፣ በሩ አልተዘጋም። ለሀገርና ለሕዝብ አንድነትና ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ምሥረታ ድምጹን እያሰማ ያለው የፖለቲካ ኃይል ኅብረት ፈጥሮ በጋራ መታገል ባይሆንለት እንኳ በጋራ ተስማምቶና እርስ በርስ የሚደረገውን አላስፈላጊ ሹኩቻ አስወግዶ ሁሉም የጋራ ጠላት ላይ እንዲያተኩር ከኢትዮጵያ ጠላቶችና ከአገዛዙ ባሻገር የኅብረት ግምባር መፍጠር ይጠበቅባቸዋል።

በሀገራችን ብሔራዊ ስሜት አብቦ ልማትንና ዕድገትን መሠረት ያደረገ ዴሞክራሲያዊ መንግሥትና አሠራር በአንድ ኢትዮጵያ ጥላ ለመገንባት ሥር እየሰደደ የመጣውን ዘርተኝነት ወደ ከፋ መበታተንና የእርስ በርስ ግጭት ውስጥ እንዳይገፋ ከተፈለገ በተለያዩ ድርጅቶች መሃል መሰባሰብን በመፍጠር በወቅቱ የሀገራችን ሁኔታ ለመምከር ውይይት ማድረግ ያስፈልጋል። በሀገራችን ለተፈጠሩ የዘር፣ የብሔር/ብሔረሰብ፣ የሃይማኖት፣ ቅራኔዎች ምንጩ በየጊዜው የተፈራረቁት ኢዴሞክራሲያዊ አገዛዞች እንጂ ኢትዮጵያ እንዳልሆነች የጋራ ስምምነት ላይ ለመድረስ የጋራ መወያየት አስፈላጊ ነው። የአምባገነኖች፣ በተለይ የወያኔ አገዛዝ ከፋፍለህ ግዛና በዘር የመጣ የመበታተን አደጋ ተዳክሞ ሁሉም በባህሉ፣ በቋንቋውና በብሔሩ ኮርቶና ተከባብሮ የሚኖርባት የጋራ ሀገር ከእራሳችን አልፋ ለአፍሪካ አርአያ ትሆን ዘንድ ወያኔ/ሻቢያን በሀገርና ሕዝብ ጠላትነት ፈርጀን መሰባሰብ አስፈላጊ መሆኑን “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!” ሕዝባዊ ንቅናቄ ሠነድ ያምንበታል።

ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችንና ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያካተተ የጋራ ኅብረት ተግባራዊ ሆነ ማለት፦ በመበታተናችንን የተጠቀሙትን ወያኔን/ሻቢያ አሳፈርናቸው ማለት ነው፣ በምሥራቅ አፍሪካ በተለይም በኢትዮጵያችን ሊከሰት የሚችለውን የእርስ በርስ ግጭት አስቀምነው ማለት ነው። ተዳክመንና ተከፋፍለን እንዳመቻቸው ሊቦጠቡጡንና አንጡራ ሀብታችንን ሊበዘብዙ የቋመጡትን ባዕዳን ኃይሎች አሳፈርን ማለት ነው። “እኛ ከሌለን ኢትዮጵያ አትኖርም” ባዮችን ዘላለማዊነታችንን አሳየናቸው ማለት ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ የ100 ዓመት ሳይሆን ከሦስት ሺህ ዘመን በላይ ያስቆጠረ የጀግነትና የማንነት ክብር መሆኑን መሰከርን ማለት ነው። በአባትና እናቶቻችን አጥንትና ደም ተከብራ የኖረችዋን ኢትዮጵያ ትንሳዔዋን አበሰርን ማለት ነው። ዛሬ በተለያየ የሀገሪቷ ክፍል ከወያኔ አገዛዝ ጋር እየተፋለሙ፣እየተዋደቁ ላሉት ወገኖቻችን በጋራ ደረስንላቸው ማለት ነው። ይህ ሲሆንም የሕዝብና የሀገር የመከራ ጊዜ ማክተሙንና ለድል መቃረባችንን አጠናከርን። በመላ ሀገሪቷ የተጀመረው ሕዝባዊ ንቅናቄ መሪ አጥቶ እንዳይቀለበስ ተዘጋጀን ማለት ነው።

## 17.0. ብሔራዊ ዕርቅ

በኢትዮጵያ እስከ ዛሬ በሥልጣን ላይ የተፈራረቁት መንግሥታት አንዱ ከሌላው የሚለዩባቸው ባህርያት ቢኖራቸውም ሁሉንም ገዥዎች አንድ የሚያደርጋቸው ፦ አብዛኞቹ ሥልጣን በኃይል መያዛቸው፣ አምባገነንነታቸው፣ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ማራመዳቸው፣ ዴሞክራሲያዊ መብትን ማፈናቸው፣ በሕዝብ መካከል የጋራ መተማመንና ከበሬታን ለመፍጠር አለመቻላቸው ሲሆን በተጨማሪም ከሀገር ዕድገትና ልማት ይልቅ መጠኑ ይለያይ እንጂ ለጉቦኝነት፣ ዝርፊያና ሙስና የተጋለጠ ቢሮክራሲያዊ አስተዳደር ነበራቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ በተለይ ከ1953ቱ የታህሳሱ መፈንቅለ መንግሥት ማግሥት እየተጠናከረ በመምጣት በሀገሪቷ መሠረታዊና ሥር ነቀል ለውጥ ጠያቂው እየተደራጀና እየተሰባሰበ የመጣበት ወቅት ነበር። ይህ የሀገርና ሕዝብን ጥያቄ አንግቦ የተነሳው የየካቲት 66ቱ ተራማጅ ኃይል ገና ከጅምሩ በአካሄዱ ተለያይቶ ነበር። የሀሳብ ልዩነትን በፀጋ ተቀብሎ ለዋናው የሀገርና ሕዝብ ጉዳይ በሰከነ ሁኔታ በመመካከርና በመወያየት ወደ ጋራ መስማማት ሊደርስ አለመቻሉ የደካማ ጎኑ ነፀብራቅ ነበር።

አምባገነን ገዥዎች የሥልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም የሰውን ልጅ መብት ይነፍጋሉ። መብትና ተጠያቂነት በአንድ ሀገር ሲጠፋ የአገዛዙ አካሎች ወደ ሙስና፣ ዝርፊያ፣ ጉበኝነት ያመራሉ። የሀገር ሀብት ዝርፊያው መረን እያጣ ሲመጣ ተመልካቹ



Andnet Park

ሕዝብ ጥያቄ ሲያቀርብ ምላሹ እስር፣ ድብደባ፣ ማንገላታት ብሎም ግድያ ይሆናል። አንድ መንግሥት የሀገር ሀብትና ንብረት ዝርፊያ ላይ ከተሰማራ፣ ስለ ሀገርና ሙብት የሚነሱ ጥያቄዎችን በእሥርና ግድያ ከፈታ የጊዜ ጉዳይ እንጂ መንግሥት እርከን ላይ ያሉት አንድ ቀን በተጠያቂነት ለሕዝብ ፍርድ መቅረባቸው አይቀርም። ምክንያቱም ያለ አግባብ በሀገርና ሕዝብ ሀብት በልጽገዋልና፣ ያለአግባብ ሕዝብና ልጆቹን አስረዋል፣ አሰቃይተዋል ብሎም ገድለዋልና።

በዚህ ሂደት በተለይ የመንግሥት ተቃዋሚ ኃይሎች በሚያደርጉት እንቅስቃሴ በተደጋጋሚ የሰላምና ብሔራዊ ዕርቅ ጥያቄ ለገዥው አካል ቢያቀርቡም ሰሚ ጆሮ አያገኝም። መንግሥትና የከበቡት በከፍተኛ ተጠያቂነት ላይ ስላሉ ጥርጣሬና ፍርሃት ስላለባቸው ከማንኛውም ተቃዋሚ ኃይል ጋር ዕርቅ አይፈልጉም። ተገደውም በዕርቅ ጠረጴዛ ዙሪያ ቢቀመጡ "ምን ያለበት ዝላይ አይችልም" እንዲሉ ድርድሩንና ውይይቱን ሊቆጣጠሩ፣ እነሱ በፈለጉት አቅጣጫ እንዲጓዝ ይፈልጋሉ፣ ይጥራሉ። የዚህም ሂደት ውጤት አምባገነን ገዥዎች ስለ ሰላምና ዕርቅ ሊሰሙም አይፈልጉም። በኃይልና በጉልበት እንደገዙ በኃይልና በጉልበት ይወርዳሉ እንጂ።

ሌላው የአምባገነኖችና የገዳዮች ባህሪ በኃይል ተገፍተው ሥልጣናቸውን ከለቀቁ በኋላ ስለ ዕርቅና ሰላም ዋና ሰባኪዎች ይሆናሉ። በሕዝብ ላይ በሠሩት በደልና ግፍ ሀገርንና ሕዝብን ይቅርታ ከመጠየቅ ይልቅ በዕርቅ ስም በገርና ሕዝብ ላይ ያደረሱት ጥፋት ሽፋን እንዲያገኝና ዳግም እንዳይነሳባቸው ይጥራሉ። በአጭሩ ለዚህ የደርግ ኢሠፓ ተጠያቂዎች ዋንኛ ምሥክሮች ናቸው። "ታሪክ እራሱን ይደግማል" እንዲሉ ወያኔ ሥልጣን ከመያዙም ሆነ አሁን በሥልጣን ላይ እያለ በተለያየ የእርስ በርስ ሹኩቻቸው ከወያኔ ሥልጣን እርከን የተባብርሩ ወይም የለቀቁ በቅድሚያ የበደሉትን ሕዝብ ይቅር ከማለት ይልቅ እራሳቸውን ለመከላከል ሲዘጋጁና እንደውም የተቃዋሚው ዋና ተዋናይ ለመሆን ሲጥሩ ይስተዋላሉ። የዚህ ክስተት ሂደት የሚያሳየው ብዙ ጊዜ በተለይ ከግድያና ከዝርፊያ ጋር ተጠያቂነት ያለበት ግለሰብም ሆነ መንግሥት ይቅርታ ከመጠየቅ ይልቅ ለጥፋቱ መሸፈኛ ሌላ ጥፋት ፍለጋ ሲኳትኑ ይስተዋላሉ።

ከሌላ አንፃር ሲታይ በተለይ በወያኔ አገዛዝ ዘመን በኢትዮጵያ በርካታ በብሔር/ ብሔረሰብ የተደራጁና ኅብረብሔር የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ። የአብዛኛዎቹ ዋናው ድምጻቸው ስለ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር፣ መንግሥት በሀገራችን መፈጠር ሲሆን ይህንን ስኬታማ ለማድረግ ሁሉም የራሴ የሚለው አካሄድ ያለ ይመስላል። አንዳንዶቹ ከዋናው ጠላትና ከሚታገሉት አገዛዝ በባሰ የእርስ በርስ ሹኩቻቸው ይበልጥ ይጎላል። በግለሰብ ተክለሰውነት፣ በድርጅታዊ ውስጣዊ አሰራርና በመሳሰሉት ለትግሉ መስጠት የሚገባቸውን ጊዜና ዕውቀት ለእርስ በርስ መነታረክ ሲያውሉት ከመስተዋል አልፈው እየተከፋፈሉ የተሰነጣጠቁም አሉ። አለመስማማቱና መለያየቱ አድማሱን አስፍቶ አንዱ የደረሰበት ሌላው ዝር ሊል አይፈልግም። ሌሎች ደግሞ ከእኛ ወዲያ ፖለቲከኛ፣ ከእኛ ወዲያ ታጋይ ብለው ሊቆጣጠሩት ካልቻሉ ማንንም ማስጠጋት አይፈልጉም። ሁሉም ስለኅብረት ትግል ያወራሉ፣ ሁሉም ስለ ጋራ ትግል ያወራሉ፣ በተግባር ግና አንዱ ሌላውን ሲያብጠለጥሉ ይታያል።

የሀገራችንን ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ችግር ለመፍታትና አዲሲቷ ኢትዮጵያ ትኩረቷን ወደ ዕድገትና ልማት አቅጣጫ አድርጋ ዓለም እደረሰበት ሥልጣኔ ደረጃ ትደርስ ዘንድ ሁሉም ዜጎቿ በአንድነት እጅ ለእጅ ተያይዘው ሊያግዟት ይገባል። ለዚህም በፖለቲካው፣ በዘር ልዩነት፣ በሃይማኖት፣ ሥልጣንን ያለ አግባብ በመጠቀም በዜጎቿ ላይ በየጊዜው የደረሰውን በደልና ግፍ ይቅር ተባብሎ ቀጣይ አቅጣጫን ለመቀየስ ብሔራዊ መግባባትና ዕርቅ አስፈላጊ መሆኑን ይህ ሠነድ ትኩረት ይሰጠዋል።

"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!" ሕዝባዊ ንቅናቄን እውን ለማድረግና የሀገርን ሉዓላዊነት ለመጠበቅ በተለያዩ አገዛዞች የተፈጠረውን ቁርሾ በተለይ በደርግ አንድ ትውልድ ማጥፋት ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር እንዲሁም በህወአት/ኢሕአዴግ የዘር ማጥፋት ወንጀል ዳግም እንዳይደገም ትምህርት ሰጪ ማድረግ ሲገባ ነው። ይህ ግና ተግባራዊ ይሆን ዘንድ የተደረጉ በደሎችን፣ ጥፋቶችንና እውነታዎችን እውቅና መሰጠት ይኖርበታል። የተፈጸሙ በደሎችና ግፎች ዳግም እንዳይከሰቱና በዳዮችንም ከኅብረተሰቡ የመገለል አዝማሚያ እንዳያመጣ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል። ግባችን ሀገራችንን ኢትዮጵያ አንድነቷን ጠብቃ የሕዝባችንን ብሔራዊ ስሜት ለመገንባት ከሆነ ይቅርታን አስተማሪ ማድረግ ይጠበቅብናል። ብሔራዊ ዕርቅ ሀገራዊ መግባባትን በማስፈን ደረጃ ፣ ሀገራዊ አንድነትን ከመገንባት አንጻር ጉልህ ሚና ይጫወታልና።

ብሔራዊ ዕርቅ ሲባል ከማን ጋር? የሚለው የሚነሳ ጉዳይ ነው። ብሔራዊ ዕርቅ ለሀገርና ሕዝብ ሲባል የሚከናወን ነውና ይቅር በይን የምንለው ሀገራችንንና ሕዝባችንን ነው።

- ኢትዮጵያ ሀገራችን ዛሬ ያላትን ጂኦግራፊያዊ ቅርጺን እንድትይዝ በተደረገው የሀገር ግንባታ የተከሰቱ ጥፋቶች አሉ።
- ኢትዮጵያን በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ሥር ለማዋቀር በተካሄዱ ጥረቶች የተከሰቱ ችግሮች እየተንከባለሉ ዛሬም ይነሳሉ።
- በየወቅቱ የተፈራረቁ አገዛዞች የመንግሥት ሥልጣናቸውን ተገን በማድረግ ጥፋት አድርገዋል፣ የሀገርና ሕዝብ ሀብት ዘርፈዋል፣ መጠኑ እንደዘመናቸው ይለያይ እንጂ የተቃወሚቸውንና ተቀናቃኝ ያሏቸውን፣ ለሥልጣኔ ያሰጋኛል ያሉትን ሕይወት ቀጥፈዋል።
- የፖለቲካ ድርጅቶች እርስ በርሳቸው ያለውን መለስተኛ ቅራኔ በውይይትና በመግባባት መፍታት አቅቷቸው ችግራቸው ለሀገርና ሕዝብ ሆኗል።
- በአንድነት በተነሱ ፖለቲካ ድርጅቶች መካከል መለያየትና አለመግባባት ብቻ ሳይሆን እርስ በርስ ሕይወት ጠፍቷል።
- በሁለቱ ታላላቅ ሃይማኖቶች ማለትም በእስልምናና በክርስትና መካከል እንዲሁም በተለያዩ የክርስትና እምነት ተከታዮች መካከል በተጨማሪም በአማኙና እምነት የለሹ ማኅበረሰብ መካከል ያሉ የበላይነት፣ የዝቅተኝነት ስሜትና አለመግባባት የጎዳው ቢኖር ሀገርና ሕዝብን ነው።
- በተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦች መካከል፣ በአንድ ብሔር ውስጥም በተለያዩ አካባቢዎችና ክልሎች ያለው መናናቅ፣ እኔ ነኝ የዚህ ብሔር ወካይ ስሜት፣ ይበልጡንም አሁን ያለው ህወሀት/ወያኔ ያባባሰው የዘር ፖለቲካ ልዩነትና ቅራኔ ያደረሰውና ሊያደርስ የሚችለው ጥፋት የሚጎዳው ሀገርና ሕዝብን ነው።
- በአንድ ኅብረተሰብ ክፍል የሚደረግ የቡድን ድብድብና ጥቃት፣ በአካባቢው ያለውን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ መቆጣጠር አለብን፣ "ግዛቱ የእኛ ነው" ዓይነት ቡድናዊ ስሜት  አካባቢን ከማወክ አልፎ ሀገርና ሕዝብን የሚያዳክም ነው።
- ጊዜ የሰጣቸው የሀገርና ሕዝብ ሀብት ዘራፊዎችና ቅጥ ያጣ የየዕለት ባህሪያቸው በአንድ በኩል፣ በሌላ ገጽታ ሚላስ ሚቀመስ አጥተው በየቤቱ የተኮራመቱ፣ በየሆቴሉና ምግብ ቤቶች በራፍ ለትርፍራፊ የሚቁለጨለጩ ለዚህ ያልታደሉትም ለቆሻሻ ገንዳ የሚጋደሉ ኅብረተሰብ ውስጥ የተፈጠረው የአኗኗር ቅራኔ እምዬ ኢትዮጵያን አስለቅሷል፣ ሕዝባችንን አስተክዟል። ወዘተ. ወዘተ.

የእነኚህ ሁሉ ጥርቅም ውጤት በተንሹ ለአለፉት 50 ዓመታት የብልሹ አስተዳደር ውጤት ናቸው። የእነዚህ ብልሹ አስተዳደር ውጤቶች ሕዝብ ከአገዛዝ ጋር ብቻ ሳይሆን ኅብረተሰቡ በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በባህል፣ በሃይማኖት ወዘተ እርስ በርሱ እንዲቃረን ያበረከተው ውጤት ቀላል አይደለም። እነዚህን መሠረታዊ ጉዳዮች ሁሉ የዳሰሰ ብሔራዊ መግባባትና ዕርቅ ለሀገራችን የወደፊት ራዕይ አስፈላጊ መሆኑን አስምረንበታል።

ብሔራዊ ዕርቅ ሀገራችን ያጋጠማትን ውስብስብ ችግሮች መፍቻ መሆን ይገባዋል። አሁንም መጤን የሚገባው በተለይ የፖለቲካ ድርጅቶች የፖለቲካ የበላይነት ለማግኘትና ጊዜው የእኛ ነው በሚል ለመጠቀሚያ ሊያውሉት ከተሞከረ ግቡን አይመታም። ብሔራዊ ዕርቅ እንዲሰምር ካስፈለገ በቅድሚያ ጊዜው የሀገርና የሕዝብ መሆኑን መቀበል ይጠይቃል። የዚህ ጊዜ እራስን ለማዳን ሳይሆን ሀገርና ሕዝብን ለማዳን፣ ሀገርና ሕዝብን ከፍ ከፍ ለማድረግ ይሆናልና ይቅር ተባብለን ትውልድን እናስደስታለን። በብሔራዊ ዕርቅ ስኬታማነት አሸናፊ ማንም ኃይል ሳይሆን ኢትዮጵያችንና ሕዝቧ መሆን ይኖርበታል። በሀገራችን ለቀጣይ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የዚህ ጊዜ የመሠረት ድንጋይ ጣልን ማለት ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ ከድህነትና ኋላ ቀርነት ተላቃ ወደ ብልጽግና ጎዳና ታመራ ዘንድ እጅ ለእጅ ተያያዝን ማለት ነው። የዚህ ጊዜ የሀገራችን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት አስተማማኝ ሲሆን፣ የሕዝባችንን ዴሞክራሲያዊ አንድነት አስጠብቀን ሀገሩን ተመልካች ዜጋ ፈጠርን ማለት ነው።

በሀገራችን ኢትዮጵያ የሚካሄደው ብሔራዊ ዕርቅ እንደ ባህላችንና ሃይማኖታችን መሆን ይገባዋል። የእኛ ሀገር ነባራዊ ሁኔታና የሌላው ይለያያልና እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን በሚገባ መጠናት ይኖርበታል።፡ይህ ብሔራዊ መግባባትና ዕርቅ ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የብሔር/ብሔረሰብ ድርጅቶች፣ ሁሉንም የብዙኃን ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ የሰብዓዊ

መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ ሁሉንም የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ምሁራንን፣ በደርግ ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር ሰለባ የሆኑ ኅብረተሰብ ክፍሎች ተወካዮች፣ በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ጉዳት የደረሰባቸው፣ የተገደሉ ኅብረተሰብ ክፍሎች ተወካዮች፣ ወዘተ እና በታዛቢነት የተለያዩ ዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ተቋማት፣ እና ሌሎች ያካተተ ቢሆን ይመረጣል።

በኢትዮጵያችን ለብሔራዊ ዕርቅ ስኬታማነት ከላይ እንዳስቀመጥነው ትግሉን በተቀናጀና በጋራ ለማካሄድ የሚሰባሰበው ኅብረት/ግብረኃይል ትልቅ አስተዋጽዎ ይኖረዋል። በሀገራችን አንድነትን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት በቀጣይነት እኔ ያልኩት ብቻ ባይ የፖለቲካ ድርጅትና ዝናን ፈላጊ ግለሰብ ለጋራ አመራርና ለብሔራዊ ዕርቅ መገዛት እንዳለበት ይህ ሠነድ አስቀምጧል።

## 18.0. የቅራኔ አያያዝ መርሆዎች

- በተናደድህና ስሜታዊ በሆንክ ጊዜ በተነሳው ጉዳይ ላይ ሀሳብ ከመስጠት በመቆጠብ መጀመሪያ ለመረጋጋት መሞከር
- በሀሳብ አቅራቢው ላይ ሳይሆን በቀረበው ሀሳብ ላይ ማተኮር፣ ለሀሳብ አቅራቢውም ምስጋና ማቅረብ
- ሀሳብን በስነ ሥርዓት ማቅረብ፣ ኃይለኝነትንና ቁጣን አለመደባለቅ፣ ሀሳብ አቅራቢውን በመኮነን አለመጀመር
- የራስን አማራጭ ሀሳብ ከመሰንዘር በፊት የቀረበው ሀሳብ ላይ ትንታኔ መስጠት
- የሰዎችን የተለያየ ሀሳብ መቀበልና ማክበር ልምድ ማድረግ፣ ለማሳመን ኃይልን እንደአማራጭ አለመውሰድ፣ የጋራ መስማማትን ከሰዎች ጋር ለመፍጠር ጥረት ማድረግ
- የተነሳው ሀሳብ ተቀባይነት ቢያጣ እንደ ተሸናፊነት፣ ተቀባይነት ቢያገኝ እንደአሸናፊነት አለመውሰድ፤ ሁለቱም ወገኖች በጋራ የተነሱበት ጉዳዮች አሏቸውና
- ላለመስማማትና ላለመግባባት ከመጣር ይልቅ በጋራ ጉዳዮችና ጥቅሞች ላይ ማተኮር
- በሀሳብ አቅራቢው ለምን አቀረበው በሚል ድምዳሜ ላይና ወደ ሌላ ግምት አለመሄድ
- የሌሎችን ሀሳብ ያለማቋረጥ ማድመጥ፣ ተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለገ ጥያቄ መጠየቅ
- በተነሳው ሀሳብ የአንድ ሰው ፍላጎት መሟላት ወይም ምላሽ አገኘ ማለት ሀሳቡ ሌሎችን አይመለከትም ማለት አይደለም
- በአለፈው በተነሳ ሀሳብ ቂም ይዞ ለቀጣይ ሥራ እንቅፋት መሆን የለበትም
- በቀረበው ሀሳብ የጋራ ስምምነትን መገንባት እንጂ ኃይልን ማሳየት አግባብ አይደለም
- ለሀሳብ አቅራቢው በመደማመጥ ለተደረገው ውይይትም ምስጋና ማቅረብን አለመዘንጋት

## 19.0. የባዕዳን ኃይሎች ሤራ

ኢትዮጵያ ሀገራችንን ባዕዳን ከጥንት ጀምሮ አጥቅተዋታል። እንግሊዞች ታሪካችንን በርዘዋል፣ ቅርሳችንን ዘርፈዋል፣ በኅብረተሰባችን ዘንድ መርዛቸውን ረጭተዋል፣ ማንነታችንን ለማጥፋት ጥረዋል። ዛሬም ጥንት የቀበሩትን የጥፋት ፈንጂ በተዘዋዋሪ እንዲተረጎም ይፈልጋሉ፤ እንደፈለጉ ሊጋልቡን የወያኔ ጀርባ ተመችቷቸዋል። ጣልያን ኢትዮጵያዊነታችን ላይ ዘምታለች፣ ቅርሶቻችንን አጥፍታለች፣ ዘርፋለች የሀገራችንን ክፍል ለ60 ዓመታት በቅኝ ይዛለች። ጥንት የዘራችው ኢትዮጵያን በዘር የመከፋፈል ጥንስስ ዛሬ የሀገራችን ጉዶች እየተገበሩላት ነው። የዐባይ ወንዝና ተፋሰሶች ተጠቃሚ እንዳንሆን ከጥንት ጀምሮ የማይተኙልን ግብፆችና አረቦች ሰላማችንን አይወዱም። ኢትዮጵያ የልጇ እንድትሆን አይፈልጉም። ለዚህ ተግባራቸው ደግሞ የሀገርንና የሕዝብን ህልውና ገንዘብና መሣሪያ ለሰጠው ሁሉ የሚሸጠው ወያኔ ይመቻቸዋል። አሜሪካ በሀገራችን ላይ ካላት ስትራቴጂያዊ ጥቅም አንፃር የተስማማት አገዛዝ ነው። ለሕዝብ ተጨንቀው አያውቁምና። እነሱ በአንድ ሀገር ላይ ስለ ሰብዓዊ መብት መጣስ የሚጨነቁት፣ የዚያ ሀገር ዜና ዜናቸው የሚሆነው የማይመቻቸው፣ ከቁጥጥራቸው ውጭ የሆነ አገዛዝ ሲኖር ነውና ፍላጎታቸው እስከሰመረ ድረስ የሕዝብ ስቃይ

አያስጨንቃቸውም፡፡ የሀገርን ህልውና አሳልፎ ለመስጠት ቅድመ ሁኔታው ገንዘብ የሆነው ወያኔ አስደስቷቸዋል፡፡ የወያኔ በሀገር ላይ የሚያደርሰው ግፍና መከራ በዓለም ደረጃ እርቃኑን እየወጣ እነሱንም እያሳጣቸው ከቁጥጥር ውጪ ከሆነባቸው ደግሞ አሁንም ፍላጎታቸውና ጥቅማቸው እንዳይጓደልባቸው በለውጥ ስም የራሳቸው አገልጋይ፡ አሁንም የሕዝብን ስሜት የማያዳምጥ አስቀምጠውልን እስቲ እንያቸው ስንል ሌላ 25 ዓመት እንድንቆጥር ያደርጉናል፡፡

ወያኔ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ለማጥፋት ታጥቆ የተነሳ ለመሆኑ አስረጅ የሚያስፈልግ አይደለም፡፡ "እኛ ከሌለን ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር አትኖርም" የሚለው ተደጋጋሚ አባባል ሌላ መጥቀስ አስፈላጊ አይደለም፡፡ በመጨረሻው ሰዓትና ሲበቃው የቀበረውን ፈንጂ ይለኩሰልናል፡፡ የወያኔ ዝግጅቶች፣ ሂደቶች፣ ጉዞዎች ሁሉ ሀገር ወደ ማጥፋት ያመራሉና፡፡ ይህንን ማየት አለብን ካልን፡ የዚያ ግዜ ሀገር፣ ኢትዮጵያ የምትባል የለችምና፣ አትኖርምና፣ የምናየው ቢኖር የጥፋት ዘመንን ነውና እጅጉን ሊያሳስበን ይገባል፡፡ የወያኔ የመጨረሻ ደርጃ መጨረሻ አለው፡፡ በአንድ በኩል እስከቻለ ይገዛል፣ ይዘርፋል፣ ያራቁታል፡፡ ሲበቃው፣ ሲያቅተው፣ ሀገሪቱን በብሔር/ብሔረሰብ፤ በሃይማኖት ሊበጣጥስና ሊያስተላልቅ ያጠመዳቸውን የጥፋት ዕቅዶች ይተገብራል፡፡ ይበልጥ ያነደዋል፡፡

በሌላ በኩል በወያኔ አገዛዝ የሀገራችንን ጥቅም የሚነካ ውል ከአገዛዙ ጋር የተዋዋሉ፣ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን አለ አግባብ የያዙ፣ ከአገዛዙ ጋር በመመሳጠር በዝርፊያ የተሰማሩ ወዘተ. የውጭ ኃይሎች (አሜሪካ፡ ቻይና፡ ኔዘርላንድስ፡ ኖርዌይ፡ ጀርመን እና ሌሎችም) በሀገሪቷ ላይ የዘረጉት ፕሮጀክቶች ቀጣይነት ይኖራቸው ዘንድ፡ የተዋዋሉት ውል እንደፀና ይቀጥልላቸው ዘንድ ቀጣዩን አገዛዝ እራሳቸው አዘጋጅተውልን በለውጥ ስም እንድንቀበል ይጭኑብናል፡፡ ይህ ሌላኛው አማራጭ ነው፡፡

## 20.0. ምን መደረግ አለበት

ቢያንስ ወያኔ በትረ ሥልጣኑን ከያዘ ለአለፉት 25 ዓመታት የሀገራችን ኢትዮጵያ ሁኔታ ከዛሬ ነገ ጠንከር ያለ አታጋይ የፖለቲካ ድርጅት ብቅ ብሎ መፍተሄ ይገኛል ብለን ስንመለከት ኖረናል፡፡ በየወቅቱ ሁኔታው እየተባባሰ፣ ችግራችን ውስብስብ እየሆነ ከአለው አገዛዝ ጋር ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳቸው እንኳ መግባባት ያቃታቸው የፖለቲካ ድርጅቶችንና ኃይሎችን እየታዘብን እዚህ ደርሰናል፡፡ አሁን ግን የሀገራችን ኢትዮጵያ የህልውና ጉዳይ አጠያያቂ ነው፡፡ ሀገራችን እንደ ሀገር የመቀጠል ሁኔታዋ ከመቼውም ጊዜ በላይ አሳሳቢ እየሆነ ይታያል፡፡ በወያኔ የተጠነሰሰ ሌሎችም አሰፍስፈው የሚቋሙጥለት የእርስ በእርስ ግጭት እያንዣበበ ይታያል፡፡ ወያኔ ከፍተኛ የዘር ጥላቻ ውስጥ እንድንዘፈቅ ጥሯል፡፡ ወያኔ ከፍተኛ የሃይማኖት ግጭት ውስጥ እንድንገባ የሠራል፡፡ ኢትዮጵያዊነት ስሜት ተሸርሽሮ ሁሉም በጎጡ እየተያየ ያለበት ሁኔታ ጐልቶ ወጥቷል፡፡ ይህ ደግሞ አንዴ ከፈነዳና መስመሩን ከሳተ በህዝባችንና በሀገራችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያመጣ መተንበይ አይከብድም፡፡

ግብጽ በዐባይ ጉዳይ መበታተናችንን ትፈልገዋለችና ማንኛውንም ዘረኛ ቡድንና ሀገር ሊያዳክምላት የሚችለውን ድርጅት ከመደገፍና ከመርዳት ወደ ኋላ አትልም፡፡ በወያኔ ኢትዮጵያን ተቀራምተው እየቦጠቦጧት ያሉት ቻይናና የውጭ ባለሀብቶች ምዕራባውያንን ጨምሮ ከወያኔም በኋላ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ እንደወያኔ ሚሰግድላቸው መንግሥት ይተካ ዘንድ ከማደራጀትና ለእኛ የሚሆነውን እነሱ ከማዘጋጀት ወደ ኋላ አላሉም፡፡ ለነሱ ጥቅማቸው እስከተሟላ ድረስ ስለ ሀገራችንና ሕዝባችን እንደማይጨነቁ ጠንቅቀን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ እነሱ የሀገራችንን ወዳጅነት ሲሉ ከጥቅማቸው አንፃር ነውና፡፡

በወያኔና ሻቢያ እኩይ ሀገር የማጥፋት ተግባር የተተለሙ ዕቅዶች ተግባራዊ ይሆኑ ዘንድ በተቃዋሚ ስም የተለያዩ የዘርና የሃይማኖት ድርጅቶች እንደሚረዱና ለጥፋት ተልዕኳቸው እንደሚያደራጁ መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ የምሥራቅ ኢትዮጵያና የኦጋዴን ጉዳይ፣ የኦሮሞ ወገኖቻችን ጉዳይ፣ በኢትዮጵያ በየሠፈሩ የተሰገሰጉት የሶማሊያ ስደተኞች ጉዳይ፣ በዓለም ደረጃ አሳሳቢ ጉዳይ የሆነው የአሸባሪነት እንቅስቃሴ በአብዛኛው ሲታይ ከኢትዮጵያዊነት አጀንዳ ይልቅ የመበታተንን፣ የመገንጠልን፣ የመፈራረስን ያነገበ ነውና እንዴት ልናስቆመው እንደምንችል መዘጋጀትና የራሳችንን አስተዋጽዎ ማበርከት ይኖርብናል፡፡

ያለምንም ፍራቻ ኢትዮጵያዊነትን አጀንዳችን አድርገን «አንድ ኢትዮጵያ! አንድ ሕዝብ!» ብለን አማራጭ መሆን ይኖርብናል፡፡ ለዚህ ደግሞ ጊዜ የሰጣቸው ፖለቲከኞች የእኛን መዳከም በመጠቀም ሆይ ሆይታው በዛ እንጂ አብዛኛው

ሕዝብ እንደ ጥንቱ አንድነቱንና ፍቅሩን ጠብቆ በዘርና በሃይማኖት ሳይከፋፈል መኖርን መራጭ ነውና በአጭር ጊዜ ወደ ተቀባይነት እንደምንገሰግሥ መገመት ይኖርብናል።

በብሔራዊ ስሜት የተገነባ ኢትዮጵያዊነትን ከፍ አድርገን የሁሉም ዜጋ መብትና ነፃነት የተከበረባትንና እውን የሚሆንባትን ሀገር ለመመሥረት በወሬ ሳይሆን በተግባር የሚንቀሳቀስ “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!” ሕዝባዊ ንቅናቄ እውን ለማድረግ ይህ ሠነድ ተዘጋጅቷል።

25 ዓመት ሙሉ ሌሎችን ስናይ እርስ በርስ ከመባላት የዘለለ ያስመዘገቡት ዕድገት የለም ማለት ይቻላል። ስለ ሀገራቸው ያላቸውን ዓላማ፣ ተልዕኮና ራዕይ እንኳ በአግባቡ አውቀው የሚንቀሳቀሱ እጅግ ጥቂቶች ወይም የሉም ቢባል ያስኬዳል። በመሆኑም ለሀገራችንና ለሕዝባችን ከላይ የቀረቡትን ዋና ዋና ነጥቦች መነሻ በማድረግ ይህ ሠነድ በአንባቢያን ዳብሮና ተሻሽሎ የንቅናቄው ማታገያ ይሆናል። “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!” ሕዝባዊ ንቅናቄ እንደአማራጭ የራሱ የፖለቲካ ፕሮግራም ያለውና በድርጅታዊ ውስጠ ደንብ ተሞርኩዞ በሀገራችን ጉዳይ ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ ለመሆን ዝግጅቱን አጠናቋል።

በዚህም ምክንያት ይህ ሠነድ በዚህ ጉዳይ ሊተባበሩ፣ ሀሳብ ሊያካፍሉ፣ ፍላጎቱ እንኳ ባይኖራቸው በሥነ ሥርዓት ሀሳባቸውን ይገልፃሉ ለተባሉ የተወሰኑ ወገኖች ተልኳል። ያለንን ልምድና ተመክሮ ዛሬ ለሀገራችንና ለሕዝባችን ማካፈል ይገባናል ነው የዚህ ሠነድ ጥሪ። እኛ የገንዘብም የጥቅምም ሰዎች አይደለንም። የሥልጣንም ፍላጎት የለንም። ግና ይመራሉ፣ ትግሉን ከግብ ያደርሳሉ እያልን የምንመለከታቸው ቢያንስ በዚህ 25 ዓመታት የት ደረሱ? እንደውም በሚያሳዝን መልኩ በየጊዜው ከአንዱ ወደ ሌላው ሲገለባበጡ፣ ህዝቡንና መታገል የሚፈልገውን ኃይል ግራ እያጋቡ እንመለከታለን። አሁን አሁን ደግሞ ዳግማዊ የዘር ፖለቲካ በሌላ መልኩ በቀጣይነት ሊመጣ እየተንደረደረ እናያለን። ይህን ሁሉ አሁን ቁጭ ብለን የምንመለከት መሆን አግባብ አይደለም። በሌሎች አመራርነት ለሀገራችንና ለሕዝባችን ገንዘባችንን፣ ጊዜያችንን፣ ዕውቀታችንን፣ ሕይወታችንን ጭምር ሰጥተን ሞክረናል ግና የአመራር ችግር ትግሉን የትም አላደረሰውምና ዛሬ አለንበት ደርሰናል። አሁን እኛም ያለንን ተመክሮ እራሳችንን ዝቅ ካላደረግን በቀር ልንጠቀምበት መቻል ብቻ ሳይሆን ለሌላም ለሀገርና ለሕዝብም እንተርፋለንና እራሳችን አመራር በመስጠት ለሀገርና ለሕዝብ መድረስ ስለሚኖርብን ይህ ሰነድ ሊደርሳችሁ ችሏል። ሁኔታውን ከተለያየ አቅጣጫ ተመልክታችሁና ገምግማችሁ ዛሬ ነገ ሳትሉና ሳታመነቱ ተባባሪነታችሁ ይጠበቃል። ያላችሁን አስተያየት በመላክ ተባበሩን።

## 21.0. ዋናው ትኩረታችን

1. የሚመሰረተው ሕዝባዊ ንቅናቄ የፖለቲካ ድርጅት ለጊዜው በአብዛኛው በህቡዕ ይንቀሳቀሳል። ከዚህ በፊት በተለያየ መድረክ የማይታወቁ ለአንዳንድ ጉዳይ ለጋዜጣዊ መግለጫና ለመሳሰሉት ካስፈለገ ብቻ እንዲታወቁ ይደረጋል
2. ትግሉ ሀገር ቤት እዚያው ሀገራችን ምድር ላይ መሆን ስለሚገባው። ሙሉ በሙሉ እንቅስቃሴው ሀገር ቤት ይሆናል።
3. በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ዋናውን ሚና የሚጫወቱት ወጣቶችና ተማሪዎች በመሆናቸው አዲሱ ትውልድን ያቀፈ ብቻ ሳይሆን ዋናውን ሚና እነሱ ይጫወቱ ዘንድ ማመቻቸት።
4. በኢትዮጵያ ታሪክ ከጥንት ጀምሮ የሴቶች ሚና ቀላል አይደለምና የሴቶች እህቶቻችን ተሳትፎ ጉልህ ይሆን ዘንድ ትኩረት መስጠት
5. ትግላችን ሀገር የማዳን ብሔራዊ ጥሪንም ያካትታልና አዛውንት እናት አባቶችን ጨምሮ ታዳጊ ሕፃናት የእንቅስቃሴው ዋና አካል ይሆኑ ዘንድ ጥረት ማድረግ
6. በመላ ሀገራችን እና በውጭው ዓለም ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችን፣ የብዙሃን ድርጅቶችንና ሌሎች አካላትን ያካተተ የጋራ ኅብረት ለመመስረት ጥረት ይደረግ ዘንድ ማመቻቸት
7. ለዘመናት ተከባብሮና ተፋቅሮ ያለውን የእስልምና እና የክርስቲያን እምነት ተከታይ ወገኖቻችን ለሀገራቸው አንድነት ሲሉ እምነታዊ ግዴታ አለባቸውና የዚህ ጥሪ ተካፋይና ቀደምት ተዋናይ ይሆኑ ዘንድ ማመቻቸት

8. በወያኔ አገዛዝ የተበተነው የኢትዮጵያ ሠራዊት አባላትና የአሁኑም በወያኔ አገዛዝ ሥር ያሉ የሠራዊቱ ኃይሎች ለሀገራችንና ለሕዝባችን አንድነትና ደህንነት አደራ አለባችሁና የአምባገነን ገዥዎች መሣሪያ ከመሆን በመቆጠብ ከሕዝብና ሀገር ጋር ሠልፋቸውን ያደርጉ ዘንድ ይህ ሠነድ ጥሪ ያደርጋል
9. የተለያዩ የሙያ ማህበራት (የሠራተኛ፣ የመምህራን፣ የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የደራሲያን፣ የጋዜጠኞች ወዘተ) የዚህ እንቅስቃሴ ደጋፊና ተሳታፊ ይሆኑ ዘንድ መሥራት
10. በውጭው ዓለም ያሉ ወገኖቻችን በተቻለ አቅም ድጋፋቸውን በመስጠት በመተባበር ይሳተፉ ዘንድ የሚቻለውን ማድረግ
11. በመላዋ ኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ (በተለይ በኦሮሞና አማራ ክልል) ማጠናከርና ትግሉ አንድ ወጥ አመራር ያገኝ ዘንድ መሥራት
12. ዘረኛው ወያኔ በስማቸው የሚነግድባቸው የትግራይ ልጆችና ፖለቲካ ድርጅቶች ከሀገርና ሕዝብ ጎን ሠልፋቸውን አድርገው የህወሀት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ያበቃ ዘንድ ሀገራዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ መጣር
13. የ"አንድ ኢትዮጵያን አንድ ሕዝብ" ሕዝባዊ ንቅናቄ የሚያንፀባርቅ ድረ ገጽ፣ በኢትዮጵያ አንድነት ላይና በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገ የድርጅቱ ልሳን፣ የ"አንድ ኢትዮጵያን አንድ ሕዝብ" ሕዝባዊ ንቅናቄ የፖለቲካ ፕሮግራም በቅርቡ ይፋ ይደረጋል

## 22.0. አዲሱን ትውልድና ወጣቶችን ያቀፈ

ትውልድ ይሄዳል ትውልድ ይተካል። በሀገራችን በየወቅቱ ብቅ ያሉ ትውልዶች ከነበረው ወቅታዊ እንቅስቃሴ አኳያ ሚታወቁበት ስያሜ አላቸው። ዘመነ መሳፍንት፣ ጀግኖች አባቶቻችን፣ አርበኞች፣ ያ ትውልድ  እያልን ስንጠራ የትኛውን ዘመን እንደምናነሳ ይገመታል። መጪው ትውልድ ከቀደምት ትውልዶች ትምህርት በመቅሰም የራሱን ዘመን ታሪክ ይሠራል። ከእሱ በፊትና ቀደምት ትውልዶች ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ያበረከቱትን አስተዋጽዎ በመገምገም፣ ታሪካቸውን በማጥናት ለአለበትና ለመጪው ትውልድ ይሆናል የሚለውን በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውና በማህበራዊ ሕይወት በማቀድ ለመተግበር ይጥራል። በዚህ ሁሉ ጉዞ መልካም አስተዳደር ባለመኖሩ ግጭቶች ከአገዛዝና ብሎም ከሥርዓቱ ጋር ይሆናል። እነኚህ ግጭቶች መፍትሄ ሳያስገኙ ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው እየተሸጋገሩ ታሪክ ሁነው ይቀራሉ።

በሀገራችን የጀግኖች አባቶቻችንና አርበርኞች ዘመን በሕዝቡ ላይ ያለው ጭቆናና መብት ጥማት እንደተጠበቀ የሀገራችንን አንድነትና ሉዓላዊነት በማስጠበቅ የከፈሉት መስዋዕትነት እስከዛሬም ታሪክ ሆኖ ትምህርት ይቀሰምበታል። የሀገሪቷ አንድነትም እንደተጠበቀ በነበረው አገዛዝና ሥርዓት መሻሻል ላይ እንቅስቃሴ ያደረጉ በጋራም ሆነ በተናጠል ያስመዘገቡት ተጋድሎ ዛሬም ከታሪክ ማኅደር እየተለቀሙ ጥናት ይካሄድባቸዋል። የአሁኑም ትውልድ ቀጣይቷን ኢትዮጵያ እንዲመለከት ታሪካቸው የጀርባ አጥንት (Back ground) ይሆነዋል።

በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ዋናውና ጎልቶ የሚነሳው የየካቲቱ ያ ትውልድ ተጋድሎ ነው። የኢትዮጵያ የካቲት አብዮት መክሸፍና ያስከተለው ዕልቂት ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለዓለም አስተማሪ ታሪክ ነው። ከአምባገነን አገዛዞችና ኢዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ጋር እንቅስቃሴ የሚያደርጉ የፖለቲካ ድርጅቶች ከ1960ዎቹና 70ዎቹ የያ ትውልድ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ በርካታ ትምህርት ይቀስማሉ። ያን የመሰለ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እንዴት ሊኮላሽ፣ ሊመታ ቻለ? ደካማ ጐኑ የቱ ላይ ነው? ጠንካራውስ? አስተማሪነቱ ከሀገራችንም አልፎ ለሌሎች ነፃነትና ዴሞክራሲያ ለተጠሙ ዓለማት ጭምር ነው።

ያ ትውልድ በዘመኑ በመጠኑም ቢሆን ከቀደምት አባቶቹና እናቶቹ የሀገር ፍቅር ስሜት የወረሰውን ታሪክ ከዘመናዊ ሥልጣኔ ጋር ለማዛመድ በመሞከር ለሀገራችን ይበጃታል ያሉትን ተግባራዊ ለማድረግ ጥረዋል። በቀደምት ትውልድና በራሱ ትውልድ ጊዜ የነበረው ትስሥር በመጠኑም ቢሆን ቀጣይነት ነበረው። በተማሪው እንቅስቃሴ ብልጭታውን ያሳየው የነ መላኩ በያን ሀገር ፍቅር እንቅስቃሴ ወደ እነ ፕሮፌሰር እዝቂያስ ተሸጋግሮ እነ ጥላሁን ግዛው ተረከበውት፣ በፖለቲካ ፓርቲና በድርጅት መልክ እነ መኢሶን፣ ኢሕአፓ፣ ኦነግ፣ ሻቢያ፣ ጀብሃ፣ ህወሀት፣ ሶማሌ አቦ ወዘተ ተግባራዊ አድርገውት በሀገራችን ትልቅ ምዕራፍ የያዘ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በየአቅጣጫው የመጋጋሉን ውጤት አስመዝግቧል። እንደታሪክነቱ ልክ ሆነም አልሆነ

የተሳካላቸው እንዳሉ ሁሉ የከሸፈባቸውም አሉ። ሻቢያና ህወሀት በለስ ሲቀናቸው፣ መኢሶን፣ ኢሕአፓ፣ ኦነግ፣ የመሳሰሉት በሀገር ደረጃ ትግላቸው ተኮላሽቶ ለቀጣይ ትውልድ ታሪክ ትቶ አልፏል።

በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ የትውልድ ትስስርን መበጠስ ብቻ አይደለም ያኮላሸ አዝዝ በዋናነት መጠቀስ የሚገባው የደርግ ወታደራዊ አገዛዝ ነው። ደርግ ከነበረው ወታደራዊ ባህሪ በመነሳት ማንኛውንም ተቃዋሚ ግለሰብና ቡድን ለመደምሰስ ባደረገው የ17 ዓመት የጦርነትና የመደምሰስ ፖሊሲ ኢትዮጵያ እስከዛሬም ልታገግም ያልቻለችበትን ሊተካ የማይችል አንድ ትውልድ እምሽክ አድርጎ ቀበረ። በተለይ በሀገር ፍቅሩና ለዓላማውና ለሕዝቡ በአለው ታማኝነትና በቆራጥነት ሊታመን የማይችል ትውልድ ደርግ በሕዝብና ሀገር ስም አጠፋ። በአጋጣሚ ከዚህ አስከፊ ዘመን የግድያ ዘመቻ የተረፈውም ትውልድ የቁም ሞት እንደሚባለው ተሸማቆ መደበቂያውን ዋሻ ይፈልግ ተገደደ። ቤተ ክርስቲያን/እምነት ፣ ስደት፣ መጠጥ፣ ግለኝነት፣ ፍርሃት፣ ዝምታ… እንደየስሜቱ ተቀራመቱት። በያ ትውልድና በቀጣይ ትውልድ የነበረው ሰንሰለት "ዕድሜ" ለደርግ ተበጠሰ።

በያ ትውልድ ላይ በደረሰው ጭካኔያዊ ወታደራዊ በትርና ጭፍጨፋ የተነሳ ለቀጣይ ትውልድ ታሪክን ከመዘከር ከማስተላለፍ ይልቅ ዝምታ አየሩን ሞላው። ስለዚያ ትውልድ ለሕዝብ መንግሥትና ለዴሞክራሲያ መብት የተደረገው ትግል የገንጣይ፣ ያስገንጣይ፣ የአሸባሪ (አናርኪስት)፣ የቅጥረኛ ወዘተ ትግል ተደርጐ በሰፊው ይሰበክ ጀመር። ገዳዮች ጥፋታቸውን ለመሸፈን "እርስ በርሱ የተላለቀ ትውልድ" የሚል ተደጋጋሚ በትር ወረወሩበት። ለዚህ ዓይነቱ ስያሜ ደግሞ በትግሉ አብረው የነበሩ ሁሉ ተባባሪ ሆነዋል። የያ ትውልድን ቀጣይ ትውልድ ሀገሩን እንዲወድ ለሕዝብና ለሰው ልጆች መብት እንዲሞግት ከነበርንበትና ካሳለፍነው የትግል ተመክሮ በመነሳት ለማስተማር ከመጣር ይልቅ "ፖለቲካና ኤሌክትሪክ በሩቁ" በሚል ደካማ ስሜት አርፈው እንዲቀመጡ፣ ከትምህርት ውሏቸው ሌላ ጉዳይ ላይ እንዳይገቡ እያስጠነቀቅንና እያስፈራራን ያሳደግናቸው ልጆች ውጤቶች ናቸው ዛሬ ያሉት። እኛ ፈሪ አድርገን አሳድገናቸው "ምነው ወኔ ያጣ ትውልድ ሆነ" እንላለን? እኛ እራስህን አውጣ እያልን ሰብከናቸው ምነው "እራስ ወዳድ ትውልድ" እንላቸዋለን? እኛ እየተሰደድን ምነው "ባዕድ አፍቃሪ ትውልድ" እንላቸዋለን? ወዘተ ዛሬ ላለው ትውልድ ወደድንም ጠላን፣ አውቀንም ሆነ ሳናውቅ የነበረው የሀገር ፍቅርና የትግል ስሜት ይቀዘቅዝ ዘንድ አስተዋጽዎ አድርገናል።

ደርግ ያሸማቀቃቸውን ሕፃናት ወያኔ ተረክቦ ከኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜት ይልቅ ዘረኝነት የበላይነት እንዲይዝ ተጠቅሞበታል። ደርግ የቀበረውን ሀገርና ሕዝብ ወዳድ ትውልድ ተከታዮች ወያኔ ገንዘብና እራስ ወዳድ ሊያደርግ ጥሮበታል። ደርግ የቀጠቀጠውንና ያኮላሸውን ትውልድ ተገን በማድረግ ወያኔ እንደልቡ እንዲጨፍር አረድቶታል። ይህ ሁሉ የታሪክ ብረዛ፣ ትውልድ የማቀጨጭ፣ ኢትዮጵያን የማዳከም ዘመቻ በተለያየ አቅጣጫ እየተካሄደ በሌላ በኩል የሚያስደስተው አሁንም ኢትዮጵያ ብርቅዬ ልጆች እንዳሏት ነው። የወያኔን አፈና እና እመቃ እየበጠሱ ለእሥርና ለሞት የተዳረጉ በርካታ የአሁኑ ዘመን ትውልዶች ለዚህ ምስክር ናቸው።

በመሆኑም ኢትዮጵያን እንደሀገር የሚያስቀጥላት ብቻ አይደለም የሰውን ልጅ የሰብአዊና የዜግነት መብት የሚያስጠብቁ ወጣቶች ለነገዋ ሀገራችን ተስፋዎች ናቸውና ቀጣይ የኢትዮጵያ ዕድል ሙሉ በሙሉ በወጣቱና በአሁኑ ትውልድ ትከሻ ላይ መሆኑን ማስተማር ሳይሆን እንዲገነዘቡና እንዲረከቡ በሩን መክፈት ይኖርብናል። እኛ የያ ትውልድ አካሎች ለሀገራችንና ለሕዝባችን በወጣትነታችን ዘመን ባይሳካልንም ከአምባገነን አገዛዝ ጋር አኩሪ ተጋድሎ አድርገናል። ዛሬም በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶ፣ በብዙኃን ድርጅቶች እንዲሁም በተለያዩ ሰብአዊ መብት ተቋሞች፣ የእምነት ተቋማት ዘንድ ከፍተኛውን አስተዋጽዎ እያደረግን መገኘታችን ለሀገራችንና ለሕዝባችን ያለንን ከበሬታ ያለመዘንጋታችን ውጤት ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያና ሕዝባችን ያሉበት አጣብቂኝ መንገድ ከሚያሳስቡት ወገኖች አንዱ የያ ትውልድ ፈርጦች ነን። ለሀገራችን ኢትዮጵያ በቀጣይነት ለትውልድ የሚተላለፍ ሥርዓት ተመስርቶ ሀገራችን አንድነት እንደተጠበቀ የህዝባችን መከራ የሚያበቃበትና ሙሉ መብታቸውን የሚጎናጸፉበት ሥርዓት ለመዘርጋት የምናደርገው ጥረት እንደተጠበቀ ትግሉንና ቀጣይ አመራርን አዲሱ ትውልድ ይረከብ፣ ያካሂድ ዘንድ መሥራት ይጠበቅብናል። የእኛ የትግል ተመክሮ ለአሁኑ ትውልድ ትምህርት የሚሆነው ሀገርና ሕዝቡን ሲመለከት ብቻ ሳይሆን ከፍ ብሎ ሲመራ ነውና ብቃት ያለው አመራር ሰጪ ኃይል ከወጣቶችና ጎልማሶች ያቆጠቁጥ፣ ይረከቡ ዘንድ ዕድሉን ማመቻቸት ይጠበቅብናል። ጊዜው የነሱ ነውና። የዚህ ድርጅት ዋና ተግባር የዛሬውና የነገው ሀገር ተረካቢ ወጣቶችና ሴቶች እህቶቻችን ላይ ትኩረት ያደረገ ሊሆን ይገባዋል። የያ ትውልድ አካላትን ያሳተፈ የወጣቶች አመራር ይጎለብት ዘንድ ከተሠራ ለነገይቷ ኢትዮጵያ ተስፋ ሰጪ ኃይል ተገነባ፣ ተደራጀ ማለት

ነው። በእኛ እና በአሁኑ ትውልድ መካከል የላላውን የታሪክ ክፍተት ልናጠብ የምንችልበት ጊዜ በጣም ውሱን ስለሆነ የነገይቷን ኢትዮጵያ ተስፋ ለማየት ከተፈለገ ወጣቶች ላይ መረባረቡ አጠያያቂ ሊሆን አይገባውም። የነገዋ ኢትዮጵያ ለነሱ የአመራር ጊዜ ለእኛ እፎይ ብለን የምናርፍባት መሬታችን ናትና። አሸልበን የምናርፍባት መሬት ለማግኘት ግና ሀገራችንን ከበታኞችና ከፋፋዮች መንጭቀን ለልጆቿ ስናደርግ ነው። እፍረተቢሱ ወያኔ እንኳን በሕይወት ያሉትን ሙታንንም እያፈናቀለ ነውና።

## 23.0. ለትውልድ ዘላቂነት ያለው ሕገ መንግሥት

የሰው ልጅ መብት በሕግ ሽፋን በፍፁም መደርመስና፣ መደፈር አይገባውም። ሰው በሰውነቱ ከተፈጥሮ ያገኘው ፀጋ መከበር ይኖርበታል። ሰብዓዊ መብት ማንኛውም ዜጋ መብትና ነፃነቱን የማይነጠቅ አሳልፎም የማይሰጥ መሆኑን በማንኛውም መንገድ በአካሉና በሕይወቱ ጉዳት፣ ቁስልና ጠባሳ የሚያደርስ ጥሰት እንዳይገጥመው፣ በስልጣን ያሉ የሥርዓቱ አገልጋዮች በሕግ ሽፋን ደህንነቱን ነፃነቱንና መብቱን እንዳይጋፉት መጠበቅ ይኖርበታል።

**ፍትሐ ነገሥት** በ1240 አካባቢ በግብጽ አገር ቅብጡ አቡል ፋዳዒል እብን አል-አሣል በአረብኛ የጻፉት ሕገ መንግሥት ነው። እብን አል-አሣል ሕጎቹን የወሰዱት በከፊል ከሃዋርያት ጽህፈቶችና በከፊል ደግሞ ከድሮ ቢዛንታይን ነገስታት ሕጎች ነበር።

አንደኛው ክፍል ስለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ሲሆን የቤተክርስቲያን ስነሥርዓትና ምስጢራትን ይገልጻል። የተለቀሙት መጻሕፍት መጽሐፍ ቅዱስ የአበው ለምሳሌ የአቡሊድስና የባስሌዮስ ጽሕፈቶችና በኒቂያ ጉባኤ ወይም አንጥያኮስ ጉባኤ የተወሰኑ ሥርዓቶች ናቸው።

ሁለተኛው ክፍል ተራ ምዕመናንን (ካህን ያልሆኑ) የሚነካ ጉዳይ ያስረዳል፣ ይህም ማለት የቤተሠብ፣ የእዳና የብሔራዊ አስተዳደር የመሳሰሉትን ሕግጋት ያጠቃልላል። ይህ ክፍል ደግሞ እላይ ከተጠቀሱት ምንጮች ቢለቀምም ሌሎቹ በብዛት የተጠቀሙት መጻሕፍት «4 የነገስታት ቀኖና» የተባሉት ናቸው። አንዳንድ ሊቃውንት እነዚህን መጻሕፍት በአርእስት አሳውቀዋል:-

1. «ፕሮቀይሮስ ኖሞስ» - በ866 ዓ.ም. አካባቢ በባይዛንታይን ንጉሥ ባሲሌዮስ መቄዶናዊ የተዋጀ ሕግ መጽሐፍ
2. በ472 ዓ.ም. ያሕል በግሪክ የተጻፈ «የሶርያ-ሮማውያን ሕግ መጽሐፍ» (አረብኛ ትርጉም)
3. «ኤክሎጋ» - በ718 ዓ.ም. በባይዛንታይን ንጉሥ ሌዮ ኢሳውራዊ እና በልጁ የተዋጀ ሌላ ሕግ መጽሐፍ (አረብኛ ትርጉም)
4. «የብሉይ ኪዳን ደንቦች» - ስሙ ባልታወቀ ክሪስቲያን የተጻፈ የሕገ ኦሪት መግለጫና ትርጓሜ

ናቸው።

ከነዚህ መሃል ሦስቱ ምንጮች የባይዛንስ ንጉስ የዩስጢኒያኖስ ሕገ መንግሥት ጽኑ ተጽኖ ስላላቸው የእብን-አሣል ሥራ በተለይ እንደ ሮማ ሕጎች ይመስላል። መጀመርያ «የቀኖና ክምችት» ተብሎ ዛሬ የአረብኛ እትም «የእብን አል-አሣል ቀኖና» ይባላል። ሲጽፉት ለቅብጦች ጥቅም እንዲሆን አስበው እነሱም ትልቅ ሥልጣን እንዳለው ሰነድ አከበሩት።

መጽሐፉ በግዕዝ ተተርጉሞ ወደ ኢትዮጵያ የገባበት ወቅት በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን በ1450 ዓ.ም. አከባቢ እንደነበር የሚል ታሪካዊ መዝገብ አለ። ቢሆንም መጀመርያ እንደ ሕገ መንግሥት መጠቀሙን የተመዘገበው በዓፄ ሠርፀ ድንግል ዘመን (ከ1555 ዓ.ም. ጀምሮ) ነው።

የግዕዝ ትርጉም በጴጥሮስ አብዳ ሳዒድ ስም ተደርጎ ለአረብኛው ሁልጊዜ ትክክለኛ አልነበረም፣ በአንዳንድም ስፍራ ቋንቋው ለአስተርጓሚው ሲያስቸግራቸው በፍጹም የተለየ ንባብ ይሰጣል። መጀመርያው ክፍል (ቤተክርስቲያን የሚነካ) ከዚህ በፊት ሲኖዶስ ተብሎ በኢትዮጵያ እንደታወቀ ሊቃውንት ገልጸዋል። ሁለተኛው ክፍል ብቻ ለኢትዮጵያ አዲስ ስለሆነ ስሙ «ፍትሐ ነገስት» የተወሰደው ከዚሁ ክፍል ነበር ይላሉ።

ፍትሐ ነገስት እስከ 1923 ዓ.ም. የብሄሩን ዋና ሕግ ሆኖ ቆየ። ያንጊዜ ዘመናዊ ሕገ መንግሥት በአጼ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የታወጀ ቢሆንም ቀድሞ በ1922 ዓ.ም. በፍትሐ ነገሥት መሠረት አዲስ የወንጀል ሕግ ተሰጠ። ደግሞ በ1914 ዓ.ም. ንጉሥ ሳይሆኑ እንደራሴ በሆኑበት ወቅት በፍትሐ ነገስት የተገኙት ጨካኝ ቅጣቶች ሁሉ (ለምሳሌ ለስርቆት እጅ መቆረጥ) ፈጽሞ እንዲተዉ አስደርገው ነበር።

ኢትዮጵያ መጀመርያ ዘመናዊ ሕገ መንግሥት የተቀበለችው በ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምኅረት በቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ የታወጀ ሲሆን የሕግ አማካሪ ቤቶች በሁለት ያስከፈለ ነው። ይህ የመንግሥታቸው ዋና መሠረት ሆኖ እስከ ፲፱፻፵፰ ዓ.ም. ካገለገለ በኋላ በዚያ ዓመት የንጉሡ ነገሥቱ ኢዮቤልዩ የዘውድ በዓል በሚከበረበት ዕለት ተሻሽሎ በወጣ ሕገ መንግሥት ሕዝቦች በመንግሥት ሥራ የሚጫወቱት ሚና እንደገና ተስፋፋ። ይህ የአገሪቱ ሕገ መንግሥት አብዮት እስከፈነዳበት ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ድረስ በአገልግሎት ላይ ከዋለ በኋላ በደርግ ውሳኔ፣ ሕገ መንግሥታዊ ባልሆነ ሂደት ተሰረዘ።

የዓፄ ኃይለ ሥላሴ ሕገ መንግሥት ሲጀምርም በንጉሡ በጎ ፈቃድ ለሕዝብ የተሰጠ፣ የተቸረ ገፀ በረከት መሆኑን ሲያስገነዝብ "...ሰጥተናችኋል..." በሚል ያስቀምጠዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልመከረበት፣ ያልተወያየበት፣ ድምፁን ሰጥቶ ያጸደቀው ሕገ መንግሥት አልነበረም። በጥቅሉ የንጉሡ ሕገ መንግሥት በትረ ሥልጣናቸውን ለማስጠበቅ የተደነገገ በአጭሩ "ንጉሥ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ" እንደተባለው የመንግሥታቸው መጠበቂያ ሕገ ንጉሥ ነበር ሊባል ይችላል።

በቀጣይነት በሀገርና በሕዝብ ስም ለ17 ዓመታት የጨፈረው የደርግ አምባገነናዊ አገዛዝ ስሙን ከአስተባባሪ ደርግነት እስከ ኢሠፓ እየቀያየረ ለመግዛት በሕዝብ ስም የራሱን ሕገ መንግሥት አጸድቋል። ለደርግም ሆነ ለወያኔ ሕገ መንግሥት ማለት ሥልጣናቸው ነበርም ነውምና ሕገ መንግስቱ የሕዝቡን ነፃነትና መብት ሳይሆን ያገዛዞቹን ደህንነት አስጠባቂና ተከላካይ ነበር፤ ነውም። ወያኔ ሕገ መንግስቱ ላይ "የብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከመገንጠል" ያላቸውን መብት በአንቀጽ 39 ቢጨምርበትም በይዘትም ሆነ በተግባር የደርግና የወያኔ ሕገ መንግሥት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸው። ደርግ በሀገር አንድነት ስም ሥልጣኑን ይከላከላል ወያኔ እኔ ከሌለሁ ሀገር የለችም በሚል ዘረኛ ፖሊሲ ስልጣኑን ይጠብቃል። ደርግ ማንኛውንም ተቃዋሚ በሕግ ሽፋን ሀገር ሊበትኑ፣ ገንጣይ፣ አስገንጣይ እያለ ጨርሷል ወያኔ አሸባሪ፣ ሰላምና መረጋጋት አደፍራሽ እያለ ፈጅቷል። ሁለቱም የተቃዋሚው ኃይል ሲበረታባቸው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እያወጡ ከሕግ በላይ በመሆን የሕዝብን መብት አፍነዋል፣ ደምስሠዋል።

ከነዚህ ሁለት አምባገነን አገዛዞች ቀጣዩ የሀገሪቷ ሕገ መንግሥት ለሀገርና ለትውልድ ዘለቄታ ይኖረው ዘንድ ከተፈለገ ሕገ መንግሥቱ በነፃ ውይይት በሕዝበ ውሳኔ መጽደቁ ብቻ ሳይሆን የሥርወ መንግሥቱ አወቃቀር ወሳኝነት ይኖረዋል። ሕዝብ ያፀደቀውን ሕገ መንግሥት መሳሪያውንና ጉልበቱን ተማምኖ መንግሥት ወይም አንድ የፖለቲካ ድርጅት የሚሽረው፣ የበላይ ሆኖ የሚቆጣጠረው ከሆነ ሕጉ ቢያምርም ተግባራዊ ሊሆን ግን አይችልም።

የወደፊቷ ኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት በሕግ አርቃቂው፣ ተርጓሚውና አስፈፃሚው መካከል የማያወላዳ የተጠያቂነት ሠንሰለት ሊኖር ይገባዋል። ሕገ መንግስቱ መንግሥትንና የመንግሥት አካላትንና አውታሮችን ግልጽነትና ተጠያቂነት ላይ ሊያስቀምጥ ካስፈለገ አስፈላጊ ተቋሞች በቅድሚያ መገንባት፣ መዳበር ይኖርባቸዋል። ለዚህም ነው ሕገ መንግስቱ ላይ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሕዝባዊ ማህበራት፣ የእምነት ተቋሞች፣ የሰብዓዊ መብት ተቋማት፣ የሕግ ባለሙያዎች ወዘተ በሚገባ መክረውበትና ሕዝብም ነፃ ውይይት አድርጎበት ተግባር ላይ ሲውል እንኳ ለተወሰነ ጊዜ የሀገሪቷ የጋራ አመራር ሕገ መንግሥቱ መሠረታዊ ጉዳዮችን እስኪያሟላ መከታተልና ማስፈጸም የሚያስፈልገው። የሀገሪቷ ሕገ መንግሥት መንግሥትንም የሚገዛ መሆን ይኖርበታል።

የመጪዋ ኢትዮጵያ ሕገ መንግስት በማዕከላዊው መንግሥትና በክፍለሀገራት/ጠቅላይ ግዛት አስተዳደሮች መካከል ያለውን የሥልጣን ዕርከን ግልጽ በሆነና በማያሻማ አኳኃን ማስቀመጥ ይኖርበታል። የማዕከላዊ መንግሥት የሥልጥን ገደብ እምን ደረጃ ድረስ መሆኑ መቀመጥ ብቻ ሳይሆን ተፈፃሚነት ይኖረው ዘንድ አስፈፃሚ ተቋማት ግንባታ አስፈላጊነታቸው ከጥያቄ መግባት የለበትም። በሌላም በኩል የተዋረድ አስተዳደሮች ሥልጣንና ኃላፊነት በአግባቡ ተግባራዊ መሆኑን ነፃ ተቋማት ይከታተሉት ዘንድ በሰው ኃይል ሥልጠናና በባለሙያዎች እገዛ መዳበር ይኖርበታል።

በሀገራችን የሕግ የበላይነት ይሰፍን ዘንድ ካስፈለገ ሕገ መንግሥቱ በሕዝብ ውሳኔ መጽደቁ ብቻውን መልስ አይሆንም። መንግሥት ሕገ መንግስቱን እንዳሻው እንዳይጠቀምበትና የሕገ መንግሥቱ ተግባራዊነት አስፈላጊ መሆንኑን በመገንዘብ ከምርጫ ፖለቲካ በቅድመ ሁኔታ የሀገሪቷ የጋራ አመራር አስፈላጊ መሠረታዊ አውታሮችንና ተቋማት በራሳቸው እስኪተማመኑ ድረስ የጋራ አመራራቸው አስፈላጊ ይሆናል።

## 24.0. ዴሞክራሲያዊ መብት

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት የዴሞክራሲ መብቱን ተነፍጐ ኖሯል። በዓፄ ኃይለሥላሴ አገዛዝ ንጉሱንም ሆነ ባላባትና መኳንንቱን በአጠቃላይ ሥርዓታቸውን መቃወምም ሆነ ከንጉሡ በጎ ፈቃድ ውጭ ማንኛውንም እንቅስቃሴ ማድረግ ወንጀል ነበር።

ደርግ ሥልጣን እንደያዘ ማንኛውንም የዴሞክራሲያዊ መብት "ኢትዮጵያ ትቅደምን እስካልተቃወመ" በሚል መብትን አፍኖና ረግጦ ገዛ። ወያኔ ሥልጣን ሲይዝ ጀምሮ "ሰላምና መረጋጋት ለማደፍረስ" በሚልና በቀጣይነትም "አሸባሪ" በማለት የሕዝብን መብት አፍኖ እያሰቃየ ይገኛል።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የዜግነት መብት የለም። የሰው ልጅ መብት የለም። ገዥዎች የሥልጣን ዕድሜአቸውን ለማራዘም በጉልበትና በኃይል ለመጠቀም ስለሚገደዱ ማንኛውንም የሰው ልጆች መብት በማፈን ተንገዳግደው እስኪወደቁ ድረስ በሀገርና ሕዝብ ላይ ጉዳት ያደርሳሉ። የሀገርንና የሕዝብን ንብረት እንዳሻቸው ለመዝረፍ የሰው ልጅን መብት ይነፍጋሉ። ይህ የአምባገነኖች ባህሪ ነው።

አዲሲቷ ኢትዮጵያ የሰው ልጆች ሰብአዊ መብት የተከበረባት ሁሉንም ዜጐቿን በእኩል ዓይን የምታይ ዘለቄታ ያለው አስተዳደር እንዲኖራት ካስፈለግ ማንም ሊገድበው የማይገባው የዴሞክራሲ መብት ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል። ይህ የሰው ልጆች መብት የኢትዮጵያ ሕዝብ ገና አልሰለጠነም፣ አልነቃም፣ ዴሞክራሲ ባህል አለመደም ወዘተ እየተባለ መሸራረፍና መገደብ ከተጀመረ አገዛዙ ያለጥርጥር ወደ አምባገነንነት እየተሸጋገረ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በሕዝብ የበላይነት ያመነ አገዛዝ የሕዝብን ያልተገደበ መብት ማክበር ይኖርበታል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በባህሉ፣ በሃይማኖቱ ጨዋ ሕዝብ መሆኑን እንኳን እራሳችን ባዕዳን መስከረውለታል። በኦሮሞ ገዳ፣ በሌላው በቤተሰብ ሸንጎ ባህላዊ ደንቦች እራሱን በራሱ ያስተዳደረ ኩሩ ሕዝብ ነበር። በተለያየ ዘሩና ቋንቋው ተከባብሮ፣ በተለያየ ሃይማኖቱ ተዋዶና ተጋብቶ፣ አንዱ ለአንዱ ተሳስቦ የኖረ ሕዝብ የጨዋነቱ ምስክር ነው። ይህን ባህሉንና ማንነቱን ያጠፉት በየጊዜው የሰፈሩበት አምባገነን ገዥዎች ናቸው። አዲሲቷ ኢትዮጵያ ከአምባገነን መንግሥት የተላቀቀች ትሁን ካልን "የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ ለሁሉም" ተግባራዊ መሆን ይገባዋል። ለሀገርና ለሕዝብ የቆመ መንግሥትና አወቃቀር ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው፣ ሀገራችን ወደ ልማትና ዕድገት ጐዳና እንድትራመድ ካስፈለገ የሕዝባችን ያልተገደበ ዴሞክራሲያዊ መብት ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል። የሚካሄደውና የተካሄደውም ትግል ለዚህ ነውና የሀገር ሉዓላዊነትና የሕዝባችን አንድነት በጠበቀ መሠረት ላይ ሊገነባ የሚችለው ያልተገደበ የዜግነት መብት ሲከበር ነው እንላለን።

ሀገራችን በርካታ ጐሳዎችን፣ ብሔር/ብሔረሰቦችን ያቀፈች፣ የተለያዩ እምነቶች ያሉባት እንደመሆኗ የዴሞክራሲ መብቶች በግልም በቡድንም ነፃ መሆን አለባቸው። ይህንን መነሻ ከአደረግን ዘንዳ፡-

- የሕዝብ ዴሞክራሲያ መብት ማለትም የፅሁፍ፣ የንግግር፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊሰልፍ ማድረግ፣ የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ፣ ከቦታ ቦታ መዘዋወር፣ የመሥራት፣ የመማር፣ የመታከም፣ ከሀገር መውጣት፣ የመደራጀት (በፓርቲ፣ በብዙኃን ድርጅት፣ በማህበር)፣ የመምረጥና የመመረጥ፣ የተመረጡ ወኪሎችን መሻር፣ ወዘተ መብትን ማስከበር።
- በኪነጥበብ ዘርፍ ከሴንሰር ነፃ የዘፈን፣ የትያትር፣ ፊልም የመሥራት መብትን ተግባራዊ ማድረግ
- ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አለፍርድ ቤት ትዕዛዝ አለመታሰር፣ ቤት አይፈተሽም፣ ኢሰብአዊ ቅጣቶች መከልከል
- በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር የብሔር/ብሔረሰቦችን መብት ማስከበር ማለትም ቋንቋቸውን መጠቀም/ማዳበር፣ ባህላቸውን መጠበቅ ማዳበር፣
- የሴቶች እህቶቻችንን የፆታ አድልዎ ማስወገድ፣ ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ መብታቸውን ማወቅ
- የዜጎችን የሃይማኖት ነፃነት መጠበቅ፣ የሃይማኖት አድልዎና ልዩነት ማስወገድ፣ ባህላዊ የእምነት ቀኖችን ማክበር
- ወዘተ

## 25.0. ምን ዓይነት ሥርዓትና ምጣኔ ሀብት

ኢትዮጵያ ሀገራችን ከ1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ አብዮት በፊት በጭሰኛና በባላባት አገዛዝ የተመሠረተ ሥርዓት ይዛ ቆይታለች። ይህ የፊውዳል ሥርዓት በአርሶ አደሩ ላይ ያስከተለው ልቅያጣ ብዝበዛ በተጨማሪ የሀገሪቷን የልማት ዕድገት ወደ ኋላ የጎተተ ነበርና ለአንዴም ለመጨረሻ ጊዜ በየካቲት 1966 ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ሊወገድ በቅቷል።

በቀጣይነት ሥልጣን ላይ የተቆናጠጠው ደርግ በመሬት ለአራሹ አዋጅ የባላባቱንና የጭሰኛውን ግንኙነት በታጥሶ "ሥር ነቀል ለውጥ" ቢካሄድም ሀገሪቷ አሁንም ወደ ልማትና ዕድገት ጐዳና ተጉዛ የልጆቿን ዴሞክራሲያዊ መብት የምታስከብር ልትሆን አልቻለችም። አምባገነኑ ደርግ ብሄራዊ ስሜትን ሽፋን አድርጎ ከሀገሪቷ ይልቅ የሥልጣን እርከኑን ማጠናከር ላይ ትኩረት ሰጠ። ለዚህም የሕዝብን የዜግነትና ሰብዓዊ መብት አፈነ። መብትና ነፃነት በታፈነበት ኅብረተሰብ ምንጊዜም ልማትና ዕድገት አይኖርምና ደርግ በሶሻሊዝም ሥርዓት ግንባታ ጀምሮ ቅይጥ ኢኮኖሚ ቢልም ከወሬና አዋጅ ያልዘለለ ሥርዓት ነበር። ደርግ የሕዝብን የዜግነት መብት በማፈኑ ማንኛውንም ጉዳይ በጦርነትና በኃይል ለመፍታት ከነበረው ትልሙ 17 ዓመት አገዛዝ ዘመኑ በጦረኝነትና በአፈና ላይ የተመሰረተ ነበር። ሂደቱም የመጨረሻ መጨረሻ በደርግ ላይ የሕዝቡን ጥላቻ ምርኩዝ በማድረግ የታጠቁትና ከደርግ ሲፋለሙ ከነበሩት ሻቢያና ወያኔ ደርግን አሸቀንጥረው ሻቢያ ኤርትራን ወያኔ ቀሪዋን ኢትዮጵያ ሊቆጣጠሩ በቅተዋል።

ህወሀት በኢሕአዴግ ስም ሀርገሪቷን በተቆጣጠረበት 25 ዓመት ሂደቱ እንደ ደርግ ዘመን ትኩረቱ ሥልጣኑ ላይ ነበር፤ ነውም። ለዚህም ይዞ የተነሳውን የዘረኝነት ፖሊሲ ተግባራዊ በማድረግ የሕዝባችንን ኢትዮጵያዊ ስሜት ለመሸርሸር ሀገሪቷን በዘር ፖለቲካ ሸነሸናት። ለዚህም ስኬቱ የኃይልና የአፈና ፖለቲካ በመጠቀሙ ወያኔም እንደደርግ እስከዛሬ ምላሽ ያልተገኘለትን የሕዝቡን ዴሞክራሲያዊ መብት በማፈን እየገዛ ይገኛል።

የወያኔ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በዜግነት መብት ላይ የተገነባ ባለመሆኑ ውጤቱ ከዕድገት ይልቅ ረሃብ፣ ከጥጋብ ይልቅ የጉርሻ ዘመን፣ ከሀገር ልማት ይልቅ የጥቂት ምርጦች ዝርፊያ፣ ዘመነ ሙስና...የተንሰራፋባት ሀገር ሆናለች። ዛሬ የሀገራችን የኢኮኖሚ ሥርዓት በጣት የሚቆጠሩ የመንግሥቱ አካላትና የውጭ ካፒታሊስቶች ወረራ ላይ የተገነባ የዝርፊያ ፖለቲካ ሀገራችንን ተቆጣጥሯታል።

ሀገራችን ዛሬ የውጭ ሀገር ምርቶች ማራገፊያ ሆናለች። ሀገሬው ወደ ዳር እየተገፋ የልመናና የስቃይ ሕይወት ባለቤት ሲሆን በአንጻሩ ለም የሆኑ መሬቶች ለውጭ ባለ ሀብቶች እየተቸበቸበ የዝርፊያና የሙስና ብልጽግና መረቡን እዘረጋበት ዘመን ደርሰናል። የሀርገራችን የተፈጥሮ ሀብት ተንከባካቢ እያጣና ወደ በረሃነት እየተቀየረ መምጣቱን በርካታ ጥናቶች ምሥክር ናቸው። እጅግ ሊታመን በማይገባው ፍጥነት ዛሬ ኢትዮጵያ በተለያዩ የውጭ ባለሀብቶችና ሀገራት ተወራለች። በሀገራችን ኢትዮጵያ ያመረቱትን ምርትና ያገኙትን ሽቀጥ እንኳ በራሳቸው በኩባንያው ስም ለተለያዩ ዓለማት ያከፋፍላሉ። ዛሬ የኢትዮጵያ ቡና፣ ጤፍ፣ ሰሊጥ፣ ቆዳ እና በርካታ የምርት ውጤቶች የባለቤትነት መብት ለሌሎች ኩባንያዎች ተቸብቸዋል። ወያኔ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንዳትቀጥል ካለው ፍላጎት አንዱ የሀገሪቷን ብሔራዊ ከበርቴዎች በማዳከም ሀገራችን የውጭ ሸቀጦች ጥገኛ ማድረግ ነውና ነገ ለምናስባት ኢትዮጵያ በትዕግስትና በበሳል አመራር ሊፈቱ የሚገባቸውን በርካታ ችግሮች ወያኔና ሻቢያ "የመቶ ዓመት የቤት ሥራ" እንዳሉት እየሰጡንና እየተዉልን ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያን የሕዝቧ ለማድረግ ከወያኔ ውድቀት በኋላ እንኳ የምንታገላቸው በርካታ ሀገራት አሉ። ለ50ና 100 ዓመታት ሰፋፊ የሀገራችንን ቦታዎች የተቆጣጠሩ፣ በርካታ የሀገሪቷ የተፈጥሮ ሀብቶች ማዕድናት፣ በነዳጅና ጋዝ ጨምሮ ለተለያዩ ኩባንያዎች ተቸብቸዋል። ይህ በኢኮኖሚው መስክ ሀገሪቷን የባዕዳን ጥገኛ እንድትሆን የተሸረበው ሴራ በባህል፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በመከላከያው ዘርፍ ወያኔ በሀገራችን ኢትዮጵያ ስም የወታተባቸውና የገባቸው መረን የወጡ ውሎች እራሱን የቻለ ሌላ ችግር መሆኑን ማጤን ይገባናል። በአጠቃላይ ወያኔ የሀገራችንን ኢኮኖሚ ያሽመደመደና ሕዝባችን የየዕለት ምግቡን እንኳ ተመጋቢ ያላደረገ፣ ሕፃናትን በምግብ እየቀጣ ከትምህርት ገበታቸው ያሰናከለ፣ ዛሬ ፖለቲካው ብቻ ሳይሆን ድህነት ለስደትና ለሽያጭ የዳረጋቸው ወገኖቻችን ሁሉ የወያኔ መርዘኛ አገዛዝ ውጤቶች ናቸው። ትግላችን ይህን ዘረኛና በሀገርና ሕዝብ የመጣ አገዛዝ ማስወገድ ብቻ ሳይሆን ትግሉ ከወያኔ ውድቀት በኋላ ከፊታችን የተደቀነው የቤት ሥራ መመለስ ነው። ለዚህም ነው በቀጣይነት ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍልና የፖለቲካ ድርጅቶችን ያካተተ የጋራ ምክክርና

አመራር ረዘም ላለ ዓመታት አስፈላጊነቱን ያሰመርንበት። በዚህ ጉዳይ በተለይ የሀገራችን ምሁራን እጅግ ከፍተኛ ሚና ስላላቸው ነው ከወዲሁ ልዩነታቸውን መሠረት ያደረገ አንድነታቸውን ያጠነከሩ ዘንድ መመካከርና መወያየት ይጀመር ዘንድ የምሁራን ሸንጎ አስፈላጊነቱን ያነሳነው።

ለመንደርደሪያ ያህል ይህን ካልን ቀጣይ የሀገሪቷ ኢኮኖሚ በምን ላይ የተመሠረተ መሆን ይገባዋል የሚለው መታየት ይገባዋል። በሀገራችን ኢትዮጵያ የሰው ልጅ ተመገቦ የሚኖርባት፣ ረሀብን የምንቋቋምበት፣ የልማት አውታሮች ተዘርግተው ሀገራችን ወደ ዕድገት ጎዳና እንድታመራ ካስፈለገ የመጀመሪያው ጉዞ ያልተሸራረፈ ዴሞክራሲያዊ መብት ማወቅ ብቻ ሳይሆን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው። የዜግነት መብትን ለመሸራረፍና ለማፈን የሚነሳ አገዛዝ ሁልጊዜ ከሀገርና ሕዝብ ይልቅ ሥልጣኑን ነውና የሚጠብቀው። ይህ ስልጣን ጥበቃ ደግሞ የተለያዩ ተቋማትን የሥራ ድርሻ በመፃረር የቡድን አሠራርን ያስከትላል። እየቀጠለም ወደ ጉቦኝነትና የነበረው ሙስና እየቀጠለ ሀገርን ከማልማት ይልቅ በለውጥ ስም የግል ዝርፊያው እንዲቀጥል በር ይከፍታል። በመሆኑም በሀገርና በሕዝብ የበላይነት የተማመነ ሥርዓት ለመገንባት ከተፈለገ የሕዝብ ነፃ መብትን ማክበር ሲቻል የዚያ ጊዜ ተጠያቂነትም ይኖራል፣ በሕግ የመገዛት ባህል ተግባራዊ ይሆናልና ሁሉም በጋራ ሀገሬ ብሎ ይተጋል። መብቱን የተነፈገ ግለሰብም ሆነ ቡድን አሁንም ፊቱ ወደ ትግል ነውና በቃ ብለን መነሳት ያለብን የዜግነት መብት መታፈንን ነው። ይህ ሲሆን መንገዶች ሁሉ ወደ ዕድገት ያመራሉ። ደርግም ሆነ ወያኔ አፋኝና አምባገነን ገዥዎች በመሆናቸው ነው ለሀገራችን ዘላቂ መፍትሄ ሊያስመዘግቡ ያልቻሉት፣ የማይችሉትም። የእነዚህ ሁለት አገዛዞች ውድቀት ምን እንደነበር ለመማር ዝግጁ ከሆንን ለትውልድ የሚተላለፍ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ሥርዓት መሠረት በመጣል ኢትዮጵያን እናድሳታለን፣ እንገነባታለን።

ኢትዮጵያ ሀገራችን የበርካታ ብሔር/ብሔረሰቦች ሀገር መሆኗን ከግምት በማስገባት፣ የሕዝቡን የተለያየ አኗኗር፣ ባህልና ቋንቋ በመመልከት፣ የክርስትናና እስልምና ሃይማኖት በሀገራችን ያላቸውን ሚና ከግምት ከማስገባት በተጨማሪ የወያኔ ሥርዓት ያጋጋለውን የዘረኝነት አባዜ በማጤንና ኢትዮጵያ የሁሉም ልጆቿ የጋራ ሀገር ትሆን ዘንድ አመቺውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት መቅረጽ አስፈላጊ ነው። ከቀደምት እንቅስቃሴዎች ልንማር የሚገባን አንዱ አብይ ጉዳይ የውጭውን/የባዕዳንን አሠራር እንዳለ ገልብጦ ከእኛ ባህልና አኗኗር የራቀውንና የተቃረነውን ሥርዓት ለማጣጣም ስንሞክር አልሆን ሲል ኃይል ስንጠቀም ሀገር ተጐድታለች። ሶሻሊዝምን እንዳለ ከመገልበጥ ሊጠቅመንና ሊጐዳን የሚችለውን ባለመመርመራችን ከጥንት ባህላችንና ሃይማኖታችን ጋር አላተመነዋል። የኢትዮጵያውያን አኗኗር እንዴት ነው? ወዘተ የሚሉትን በማጥናት ቀጣይ የፖለቲካ ሥርዓት ምን መልክ ይኑረው መመከር ይኖርበታል።

ሊበራል ዴሞክራሲ አንዱ ሲል ሌላው አይ ሶሻል ዴሞክራሲ ነው አስፈላጊው እያልን ልዩነታችንን ለማስፋትና የውጭውን እንዳለ ለመገልበጥ ከመሞከር የሁለቱንም ጠንካራና ደካማ ጎኖች ገምግሞ ለእኛ ኢትዮጵያውያን አመቺውን ለመቅረጽ ብቃቱ ሊኖረን ይገባል። ለትውልድ የሚሆን ሥርዓት መቅረጽ ሲባል ወደፊት በምርጫ ፖለቲካ ማንኛውም ፓርቲ ሥልጣን ቢይዝ አንዱ የሰራውን እያፈረሰ እንዳይሄድ መሠረታዊ ዕቅዶች ሁሌም መጠበቅ ይኖርባቸው ዘንድ የጋራ ምክር ቤቱ ኃላፊነት ይኖርበታል። ዛሬ የተዘረጋውን ነገ የሚመጣው አፍርሶ ወይም ትቶ የራሴን አደርጋለሁ ዓይነት ጉዞ ከተቀጠለ ምንም ዓይነት ለውጥም ሆነ ዕድገት ልናስመዘግብ አንችልም። የሕዝባችንን የዜግነት መብት በተግባር የተረጎመ፣ ተጠያቂነትን ማዕከሉ ያደረገ ለትውልድ ዘለቄታነት ያለው ሕገ መንግሰት እንደሚያስፈልግ ሁሉ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ሥርዓታችንም ዘላቂነት ያለው አመሰራረትና አወቃቀር ያስፈልገዋል። ይህ ሲሆን በአመራር ላይ የወጣ ፓርቲ እስከ ምርጫ ዘመኑ ያለውን እያዳበረና አዲስ የራሱን እየጨመረ ይቀጥላል፤ ተተኪውም እንዲሁ።

ለሀገራችን ኢትዮጵያ ሊበራል ወይስ ሶሻል ዴሞክራሲ ሥርዓት ነው የሚያስፈልገው ከማለታችን በፊት እስቲ በአጭሩ የሁለቱን ሥርዓቶች አንድነትና ልዩነት ከታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ እንቃኝ።

| ሶሻል ዴሞክራሲ | ሊበራል ዴሞክራሲ |
|---|---|
| መድበለ ፓርቲ ሥርዓት ይቀበላል | መድበለ ፓርቲ ሥርዓት ይቀበላል |
| አሸናፊና ተሸናፊ የሌለበት የተመጣጠነ ውክልና (Proportional Representative Democracy) | ተሸናፊው ውህዳን ለአሸናፊው ይገዛል (Majority Rule) |
| ፍትህና እኩልነት በሕገ መንግሥቱ መስፈሩን ይደግፋል፣ ለተግባራዊነቱም ይጥራል | ፍትህና እኩልነት በሕገ መንግሥቱ መስፈሩን ይደግፋል |
| ለቡድን መብት ትኩረት ይሰጣል | ለግለሰብ መብት ትኩረት ይሰጣል |
| ነፃ ገበያንና የግል ሀብት ይቀበላል | ነፃ ገበያንና የግል ሀብት ይቀበላል |
| የመንግሥት ካፒታሊዝምን ይቃወማል | የመንግሥት ካፒታሊዝምን ይቃወማል |
| በተወሰነ ደረጃ መንግሥት በነፃው ገበያ ላይ የሚያደርገውን ቁጥጥር ይደግፋል | በነፃ ገበያ እንቅስቃሴ የመንግሥትን ጣልቃ ገብነት ይቃወማል |
| ብሔራዊ ጥቅም ያላቸውን ሕዝባዊ ተቋማት እንደ ፖሊስ፣ መብራት ኃይል፣ መንገድና መገናኛ፣ የዱር አራዊት ክልል፣ የማዕድን ሀብት በመንግሥት ይዞታ ሥር ቢሆን ይደግፋል | |
| የሶሻል አገልግሎት ለምሳሌ ህክምናና ትምህርት በነፃ ይሰጣሉ። በአጠቃላይ የመንግሥት ድጐማን ለችግረኞች ይቀበላል | በየአስባቡ ለሶሻል አገልግሎት የሚመደበውን በጀት ያሳንሳሉ/ይቀንሳሉ፣ በተቃራኒው ለከበርቴዎችና ለባለሀብቶች አዲስ የሥራ ፈጠራን ለማዳበር በሚል የገንዘብ ድጎማ ያደርጋሉ |
| በአጠቃላይ ለፍትህና ለእኩልነት ትኩረት በመስጠት ለተጎዱና ለተበደሉ የህብረተሰብ ክፍሎች የቆመ ነው። | |

ከላይ የተጠቀሱትን ዋና ዋና አንድነቶችና ልዩነቶች በመውሰድ በተጨማሪ የሌሎች ሀገሮችን ተመክሮ ከሀገራችን ባህልና አኗኗር ጋር በማጣጣም አመቺውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት መቅረጽ ይኖርብናል። ለምሳሌ መብትን በተመለከተ ለሀገራችን የግለሰብ ነፃነት ነው ወይስ የቡድን አስፈላጊው ብሎ ክርክር ከመክፈት ሁለቱንም ያጣመረ ቢሆን ምን ጉዳት አለው? የሚለውን መመልከት ጠቀሜታ አለው። የግለሰብ ነፃነት ስንል ማንም ሰው በሀገሩ የዜግነት መብቱን ሊነፈግ አይገባውምና ጥያቄ የሌለው አማራጭ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ሀገራችን የበርካታ ብሔር/ብሔረሰቦች ሀገር መሆኗን እስከአወቅንና በተለይ ወያኔ የዘራውን የዘር ፖለቲካ በሂደት ለማለዘብና ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት እንዲገነባ ካስፈለገ የነኚህን ብሔር/ብሔረሰቦች መብት ማክበር ማለት የቡድን መብት ውስጥ ይካተታልና ከሀገራችን አንፃር አስፈላጊ ነው። የሴቶች፣ የወጣቶች፣ የታዳጊ ሕፃናት፣ የተማሪዎች፣ የመምራን፣ የሠራተኛው ወዘተ የመደራጀትም ሆነ ሌላ መብት የቡድንን መብት ይመለከታል።

በኢኮኖሚው መስክ ስንሄድ በሀገራችን ልቅያጣውን ብዝበዛ፣ ሙስናና ዝርፊያ በአጠቃላይ በሀገር ሀብትና ገንዘብ አለአግባብ ብልጽግና ሊገታ የሚችለው መንግሥት መለስተኛ ቁጥጥርና ክትትል ሲያደርግ ነውና የመንግሥት ጣልቃ ገብነት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ጉዳዩ የሚበላሸው መንግሥት እራሱን ጉልበተኛና ዘራፊ ማድረግ ሲጀምር ነው፡ ይህንን ለመግታት ደግሞ ቀደም ሲል እንዳስቀመጥነው ተጠያቂነትንና ግልጽነትን መርሆው ያደረገ አሰራርና አወቃቀር ሲኖር ነው።

በጥቅሉ የሀገሪቷን አንድነትና የሕዝቡን እኩልነት በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመጠበቅ ብቻ ሳይሆን ቀጣይ ትውልድም የሚጀመረውን አቅጣጫ ይዞ ይጓዝ ዘንድ የተለያዩ ብሔር/ብሔረሰብ ሀገር መሆኗን፣ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪነታችንን ተቀብለን፣ የተለያዩ ሃይማኖቶችን አቅፋ የያዘች ሀገር መሆኗን ከግምት በማስገባት የኢትዮጵያን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ብሎም ሶሻል ሥርዓት መቀየስ ይገባናል ብለን እናምናለን።

### 26.0. የምሁሩ ሚና

## 26.1. ምሁር ስንል

በተለያዩ ወቅቶች እና ቦታዎች መታዘብ እንደምንችለው ‹ምሁር› የሚለው ስያሜ በሀገራችን ተለጥጦ ፊደል የቆጠረን ሁሉ አካትቶ ይዟል፡፡ ኮሌጅ የበጠሰ ሰውማ የሊቀ-ሊቃውንትነት ካባን ይደርባል፡፡ እዚህ ላይ በመጀመሪያ የምናገኘው ችግር ምሁርን (Intellectual) ከባለሙያ (Professional) መደባለቅን ነው፡፡ ባለሙያ የሚለውን ማዕረግ ከሳቴ ብርሃን የአማረኛ መዝገበ ቃላት «ሥራን ዐዋቂ መኾን፣ ልዩ ልዩ የትምህርት ሥራን፣ የእጅ ሥራ ጥበብን፣ ማወቅ ወይንም የአንድ ቀን ሥራን ሠርቶ ደመወዝን ማግኘት።» በማለት የተወሰነ ስራን መስራት እና ምንዳን እንደ ምላሽ ማግኘት (Quid Pro Quo) በማለት ያቀርበዋል፡፡ ምሁር የሚለውን ስያሜ ደግሞ ‹ከፍተኛ የሆነ የማሰብና የመመራመር ችሎታ ያለው፤ ሊቅ የተማረ በኹሉ ምሉ ትምህርት ያለው ሰው› ብሎ ሰፊ ደርዝ በማስያዝ ምሁርነት ከፍ ያለ ጉዳይ እንደሆነ ያሰረዳል፡፡

## 26.2. የእኛዎቹ ወዴት ናቸው?

ምሁር መባል እንዲሁ ቀላል ነገር እንዳልሆነ ከትርጉሞቹ ለማየት ችለናል፡፡ ምሁርነትም መለያ ባህሪውን በራሱ አሳቢ መሆን በማድረግ፤ ምጡቅነትን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው ማለት ነው፡፡

እናም በሀገራችን በኢትዮጵያ እነዚህን አሳብያን ከወዴት አሉ? ብለን እንጠይቃለን፡፡ በመጀመሪያ የተማረ ሰው ሁሉ ምሁር እንዳልሆነ ለማሳየት ሞክረናል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያስመርቋቸውም ተማሪዎች ባለሙያዎች እንጅ ምሁራን እንዳልሆኑ ከትርጉሙ እና ማሟላት ካለባቸው መሰጠቶች አንፃር አይተናል፡፡

እናም ይሄ ኢትዮጵያዊ ምሁር ወዴት አለ? ፍትህ ተጓደለ የሚለው ሊቅ፣ መብት ይከበር ማለት የሚገደው ልበ ብርሃን፣ ደፋሩና ፅኑው ምሁር ኢትዮጵያ ውስጥ ወዴት ነው? (ዞን9 ድረ ገጽ)

## 26.3. ምሁር ማነው

የሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ አንድ ምሁር «ምሁር» የሚያስብሉ አሥር ነጥቦችን ያስቀምጣል፡፡ የተወሳሰቡ ችግሮችን የመተንተን አቅም ኖሮት መፍትሔ የሚያመጣ፣ ያልተሞከሩና ያልተጠየቁ ጉዳዮችን በማንሳት ከዚህ ቀደም ሲል ተንሰራፍቶ የቆየውን አስተሳሰብ የሚቀይር፣ ጠቃሚ ከማይመስሉ መረጃዎች ጠቃሚ ነጥቦችን በፍጥነት ለይቶ የሚያወጣ፣ በቡድን በመሥራት የሚያምን፣ በግሉም በሙሉ ድፍረት ኃላፊነትን የሚወጣ፣ ሌሎችን የማሳመን አቅም ያለው፣ መረጃዎችን ለአውዱ አመቺ በሚሆን ጽንሰ ሀሳብ ለውጦ ማስቀመጥ የሚችል፣ አንድን ሐሳብ አንስቶ ሲወያይ የሚተገበርበት ሁነታ ላይ የሚያነጣጥር፣ የተበታተኑ ሐሳቦችን ሰብስቦ ጭብጡን የሚያስረዳ፣ አንድን ጥቅል ሐሳብ በታትኖ ማስረዳት የሚችል፣ ችግሮችን ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ካለፈው ታሪክ ጋር አጣምሮ መፍታት የሚችል ምሁር ነው ይለናል።

በሌላ በኩል የተማረ ሰው ማለት ሰርትፍከት መያዝ ማለት አይደለም። ምሁር ማለት አንድን አስተሳሰብ አንብቦ እንደ ሃይመኖት ቀኖና እንደ ወረደ ማስተጋባትም አይደለም። ምሁርነት ማለት ለተወሳሰቡ ችግሮች መፍትሔ ማምጣት ነው። ላሉበት ነባራዊ ሁኔታ አመች የሚሆኑ ቀመሮችን መቀመር ነው። ምሁርነት ማለት ጠቃሚና ትክክለኛን ነገር መፈለግ ነው። አዕምሮን ማልማት ነው።

ይህን ያህል ለመንደርደሪያ ካልን በፖለቲካው መስክ ለሀገራችን ድምፃቸውን የሚያሰሙ፣ ብዕራቸውን ከወረቀት የሚያገናኙ ምሁራን ኃላፊነት ቀላል አይደለም። በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ምሁራን የመሰላቸውንና ያመኑበትን፣ ከሌላ ዓለም ተመክሮ በማጣቀስ፣ ከአነበቡት፣ ከሕይወት ውጣ ውረዳቸው በማያያዝ ስለ ትላንቷ፣ ዛሬይቱና መጪዋ ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ደረጃም ሆነ በአነስተኛ መጣጥፍ ደረጃ ወይም በተለያዩ መድረኮች ሀሳባቸውን ይሰነዝራሉ፣ ያስተምራሉ። እሰየው ያሰኛል።

የዛኑ ያህልም ከመጣው አምባገነን ገዥ ጋር እየተገለባበጡ የሕዝብንና የሀገርን መከራ የሚያራዝሙ ምሁራንም እንዳሉ መዘንጋት የለብንም። ለዚህም ነው ከሌሎች ለመለየት "ባንዳ ምሁራን"፣ "አድርባይ ምሁራን" የሚል ቅጥያ የሚሰጣቸው።

የሀገራችን ምሁራን ከወያኔ ያልወገኑት እንኳ ስለ ሀገራችን ያላቸው እይታ እጅጉን የተለያየ ነው። አንድ ዓይነት አመለካከት ያላቸውም ቢሆኑ የሚጓዙት በተናጠል ነው። የግላቸውን ወረወሩ በቃ። ይህ መቀየር ይኖርበታል። ስለ ኢትዮጵያና ሕዝባቸው የሚሞግቱ ምሁራን የራሳቸውን መወያያ መድረክ መፍጠር እንዳለባቸው ሊገነዘቡት ይገባል። ይህ ጠቀሜታው የጐላ ሲሆን ጠቀስ ለማድረግ፡-

- የሀገራችንን የወደፊት አቅጣጫ ለመቀየስ በቅድሚያ ያላቸውን የየግል አቋም በጋራ በመወያየት የጋራ መስማሚያ ላይ እንዲደርሱ ያደርጋቸዋል፣
- በሀገራችን ቅድመ ታሪክ ላይ ያለውን የተዛባ አመለካከት በመመርመርና ትክክለኛ መረጃዎችን የተመረኮዘ ትንታኔ መስጠት ያስችላቸዋል፣
- ኢትዮጵያ ሁሉንም ብሔር/ብሔረሰቦች በዴሞክራሲያዊ መንገድና በእኩልነት መርህ ይዛ አንድነቷንና የግዛት ሉዓላዊነቷ ይጠበቅ ዘንድ መደረግ ያለበትን ሠነድ ሊያዘጋጁ በር ይከፍታል፣
- የአዲሲቷን ኢትዮጵያ አቅጣጫ ጠቋሚዎች ይሆኑ ዘንድ ወያኔ ከተወገደ በኋላ ዳግም ኢትዮጵያ ውስጥ አምባገነን ሥርዓት እንዳይመሠረትና የህዝብንና የሕግ የበላይነት የሚሰፍንበትን የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ወገንተኝነት ሳይዙ ሊያረቁና ወደፊት ለሚመሠረተው የጋራ መንግሥት ቅድመ ዝግጅት ሊያደርጉ ያስችላቸዋል፣
- ለትውልድ ሚተላለፍና ዘለቄታዊ ሕገ መንግሥት ተግባራዊ ይሆን ዘንድ፣ በማንም ሥልጣን ላይ በተቀመጠ መንግሥት ሊጣስ፣ እንደተፈለገ ሊተረጎም የማይችል ይሆን ዘንድ የመንግሥት አወቃቀርን ጨምሮ አስፈላጊ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትና ተዛማጅነት ያላቸው የሕግ አውታሮች ምን መልክ እነደሚኖራቸው ሀሳብ ሊያቀርቡ ያመቻቸዋል፣
- ወያኔ በዘር የከፋፈላት ሀገራችን ከዘረኝነት ሃባዜ ተላቃ ሁሉንም ጐሳዎች ሙብት ባስከበረ መልኩ እንዴት ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት መገንባት ይቻላል የሚለውን በጋራ መንደርደሪያ ሊያቀርቡ ያስችላቸዋል፣
- ወደፊት የሀገሪቷ የፖለቲካ ሥርዓት (ካፒታሊዝም፣ ሶሻሊዝም፣ ሊበራል ዴሞክራት፣ ሶሻል ዴሞክራት ወዘተ) የውጭውን ሙሉ በሙሉ ከመኮረጅ ከሀገራችን ባህልና ዕምነት አኳያ ምን መሆን እንዳለበት ፈጠራ የተሞላበት የራሳችንን አካሄድ ሊያስቀምጡ ያስችላቸዋል፣
- በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ያለውን አለመግባባት በተለይ በደርግ አገዛዝ ዘመን በደረሰው የአንድ ትውልድ ጭፍጨፋ ጥሎ ያለፈውን ቁርሾና ቂም በቀል እንዴት ማስታረቅ ይቻላል የሚለውን ግንዛቤ ሊያስጨብጡ ያስችላቸዋል፣
- ኢትዮጵያ ወደፊት የኤርትራን መገንጠልና ሀገርነቷን ከተቀበለች ኤርትራ ያለ አግባብ ስለተቸራት የአሰብ ወደብ በምን መልኩ ማስመለስ ይቻላል የሚለውን ሊመክሩበት ያስችላቸዋል፣
- የወደፊቷ ኢትዮጵያ አሁን ያለችበት የዘርና ብሔር/ብሔረሰብን ሹክቻና አንዱ ከሌላው ማበላለጥ በተለይ የወያኔ ዘረኝነት ፖሊሲ ተውግዶ ሁሉም ሀገሬ ብሎ ትኩረቱ የጋራ ዕድገትና ልማት ላይ በማድረግ ሀገሩን በምርምርና በጥናት ወደ ከፍተኛ የዕድገት ጎዳና ለማድረስ የሚያስችለውን አቅጣጫ ሊመክሩበት ያስችላቸዋል፣ ወዘተ.

በጥቅሉ የሀገራችን ምሁራን ኢትዮጵያችንና ሕዝባችን በትንሹ ለአለፉት 50 ዓመታት ከገቡበት ብልሹ የመከራ ሕይወት ተላቀው ለአንዴም ለመጨረሻ ጊዜ ሙብትና ነፃነት የሰፈነባት በልጆቿ ለልጆቿ የሆነች ኢትዮጵያ ትመሠረት ዘንድ ኃላፊነት አለባቸውና በሀገር ቤትም በውጭው ዓለም ያሉትን አካቶ ማንንም ሳያገል የኢትዮጵያ ምሁራን ሸንጎ ይመሠረት ዘንድ ይህ ሠነድ ለምሁራን ያለውን ጥሪ ያቀርባል።

የኢትዮጵያ ምሁራን በስደትም በሀገር ቤትም ያሉ እርስበርስ ያለባቸውን መናናቅና ሹኩቻ፣ ቂም በቀል አስወግደው ስለሀገራችንና ህዝባችን ያላቸውን የአመለካከት ልዩነት እንደያዙ ወደ አንድ ጠረጴዛ በመምጣት ለሌሎች አርአያ መሆን ይጠበቅባቸዋ። የሀሳብ ልዩነት ሁልጊዜም አለ። ልዩነቱን ለመከፋፈል ሳይሆን ለጥንካሬ ልንጠቀምበት ይገባል። ከሀሳብ

ፍጭትና ከልዩነት አንድነት ይወለዳል። ለዚህ ያላቸውን ብቃት በማሳየት ለሀገራችንና ለሕዝባችን ትውልድ የሚወርሰው ሠነድ ሊያዘጋጁ የሚችሉት በአንድ የውይይት ገበታ ቀርበው ሲቋደሱ ነውና ለዚህ ዝግጁ መሆን ይጠበቅባቸዋ። እናንተ ይህን ስታደርጉ ሌሎችንም ትስባላችሁ፣ የፖለቲካ ድርጅቶችን ታቀራርባላችሁ፣ ኢትዮጵያችን የተለያዩ ዘሮች እናት መሆኗን ትቋጫላችሁ።

በመጨረሻም "አንድ ሕዝብ፣ አንድ ሀገር" በሚል የተዘጋጀው ይህ የአንድነት ጥሪ ሠነድ የተሟላ እንዲሆን አስተያየታችሁንና ሀሳባችሁን በመሰንዘር ልታዳብሩት ጥሪ እናደርጋለን። ሠነዱም የሀገርና ሕዝብ ሀብት በመሆን በተለይ ለወጣቱ ትውልድ እንደ መመሪያ (ቀኖና) ያገለግል ዘንድ እገዛችሁ አስፈላጊ ነው። በዚህ ሠነድ መሠረት ለሚደረገው ሕዝባዊ እንቅስቃሴና ለሚመሠረተው ሕዝባዊ ድርጅት ድጋፍና እገዛ በማድረግ ሀገራዊ ሀላፊነታችሁን ትወጡ ዘንድ በአክብሮት ጥሪያችንን እናቀርባለን፣ ድምጻችንን እናሰማለን።

### 27.0. የትግል ስልት

በአንድ አምባገነንና ኢዴሞክራሲያዊ በሆነ አገዛዝ ሥር የሚማቅቁ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ነፃ ለማውጣት የሚታገል የፖለትካ ድርጅት በሚያካሂደው ሕዝባዊ ትግል ውስጥ ከሀገሪቷና ዓለም አቀፋዊ ተጨባጭ ሁኔታዎችን በመገምገም የሚያካሂደውን የትግል ስልት፣ ዘዴዎችና ትልሞቹን ይቀይሳል።

የትግል ስልት በጥቅሉ በሦስት አማራጭ መንገዶች ሊቀርብ ይችላል። እነሱም

1. ሰላማዊ የትግል ስልት
2. የትጥቅ ትግል ስልትና
3. ሰላማዊና የትጥቅ ትግልን ያጣመረ ሁለገብ የትግል ስልት ናቸው።

## 27.1. ሰላማዊ የትግል ስልት

በአንድ ሀገር ለሚደረግ የፍትህ፣ የዴሞክራሲ መብትና የሕዝብ መንግሥት ምሥረታ ትግል ማንኛውንም ዓይነት የጦር መሳሪያ ያላካተተ ትግል የሰላማዊ ትግል አካል ነው።

ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ሁኔታዎች እስከፈቀዱ ድረስ ሕዝቡን አደራጅቶ በሰላማዊ መንገድ ታግለው ለውጥ ማምጣቱን ይመርጣሉ። በሰላማዊ መንገድ የሚደረግ ትግል በሥልጣን ላይ ከአለው መንግሥትም ሆነ ለየት ያለ አመለካከት ካላቸው ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የሀገርንና የሕዝብን ችግር በውይይት፣ በክርክር ለመፍታት በር ይከፍታል። ሰላማዊ ትግል በሕዝብና በሀገር ንብረቶች እንዲሁም በሀገሪቱ ኢኮኖሚና የመገናኛ አውታሮች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን ይቀንሳል።

በሥልጣን ላይ ያለ መንግሥት በቅድሚያ በፖለቲካ ከተደራጀ ኃይል ትግል ሊገጥመው የሚችለው የሕዝብንና የሀገርን ጥያቄ በአግባቡ ባለመመለሱ ነው። የሰው ልጅ የዜግነት መብቱን ሲነፈግ፣ የዴሞክራሲ መብታቸውን ሲያጡ፣ ጭቆናና ቅጥያጣ ብዝበዛ ሲበዛባቸው፣ በህክምናው፣ በትምህርቱ አድሎው ሲበዛና በተጨማሪም በመንግሥት ሙስናና ዘረፋ ሀገሪቷ ዕድገትና ልማት እየላሸቀ ድህነት ተንሰራፍቶ ሕዝቡ የዕለት ተዕለት ኑሮውን መግፋት ሲያቅተው ጥያቄዎች ይነሳሉ። እነዚህን ጥያቄዎችና የሕዝብን ብሶት የሚያደምጡ ምሁራንና የሕዝብ አለኝታዎች ለሕዝብ መብትና ነፃነት መፍትሄው ትግል መሆኑን ሲያሰምሩበት ለትግሉ ቀና መስመር መያዝና ከግብ መድረስ ደግሞ የተደራጀ ኃይል አስፈላጊነቱን ስለሚገነዘቡ ሕዝብን አደራጅቶ ለመታገል የፖለቲካ ድርጅቶች የራሳቸውን ማታገያ ፕሮግራም ነድፈው ሕዝብን ያሰባስባሉ፣ ያደራጃሉ፣ ያታግላሉ።

አምባገነን ገዥዎች በአገዛዝ ዘመናቸው የሕዝብን ጥያቄ በማፈን የሥልጣን ዘመናቸው ይራዘም ዘንድ በሚወስዷቸው ጉልበት አዘል እርምጃዎች (ማሰር፣ ማፈን፣ ደብዛ ማጥፋት፣ ማስፈራራት፣ ማሰቃየት ብሎም መግደል) የሕዝብ ትግል ጥንካሬ እያገኘ ይመጣል። መንግሥት ይህንን በሰላማዊ መንገድ እየተንቀሳቀሰ ያለን ትግል በአቅሙም፣ በጥንካሬውም፣ በሕዝብ ድጋፉም እየጎለበተ መምጣቱን ሲገነዘብ ትግሉን ለማኮላሸትና ለማዳከም የአላቸውን ኃይል ሁሉ ይጠቀማሉ። አምባገነናዊ ባህሪያቸው ይበልጥ እየጎላ ይመጣል። ሰላማዊ የትግል ጎዳና ከአገዛዙ በኩል የሚደርስበትን ዕመቃና ዱላ መቋቋም ከሚያቅትበት ሁኔታ ሲደርስ ትግሉን ቢቀጥልም አደረጃጀቱን ግና ምስጢራዊ ለማድረግ ይገደዳሉ። ለዚህም ነው ትግሉ ሰላማዊ ቢሆንም አደረጃጀቱ ግና በዕቡህ ለመሆን የሚገደደው።

የሀገራች ኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለከት በአሁኑ ወቅት በሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ በሰላማዊ መንገድ ሊገረሰስ የሚችልበት አማራጭ አለ። አማራጩ ግና ትግሉ በሰላማዊ ቢሆንም መስዋዕትነትን እንደሚጠይቅ መገንዘብ ያስፈልጋል። ትግል ምን ጊዜም ቆራጥነትንና መስዋዕትነትን ይጠይቃል። ትግል ዓላማ ነው። ለአንድ ዓላማ የቆመ ታጋይ ደግሞ በቅድሚያ ለመስዋዕትነት የተዘጋጀ መሆን ይገባዋል። የጠላት ኃይል ባየለ ወቅት ሸብረክ የሚል ከሆነ ትግሉንም ይጎዳዋል፣ ያለበትንም የፖለቲካ ድርጅት ያሽመደምደዋል። ትግል መስዋዕትነትን ጠያቂ ነው ሲባል መታገል በራሱ ጊዜን፣ ገንዘብን፣ ችሎታን ወዘተ ስለሚጠይቅ፤ ለነዚህ ሁሉ መስዋዕትነት ይከፈላል። ትግሉ ሲጠነክርም መታሰርን፣ መደብደብን፣ እራስን መቀየርን ማለትም በጠላት እጅ ላለመውደቅ አካባቢን መቀየር፣ ሥራን/ትምህርትን መተው ሲከፋም መሰደድን ሊጠይቅ ይችላል። ትግል ነውና የገዥዎች አልሞት ባይ ተጋዳይነት ሲገፋም እስሩ ወደ ማሰቃየት ብሎም ወደ ግድያ ሊያመራ ይችላል። ግድያውም ከግለሰብ እስከ ጅምላ ሊዘልቅ ይችላል። በዚህ ሂደት መንግሥት ሥልጣኑን ለመጠበቅ ሲል በሕዝብና ሀገር ላይ ቅድሚያ ሽብር ይለቃል። የመንግሥት መገለጫዎች ይበራከታሉ፣ ያስፈራራል፣ በመንግስት በኩል ትግሉ ሌላ ስያሜ ይሰጠዋል (አሸባሪ፣ አናርኪስት፣ ሀገር በታኝ፣ ፀረ-ሕዝብ ወዘተ)፣ ሲከፋም አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማውጣት ትግሉን ለማኮላሸትና ለማፈን የአለውን አቅም ሁሉ ይጠቀማል። ይህ ሁሉ ሂደት ነው ሲጀመርም ትግሉ ሰላማዊ ትግል ቢሆንም ከፍተኛ መስዋዕትነትን እንደሚጠይቅ መታወቅ የሚኖርበት። ትግል የዓላማ ጽናት ነው።

ከኢትዮጵያ የትግል ተመክሮ በቅንነት እንማር ከተባለ የ1966 የካቲት ሕዝባዊ አብዮት የዘውድ አገዛዝን ለአንዴም ለመጨረሻ ጊዜ ቢገረስሠውም የሕዝብን ጥያቄ ሳይመልስ እስከዛሬ ታሪክ ሁኖ ይወሳል። የወታደራዊው ደርግ የትግሉን አቅጣጫ አስቶ ሥልጣኑን በመጨበጥ ከምርጥ መኮንንኖች ወደ አንድ ፈላጭ ቆራጭ አምባገነን ለመሸጋገር በርካታ የኃይልና የጉልበት እርምጃዎች በታጋይ ኃይሎችና ፖለቲካ ድርጅቶች ላይ ተወስደዋል። ደርግ ሥልጥን ከያዘ ጀምሮ በነበሩት ሁለት ዓመት ትግሉ ሙሉ በሙሉ ሰላማዊ ነበር። በዚህ የሁለት ዓመት ሂደት ደርግ የነበረውን ሕዝባዊ ትግል ለማፈንና ለማኮላሸት አስሸኳይ ኪዜ አዋጅ ከማወጅ ጀምሮ፣ በእስር፣ አፈናና በግድያ ሰላማዊውን መንገድ አቅጣጫውን አስቶታል። በተመሳሳይ መልኩ ወያኔ በተለይ በ1997 ዓ.ም. በቅንጅትና የኅብረት እንቅስቃሴ ዘመንና የመጨረሻው የምርጫ ውጤት መሸነፉን ላለመቀበል ባወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሁሉንም የወታደራዊ እና የደህንነት ዕዝ ሰንሰለት በአንድ ግለሰብ መለስ ዜናዊ እጅ በማስገባት የተወሰደው የእሥር፣ ድብደባ፣ ማሰቃየት፣ ግድያ ወዘተ ዘመቻ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። በተደረጉት ሰላማዊ ትግሎች የደርግም ሆነ የወያኔ ተዛማጅነት ሲኖራቸው በደርግ ዘመን የሰላማዊ ትግሉ በር ሲዘጋ ተቃዋሚው ኃይል መሳሪያ በማንሳቱና ትግሉ ይበልጥ ቀጣይነቱን በማስመዝገቡ የጅምላ ጭፍጨፋ በስያሜ እንደሚታወቀው “ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር” በመንግሥት ደረጃ በአዋጅና በዘመቻ ተካሂዶ ደርግ “የበላይነቱን” አስረግጦ ጥቂት ዓመታት ሊጓዝ ችሏል። አሁን ባለው አገዛዝ የ1997ቱ በመቶዎች የሚቆጠር የሕዝብ ልጆች ግድያና በወቅቱ የነበረው የቅንጅትና የኅብረት እንቅስቃሴ በወቅቱ የታወጀውን አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተጋፍጦ ለመጓዝ የተዘጋጁም አልነበርና ገደል አፋፍ ላይ የቆመው ወያኔ እንደገና በማንሰራራት ዛሬ አለንበት ላይ ደርሰናል። ወያኔ በ1997 ያሳየን የ196 ሰዎች ግድያና ሌላም የደርግ ቀይ ሽብር ትንሿ ምልክት ነበረች።

ከእነዚህ በባህሪያቸው አንድ ከሆኑ አገዛዞችና ከአለፈው ትግላችን የምንማረው ቢኖር በሰላም የሚደረጉ ትግሎች ሕይወት እስከመስጠት ድረስ መስዋዕትነትን ጠያቂዎች መሆናቸውን ነው። የፖለቲካ ትግል ተወደደም ተጠላ የሥልጣን ጥያቄ ነው። እንደሚወራው ሥልጣኑ ሲያዝም ተግባራዊ ከሆነ የሕዝብ ሥልጣን ጥያቄ ነው። ሕዝብ የጠየቀው ጥያቄና የዜግነት መብቱ ምላሽ የሚያገኘው በራሱ የሥልጣን የበላይነት ነውና። በመሆኑም እዚህ ሕዝባዊ ሥልጣን ላይ ለመድረስ የሚከፈሉ መስዋዕትነቶች ክቡርነታቸውን ተቀብሎ ሀገር ልትኖር፣ ሕዝብ የዴሞክራሲ መብቱን እንዲጎናጸፍ፣ ኢትዮጵያ ለልጆቿ

እንድትሆን እስከሆነ ትግሉ ለተነሳበት ዓላማ ግንባሩን የማያጥፍ ጠንካራ ታጋይ ኃይል ማዘጋጀት ዛሬም ይጠይቃል። ትግል ፈራ ተባ እያሉ የሚጓዙት አይደለም።

## 27.2. ሰላማዊ ትግልና የምርጫ ፖለቲካ

አሁን በአለው የወያኔ አገዛዝ በአጭሩ የምርጫ ፖለቲካ አይሠራም ማለት ይቻላል። እዚህም ድምዳሜ ላይ ሊደረስ የሚቻለው ወያኔ በምንም መንገድ ሥልጣን የመልቀቅ ፍላጎት ስለሌለው ነው። የመጣበትን ሕዝብ የመከፋፈልና ሀገር የመበታተን አጀንዳ እስከመጨረሻው ጠብታ ድረስ ለማስፈጸምና ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ኋላ አይልምና። እስካመቸው ድረስ እየተደረገ ያለው የሀገር ሀብት ዘረፋው፣ ሽያጩ፣ ሙስናው ወዘተ እየቀጠለ በሌላ በኩል ሕዝብን እያሰቃዩ በረሀብ አለንጋ እየገረፉ መጓዙ ለወያኔ ይዘው የመጡት ዓላማ ነውና የስኬታማነታቸው ውጤት ነው። ለእነሱ ሕዝብ ማለት እራሳቸው ናቸው። ለእነሱ ሀገር ማለት ስልጣናቸው ነው። ለእነሱ ሰንደቅ ዓላማ ማለት ጨርቅ ነው። ለእነሱ አክሱም ማለት ድንጋይ ነው። ለእነሱ ኢትዮጵያ ማለት ተረት ተረት ነች። ለእነሱ ዐድዋ ማለት ነፍጥ ነው። በእንቆቅልሽ ጥያቄ ያገኟትን ኢትዮጵያ ዛሬ "ሁሉ በእጇ ሁሉ በደጇ" ብለው እየበሏት፣ እየቦጠቦጧት ነውና እነሱ ዕቅዳቸውን ከግብ እያደረሱ ናቸውና በሰላማዊ ሆነ በትጥቅ ትግል ወደ ከርሰ መቃብራቸው የሚወረወሩት በኃይል ብቻ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

"የመንግሥት ዓይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ" ማለት ወያኔ ነውና የምርጫን ፖለቲካ መቶ በመቶ የበላ ደፋር ነው። ለወያኔ በዓለም አቀፉ መንደርና አይዞህ ባዮቹ ዴሞክራቲክ ባህሪ አለው ለማስባል ካልሆነ በቀር የምርጫ ፖለቲካ እንዳበቃለት እራሱ ወያኔ መልስ ሰጥቶበታልና የዚህ አጃቢነት ማብቃት እንዳለበት ታጋይ ኃይሎች መገንዘብ ይኖርባቸዋል።

ምን ዓይነት ሰላማዊ ትግል

ወያኔ አፋኝነቱን፣ ገዳይነቱን፣ ጨካኝነቱን ከአለፉት 25 ዓመታት አገዛዝ ዘመኑ ከተገነዘብን ዘንዳ የሰላማዊ ትግሉም ጥንቃቄ የተሞላበት ሊሆን ይገባዋል። በሚገኘው ማንኛውም ሕጋዊ ቀዳዳ መጠቀም አንዱ የሰላማዊ ትግል አካሄድ ቢሆንም ጠንካራ ፖለቲካ ድርጅት ግና አባላቱን ከወያኔ ጥቃት ለመከላከልና ትግሉንም በጥንቃቄ ለመምራት በተለይ በሀገር ውስጥ በህቡህ መንቀሳቀስ ይጠቅማል። እንቀቃሴን በህቡህ አድርጎ ዛሬ በአለው የዓለም የመገኛኛ ሶሻል መድረኮች (ኢንተርኔት፣ ድረ ገጽ፣ ምስለ ገጽ፣ ቲዊተር፣ ቫይበር ሌላም ሌላ) እና ሌሎችም በመጠቀም ሰፊ የግንኙነት ሰንሰለት መዘርጋት ይቻላል። በየክፍለሀገሩ፣ አውራጃ፣ ወረዳ፣ በከተሞች፣ ከፍተኛና ቀበሌ የተለያዩ ግንኙነቶችን በመፍጠር የተቀናበረ ሕዝባዊ ንቅናቄ ወያኔ ላይ ለማስነሳት መዘጋጀትን ይጠይቃል። ይህ ሕዝባዊ ንቅናቄ እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት (ጊዜ ቀድሞ በአሁኑ ወቅት በኦሮሞና አማራ ክልል አካባቢ ሕዝባዊ ህምቢተኝነት ከወያኔ ጋር እየተፋለመ ይገኛል) አስተማማኝ ቅድመ ሁኔታዎችን ያሟላ መሆን ይገባዋል። በወጣቶች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በሴቶች፣ በታክሲ ነጅዎች፣ በመምህራን፣ በተለያዩ ህዝባዊ ማህበራት (ዕድር፣ ዕቁብን ጨምሮ)፣ በሠራተኛው ዘንድ፣ ምሁራንን፣ እናቶችና አባቶችን፣ በወታደሩ ክፍል ጭምር የተጠናከረ መሠረትን ይዞ መንቀሳቀስ ይኖርበታል። ሕዝባዊ አመጹ ስኬታማ ይሆን ዘንድ ትምህርት በማቆም፣ የሥራ ማቆም አድማ በማድረግ፣ የኢኮኖሚ ማዕቀብ በማድረግ፣ በየአካባቢዎች ሕዝባዊ እምቢተኝነትን በማሰማት በተለይ በአዛውንቶችና በሕፃናት አጋዥነት የታጀበ መሆን ይገባዋል። ይህ መሣሪያ ያላነሳ ሕዝባዊ መነሳሳት በበሳል አመራር ከተቀነባበረ በቋፍ ያለውን ወያኔ ለመገርሰስ የሚያቅት አንዳችም ኃይል የለም። ዛሬ ወያኔ እስከታች ድረስ ወጣቶችንና ሕዝቡን አምስት ለአንድ ቢጠነፍርም ሁሉም ያለው ከሕዝብና ሀገር ጋር መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

ከትግል ተመክሮ እንደተማርነው ለሕዝብ የቆመ ፖለቲካ ድርጅት የትግል ስልቱ ሰላማዊም ሆነ የትጥቅ ዋናው ቁም ነገሩ የጥንካሬውን መሠረት በሕዝብ ዘንድ መገንባት ቢሆንም በአንድ በኩል በጥቃቅን ስህተት ትግሉ በአለው አገዛዝ እንዳይኮላሽ በሌላ በኩል በታጋይ ድርጅቱ ውስጣዊ ችግር ምክንያት ትግሉ አቅጣጫውን ስቶ ሌላ አምባገነን በትግል ስም ብቅ እንዳይል ከፍተኛ ጥንቃቄንና የአመራር ብቃትን ይጠይቃል። በሰላማዊ መንገድ ትግሉን የሚገፋ የፖለቲካ ድርጅት ከሌሎች የተለየ ፕሮግራም ይዘው ከሚንቀሳቀሱ የትግል አጋር ፖለቲካ ድርጅቶች ጋርም ቀና ግንኙነትን ለመፍጠር መጣር ይኖርበታል። የፖለቲካ ሥልጣን ይዞ የሕዝብንና የሀገርን ዘርፈ ብዙ ጥያቄ ሊፈታ የሚታገል የፖለቲካ ድርጅት በትግል ላይ ካሉ

መለስተኛ የፖለቲካ ልዩነት ካላቸው ድርጅቶች ጋር ቀና ግንኙነት መፍጠር ከድል በኋላ ለሚኖረው የጋራ አመራርና ምክክር ከወዲሁ ዝግጅቱን ያሳምራልና ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ ሊጤን ይገባዋል።

## 27.3. የትጥቅ ትግል

የትጥቅ ትግል በመሠረቱ የመሳሪያ፣ የሽምቅ ውጊያ ብሎም ጦርነት ነው። የሕዝብንና የሀገርን ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ መፍታት እማይቻልበት ደረጃ ሲደርስ፣ ከአለው አምባገነን ገዥ ጨካኝ እርምጃ የተነሳ የሰላም በሮች ሲጠቡ ወይም ሲዘጉ ያለውን አገዛዝ ለማስወገድ የሚወሰደ የመጨረሻ አማራጭ ነው።

የሕዝብ አታጋይ ፖለቲካ ድርጅቱ በእርግጥ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ዓላማ ያለው ከሆነና የሕዝብና ሀገርን ጥቅም አስቀድሞ የሚደረግ ከሆነ በተጨማሪም የህዝብ ጠላት የሆነን ጨፍጫፊ፣ ሕገ-ወጥ፣ አፋኝ አምባገነን መንግሥት ከሥልጣን ለማስወገድ የሚደረግ ሕዝባዊ ትግል ከሆነ ፍትሃዊና የሚደገፍም ነው። ከትግላችን ተመክሮ በሌላ አንፃር ትጥቅ ትግል የሀገርን ሳይሆን የአንድን ጠባብ ቡድን (በዘር፣ በሃይማኖት ወዘተ ተደራጅቶ) ፍላጎት ለማሟላት የሚደረግ ከሆነ ሕዝባዊነቱና ሀገራዊ ይዘቱ ያልተሟላ ብቻ ሳይሆን ኢዴሞክራሲያዊና ኢፍትሃዊ ባህሪው ስለሚያመዝን የማይደገፍ ይሆናል።

በሌላ በኩል ሀገር በጉልበተኛና ቀማኛ ቅኝ ገዥዎች፣ ወራሪ ኃይሎች ሲጠቃ፣ ሲወረር፣ የግዛት አንድነት/ዳር ድንበር ሲደፈር የሀገር ሉዓላዊነትን ለማስከበር የሚደረግ የትጥቅ ትግል በፀረ-ሰላምና አሸባሪነት ሊፈረጅ አግባብነት የለውም።

አንድ የፖለቲካ ድርጅት የሽምቅ ውጊያ በገጠርም ሆነ በከተማ ሊያካሂድ ይችላል። መሣሪያ ወደ ማንሳትና ወደ ተኩስ ከመገባቱ በፊት ግና መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በሚገባ መመርመርና ዝግጁነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

የትጥቅ ትግል ለማካሄድ መሟላት የሚገባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች፡-

1. ትግሉን ለመጀመር የሚያስፈልግ በሚገባ የተጠናና ከተፈጥሮአዊ አቀማመጡ ጋር ለወታደራዊ ጥቃት መከላከል አመቺ የሆነ ወታደራዊ ሠፈር (ቦታ)
2. በተመረጠው ቦታና አካባቢ ትጥቅ ትግሉን ከመጀመር አስቀድሞ ጠንካራ የፕሮፓጋንዳና የፖለቲካ ሥራ መሥራት። የአካባቢውን ነዋሪ ከአኗኗሩ ዘይቤ፣ ከባህሉና ከእምነቱ ጋር የተዛመደ ቅስቀሳ በመሥራት የፖለቲካው ድርጅት በአካባቢው ነዋሪ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትና ዘለቄታ የድጋፍ መሠረት ከለላ እንዲኖረው ማድረግ፣
3. በአካባቢው ያሉ ወጣቶችና ጎልማሶች በሚገባ አምነውበት የትግሉና የትጥቅ ትግሉ አካል እንዲሆኑ ማድረግ፣
4. የጦር ሠፈሩ የፖለቲካ ድርጅቱ ነፃ ክልል ከሆነ በአካባቢው ላሉ ነዋሪዎች ቢያንስ ትምህርት፣ ሕክምናና አስፈላጊ የዕለት ተለት የኑሮ ዋስትና እንዳይጓደል በእርሻ፣ በጓሮ አትክልት እገዛና ትብብር ማድረግ፣
5. ለሚንቀሳቀሰው ኃይል የምግብ፣ የህክምና አገልግሎት በተጨማሪ ማንኛውንም ቁሳቁስ ለማቅረብ የሚቻልበትን መስመር ማመቻቸት፣
6. ቢቻል ከአጎራባች ሀገራት ድጋፍ በማግኘት የመውጫና መግቢያ መሥመሮችን መቀየስ ሊኖር ይሚችለውን የጦር መሣሪያ፣ የህክምና መሣሪያና መድሐኒቶች፣ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶችን አቅርቦት እጥረት ሊቀንስ ይችላል፣
7. የትጥቅ ትግሉ ከመጀመሩ በፊት ለተዋጊው ኃይል አስተማማኝ ወታደራዊ ሥልጠናና የስነ ልቦና ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ብቃት ያላቸው ወታደራዊ ልምድና የሽምቅ ውጊያ ሥልጠና ያላቸው አመራር ሰጪዎች አስፈላጊነቱን በማጤን መዘጋጀት፣
8. የተዋጊውን ድርጅታዊ ግንኙነትና ሰንሰለት ለማጠናከር ጠንካራ ድርጅታዊ መዋቅር መዘርጋት
9. ተዋጊው ክፍል የስነ ልቦና ዝግጅትና ንቃተ ኅሊናውን በሀገሩና በሕዝቡ ብሶት አኳያ እያዳበረ እንዲጓዝ ያልተቋረጠ ውስጣዊ ጋዜጣ ከማዘጋጀት በተጨማሪ የመወያያ መድረኮችን ማዘጋጀት

10. የትጥቅ ትግሉ አድማሱን እያሰፋ ሲሄድ ተዛማጅነት ያላቸው ንዑስ ወታደራዊ ጣቢያዎችን በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች መመሥረት

በጥቅሉ ከላይ የተዘረዘሩት ቅድመ ዝግጅቶች ይበልጡን ከገጠር ወደ ከተማ ለሚደረጉ የተራዘሙ የሽምቅና የትጥቅ ትግል ዝግጅቶች በመሆናቸው ትግሉም የዚያኑ ያህል እልህ አስጨራሽና አድካሚ ጉዞ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ትግሉ እስከአፍንጫው ከታጠቀ አገዛዝ፣ የሀገሪቷን ገንዘብ፣ ቁሳቁስና የሰው ኃይል በሙሉ ለሥልጣኑ መራዘም ሲል የሚካሄደውን የትጥቅ ትግል ለመደምሰስ ስለሚውል ጉዞው አንዴ በመሸሽ፣ ሌላ ጊዜ በመከላከል ሲያመች በማጥቃት የሚካሄድ ውጣ ውረድ የሚበዛበት ተፈታታኝ ትግል በመሆኑ ለመታገል የቆረጠ ኃይል መገንባቱን በሚገባ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። በተጨማሪም ጥቅማቸው ከአገዛዙ ጋር የተያያዘ ባዕዳን ኃይሎች በመንግሥታት ደረጃ ያለውን መንግሥት እስከአፍንጫው በዘመናዊ መሣሪያ ከማስታጠቅ አልፈው ትግሉን በአሸባሪነትና በፀረ ሰላም ደረጃ ሊፈርጁት እንደሚችሉ መገመትም ይኖርበታል።

ትግሉን በትጥቅ ትግል ያደረገ ፖለቲካዊ ድርጅት የከተማ ሽምቅ ውጊያ በተለይ በሀገሪቱ ዋና ዋና ከተሞችና የአገዛዙ ዋና ከተማ እጅግ በጥንቃቄና አስተማማኝ ወታደራዊ መሠረት ከተገነባ በኋላ ቢሆን ይመረጣል። በአራቱም የሀገሪቷ አቅጣጫዎች ቢያንስ መለስተኛ ንዑስ ወታደራዊ ክልሎች ተቋቁመውና የመንግሥትም ጥንካሬ እየተመናመነ እመጣበት ደረጃ ወቅት ቢሆን የመረጣል።

## 27.4. ሁለገብ የትግል ስልት

ሰላማዊና የትጥቅ ትግልን ያጣመረ እንቅስቃሴ ሁለገብ የትግል ስልት ይባላል። አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች ሲጀምሩም ወታደራዊ ሠፈር አቋቁመው የትግል ሥልታቸውን በትጥቅ ትግል አድርገው እንደ አመቺነቱ የሰላም ትግሉንም ጐዳና ይጠቀሙበታል። ሌሎች ደግሞ ሲጀምሩ በሰላማዊ የትግል ጐዳና ተጉዘው በአለው አምባገነን አገዛዝ እመቃና ጭፍጨፋ፣ እንግልት ምክንያት ያላቸው ትዕግስት ተሟጦ ወደ ትጥቅ ትግሉ ይበልጥ ያተኩራሉ። በሦስተኛ ደረጃ ሊመደቡ የሚችሉት ሲጀምሩም ትግላቸው ሁለገብ ሁኖ ወታደራዊ ግንባታውንም የሰላም ትግሉንም እኩል እያካሄዱ ይቀጥላሉ። እነኚኛዎቹ የአምባገነኖች አገዛዝን ባህሪ ከመረዳት አንፃር የትጥቅ ኃይላቸውንም እየገነቡና እያጠናከሩ ጐን ለጐን ሰላማዊ ትግሉንም እየቀጠሉ በመጓዝ በስተመጨረሻው ወታደራዊ ኃይላቸውን አጐልብተው ይታገላሉ። ይህ አካሄድ በገጠርም በከተማም ትግሉ ጐን ለጐን ሊካሄድ ይችላል። በከተማውና በገጠሩ ትግል መካከልም ያልተቋረጠና ጠንካራ ድርጅታዊ ግንኙነትና መዋቅር አለው።

## 27.5. የትኛው ይሻለናል?

ዛሬ ዓለም ያለችበትን ተጨባጭ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና ከላይ ካስቀመጥናቸው ለትጥቅ ትግል ከሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች በመነሳት በተጨማሪ ዛሬ በረሃ ለበረሃ ተንከራቶ እንደ ጥንቱ "ፋኖ ተሰማራ" ሊል የሚችል ቆራጥ ታጋይና አታጋይ የሰው ኃይል መገንባቱ እራሱ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ዛሬ ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት በተሸረሸረበት ዘመነ ወያኔ ይህንን ለሀገርና ሕዝብ ከራስ በፊት ቅድሚያ ሰጥቶ ሚታገልና የሚያታግል ኃይል በተለይ በዱር በገጠሩ መገንባት ቀላል አይደለም። ከአለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ትግሉን ማቀናጀትና ማካሄድ የግድ ይላል። ከጎረቤት ሀገሮችም ሆነ ከዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ሊገኝ የሚችለው ድጋፍ እራሱን የቻለ ሚዛን ነው ለትግል ስልት ምርጫ። አምባገነን ገዥዎች አሁን ዓለም ባለችበት ሁኔታ መሣሪያ የያዘን ኃይል በአሸባሪነት መፈረጁ ተመቻቷቸዋልና ትግሉን ለማኮላሸት ለሀሰት ቅስቀሳቸው እንደሚጠቀሙበት መገመት ቀላል ነው። እነኝህን ነባራዊ ኩነቶች ከግምት በማስገባት በሰላማዊ ትግል በመጠቀም ሕዝባዊ ንቅናቄ ሊነሳሳ የሚችልበትን መንገድ ለመቀየስ ትግሉ "ሰላማዊ ሕዝባዊ ንቅናቄ" ቢባልና ሰላምንና ሕዝባዊ እምቢተኝነትን ያጣመረ መልክ እንዲኖረው ማድረግ ይቻላል።

በዚህ "ሰላማዊ ሕዝባዊ ንቅናቄ" እንደ ትግሉ ጥንካሬና ሂደት መሣሪያ ጨርሶም አይያዝም ማለት አይደለም። ትግሉን በገንዘብና ቁሳቁስ ለመርዳት፣ ለማገዝ፣ አንዳንድ የድርጅቱ ንብረቶችን ለመጠበቅ፣ ከፍተኛና በአመራር ደረጃ ያሉትን

ለአስተያየት የቀረበ

አባላቱን ለመከላከልና ለመጠበቅ መሳሪያ መጠቀም ግድ ሊል ይችላል። ሕዝባዊ ዓመጹም አስተማማኝ ደረጃ ሲደርስ በሁሉም አቅጣጫ እንቅስቃሴው ተፋፍሞ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ሲደርስ ትግሉ በመፈረካከስ በአለው የወያኔ ጀሌዎችና ሌሎች ኃይሎች ለጥቃት እንዳይጋለጥና እንዳይቀለበስ ለሚደረገው ጉዞ አሁን ትግሉን መከላከል ነውና የዚህ ጊዜ መሳሪያ ማንሳቱ አግባብነት ሊኖረው ይችላል።

በጥቅሉ ግን የዚህ ትግል አቅጣጫ የወያኔን አገዛዝ በተቀነባበረ

- የሥራ ማቆም አድማ :- በሠራተኛው (በተለይ በቴሌ ኮሙኒኬሽን፣ በመብራት ኃይል፣ በውኃና ፍሳሽ አገልግሎት፣ በባንክ፣ በኢንሹራንስ፣ በፋብሪካ ወዘተ)፣ ታክሲ ነጂዎችና ማንኛውም የትራንስፖርት አቅገልግሎት (የአየር፣ የከተማ አውቶብሶች፣ የክፍለ ሀገር አውቶብሶች፣ ወዘተ)፣ በመምህራን (ከአንደኛ ደረጃ፣ በሁለተኛ ደረጃ፣ በዩንቨርስቲና ኮሌጅ ጭምር)፣ በወታደሩ ክፍል፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ጭምር እንዲካሄድ፣
- ትምህርት ማቆም :- ማንኛውም የመንግስትም ሆነ የግል ትምህርት ቤቶች ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩንቨርስቲ ኮሌጅ ያሉትን ጨምሮ ያልተቋረጠ የትምህርት ማቆም አድማ ማድረግ።
- ሰላማዊ ሰልፍ :- በሁሉም የሀገሪቷ ክፍሎች በተለይ በከተሞች ያልተቋረጠ ሰላማዊ ሰልፍ በተለይ በአዛውንት እናቶችና አባቶች በታዳጊ ሕፃናት የበላይነት የሚመራና ሁሉም የኀብረተሰብ ክፍል የተቀላቀለው ማካሄድ፣ ወጣቶች በየአካባቢው በአዛውንቶች የታገዘውን እንቅስቃሴ ማጧጧፍ
- የኢኮኖሚ ማዕቀብ :- ከማንኛውም የመንግሥትና የወያኔ ግለሰቦች የሚደረገውን ግብይት ግዥና ትብብር ማቋረጥ (በኢትዮጵያ አየር መንገድ አለመጠቀም፣ ከኢፈርት ኩባንያዎች፣ ከሜጋ ድርጅቶች ወዘተ ግብይቶችን ማቆም)
- የቅስቀሳ ሥራ :- በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍሎችና በከተሞች ያላቋረጠ በፖለቲካ ድርጅቱ የታገዘ ወቅታዊ መፈክሮችን የያዘ የወረቀት ብተና፣ የግርግዳ ላይ መፈክር ለጠፋና ጽሑፎች የመሳሰሉትን ሳያቋርጡ በተለያዩ የሀገሪቱ ቋንቋዎች መለጠፍ፣ መስቀል፣
- የረሃብ አድማ :- ለዴሞክራሲና ለሕዝብ መንግሥት የሚደረገውን የመጨረሻ ተጋድሎ ከግብ ለማድረስ በረሃብ አድማ ትግሉን ድምቀት መስጠት፣
- የተለያዩ ተቃውሞዎች :- በየአካባቢው ያለው ነዋሪ ከአገዛዙ ሊመጡ የሚችሉ ጥቃቶችን ለመከላከል ዋና ዋና መንገዶችን በድንጋይ፣ በአጣና፣ በቆሻሻ ክምችትና በመሳሰሉት መዝጋት ማሰናከል፣
- በየአካባቢው ያሉ የመንግሥት አካላትን (መንግሥት ለጥበቃና ለደህንነት የሚጠቀምባቸውን) እንደ ቀበሌ፣ ዞን፣ ወረዳ፣ አውራጃ ጽ/ቤቶች እንቅስቃሴን ማሰናከልና ለመቆጣጠር መሥራት፣
- እንቅስቃሴው በምንም መልኩ ዘርንና ሃይማኖትን ተገን ሳያደርግ ሁሉም የኀብረተሰብ ክፍል ይካፈልበት ዘንድ መጣር ለዚህም የእስልምናም ሆነ የክርስትና እምነት ተከታዮችና በተለይ በየቤተክሲያኑና መስጊዱ ያሉ አባቶች በፀሎት የተደገፈ ከፍተኛ ቅስቀሳ ስለሀገራቸውና ሕዝባቸው ብሶት ያሰሙ ዘንድ መጣር፣ . . . ወዘተ

በመሳሰሉት ትግሉ በሰላማዊ መንገድ ያለውን የወያኔ አገዛዝ ማናጋት ብቻ አይደለም አንዴ ከተጀመረ የማያቋርጥና ሊቀለበስ የማይችል እንቅስቃሴ በማድረግና ሊከፈል የሚገባውን መስዋዕትነት በመክፈል ድሉን የሕዝብና የሀገር ለማድረግ ቁርጠኝነትን ማሳየት።

## 28.0. ለምን አስፈለገ?

ኢትዮጵያ ሀገራችን በትንሹ ለአለፉት አርባ ዓመታት እጅጉን ሊታመን የማይችል አጣብቂኝ ውስጥ ገብታለች። የ66ቱን ትውልድ ያጣችው ሀገራችን ለ17 ዓመት በጦርነትና በግፍ ጭፍጨፋ ታምሳ "ከድጡ ወደ ማጡ" እንዲሉ አሁን በአለው የወያኔ አገዛዝ የእርስ በርስ ግጭትና መበታተን አደጋ እያንዣበበባት ይገኛል። የደርግን አገዛዝ ለመጣል ሕዝባዊ መሠረትና ሀገራዊ አጀንዳ ይዞ የተነሳው ኢሕአፓ በደርግ "ቀይ ሽብር" ከተኮላሸ በኋላ ጠንካራ አወቃቀር፣ አደረጃጀትና ግልጽ ዓልማና ራዕይ ይዞ የተነሳ የፖለቲካ ድርጅት ሀገራችን አልገጠማትም ሊባል ይቻላል። በወያኔ ዘረኛ ፖሊሲ ምክንያት ትግሉን

ሀገራዊና ሕዝባዊ አጀንዳ አሲይዞ ከመነሳት ይልቅ የክልልና የዘር ድርጅቶች መበራከት እየታየ ነው። ሀገራዊ አጀንዳም የያዙት ድርጅቶች ትላንት ተፈጥረው ዛሬ የሚከስሙ መሆናቸው እየታየ ነው። አንዳንዶችም እራሳቸውን ሀገር ቤት መትከል አቅቷቸው በባዕድ ሀገር "እኛም አለን" ከማለት የዘለለ ተግባር እንደሌላቸው ይታያል። በአጠቃላይ በአለፉት 25 ዓመታት የወያኔ አገዛዝ ጎልቶ የወጣ ታጋይና አታጋይ የፖለቲካ ድርጅት የለም ቢባል ያስኬዳል። አብዛኞቹ ድርጅቶች ዓላማቸውና ተልዕኳቸው እንኳ በደንብ የተቀመጠ አይደለም። ማታገያ ፕሮግራም ጨርሶውን የሌላቸውም በርካታ ናቸው። አንድና ሁለት ሆነውም እኛም አለን የሚሉም አልጠፉም። "ከእኛ ሌላ ማንም የለም" ብለውም እንደፈለጉት በሀገር እልውና ላይ የሚፈርዱም አልጠፉም። ስለ ሀገራችን አየሩን የሞላው ፖለቲካ ይህ ነው።

"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!" ሕዝባዊ ንቅናቄ ብለን ከተነሳን "ኢትዮጵያዊ አይደለንም፣ የእኛ ችግር የኢትዮጵያ ችግር አይደለም" ብለው ወያኔ ሊበታትናት ያጠመደውን ፈንጂ ሊረግጡ ሚከጅሉ ከሀገር ሉዓላዊነትና ከሕዝብ አንድነት አንፃር ልንመለከታቸው ይገባል። ከወያኔ ውድቀት በኋላ ኢትዮጵያ ሁሉንም ልጆቿን በእኩልነት ይዛ ትጓዝ ዘንድ መሠረቱን ለመጣልና አቅጣጫ ለማስያዝ የፖለቲካ ዓላማው ግልጽ፣ ተልዕኮና ግቡ በማያወላዳና በማያምታታ መልኩ የተቀመጠ አታጋይ ድርጅት አስፈላጊነቱ አጠራጣሪ አይደለም።

ደርግ 17 ዓመት ሀገር ገደለ አንድ ትውልድ ጨረሰ ስንል ሥርዓቱ ቢንኮታኮትም፣ የደርግና የመንግሥቱ ፖለቲካ ድርጅት ኢሠፓ ቢቀበርም ዕልባት ያላገኙ ተጠያቂዎች ሌላ ቢቀር ከወያኔ ውድቀት በኋላ በቀጣዩ መንግሥት አደብ ገዝተው ይቀመጡ ዘንድ ዕድል ካገኙ ከበቂ በላይ ነው። ዛሬ አንዳንድ ፖለቲካ ድርጅቶች የደርግና ኢሠፓ ወንጀለኞችን አቅፈው ወያኔን ሊጥሉ ቢችሉም በምንም መልኩ ለሕዝባችን የዜግነት መብቱን አያጎናጽፉትም። ዴሞክራሲያዊ መብት ከሌለ ደግሞ የሀገር ዕድገትና ልማት ሲያምር ይቀራል። ተጠያቂነት ከሌለ ደግሞ የነበረው ቢሮክራሲያዊ አሠራር ይቀጥልና ሙስና፣ ጉቦኝነትና ዘረፋ በለውጥ ስም ይቀጥላሉ። ይህ ሲሆን አዲስ አገዛዝ መጣ እንጂ ለሀገርና ለሕዝብ ለውጥ አላመጣም። የዚህ ዓይነት ውጤት ምክንያቱ ወንጀልን የተሸከሙ ኃይሎችን በየፖለቲካው ድርጅቱ መሰግሰግ ብቻ አይደለም ጎላ ብለው ይታዩ ዘንድ የሚደረገው ሂደት ትግሉን እየጎዳው ከመሄድም አልፎ ለዳግም አምባገነን አገዛዝ ይዳርጋል።

በሌላም በኩል ለሀገራችን ዕልውና፣ ለሕዝባችን አንድነት ፀር የሆኑ ባዕዳን ሀገሮችን ተገን አድርጎ የሚመጣ ለውጥ ከባርነት የዘለለ አይደለም። እንደ ሻቢያ ያለ ፀረ ኢትዮጵያ ድርጅት ለትግላችን እንቅፋት ለሀገራችንና ሕዝባችን መቅሰፍት እንደሆነ መረዳት ካቃተን ሥልጣኑ ቢያዝም ተፈላጊው ነፃነትና ዴሞክራሲያ አይመጣም።

በኢትዮጵያ አንድነት አምነው በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ ኅብረብሔር የፖለቲካ ድርጅቶችም በዚህ 25 ዓመት ውስጥ አለን፣ እየተንቀሳቀስን ነው፣ ሲሉ ቢደመጡም በሀገር ውስጥ ነባራዊ ሁኔታዎች ተሟልተው ሕዝቡ እራሱ በየአካባቢው እንቅስቃሴ ሲጀምር እንዴት እንደኖሩ ይታያሉ። የተነሳውን ትግል አጠናክሮ ለማስቀጠል ሕዝቡ ጐን የሉምና የተለመደ ትብብር፣ ኅብረት ከማለት የዘለለ ተግባር አይከናወንም። የሀገሪቷን ችግር ለመፍታት በጋራ መመካከርና መጓዙ ጠቀሜታው የጐላ ቢሆንም አንድ የፖለቲካ ድርጅት ብቻውን ብዙ ሚና ሊጫወት ይችላል። አይሳካለት እንጂ ኢሕአፓ ብቻውን እኮ ነው ደርግን ያንቀጠቀጠው። ዋናው ቁም ነገሩ ትግሉ ሕዝብን ያቀፈና ሕዝቡ ውስጥ መሆኑ ነው።

ከላይ በመጠኑ ገለጽ ለማድረግ እንደተሞከረው የ"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!" ሕዝባዊ ንቅናቄና ፖለቲካ ድርጅት ሊመሠረት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት፡-

- በኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ላይ ከማንም ሳንደራደር "አንድ ኢትዮጵያ" ብለን በመነሳታችን
- ኢትዮጵያ የሁሉም ዘሮች፣ ብሔር/ብሔረሰቦች ሀገር መሆኗን ተቀብለን ሁሉንም በእኩልነት የምትመለከት "አንድ ሕዝብ" ብለን መነሳታችን
- በውጭው ዓለም የሚደረጉ ዲፕሎማሳዊ እንቅስቃሴዎችና በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን ለትግሉ የሚያበረክቱት እገዛ እንደተጠበቀ ትግሉን ሙሉ በሙሉ በሀገር ቤት በማድረግና እንቅስቃሴውንም እዚያው በሀገር ቤት ያሉት ወጣቶችና ጎልማሶች በአጠቃላይ የአሁኑ ትውልድ ኃላፊነቱን እንዲረከብ ለማድረግ

- በተለይ በአለፉት አርባ ዓመታት የትግል ታሪክ የአገዛዝ ሥልጣናቸውን ተገን አድርገው የሀገር ሀብትና ንብረት የዘረፉ፣ የሕዝብ ልጆችን ሕይወት የቀጠፉ ወንጀለኞች ከወያኔ ውድቀት በኋላ በሚደረገው ብሔራዊ ዕርቅ በሀገርና ሕዝብ ላይ የደረሰውን በደል እውቅና ሰጥቶ መጓዝ የሚቻልበትን አቅጣጫ ለመቀየስ
- የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በባህል፣ በሃይማኖት፣ በአኗኗር የተሳሰረ ቢሆንም ወያኔና ሻቢያ በፈጠሩት የሀገር መበተን አጀንዳ ኤርትራ ተገንጥላለች። በዚህ ሠነድ መሠረት ወያኔና ሻቢያ የኢትዮጵያና የሕዝባችን ጠላቶች በመሆናቸው ቀጣዩ መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ ውሳኔ መሠረት ለኤርትራ እንደ ሀገር እውቅና ከሰጠ ከኤርትራው አምባገነን ገዥና ሻቢያ ጋር የሚኖረው ግንኙነት እጅግ የተገደበ መሆን ስለሚገባው
- ኤርትራ በሻቢያና በወያኔ የጋራ ስምምነት ያለአግባብ የወሰደችውን አሰብ ወደብን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለኢትዮጵያ መመለስ እንደሚኖርባት የሚሞግት ፖለቲካ ድርጅት አስፈላጊ በመሆኑ
- ለትውልድ የሚተላለፍ ዘለቄታዊ ሕገ መንግሥት ለማርቀቅና ተግባራዊ ለማድረግ ለሚደረገው አስተዋጽዎ የኢትዮጵያንና የሕዝቧን አንድነት ለማስረገጥና በታሪክ ጠባሳ ጥሎ ላለማለፍ የዜግነት ግዴታን መወጣት ስለሚያስፈልግ
- ከወያኔ ውድቀት በኋላ ለተወሰነ ዓመታት ሀገሪቷ በጋራ አመራር ትጓዝ ዘንድ በቀረበው በዚህ ሠነድ መሠረት በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና እንዲሁም ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ የጋራ ኅብረት ስምምነት ይፈጠር ዘንድ አስተዋጽዎ ማድረግ በማስፈለጉ
- ወዘተ "አንድ ሕዝብ! አንድ ሀገር!" ሕዝባዊ ንቅናቄና የፖለቲካ ድርጅት ማቋቋሙን አምነንበታል።

## 29.0. ቀጣይ ሂደት

የሀገራችንን ሁኔታ አስመልክቶ ከላይ በቀረቡት ዋና ዋና ጉዳዮች ሠነዱ የደረሳቸው ወገኖች በሚሰጡት አስተያየት መስተካከያ ተደርጎበት ስምምነት ላይ ከተደረሰ ለቀጣይ ሂደት ከአሁኑ ጊዜያችንን ለትግሉ ልንሰጥ መዘጋጀት ይኖርብናል።

ምን መደረግ አለበት? በሚል በቀረበው መሠረት "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!" ሕዝባዊ ንቅናቄ ግቡን ይመታ ዘንድ በቅርብ ይፋ በሚሆነው አታጋይ የፖለቲካ ድርጅት ተገንነት ስለሀገራችንና ሕዝባችን ያለንን ራዕይ ተግባራዊ ለማድረግ በርካታ የሚሠሩና የሚከናወኑ ጉዳዮች ይኖራሉ። እንቅስቃሴአችን ዕውቀት ይጠይቃል፣ ያለንን ችሎታ ይፈልጋል፣ ገንዘብና ቁሳቁስ ያስፈልገዋል፣ የአመራር ብቃታችንን ምናሳይበት ለመሆን መዘጋጀት ይኖርብናል። ለዚህ ደግሞ ከማንኛውም በበለጠ ያለንን ትርፍ ጊዜ ለዚህ ለማዋል መዘጋጀት ይኖርብናል። ኃላፊነቱ ለአንድ ወይም ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ የሚተው ጉዳይ አለመሆኑን ማጤን ይጠይቃል። በቀረበው ሀሳብ ፍላጎቱ ኖሮን በሙሉ ፍላጎት አስተዋጽዎና ትብብር የማድረግ ፍላጐት ላላችሁ ወገኖች ሁሉ ቀና ትብብራችሁን በቅድሚያ እናደንቃለን።

የምንጓዘው ጎዳና ቀላል አይደለም። ከጠላት የባሰ በአቅራቢያችን ያሉ ወዳጆች ናቸው ማጥላላቱንና ማሰናከሉን የሚሞክሩት። ለዚህ ደግሞ አንድ ነገር ሲጀመር ከጥቂት ተነስቶ ነውና የሚጎለብተው የጥንካሬአችን ውጤት የሥራችንና የአመራር ብቃታችንን ያመለክታልና እንችላለን፣ እናደርገዋለን ብለን መጀመር ያለብን ጉዳይ መሆኑን በቅድሚያ አትኩሮት መስጠት ይኖርብናል።

## አባሪ 1. "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ሕዝባዊ ንቅናቄ ዓርማና መግለጫ፡

***የኢትዮጵያ ካርታ፡*** በአርማው ላይ የሚታየው የኢትዮጵያ ካርታ ከዛሬ 25 ዓመት በፊት ያለአግባብ የተገነጠለችዋን ኤርትራ ለየት ባለ ቀለም አስቀምጠናል። ንቅናቄው የኤርትራን ሀገርነት ወደፊት ኢትዮጵያ በሕዝበ ውሳኔ እውቅና ከሰጠች ከኤርትራ ጋር ቀና ግንኙነት ለመፍጠር ያለምንም ቅድመ ሁናቴ ኤርትራ አሰብ ወደብን ለኢትዮጵያ መመለስ አለባት ብለን እናምናለን። በመሆኑም በኤርትራ ግዛትና በአሰብ መካከል የወሰን መስመር አድርገናል። ይህ የአሰብ ክልል ለኢትዮጵያ ይገባታልና የኤርትራ ግዛትነቱን ባለመቀበላችን ለብቻው ከኢትዮጵያ ግዛት ጋር በሚኖረው አቀማመጥ አካተነዋል።

***ኢትዮጵያን የከበቡት የተያያዙ እጆች፡*** ኢትዮጵያ በጀግኖቿ ደምና አጥንት የተገነባች መሆኗን ሲያሳይ በሌላ በኩል ሁሉም ዜጎቿ በአንድነት እጅ ለእጅ ተያይዘን በ "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ሕዝባዊ ንቅናቄ" ዳግም ትንሳዔዋን እንደምናበስር ያለንን ተስፋ ያንጸባርቃል።

***ኢትዮጵያን የከበባት ዘንባባ፡*** ዘንባባው ልምላሜን፡ ዕድገትንና ሰላምን ያሳያል። አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ሕዝባዊ ንቅናቄ ይዞት የተነሳው ዓላማ ህያው መሆኑንና የልጆቿ የሆነች ኢትዮጵያ ወደ ልምላሜና ሰላም ጎዳና እንደምታመራ ያለውን የወደፊት ራዕይና ተስፋ ያሳያል።

***ኢትዮጵያን ዙሪያ የከበባት ሰንደቅ ዓላማ፡*** የኢትዮጵያን ካርታ ዙሪያዋን የከበበው አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ዓርማችን የአንድ ኢትዮጵያ ሀገራችን ብሔራዊ መለያችንና የነጻነት ዓርማችን ዘለዓለማዊ መሆኑን ያንጸባርቃል።

***አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ሕዝባዊ ንቅናቄ ፡*** በቅስት መልክ ከላይ እና ከታች የተጻፈው የንቅናቄው ስያሜ መሆኑን ይገልጻል።

***ኢትዮጵያችን፡*** ኢትዮጵያ ካርታ መሀሉ ላይ በቢጫ የተጻፈው ኢትዮጵያችን የሁሉም ብሔር/ብሔረሰቦች ማዕከል/አስኳል መሆኗን ለማስረገጥና የልጆቿ እና የሕዝቧ የሆነች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንደምንገነባ ያለንን ተስፋ ያመላክታል።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

አንድ ሀገር ! አንድ ሕዝብ ! ሕዝባዊ ንቅናቄ

ከአክብሮትና ምስጋና ጋር
ነሐሴ 24 ቀን 2008 ዓ.ም.
(September 30, 2016)

ኢሜል ፡ ethiopiachen@gmail.com
info@ethiopiachen.org

ኢትዮጵያችን